የሐዋርያት ሥራ

አስተዋፅኦ

መግቢያ (1፥1-11)

I. *የመንፈስ ቅዱስ መውረድ* (1፥12—2፥41)

(ሀ) *ለተስፋው መዘጋጀት* (1፥12-26)

(ለ) *የበዓለ ኀምሳ ቀን* (2፥1-41)

II. *በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት* (2፥42—8፥1ሀ)

(ሀ) *ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ባሕርያት* (2፥42-47)

(ለ) *አስደናቂ ታምራትና ውጤቶቹ* (3፥1—4፥31)

(ሐ) *በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ለመረዳዳትና ለመደጋገፍ የተጀመሩ ቀጣይ ልምምዶች* (4፥32—5፥11)

(መ) *ተጨማሪ ፈውሶችና ከሃይማኖት ድርጅት የመጣ ተቃውሞ* (5፥12-42)

(ሠ) *የሰባቱ ዲያቆናት መመረጥ* (6፥1-7)

(ረ) *እስጢፋኖስ፥ የመጀመሪያ ክርስቲያን ሰማዕት* (6፥8—8፥1)

III. *ስደት መስፋፋትን እንደሚያመጣ* (8፥1—9፥31)

(ሀ) *በይሁዳና በሰማርያ የተበተኑ ክርስቲያኖች* (8፥1-4)

(ለ) *ፊልጶስ፥ የወንጌላዊ አገልግሎት* (8፥5-40)

(ሐ) *የጠርሴሱ ሳውል፥ የአሳዳጁ መለወጥ* (9፥1-31)

IV. *ክርስትና ለአሕዛብ መሠራጨት መጀመሩ* (9፥32—12፥25)

(ሀ) *በልዳና በኢዮጴ የነበረው የጴጥሮስ አገልግሎት* (9፥32-43)

(ለ) *የጴጥሮስ ተልእኮ ቂሣሪያ ለነበሩት አሕዛብ* (10፥1-48)

(ሐ) *ጴጥሮስ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ያቀረበው ሪፖርትና የወለደውም እርምጃ መጽደቅ* (11፥1-18)

(መ) *አንጾኪያ፥ የመጀመሪያይቱ የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን* (11፥19-30)

(ሠ) *በቀዳማዊ ሄሮድስ አግሪጳ የተካሄደ ስደት* (12፥1-23)

(ረ) *ያቤተ ክርስቲያንን እድገት በተምሳሌት ማጠቃለያ* (12፥24-25)

V. *የጳውሎስ የመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ* (13፥1—14፥28)

(ሀ) *አንጾኪያ ባለችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስና በርናባስ መላካቸው* (13፥1-3)

(ለ) *ወንጌል የተሰበከላቸው አገሮች* (13፥4—14፥28)

VI. *የኢየሩሳሌም ጉባኤ* (15፥1-35)

VII. *የጳውሎስ ሁለተኛው የወንጌል ጉዞ* (15፥36—18፥22)

(ሀ) *በጳውሎስና በበርናባስ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት* (15፥36-40)

(ለ) *ቀደም ሲል ወንጌል የተሰበከባቸውን አገሮች እንደ ገና መጐብኘት* (15፥41—16፥5)

(ሐ) *ወንጌል የተሰበከባቸው አዳዲስ አገሮች* (16፥6—18፥21)

(መ) *በሶርያ ወዳለችው አንጾኪያ መመለስ* (18፥22)

VIII. *የጳውሎስ ሦስተኛው የወንጌል ጉዞ* (18፥23—21፥16)

(ሀ) *እግረመንገድ ወደ ኤፌሶን* (18፥23)
ተጨማሪ ሆኖ የገባ ሐሳብ፥ የአጵሎስ አገልግሎት (18፥24-28)

(ለ) *በኤፌሶን የተካሄደ ረኀቡም አገልግሎት* (19፥1-41)

(ሐ) *ወደ መቄዶንያና ግሪክ መሄድ ከዚያም ወደ መቄዶንያ መመለስ* (20፥1-5)

(መ) *ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገ የመልስ ጉዞ* (20፥6—21፥16)

IX. *የጳውሎስ መያዝና በእስራቱ ዘመን የነበረው አገልግሎት* (21፥17—28፥31)

(ሀ) *በኢየሩሳሌም* (21፥17—23፥35)

(ለ) *በቂሣርያ* (24፥1—26፥32)

(ሐ) *ጉዞ ወደ ሮም* (27፥1—28፥15)

(ሙ) በሮም (28፥16-31)

ጸሓፊው፤ *ሉቃስ*

ዋና ሐሳብ፤ *በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ወንጌል በድል አድራጊነት መሠራጨቱ*

የተጻፈበት ዘመን፤ *በግምት 63 ዓ.ም.*

ታሪካዊ ዳራ

የሐዋርያት ሥራ የተጻፈው ልክ እንደ ሉቃስ ወንጌል "ቴዎፍሎስ" (1፥1) ለተባለ ሰው ነው። በሁለቱም መጽሐፍ የጸሓፊው ስም ባይገለጽም የጥንቱ የክርስትና ማኅበረሰብ በአንድ ድምፅ የሚሰጠው ምስክርነትና የሁለቱ መጻሕፍት የውስጥ መረጃ የሚያቀርበው ማረጋገጫ ጸሐፊው፣ "የተወደደው ሐኪሙ ሉቃስ" (ቈላ 4፥14) እንደሆነ ነው።

የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን የክርስትናን አጀማመር ሙሉ ታሪክ ለማወቅ ያላትን ፍላጎት ለማሟላት መንፈስ ቅዱስ ሉቃስን ለቴዎፍሎስ እንዲጽፍለት ገፋፋው፣ (1) የእርሱ ወንጌል የሆነው፣ "ቀደም ያለው" መጽሐፍ ስለ ኢየሱስ ሕይወት የሚናገር ሲሆን፣ (2) እርሱ የጻፈው የታሪክ መጽሐፍ የሆነው ሁለተኛው የሐዋርያት ሥራ ደግሞ የሚተርከው በኢየሩሳሌም ስለወረደው መንፈስ ቅዱስና ስለ ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ቀጣይ እድገት ነው። ሉቃስ ልዩ ችሎታ የነበረው ጸሓፊ፣ ታሪክን ጠንቅቆ የሚያውቅና በመንፈስ ቅዱስ የሚነዳ የሥነ መለኮት ሰው እንደ ነበር ግልጽ ነው።

የሐዋርያት ሥራ በመጀመሪያዎቹ ሠላሳ ዓመታት የተከናወነውን የቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ታሪክ ይሸፍናል። እንደ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሓፊ ሉቃስ ከ32 ያላነሡ አገሮችን፣ 54 ከተሞችን፣ 9 የሚድትራኒያን ደሴቶችን፣ የ95 የተለያዩ ሰዎችን ስም እና አያሌ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን እንዲሁም አስተዳዳሪዎችን ብትክክለኛው ማዕረጋቸው በመጥቀስ ከኢየሩሳሌም እስከ ሮም የተካሄደውን የወንጌል ሥርጭት በዝርዝር አመልክቶአል። የሥነ ቅርስ ጥናትም ሉቃስ በጠቀሳቸው ዝርዝር ጒዳዮች ላይ አስገራሚ ማረጋገጫዎችን በመስጠት ላይ ይገኛል። እንደ ሥነ መለኮት ሰው ሉቃስ ጥበብ በተሞላ አገላለጽ በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ዓመታት ላይ የነበሩትን አያሌ ልምምዶችና ሁነቶች አቅርቦአል።

በመጀመሪያዎቹ ደረጃዎች፣ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ሁለት ሰብስቦችን ይዞአል፣ (1) አራቱ ወንጌሎች (2) የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሁለቱን ሰብስቦች በማያያዝ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን አደርጎአል፣ በዚህም አሁን ያለበትን ተገቢውን ቀኖናዊ ቅደም ተከተሉን ይዞአል። ከምዕ 13—28 ያለው ክፍል የጳውሎስን አገልግሎትና መልእክቶች በይበልጥ ለመረዳት የሚያስችሉ ታሪካዊ ዳራዎችን አቅርቦአል። ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ባሉ ምንባቦች "እኛ" (16፥10-17፤ 20፥5—21፥18፤ 27፥1—28፥16) በማለት የገለጸው፣ በሐዋርያው ጳውሎስ ጉዞዎች ውስጥ እርሱም በግሉ መሳተፉን ለማመልከት ነው።

ዐላማ

ሉቃስ የቤተ ክርስቲያንን ጅማሬ በዝርዝር ሲገልጽ፣ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ዐላማዎች ነበሩት፣ (1) ተቃውሞና ስደት ቢኖርም ጠበብ ካሉት የአይሁድ እምነት ድንበሮች ወደ አሕዛቡ ዓለም ወንጌል በአሸናፊነት መንቀሳቀሱን ለማሳየት፣ (2) ወንጌልን ለማወጅና የኢየሱስን አገልግሎት ለመቀጠል ቤተ ክርስቲያንን በኀይል የሚሞላው የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንደ ሆነ በአጽንዖት በመግለጽ፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወትና ተልእኮ ላይ መንፈስ ቅዱስ ያለውን ሚና ለማመልከት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በልሳን ከመናገር ጋር የተያያዘ መሆኑን ሉቃስ ሦስት ጊዜ በግልጽ ጠቅሶአል (2፥4፤ 10፥45-46፤ 19፥1-7)። የእነዚህ ምንባቦች ዐውድ በልሳን መናገር በጥንት ክርስትና በሁሉም ዘንድ የተለመደና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት ቋሚ መመሪያ እንደ ሆነ ያመለክታል።

ቅኝት

የሉቃስ ወንጌል፡ "ኢየሱስ ለማድረግና ለማስተማር የጀመረው" (ሐሥ 1፥1) ሁሉ የተጻፈበት ሲሆን፣ የሐዋርያት ሥራ ደግሞ ኢየሱስ ከዕርገቱ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በደቀ መዛሙርትና በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት በመቀጠል ያደረገውና ያስተማረው ነገር የተጻፈበት ነው። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ (1፥9-11) ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው

የመጨረሻው ምክር በመንፈስ ቅዱስ እስኪጠመቁ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቈዩ ነበር (1፥4-5)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዋና ጥቅስ (1፥8) የመጽሐፉን ሥነ መለኮታዊና ጂአግራፊያዊ ማእከላዊ መግለጫ የያዘ ነው፤ ይኸውም መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኀይልን እንደሚቀበሉ የተሰጣቸው ተስፋ ነው፤ ምስክሮቹ የሚሆኑትም፣ (1) "በኢየሩሳሌም" (ምዕ 1—7)፣ (2) "በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ" (ምዕ 8—12)፣ (3) "እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ" ነው (ምዕ 13—28)።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መለኮታዊውንና የሰውን ድርጊት አጣምሮ የያዘ ነው። ሐዋርያት ብቻ ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ባጠቃላይ፣ "በሄዱበት ሁሉ ቃሉን ሰበኩ" (8፥4)። እንደ እስጢፋኖስና እንደ ፊልጶስ ያሉት ዲያቆናት (6፥1-6) "ድንቅ ነገሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን" (6፥8) በማድረግ በመንፈስ ቅዱስና በእምነት ኀይል ሆኑ፤ ከተሞችን በሙሉ በወንጌል አናወጡ (8፥5-13)። የእግዚአብሔር ሰዎች አጥብቀው ጸለዩ፣ መላእክት ተገለጡላቸው፣ ራእይን አዩ፣ ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን መስከሩ፣ እጋንንትን አስወጡ፣ በሽተኞችን ፈወሱ፣ በታላቅ ድፍረትና ሥልጣን ወንጌልን ዐወጁ። በአይሁድ አማኞችና በአሕዛብ አማኞች መካከል ያለውን ውጥረት ዐይነት የመሰለ (ምዕ 15) የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ችግር ቢኖርም እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በሃይማኖት መሪዎችና በመንግሥት ባለሥልጣኖች በኩል የሚያጋጥሩ የስደት ማዕበል ቢነግም የጌታ ኢየሱስ ስም በቃልና በድርጊት ከአንዱ ከተማ ወደሚቀጥለው ከተማ እየገነነ ሄደ።

ከምዕ 1—12 ባለው ክፍል የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሥርጭት ዋና ማእከል ኢየሩሳሌም ነበረች፣ በዚህ ስፍራ ወንጌልን ለማሠራጨት እግዚአብሔር መሣሪያ አድርጎ የተጠቀመበት ሰው ጴጥሮስ ነበር። ከምዕ 13—28 ባለው ክፍል የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሥርጭት ዋና ማእከል የሶርያዋ አንጾኪያ ነበረች፣ በዚህ ስፍራ ደግሞ ወንጌልን ለአሕዛብ ለማሠራጨት እግዚአብሔር መሣሪያ አድርጎ የተጠቀመበት ሰው ጳውሎስ ነበር። የሐዋርያት ሥራ ትረካ ድንገት የሚያበቃው ጳውሎስ በቄሣር ፊት ለፍርድ የሚቀርብበትን ሁኔታ በሮም እየተጠባበቀ ባለበት ሁኔታ ላይ ነው። የፍርዱ ሁኔታ በእንጥልጥል ላይ እንዳለ ቢሆንም ጳውሎስ አሁንም በአስር ላይ ሆኖ ማንም ሳይከለክለው በግልጽ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ መሰበኩንና ማስተማሩን በሚገልጽ አሸናፊ መልእክት መጽሐፉ ተጠቃሎአል (28፥31)።

ልዩ ገጽታዎች

የሐዋርያት ሥራን ልዩ የሚያደርጉት ዘጠኝ ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፣ (1) ቤተ ክርስቲያን፣ በማንኛውም ትውልድ ቤተ ክርስቲያን የምትመራበትን መርሐ ጨምሮ የሐዋርያት ሥራ የቤተ ክርስቲያንን ዮኀይል ምንጭና የተልእኮዋን እውነተኛ ባሕርይ ይገልጻል፣ (2) መንፈስ ቅዱስ፣ የሥላሴ ሦስተኛ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ በተለይ 50 ጊዜ ያህል ተጠቅሶአል፣ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና በእርሱም ሥልጣን ማገልገል ኀይልን (1፥8)፣ ድፍረትን (4፥31)፣ እግዚአብሔርን በቅዱስ ፍርሃት መፍራትን (5፥3፡5፡11)፣ ጥበብን (6፥3፡10)፣ ምሪትን (16፥6-10) እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን (19፥6) ያስተላልፋል፣ (3) የጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን መልእክቶች፣ ሉቃስ የጴጥሮስን፣ የእስጢፋኖስን፣ የጳውሎስን፣ የያዕቆብንና የሌሎቹን በመንፈስ ቅዱስ የተሰጡ መልእክቶችን በጥበብ ተርኮአል፣ ይህም በአዲስ ኪዳን በሌላ ስፍራ የማይገኝ ሲሆን፣ ስለ ጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን በጥልቀት ለመረዳት የሚያስችል ነው፣ (4) ጸሎት፣ የጥንት ክርስቲያኖች ለዘወትር እና አንዳንዴ ሌሊቱን በሙሉ ለማደረግና ታላላቅ ውጤቶችን ለሚያስገኝ ጥብቅ ጸሎት ራሳቸውን የሰጡ ነበሩ፣ (5) ምልክቶች፣ ድንቆችና ታምራት፣ እነዚህ የኀይል መግለጦች በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ከሚታወጅ ወንጌል ጋር የተያያዙ ናቸው፣ (6) ስደት፣ ወንጌልን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ማወጅ ከሃይማኖትም ክፍሎች ሆነ ከዓለም ተቃውሞና ስደት ማስከተሉ አይቀርም፣ (7) የአይሁድ/የአሕዛብ ተከታታይነት፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ወንጌል በመጀመሪያ ለአይሁድ ቀጥሎም ለአሕዛብ ተሰበከ፣ (8) ሴቶች፣ ቀጣይ በሆነው በቤተ ክርስቲያን ሥራ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ለየት ባለ መንገድ ተጠቅሶአል፣ (9) አሸናፊነት፣ ምንም ዐይነት መሰናክል (ብሔራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ ወይም የዘር)፣ ምንም ዐይነት ተቃውሞ ወይም ስደት የወንጌል ሥርጭትን ማጨናገፍ አይችልም።

ሥነ ፍታቴያዊ መርሕ

አንዳንድ ተርጓሚዎች የሐዋርያት ሥራን የተረዱት በአዲስ ኪዳን ሥር ያለ ሌላ ኪዳን አድርገው ነው፣ ነገር ግን መረዳት የነበረባቸው አዲስ ኪዳን፣ "የመጨረሻው ቀን"

(ከ2፥17 እና ማገ ጋር ያነጻጽሩ) ብሎ በሚጠራው ዘመን ውስጥ ባለው አጠቃላይ ጊዜ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያስቀመጠውን መለኪያና ምስክርነቷን የሚያመለክት እንደ ሆነ ነው። የሐዋርያት ሥራ የጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚናገር መጽሐፍ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለክርስትና ሕይወትና በመንፈስ ቅዱስ ለተሞላች ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም መመሪያ መጽሐፍ ነው። አማኞች የአዲስ ኪዳን መጽሐፍን ከመጻፍ በስተቀር በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ልምምድ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያንም እንደ መመሪያ አድርጋ ትይዝ ዘንድ መሻትና መጠባበቅ ይኖርባቸዋል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ነፃል ስትንቀሳቀስ እውን ሊሆኑ ይችላሉ። ምልክቶች፣ ድንቆች፣ ታምራት፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች ወይም ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት የተሰጣት ሐዋርያዊ መለኪያና አገልግሎት በአጠቃላይ ለጊዜው ወይም በቋሚነት ከሐዋርያት ዘመን መጨረሻ በኋላ ድንገት እንዳበቁ የሚያመለክት ቦታ በሐዋርያት ሥራም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ፈጽሞ አይገኝም። ስለዚህ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጻፈው ነገር ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም ትውልድ በመንፈስ ቅዱስ የጴንጤ ቁስጤ ነፃል የኢየሱስን አገልግሎት እየቀጠለች ሳለ ምን መሆን እንዳለባትና ምን ማድረግ እንደሚገባት የሚያመለክት ነው (7፥44 እና ማገ ይመ)።

የሐዋርያት ሥራን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የሐዋርያት ሥራን ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ46 ቀን መነበብ ይኖርበታል።

❑ 1 ❑ 2፥1-36 ❑ 2፥37-47 ❑ 3 ❑ 4፥1-31 ❑ 4፥32—5፥11 ❑ 5፥12-42 ❑ 6 ❑ 7፥1-53
❑ 7፥54—8፥8 ❑ 8፥9-40 ❑ 9፥1-31 ❑ 9፥32-43 ❑ 10፥1-23 ❑ 10፥24-48 ❑ 11፥1-18
❑ 11፥19-30 ❑ 12 ❑ 13፥1-12 ❑ 13፥13-52 ❑ 14 ❑ 15፥1-21 ❑ 15፥22-35
❑ 15፥36—16፥15 ❑ 16፥16-40 ❑ 17፥1-15 ❑ 17፥16-34 ❑ 18፥1-23 ❑ 18፥24—19፥7
❑ 19፥8-41 ❑ 20፥1-26 ❑ 20፥27-38 ❑ 21፥1-16 ❑ 21፥17-36 ❑ 21፥37—22፥21
❑ 22፥22—23፥11 ❑ 23፥12-35 ❑ 24 ❑ 25፥1-12 ❑ 25፥13-26፥1 ❑ 26፥2-18 ❑ 26፥19-32
❑ 27፥1-26 ❑ 27፥27-44 ❑ 28፥1-16 ❑ 28፥17-31

ማስታወሻ

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐረገ

1 ቴዎፍሎስ ሆይ፤ ኢየሱስ ለማድረግና ለማስተማር የጀመረውን ሁሉ ቀደም ባለው መጽሐፌ ጽፌልሃለሁ፤ 2 ይኸውም እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ለመረጣቸው ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሰጣቸው ትእዛዝ ነው። 3 ከሕማማቱም በኋላ ራሱ ቀርቦ ሕያው መሆኑን፣ ለእነዚህ በብዙ ማስረጃ እያረጋገጠላቸው አርባ ቀንም ዐልፎ ዐልፎ እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገራቸው። 4 እነርሱም ጋር በማእድ ተቀምጦ ሳለ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ "ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤ 5 ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበር፤ እናንተ ግን ከዋቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ።"

6 እነርሱም ተሰብስበው ሳሉ፣ "ጌታ ሆይ፤ የእስራኤልን መንግሥት መልሰህ የምታቋቁምበት ጊዜው አሁን ነውን? ብለው ጠየቁት።

7 እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት ማወቁ ለእናንተ አልተሰማችሁም፤ 8 ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣

ሐሥ 2፡4-13

1፡5 ማር1፡4፡8 1፡6 ማቴ17፡11፡ ሐሥ3፡21
1፡7 ዘዳ29፡29፡ መዝ102፡13፡ ማቴ24፡36
1፡8 ማቴ28፡19፡ ሉቃ24፡48፡ ሐሥ2፡1-4፡ 8፡1-25

1፡1 **ቀደም ባለው መጽሐፌ**፤ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል (ሉቃ 4፡1፡18) ለማስተማርና ለማድረግ የጀመረውን ቀዳሚ ታሪክ እናገኛለን። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የኢየሱስ ተከታዮች በዚያው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ያንኑ ወንጌል እንደ ሰበኩ፣ ተመሳሳይ ታምራት እንዳደረጉና አንድ ዐይነት ሕይወት እንደ ኖሩ የሚያመለክት ቀጣይ ታሪክ እናገኛለን። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሥነ መለኮታዊ ቁልፍ ሐሳብ፣ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ሕይወትና አገልግሎት በጠቅ ክርስቲያን እንዲገለጥ ማድረጉ ነው። መጽሐፉ፣ "የመንፈስ ቅዱስ ሥራ" ተብሎ ሊጠራ ይችላል። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተጻፈውን የሚከተለውን ልብ ይበሉ፡

(1) ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለውን ታሪካዊ ትረካ ጨምሮ ትምህርታዊና ሥነ መለኮታዊ አስፈላጊነት አላቸው፤ ይህም በሚከተሉት ሁለት እውነቶች ይረጋገጣል፤ (ሀ) "ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያሰባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት፣ በጽድቅም መንገድ ለመቀጣር ይጠቅማሉ" (2ጢሞ 3፡16) በሚለው የእግዚአብሔር ቃል ዐዋጅ፤ (ለ) ሐዋርያው ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን ታሪካዊ ትረካዎች ለትምህርትና ለምክር የሚጠቅም ዐሳማ እንዳላቸው ተናግሮአል (1ቆሮ 10፡11)። እነዚህ ታሪኮች ለእግኙ ተግባራዊና ሥነ መለኮታዊ ጠቀሜታ ስላላቸው በምሳሌነት እንደሚረዱም በአጽንዖት ተናግሮአል (ሮሜ 15፡4)። በብሉይ ኪዳን ስለ ታሪካዊ ትረካ ቁቅም እውነት የሆነው ነገር በአዲስ ኪዳን ለሐ ዋርያት ሥራም እውነት ነው።

(2) ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተንቷን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሚከተለው መንገድ አቅርቦአል፤ እነርሱም (ሀ) በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሊከተሉት የሚገባ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ግልጽ መመሪያ፤ (ለ) የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮን ለመመሥረት የሚረዱ መረጃዎችና (ሐ) የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በክርስቶስ ከሚያምኑ ሰዎች ሕይወት ጋር እንዴት ሊዛመድ እንደሚችል የሚያሳይ መገለጥ ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሥነ መለኮታዊና በልምምድ ረገድ የታወቁ ሁለት ልዩ ጉዳዮችን ልብ ማለት ይገባል፤ (ፀ) ለአማኞች ሁሉ እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ቃል የገባላቸው በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት (2፡39 እና ማብ ይመ፤ ከ1፡5፡8፤ 2፡4፤ 4፡8፡31፤ 8፡15-17፤ 9፡17፤ 10፡44-46፤ 13፡9፡52፤ 15፡8፤ 19፡1-6 ጋር ያጻጽሩ)፤ (ፀ) በመጨረሻው ዘመን ማለትም በዚኑ ክርስቲያን ዘመን እግዚአብሔር በሕዝቡ ሕይወት እንዲሆን የሚሻውን የጽድቅ፣ የምስክርነትና የኀይል መለኪያን በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ለቤተ ክርስቲያን መስጠት።

1፡3 **እየታያቸው**፤ ማቴ 28፡9 እና ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ ስለ መታየቱ የተጻፈውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

1፡4 **አብ የሰጠውን ተስፋ**፤ አብ ሊሰጠን ቃል የገባልን ተስፋ (ኢል 2፡28-29፤ ማቴ 3፡11) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው (ቊ 5 እና ማብ ይመ)። የዚያ ተስፋ ቃል ፍጻሜ፣ "በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ" በሚለው ሐረግ ተገልጸአል (2፡4)። ስለዚህ፣ "በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ" እና "በመንፈስ ቅዱስ መሞላት" 1661 የሚሉት ሐረጉች አንዳንድ ጊዜ ቡተለዋዋጭነት በሐ ዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ።

በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ጉዳይ (በገጽ 1606 ላይ፣ "ጸጋም ልደት") ጊዜ ከምንቀበለው መንፈስ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ አይደለም። እነዚህ ሁለቱ አብዛኛውን ጊዜ በተለያየ ወቅት የሚከሠቱ የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ሥራዎች ናቸው (በገጽ 1646 ላይ፣ "የደቀ መዝሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል" በሚል ርእስ የቀረበውን የተከሩት ጽሑፍ ይመ)።

1፡5 **በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ**፤ በዚህ ዐረፍተ ነገር "በ" የሚለው መስተዋድድ "እን" የሚለው የግሪክ ትርጓሜ ሲሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ "በ ... ውስጥ" በሚል ይተረጐማል። ብዙዎች "በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ትጠመቃላችሁ" ተብሎ ቢተረጐም ይመርጣሉ። ልክ እንደዚህ "በውሃ መጠመቅ" የሚለው፣ "በውሃ ውስጥ መጠመቅ" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። አማኞችን በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ የሚያጠምቀው ኢየሱስ ራሱ ነው (ዮሐ 1፡33 እና ማብ ይመ)።

1፡8 **ኀይልን ትቀበላላችሁ**፤ ይህ ጥቅስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ወሳኝ የሆነ ቍልፍ ጥቅስ ነው። በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ዋና ዐላማ የክርስቶስ ምስክር መሆን ይቻል ዘንድ ኀይልን ለመቀበል ነው፤ ይህም የጠፉት ወደ እርሱ እንዲማረኩና ክርስቶስ ያዘዘውን ሁሉ ለመታዘዝ እንዲማሩ ያደርጋል። የመጨረሻው ውጤትም ክርስቶስ እንዲታወቅ፣ እንዲወደድ እንዲመሰገንና በእግዚአብሔር ምርጦች ሁሉ ላይ ጌታ እንዲሆን ማድረግ ነው (ከማቴ 28፡18-20፤ ከሉቃ 24፡49፤ ከሮሐ 5፡23፤ 15፡26-27 ጋር ያነጻጽሩ)።

(1) "ኀይል" (በግሪክ፣ "ዱናሚስ") ከጥንካሬ ወይም ከችሎታ በላይ ትርጕም ያለው ነው፤ ይህም ቡተለይ ኀይልን በእንቅስቃሴ ወይም በድርጊት የሚገልጽ ነው። ሉቃስ በወንጌሉና በሐዋርያት ሥራ በአጽንዖት

በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ

ሐሥ 1፥5 "ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ"

በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ በቅዱሳት መጻሕፍት ከተጠቀሱት ዐቢይ አስተምህሮዎች አንዱ ነው (1፥4 እና ማቅ እንዲሁም 1፥5 እና ማቅ ይመ)። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚከተሉትን ያስተምራል፡

(1) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በክርስቶስ ለሚያምኑ፣ ዳግም ለተወለዱና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆኑ ዘንድ ፈቃደኛ ለሆኑ ሁሉ የታሰበ ነው።

(2) ክርስቶስ በምድር ካሉት ቁልፍ ተልእኮዎቹ አንዱ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስ ማጥመቅ ነው (ማቴ 3፥11፣ ማር 1፥8፣ ሉቃ 3፥16፣ ዮሐ 1፥33)። ደቀ መዛሙርቱ ምስክርነታቸውን ከመጀመራቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንደሚገባቸውና ኀይል እስኪላበሱ ድረስ መቄዶት እንዳለባቸው መመሪያ ሰጥቶአቸው ነበር (ሉቃ 24፥49፣ ሐሥ 1፥4-5፣8)። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል እግዚአብሔር እስኪቀባው ድረስ አገልግሎቱን አልጀመረም (ሐሥ 10፥3 ይመ፣ ከሉቃ 4፥1፣18 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዳግም ልደት ጊዜ ከሚፈጽመው ሥራ ጋር የማይገናኝና የተለየ ሥራ ነው። የመቀደስ ሥራ መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ለመስጠት በፈጸመው ላይ ተጨማሪና የተለየ ሥራ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ለመስጠትና ለመቀደስ በፈጸመው ነገር ላይ ተጨማሪ ሥራ ነው። በትንሣኤው ቀን ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ በማለት፣ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" አላቸው (ዮሐ 20፥22)፣ ይህም የአዲሱ ሕይወት ማረጋገጫና የአዲስ ልደት ልምምድ ማስረጃ ነው (በገጽ 1646 ላይ፡ "የደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ከዚህም በኋላ የመንፈስ ቅዱስን "ኀይል መልበስ" እንደሚገባቸው ነግራቸው (ሉቃ 24፥49 ይመ፣ ከሐሥ 1፥5፣8 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ለደቀ መዛሙርት ከዳግም ልደት በኋላ ሊያልፉበት የሚገባ ልምምድ እንደ ሆነ ግልጽ ነው (ሐሥ 11፥17 እና ማቅ ይመ)። አንድ ሰው ገና በመንፈስ ቅዱስ ሳይጠመቅ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ሊያገኝና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሊሆን ይችላል (ሐሥ 19፥6 እና ማቅ ይመ)።

(4) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ነው (ከሐሥ 1፥5፣ 2፥4 ጋር ያወዳድሩ)። ይሁን እንጂ ይህ ጥምቀት በጸንጠ ቄስጤ ዕለት እና ከዚያ በኋላ ብቻ የሚፈጸም ነው። ከጸንጠ ቄስጤ ዕለት በፊት በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞሉት ሰዎች ሉቃስ ሲናገር (ለምሳሌ ሉቃ 1፥15፣67) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የሚለውን ቃል ፈጽሞ አልተጠቀመም። ይህ ሊሆን የሚችለው ክርስቶስ ካረገ በኋላ ብቻ ነበር (ሉቃ 24፥49-51፣ ዮሐ 16፥7-14፣ ሐሥ 1፥4)።

(5) በሐዋርያት ሥራ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በልሳን መናገራቸው ከመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ጋር የተያያዘ የመጀመሪያው ውጫዊ ምልክት ነው (ሐሥ 2፥4፣ 10፥45-46፣ 19፥6)። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ውጫዊ ምልክት ከሆነው በልሳን ከመናገር ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው፣ ስለዚህ ይህ ክሥተት የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ሲቀበሉ የሚገለጥ የተለመደ እውነታ ነው (በገጽ 1669 ላይ፣ "በልሳን መናገር" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(6) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ በአማኝ ሕይወት ውስጥ የድፍረትንና የኀይልን መንፈስ ያመጣል፣ ይህም በክርስቶስ ስም ታላቅ ሥራን ለመሥራት እንዲሁም ውጤታማ በሆነ መንገድ ወንጌልን ለመመስከርና ለመስበክ ያስችላል (ከሐሥ 1፥8፣ 2፥14-41፣ 4፥31፣ 6፥8፣ ከሮሜ 15፥18-19፣ ከ1ቆሮ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ኀይል በሰው ሕይወት ውስጥ የማይገለጥ አይደለም፣ ነገር ግን ኢየሱስ በክብሩና በሥራው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሕዝቡ ውስጥ ሀልውናውን የሚገልጥበት ነው (ዮሐ 14፥16-18፣ 16፥4፣ 1ቆሮ 12፥7)።

(7) እውነተኛ የሆነ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የሚያስገኛቸው ሌሎች ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡ (ሀ) ትንቢት መናገርና እግዚአብሔርን ማመስገን (ሐሥ 2፥14፣17፣ 10፥46፣ 1ቆሮ 14፥2)፣ (ለ) መንፈስ ቅዱስን ላለማሳዘን ኀጢአትን በእጅጉ መጸየፍ፣ ጽድቅን ለማግኘት ከፍተኛ የመሻት ጉጉትና እግዚአብሔር በርኩሰት ላይ የሚፈርደውን ፍርድ በሚገባ ማወቅ (ዮሐ 16፥8 እና ማቅ፣ ሐሥ 1፥8 እና ማቅ ይመ)፣ (ሐ) ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርን


የሚያመጣ ሕይወት (ዮሐ 16፥13-14፤ ሐሥ 4፥33)፤ (መ) አዳዲስ ራእዮች (ሐሥ 2፥17)፤ (ሠ) የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መገለጥ (1ቆሮ 12፥4-10)፤ (ረ) ለጸሎት የሚኖር ታላቅ ፍላጎት (ሐሥ 2፥41-42፤ 3፥1፤ 4፥23-31፤ 6፥4፤ 10፥9፤ ሮሜ 8፥26)፤ (ሰ) ለእግዚአብሔር ቃል የሚኖር ጥልቅ ፍቅርና ማስተዋል (ዮሐ 16፥13፤ ሐሥ 2፥42) እና (ሸ) እግዚአብሔር አባት እንደ ሆነ በይበልጥ መረዳት (ሐሥ 1፥4፤ ሮሜ 8፥15፤ ገላ 4፥6)።

(8) የእግዚአብሔር ቃል የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሊሰጥ የሚችልበትን የሚከተሉትን አያሌ ቅድመ ሁኔታዎች ይጠቅሳል፤ (ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ በእምነት በመቀበል ከኀጢአትና ከኃለም ዘወር ማለት ይገባናል (ሐሥ 2፥38-40፤ 8፥12-17)። ይህም ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር መስጠትን ይጠይቃል (“እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው” ሐሥ 5፥32)። ስለዚህ፣ “ለክቡር አገልግሎት የሚውል፣ የተቀደሰ፣ ለጌታው የሚጠቅም፣ ለመልካም ሥራም ሁሉ የተሰናዳ ዕቃ” (2ጢሞ 2፥21) ከመሆናችን በፊት እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ነገር ዘወር ማለት ይገባናል። (ለ) ለመሞላት መሻት ይኖርብናል። ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ ከፍተኛ ረሀብ ሊኖራቸው ይገባል (ዮሐ 7፥37-39 ይመ፡ ከኢሳ 44፥3፤ ከማቴ 5፥6፤ 6፥33 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ሐ) አብዛኛውን ጊዜ ይህን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የምንቀበለው የጸሎት መልስ ሆኖ ነው (ሉቃ 11፥13፤ ሐሥ 1፥14፤ 2፥1-4፤ 4፥31፤ 8፥15፡17)፤ (መ) እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቀን በማመን መጠበቅ ይኖርብናል (ማር 11፥24፤ ሐሥ 1፥4-5)።

(9) በአማኝ ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቀጣይነቱ ሊጠበቅ የሚችለው በጸሎት (ሐሥ 4፥31)፣ በምስክርነት (4፥31፡33)፣ በመንፈስ በማምለክ (ኤፌ 5፥18-19) እና በተቀደሰ ሕይወት ነው (ኤፌ 5፥18 እና ማብ ይመ)። በአማኝ ሕይወት ላይ የወረደው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል የቱንም ያህል ታላቅ ቢሆን በጸሎት ሕይወት፣ በምስክርነትና በተቀደሰ አኗኗር የሚገለጽ ካልሆነ ታይቶ የሚጠፋ ክብር ከመሆን በቀር ፋይዳ አይኖረውም።

(10) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በአማኝ ሕይወት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ የሚከሠት ሲሆን፣ አማኝ የእግዚአብሔርን ሥራ ቡነይልና በጽድቅ ሊመሰክር ወደሚችልበት ቅድስና ይመራዋል። አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቀ በኋላ አዳዲስ ሙላቶች በተከታታይ ሊቀበል እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (ሐሥ 4፥31 እና ማብ ይመ፡ ከ2፥4፤ 4፥8፡31፤ 13፥9፤ ከኤፌ 5፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድን አማኝ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር (ኤፌ 5፥18) ሊታደስ የሚችልና (4፥31) ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ወደሚያደርግበት ሁኔታ ውስጥ ያስገባዋል።

በጰንጠ ቆስጤ ቀን የተጠቀሱ ሰዎች አገሮች



© 1989 The Zondervan Corporation

በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።"

⁹ይህን ካለ በኋላ እያዩት ወደ ላይ ዐረገ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረችው።

¹⁰እርሱም በሚሄድበት ጊዜ ትኵር ብለው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ፣ እነሆ፤ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት አጠገባቸው ቆሙ፤ ¹¹እንዲህም አሏቸው፤ "እናንት የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድን ነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል።"

1፡9 ዮሐ2፡ ማር16፡19
1፡10 ዮሐ20፡12 1ዮሐ1፡1 ማቴ16፡27፡ ሐሥ2፡7
1፡12 ማቴ21፡1፡ ሉቃ24፡52
1፡13 ማቴ10፡2-4፡ ማር3፡16-19፡ ሉቃ6፡14-16፡ ሐሥ9፡37፡ 20፡8
1፡14 ማቴ12፡46፡ ሉቃ18፡1፡ 23፡49፡55፡ ሐሥ2፡42፡ 4፡24፡ 6፡4፡

ማትያስ በይሁዳ ምትክ ተመረጠ

¹²ከዚያም ደብረ ዘይት ከተባለው ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ይህም ተራራ ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል[ሀ] ይርቅ ነበር። ¹³ወደ ከተማዪቱም በገቡ ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፤ እነዚህም ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ያዕቆብ፣ እንድርያስ፣ ፊልጶስ፣ ቶማስ፣ በርተሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ የአልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ቀናኢ የተባለው ስምዖንና የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ነበሩ። ¹⁴እነዚህ ሁሉ ከሴቶቹና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ጋር እንዲሁም ከወንድሞቹ ጋር በአንድ ልብ

1፡14 ሮሜ1፡10

ሀ 1፡12 አንድ ሺህ አንድ መቶ ሜትር ገደማ ነው።

የተናገረው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ርዮስ መናፍስትን ለማስወጣት የሚያስችል ሥልጣን እንዲሁም በሽተኞችን ለመፈወስ የፈለስልንን ቅባት ያካተተ ሲሆን፣ እነዚህም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማወጅ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ምልክቶች ናቸው (ለምሳሌ ሉቃ 4፡14፤18፡36፤ 5፡17፤ 6፡19፤ 9፡1-2፤ ሐሥ 6፡8፤ 8፡4-8፤12-13፤ 10፡38፤ 14፡3፤ 19፡8-12)። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በአማኝ ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚለቀቅበት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (በገጽ 1664 ላይ፡ *"በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ሉቃስ በዘሁ ስፍራ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ያያያዘው ከደኅንነትና ከዳግም ልደት ጋር ላይሆን፣ ታላት የምስክርነት ውጤት ለማስገኘት በአማኝ ሕይወት ውስጥ ከሚገለጠው ኀይል ጋር ነው (በገጽ 1646 ላይ፣ *"የደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) በምስክርነትና ወንጌልን በማወጅ ረገድ ያለው የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ ሥራ ኀይልን ለመስጠት ወደ አማኞች ሕይወት ሙግቱን እንዲሁም የክርስቶስን የሚዳን ሥራና ትንሣኤ መመስከሩን የሚመለክት ነው (ከ2፡14-42 ጋር ያነጻጽሩ)። መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚመሰክርና ያም በግል ሕይወታችን ምን ትርጕም እንዳለው ለመረዳት የሚቀጥለውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

1፡8 ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፤ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ኢየሱስ ጌታና አዳኝ መሆኑን ለመስበክ የሚያስችል ኀይልን የሚያስተላልፍ ላይሆን (ያለፈውን ማብ ይመ)፡ የዚያን ምስክርነት ውጤታማነት በይበልጥ የሚጨምር ነው፤ ይህም የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት የተነሣ ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚፈጠረው የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት ነው (ከዮሐ 14፡26፤ 15፡26-27 ጋር ያነጻጽሩ)።

(1) መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ሀልዎት በግል ይበልጥ ግልጽና እውን ያደርግልናል (ዮሐ 14፡16-18)። ከራሱ ከኢየሱስ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲኖረን የሚያደርግ ግንኙነውም ምስክርነት ውጤቱ በእኛ በኩል አዳኛችንን ለመውደድ፣ ለማክበርና ደስ ለማሰኘት ያለንን ፍላጎት የሚጨምር ነው (በገጽ 1679 ላይ፡ *"የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን በቃል ብቻ ሳይሆን በድርጊትም ሞምር ለማክበር በሚያስችል ሁኔታ (ዮሐ 16፡14) ጽድቅንና (ዮሐ 16፡8፡10) እውነትን (ዮሐ 16፡13) በአማኝ ሕይወት ይመሰክራል። ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት የተቀበልን ሁላችን በሕይወታችን የማይ ክርስቶስን መምሰልን፣ ፍቅርን፣ እውነትንና ጽድቅን ማግለጥ ይኖርብናል (ከ1ቆሮ 13 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማኞች ስለ ክርስቶስ እንዲመሰክሩ እና የጠፋትን ስለ ነጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ለመውቀስ የሚያስችል ኀይል በመጀመሪያ የሚቀበልበት ክሥተት ነው (የሐ 16፡8 እና ማብ ይመ)። የእንደዚህ ዐይነት ለውጥ ውጤት መልእክቱን በታማኝነት በሚያውጁትም ሆነ በሚቀበሉት ሰዎች በግልጽ ይታያል (2፡39-40)።

(4) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚሰጠው ከክፉ መንገዳቸው በንስሓ ተመልሰው ልባቸውን ወደ እግዚአብሔር ላቀኑት ብቻ ነው (2፡38፤ 3፡26)። እሳቱ ሳይጠፋ ሊቀጥል የሚችለውም ተመሳሳይ በሆነ መሰጠት ለክርስቶስ በመገዛት ነው (5፡32 እና ማብ ይመ)።

(5) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፣ ቅዱስ በሆነው መንፈስ ውስጥ መጠመቅ ነው (*"ከቅድስና መንፈስ"* ጋር ያነጻጽሩ፡ ሮሜ 1፡4 ይመ)። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ባለው ሙላት ሁሉ በእውነት በሕይወታችን ቢሠራ፣ ከክርስቶስ ቅድስና ጋር በእጅጉ የሚስማማ ሕይወት ይኖረናል።

ከእነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች አንጻር፣ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቅነው እኛ በተቻለን መጠን ክርስቶስን ለማስደሰት ከፍተኛ ምኞት ይኖረናል፣ ማለትም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የማጸንንና የመቀደስን ሥራ ወደ ፍጻሜ ያደርሳል ማለት ነው። በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ የሚናገሩ፣ ነገር ግን ከቅድስና መንፈስ ጋር የሚጻረር ሕይወት የሚኖሩ የሳቱና እውነተኛ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። መንፈሳዊ ስጦታዎችን፣ ታምራትን፣ ለየት ያሉ ምልክቶችን ወይም የሚመስጡ ንግግሮችን የሚገልጡ ነገር ግን እውነተኛ እምነት፣ ፍቅርና ጽድቅ የሌላቸው እነዚህን የሚያከናውኑት በመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ባልሆነ ርዮስ መንፈስ ነው (ማቴ 7፡21-23 ይመ፡ ከማቴ 24፡24፡ ከ2ቆሮ 11፡13-15 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1694 ላይ፣ *"እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ስለ ክርስቶስ ምስክርነት የበለጠ ለመረዳት 13፡31 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

1፡14 በአንድ ልብ ሆነው ያለማቋረጥ ተግተው ይጸልዩ ነበር፤ የአንጠ ቄስጤ ልምምድ ምንጊዜም ቢሆን ሰው ሊያደርገው የሚገባውን የኀላፊነት ድርሻ መፈጸምን ይጠይቃል። በጎይል ተሞልተው የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት መንፈስ ቅዱስ

ሆነው ያሰማቂረጥ ተግተው ይጸልዩ ነበር።
15በእነዚያም ቀናት፣ ጴጥሮስ መቶ ሃያ
በሚሆኑ ወንድሞች^ መካከል ቆሞ፣ 16እን
ዲህ አለ፤ "ወንድሞች ሆይ፤ ኢየሱስን
ለያዙት ሰዎች መሪ ስለ ሆናቸው ስለ
ይሁዳ፣ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት
አፍ የተናገረው የመጽሐፉ ቃል መፈጸም
ስላለበት፣ 17እርሱ ከእኛ አንደ አንዱ
ተቈጥሮ በዚህ አገልግሎት የመሳተፍ ዕድል
አግኝቶ ነበር።"
18ይህ ሰው ስለ ክፉ ሥራው በተከፈለው
ዋጋ መሬት ገዛ፤ በዚያም በግንባሩ ተደፍቶ
ሰውነቱ እመካከሉ ላይ ፈንዳ፤ ሆድ ዕቃውም
ተዘረገፈ፤ 19ይህም በኢየሩሳሌም በሚኖሩት
ሁሉ ዘንድ ተሰማ፤ መሬቱም በቋንቋቸው
'አኬልዳማ' ተብሎ ተጠራ፤ ትርጓሜውም
'የደም መሬት' ማለት ነው።
20ጴጥሮስም በመቀጠል እንዲህ
አለ፤ "በመዝሙር መጽሐፍ፣
'መኖሪያው ባዶ ትሁን፤
የሚኖርባትም ሰው አይገኝ'
ደግሞም፣
'ሹመቱን ሌላ ሰው ይውሰደው'
ተብሎ ተጽፎአል።
21ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በመካከላችን በገባበትና
በወጣበት ጊዜ ሁሉ፣ ከእኛ ጋር ከነበሩት
መካከል አንድ ሰው መምረጥ ያስፈልጋል፤
22ይኸውም፣ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ
ኢየሱስ ከእኛ ተለይቶ እስከረገበት ቀን
ድረስ የነበረ መሆን አለበት፤ ምክንያቱ ሰው

1፡16 ቍ.20፣ ማቴ 1፡22፣ 10፡4፣ ሐሥ 6፡3፣ 11፡1፤ 12፡29፣ 14፡2፣ 18፡18፤ 27፡21፣ 7፣ 22፡5፣ ሮሜ 7፡1
1፡17 ቍ.25፣ ዮሐ 6፡70፤ 71
1፡18 ማቴ 26፡14፤ 15፣ 27፡3-10
1፡19 ዮሐ 5፡2
1፡20 መዝ 69፡25፣ 109፡8
1፡22 ቍ.8፣ ማር 1፡4፣ ሉቃ 24፡48

1፡24 1ሳሙ 14፡41፣ ሐሥ 6፡6፣ 13፡3፣ 14፡23፣ ራእ 2፡23
1፡26 ሐሥ 2፡14
2፡1 ዘሌ 23፡15፤ 16፣ ሐሥ 1፡14፣ 20፡16፣ 1ቆሮ 16፡8
2፡2 ሐሥ 4፡31
2፡4 ማር 16፡17፣ ሉቃ 1፡15

ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው
ምስክር እንዲሆን ያስፈልጋል።"
23ስለዚህ ኢዮስጦስ የሚሉትን፣ በርስያን
የተባለውን ዮሴፍንና ማቲያስን ሁለቱን
አቀረቡ፤ 24እንዲህም ብለው ጸለዩ፤ "ጌታ
ሆይ፤ አንተ የሰውን ሁሉ ልብ ታውቃለህ፤
ከእነዚህ ከሁለቱ መካከል የመረጥ፣ውን
ሰው አመልክተንና 25ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ
ስፍራ ትቶት በሄደው በዚህ አገልግሎትና
በሐዋርያዊነት ቦታ ላይ ሹመው።" 26ከዚያም
ዕጣ ጣሉላቸው፤ ዕጣውም ለማትያስ ወጣ፤
እርሱም ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር
ተቈጠረ።

በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ወረደ

2 የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም
በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስበው
ነበር፤ 2ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ
ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው
የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው። 3የእሳት
ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤
ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ወረፉ።
4ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈ
ስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች
ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር።

^1፡15 ወይም አማኞች
^2፡4 ወይም ልሳኖች እንዲሁም በቍ 11

እንዲወርድባቸው የሚፈልጉ ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመገዛት ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል (ቍ 4፡ 2፡38፣ 9፡11-17፣ ከኢሳ 40፡29-31፣ ከሉቃ 11፡5-13፣ 24፡49 ጋር ያነጻጽሩ)። መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ የወረደበትን እና መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርት ላይ የወረደበትን ተመሳሳይ ሁኔታ ልብ ይበሉ፡ (1) ከጸለዩ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ላይ ወረደባቸው (ሉቃ 3፡21-22፣ ሐሥ 1፡14፣ 2፡4)፣ (2) የመንፈስ ቅዱስን መውረድ የሚያሳዩ ተጨባጭ ክሥተቶች ነበሩ (ሉቃ 3፡22፣ ሐሥ 2፡2-4)፣ (3) የኢየሱስም ሆነ የደቀ መዛሙርቱ አገልግሎት የጀመረው መንፈስ ቅዱስ ከወረደባቸው በኋላ ነበር (ማቴ 3፡16 ከ4፡17፣ ሉቃ 3፡21-23 ከ4፡14-19 ጋር ያወዳድሩ፣ ከሐሥ 2፡14-47 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፡1 የበዓለ ኀምሳ ቀን፤ ጸንጠ ቄስጤ የሚባለው ከአይሁድ ዓመታዊ በዓላት ውስጥ ሁለተኛው ትልቁ በዓል ነው። ይህም ከአሀል ቀኖረባን የበኩራት ስመታ ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት የመከር በዓል ነው (ከዘሌ 23፡17 ጋር ያነጻጽሩ)። በተመሳሳይ ሁኔታ ጸንጠ ቄስጤ ለቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ ያሉ ነፍሳት የእግዚአብሔር መከር በመሆን የሚሰበሰቡበት ጅማሬ ነው።

2፡2-3 ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ... የእሳት ምላሶች፤ እነዚህ ውጪአዊ ምልክቶች እግዚአብሔር በታላቅ ኀይል እየሠራ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው (ከዘፀ 3፡1-6፣ ከ1ነገ 18፡38-39 ጋር ያነጻጽሩ)። «እሳት» ለክርስቶስ ክብርን የሚያመጣ ሥራ እንዲያከናውኑ (ዮሐ 16፡13፤14) እና ለእርሱም ምስክር እንዲሆኑ (ሐሥ 1፡8) እግዚአብሔር አማኞችን የሚቀድስበትንና የሚለይበትን ኀይል የሚያመለክት ነው። እነዚህ ሁለት ውጪአዊ ምልክቶች ደቀ መዛሙርት በበዓለ ኀምሳ ቀን በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁ ጊዜ በቅድሚያ የተከሠቱ ሲሆኑ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሌላ ስፍራ ተደግመው እናይዎ።

2፡4 በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ በጸንጠ ቄስጤ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት አስፈላጊነት ምንድነው? (1) በመጪረሻው ዘመን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳስሁ የሚለው በኢል 2፡28-29 የተነገረው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መፈጸም ጅማሬ በመሆኑ የተለየ ትርጉም አለው (ከ1፡4-5፣ ከማቴ 3፡11፣ ከሉቃ 24፡49፣ ከዮሐ 1፡33 ጋር ያነጻጽሩ፤ ኢል 2፡28-29 እና ማብ ይመ)።

(2) የዚህ ዘመን የመጪረሻዎቹ ቀናት በመጀመራቸው (ቍ. 17 ይመ፣ ከዕብ 1፡2፣ ከ1ጴጥ 1፡20 ጋር ያነጻጽሩ) ሰው ሁሉ ንስሓ ለመግባትና በክርስቶስ ለማመን ውሳኔ ማድረግ ከሚጠይቅ ሁኔታ ጋር ተፋጠአል (3፡19፣ ማቴ 3፡2፣ ሉቃ 13፡3፣ ሐሥ 2፡17 እና ማብ ይመ)።

(3) ደቀ መዛሙርት፣ ኀይልን ከላይ ለብሰው ነበር (ሉቃ 24፡49፣ ከሐሥ 1፡8 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ይህም ለክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ እንዲሁም ኀጢአትን፣ ጽድቅንና የእግዚአብሔርን ፍርድ በተመለከተ የጠፋትን ይወቅስ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የሚጠቀምባቸውና የጠፋትንም ኮነኒአት በክርስቶስ ወደሚገኘው ድኅነት እንዲመልሱ ያስችላቸዋል (ከ1፡8 እና ከማብ ጋር ያነጻጽሩ፤ 4፡13፡33፣ 6፡8፣ ሮሜ 15፡19፣ ዮሐ 16፡8 እና ማብ ይመ)።

(4) መንፈስ ቅዱስ በዓለም ሁሉ ያሉ ሰዎች ይድኑ ዘንድ የሚሄፍቅና የሚጥር መንፈስ እንደ መሆኑ

በልሳን መናገር

ሐሥ 2፥4 "ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፥ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር።"

በልሳን መናገር ወይም "ግሎሳላልያ" (ግሪክ፡ "ግሎሳይስ ላሌ") በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቃቸው ጋር ተያይዞ የሚመጣ የእግዚአብሔር ስጦታ ምልክት እንደ ሆነ ይታመንበል (ሐሥ 2፥4፥ 10፥45-47፥ 19፥6 ይመ)። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ በመንፈስ ቅዱስ ለተሞላ ሕይወት ዛሬም ቢሆን የሚሠራ ነው።

በእውነተኛ ልሳን መናገር፤ (1) ልሳን እንደ መንፈስ ቅዱስ መገለጫ፡ በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ዲበ ተፈጥሮአዊ መገለጫ ነው፥ ይህም ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ንግግር ሲሆን፣ አማኞች ባልተማሩት ቋንቋ (ግሪክ፡ ግሎሳ) የሚናገሩት ነው (ሐሥ 2፥4፥ 1ቆሮ 14፥14-15)። ይህ ቋንቋ በምድር ካሉት ሰዎች ከሚናገሩባቸው ቋንቋዎች አንዱ ሊሆን ይችላል (ሐሥ 2፥6)፥ ወይም ፈጽሞ በምድር ያልታወቀ ቋንቋ ሊሆን ይችላል (ከ1ቆሮ 13፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። በአንዳንድ ትርጉሞች ተገልጸ እንደታየው "ስሜታዊ የፍንደቃ ንግግር" አይደለም፥ መጽሐፍ ቅዱስ በልሳን መናገርን ለመግለጽ "ስሜታዊ የፍንደቃ ንግግርን" ፈጽሞ ተጠቅሞ አያውቅምና።

(2) ልሳን በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ የመጀመሪያው ውጫአዊ ምልክት እንደ ሆነ፡ በልሳን መናገር የአማኝ መንፈስና መንፈስ ቅዱስ ተገናኝተው በምስጋና ቃልና በትንቢት የሚገልጹት መንፈሳዊ ንግግር ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር በልሳን መናገርን ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር አያይዞታል፡ ስለዚህ በጸንጠ ቄስጤ ዕለት የነበሩትና በኋላም ያሉት አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን እንደተቀበሉ የሚያረጋግጥ ልምምድ አግኝተዋል ማለት ነው (ከሐሥ 10፥45-46 ጋር ያነጻጽሩ)። እንግዲህ ይህ ልምምድ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን የምንቀበልበትን ቦታና ጊዜ በተጨባጭ ያመለክታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማረጋገጫ ምልክት መሆኑ ሲካድ ወይም ከሐሳብ ሲጠፋ የጸንጠ ቄስጤ እውነትና ልምምድ ተሳሞአል ወይም ሙሉ በሙሉ ቸል ተብሎአል ማለት ነው።

(3) ልሳን እንደ ስጦታ፡ በልሳን መናገር ለአማኝ የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሆነም ተገልጸአል (1ቆሮ 12፥4-10)። ይህ ስጦታ የሚከተሉት ሁለት ዐላማዎች አሉት፡ (ሀ) በልሳን መናገር ከንትርጓሚው ከቀረበ በቤተ ክርስቲያን አምልኮ ውስጥ የቋንቋውን መልእክት ለጉባኤው ለማስተላለፍ ይጠቅማል፡ ስለዚህ ሁሉም ሰው መንፈስ ቅዱስ ወደሚመራው አምልኮ፣ ምስጋና ወይም ትንቢት ውስጥ ይገባል (1ቆሮ 14፥5-6፡13-17)፥ (ለ) በልሳን መናገር ለአማኝ የሚጠቅመው አማኝ በግል አምልኮው ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገርና መንፈሳዊ ሕይወቱንም ለማነጽ ነው (1ቆሮ 14፥4)፡ ይኸውም መንፈስ ቅዱስ እንደ ፈቀደው ደረጃ በመናገር ስጦታውን ለጸሎት (14፥2፡14፡15፡28)፣ ምስጋናን ለመስጠት (14፥16-17) ወይም ለዝማሬ (14፥15 እና ግብ እንዲሁም (በገጽ 1800 ላይ፥ "ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ዐላማ እንዲውል ማድረግ ነው።

በሐሰተኛ ልሳን መናገር፤ "በሌሎች ልሳኖች" መናገር ወይም ሌላ ዲበ ተፈጥሮአዊ መገለጥ ሚማንት ብቻ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ለመሥራቱና ለመኖሩ በቂ ማስረጃ ሊሆን አይችልም። በልሳን መናገር ከሰው ሐሳብ ወይም ከአጋንንታዊ አሠራር በመፍለቅ በማስመሰል ሊገለጥ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ማንኛውንም መንፈስ ማመን እንደሌለብን፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ልምምዳችን በእርግጥ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ መፈተን እንደሚገባን ያስጠነቅቀናል (1ዮሐ 4፥1 እና ማብ ይመ)።

(1) ትክክለኛ ለመሆን በልሳን መናገር፣ "መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን" (ሐሥ 2፥4) በሚለው መሠረት መሆን አለበት። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተለመደውን አሠራር መከተል ከተፈለገ፣ በልሳንመናገር ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ድንገት የሚፈጸም የመጀመሪያው ከሥፋት ነው። አማኞች ሠልጥነው ወይም ተምረው የሚናገሩት ቋንቋ አይደለም።

(2) መንፈስ ቅዱስ በመጨረሻው ቀን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የግብዝነት ሁኔታዎች (1ጢሞ 4፥1-2)፣ ከሰይጣን ጎይላት የሚሰጡ ምልክቶችና ድንቆች (ማቴ 7፥22-23 ይመ፡ ከ2ተሰ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ)፣ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን በመምሰል የሚሠሩ አታላይ

ሠራተኞች እንደሚኖሩ በግልጽ በማስጠንቀቅ ተናግሮአል (2ቆሮ 11፥13-15)። እነዚህን ማስጠንቀቂዎች በጥንቃቄ ማስተዋል የሚገባን በማስመሰል የሚፈጸሙ መንፈሳዊ መገለጦችና ምልክቶች ስለሚኖሩ ነው (ማቴ 7፥22-23፣ 2ተስ 2፥8-10)።

(3) በልሳን የምንናገረው ትክክለኛ መሆን አለመሆኑን ለመለየት ማለትም በእውነት ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጹትን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ውጤት የሆኑትን ነገሮች መመልከት ይኖርብናል (በገጽ 1694 ላይ፣ "እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በልሳን እናገራለሁ የሚል ነገር ግን ሕይወቱን ለክርስቶስና ለቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ያላስገዛ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ጥረት የማያደርግ፣ ምንም ዐይነት መገለጥ በሕይወቱ ቢከሠት ያ ከመንፈስ ቅዱስ አይደለም (1ዮሐ 3፥6-10፣ 4፥1-3 ይመ፣ ከማቴ 24፥11፣24፣ ከሥሐ 8፥31፣ ከገላ 1፥9 ማብ ጋር ያነጻጽሩ)።

5በዚህ ጊዜ ከሰማይ በታች ካለው
ሕዝብ ሁሉ የመጡና እግዚአብሔርን የሚፈሩ
አይሁድ በኢየሩሳሌም ነበሩ። 6ይህን ድምፅ
ሲሰሙ፣ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፤
እያንዳንዱም ሰው፣ ሰዎቹ በገዛ ቋንቋው
ሲናገሩ በመስማቱ ግራ ተጋባ፤ 7በመገረ
ምና በመደነቅም እንዲህ አሉ፤ "እነዚህ
የሚነጋገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉ
ምን? 8ታዲያ፣ እያንዳንዳችን በተወለድን
በት፣ በራሳችን ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማቸው
እንዴት ቢሆን ነው? 9እኛ የጳርቴና፣
የሜድ፣ የኢላሜጢም ሰዎች፣ በመስጴጦ
ምያ፣ በይሁዳ፣ በቀጰዶቅያ፣ በጳንጦስ፣
በእስያ፣ 10በፍርግያ፣ በጵንፍልያ፣ በግብፅ፣
በቀሬና አጠገብ ባሉት በሊቢያ አውራጃዎች
የምንኖር፣ ከሮም የመጣን 11አይሁድና
ወደ ይሁዲነት የገባን፣ የቀርጤስና የዐረብ
ሰዎች ስንሆን፣ ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ታላቅ
ሥራ በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን!"
12ሁሉም በአድናቆትና ግራ በመጋባት፣
"ይህ ነገር ምን ይሆን?" ተባባሉ።

2፥5 ሉቃ2፥25፣
ሐሥ8፥2
2፥7 ቁ*12፣
ሐሥ1፥11
2፥9
ሐሥ16፥6፡17፥
18፥2፣ 19፥10፣
ሮሜ16፥5፣
1ቆሮ16፥19፣
2ቆሮ1፥8፣
1ጴጥ1፥1፣
ራእ1፥4
2፥10
ማቴ27፥32፣
ሐሥ13፥13፣
14፥24፣ 15፥38፣
16፥6፣ 18፥23፣

2፥13
1ቆሮ14፥23፣
ኤፌ5፥18
2፥15 1ተሰ5፥7
2፥17 ሆዕ1፥25፣
ኢሳ44፥3፣
ሕዝ39፥29፣
ዮሐ7፥37-39፣

13እንዳንዶቹ ደግሞ "ያልፈላ ብዙ የወይን
ጠጅ ጠጥተዋል" በማለት አፌዙባቸው።

ሐሥ 2፥39

ጴጥሮስ ለሕዝቡ ንግግር አደረገ

14በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ከዐሥራ አንዱ ጋር
ተነሥቶ ቆመ፤ ድምፁንም ከፍ አድርጎ
እንዲህ ሲል ለሕዝቡ ተናገረ፤ "አናንት
የይሁዳ ሰዎችና፤ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ
ሁሉ፤ ይህን አንድ ነገር ዕወቁ፤ በጥሞናም
አድምጡ። 15ጊዜው ገና ከጠዋቱ ሦስት
ሰዓት ስለ ሆነ፣ እናንተ እንደምታስቡት
እነዚህ ሰዎች አልሰከሩም። 16ነገር ግን ይህ
በነቢዩ በኢዩኤል እንዲህ ተብሎ የተነገረ
ነው፤

17"'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው
ቀን፣
መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ
አፈሳለሁ፤

2፥17 ሐሥ10፥45፣ 21፥9
*2፥13 ወይም ባሉ-ም ወይን

ለአማኞች ባደረገው ነገር ይሆኑ ባሕርዩን ገልጦአል። በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ አማኞችም የሰው ዘር ሁሉ እንዲድን በማሰብ ተመሳሳይ በሆነ ናፍቆት ይሞላሉ (ቊ 38-40፣ 4፥12፡33፣ ሮሜ 9፥1-3፣ 10፥1)። ስለዚህ ጳንጠ ቄስጠ ወደ ዓለም ሊላክ የሚገባው የወንጌል ተልእኮ ጅማሬ ነው (ቊ 6-11፡39፣ 1፥8)።

(5) ደቀ መዛሙርት የመንፈስ ቅዱስ አገልጋዮች ሆኑ። ኢየሱስ በመስቀል እንደሞተና ከሞት እንደ ተነሣ በመስበክ ሌሎችን ወደ ንስሓና በክርስቶስ ወደ ማመን ብቻ አልመሩም፣ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸው በጳንጠ ቄስጠ ዕለት የተቀበሉትን "የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ" (ቊ 38-39) አዲስ አማኞችም ይቀበሉ ዘንድ ያደላቸው ነበር። ይህ ሌሎችን ወደ መንፈስ ቅዱስ ሞሞቀት የመሙራት አገልግሎት በአዲስ ኪዳን ላለው ሐዋርያዊ ሥራ ቁልፍ ነገር ነው (8፥17፡ 9፥17-18፣ 10፥44-46፡ 19፥6 ይመ)።

(6) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃቸው የክርስቶስ ተከታዮች የእርሱ ምድራዊ አገልግሎት ተተኪዎች ሆኑ። "ኢየሱስ ለማድረግና ለማስተማር የጀመረውን" (1፥1፣ ዮሐ 14፥12 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1527 ላይ፣ "አማኞች ሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ተጨማሪ ነገር በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ማድረግና ማስተማር ቀጠሉ።

2፥4 በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር፤ በጳንጠ ቄስጠ ዕለትም ሆነ በሌላ ስፍራ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን በልሳን የመናገርን ትርጕም እንዲሁም በሐሰተኛ ልሳን የመናገርን ሁኔታ በተመለከተ ማንዛቢ ለማግኘት (በገጽ 1669 ላይ፣ "በልሳን መናገር" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ)።

2፥13 የወይን ጠጅ፤ "ጣፋጭ የወይን ጠጅ" (ግሪክ፡ ግሉኮስ) ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው ያልፈላውን የወይን ጭማቂ ነው። በደቀ መዛሙርቱ ላይ ሲያፈሱ የነበሩት ሰዎች አዲስ ኪዳን የወይን ጠጅን ከሚገልጽበት ከተለመደው ቃል (አይናስ) ይልቅ ይህንን ቃል ሳይጠቀሙ አልቀሩም፤ ይኸውም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሲጠቀሙበት የነበረው የወይን ጠጅ ይኸኛው ወይኑት ይሆናል ብለው ስላሙ ነበር። በዚህ ሁኔታም እነርሱ ያፈዙት በእኽሙር ነበር ማለት ነው።

2፥14–40፤ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተጠቀሰው በጳንጠ ቄስጠ ዕለት ጴጥሮስ ያቀረበው መልእክት ነው። ጴጥሮስ በዚህ ጊዜና በ3፥11-26 ባቀረበው መልእክት ውስጥ ለወንጌል ዐዋጅ መመሪያ የሆነውን ነገር በዝርዝር እንደማከተለው ጠቅሰአል፤

(1) ኢየሱስ ጌታም ክርስቶስም ነው ይኸውም በመስቀል ሞተ፤ ከሞት ተነሣ፤ እንዲሁም በክብር ከፍ ከፍ አለ (ቊ 22-36፣ 3፥13-15 ይመ)።

(2) አሁን በአባቱ ቀኝ ሆኖ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በአማኞች ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስን የማፍሰስ ሥልጣን አግኝቶአል (ቊ 16-18፡32-33፣ 3፥19 ይመ)።

(3) ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በመረዳት ማንም ሰው እምነቱን በእርሱ ላይ ሚድረግ አለበት፣ ኀጢአቱ መናዘዝ እንዲሁም የኀጢአት ይቅርታ ከሚገኝትም ባሻገር መጠመቅ ይኖርበታል (ቊ 36-38፣ 3፥19 ይመ)።

(4) ከማመንና ከኀጢአት ንስሓ ከመግባት ባሻገር አማኞች በተሰፋ የሚጠበቀውን ስጦታ ወይም የመንፈስ ቅዱስን ሞሞቀት መጠባበቅ ይኖርባቸዋል (ቊ 38-39 ይመ)።

(5) ሰምተው ያመኑ ሁሉ ራሳቸውን ከዓለም መለየት ይኖርባቸዋል፣ ከዚህ በኀጢአት ከተበከለ ትውልድም መዳን ይገባቸዋል (ቊ 40፡ 3፥26 ይመ)።

(6) የእግዚአብሔርን መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለመመሥረት ኢየሱስ ክርስቶስ ይመለሳል (3፥20-21 ይመ)።

2፥16 በነቢዩ በኢዩኤል እንዲህ ተብሎ የተነገረ ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና አብረውት የሚመጡት መንፈሳዊ መገለጦች በኢዩኤል 2፥28-29 ላይ የተሰጠው ተስፋ ፍጻሜዎች ናቸው (በዚያ ምንባብ ላይ ያለውን ማብ ይመ)።

2፥17 በመጨረሻው ቀን፤ (1) በብሉይ ኪዳን፣ "የመጨረሻው ቀን" ሲባል እግዚአብሔር በታሳቅ ኀይል በክፉ ላይ ሊፈርድና ለሕዝቡ ደኅንን ለማምጣት እንቅስቃሴ የሚያደርግበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው (ከኢሳ 2፥2-21፡ 3፥18-4፥6፡ 10፥20-23፡ ከሆሴ 1-2፡ ከኢል 1-3፡ ከአሞ 8፥9-11፡ 9፥9-12 ጋር ያነጻጽሩ)፡ (2) አዲስ ኪዳን ስለ፣ "መጨረሻው ቀን" ሲናገር ክርስቶስ በመጀመሪያ የመጣበት ጊዜና በእግዚአብሔር ሕዝብ

ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ
ትንቢት ይናገራሉ፤
ጕልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤
ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ።
18በዚያ ጊዜ በወንዶችና በሴቶች
አገልጋዮቼ ላይ፣
መንፈሴን አፈሳለሁ፤
እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ።
19በላይ በሰማያት ድንቅ ነገሮችን፣
አሳያለሁ፤
በታች በምድርም ምልክቶችን አሰጣለሁ፤
ደምና እሳት፣
የጢስም ጭጋግ ይሆናል።
20ታላቅና ክቡር የሆነው የጌታ ቀን
ከመምጣቱ በፊት፣
ፀሓይ ወደ ጨለማ፣
ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ።
21ዋጌታን ስም፣
የሚጠራ ሁሉ ይድናል።'

22"የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ይህን ቃል ስሙ፤ እናንተ ራሳችሁ እንደምታውቁት፣ ከእግዚአብሔር በመካከላችሁ ታምራትን፣ ድንቅ ነገሮችንና ምልክቶችን በእርሱ በኩል በማድረግ ለናዝሬቱ ኢየሱስ መስክሮለታል።

2፥18 ሐሥ21፥9-12
2፥19 ሉቃ21፥11
2፥20 ማቴ24፥29
2፥21 ዘፍ4፥26፤ 26፥25፤ መዝ105፥1፤ ኢሌ2፥28-32፤ ሐሥ9፥14፤ ሮሜ10፥13፤ 1ቆሮ1፥2፤ 2ጢሞ2፥22
2፥22 ማር1፥24፤ ዮሐ3፥2፤ 4፥48
2፥23 ኢሳ53፥10፤ ማቴ16፥21፤ ሉቃ24፥20፤ ሐሥ3፥13፤18፥ 4፥28
2፥24 ቁሮ32፤ ዮሐ20፥9፤ ሐሥ13፥30፤33፥ 34፤37፥ 17፥31፤ ሮሜ6፥4፤ 8፥11፤ 10፥9፤ 1ቆሮ6፥14፤ 15፥15፤ ኤፌ1፥20፤ 1ቆሮ6፥14፤

23ስጊዚአብሔር በጥንት ውሳኔውና በቀደመው ዕውቀቱ ይህን ሰው አሳልፎ በእጃችሁ ሰጣችሁ፤ እናንተም በክፉ ሰዎች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። 24ስጊዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አስወግዶ አስነሣው፤ ሞት ይዞ ሊያስቀረው አልቻለምና። 25ዳዊትም ስለ እርሱ እንዲህ ይላል፤

"'ጌታን ሁልጊዜ በፊቴ አየዋለሁ፤
እርሱ በቀኜ ነውና፣
ከቶ አልታወክም።
26ስለዚህ ልቤ ደስ አለው፤ አንደበቴም
ሐሤት አደረገ፤
ሥጋዬም በተስፋ ይኖራል።
27ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤
ቅዱስህም መበስበስን እንዲያይ
አታደርግምና።
28የሕይወትን መንገድ እንዳውቅ
አደረግኸኝ፤
በፊትህም በሐሤት ትሞላኛለህ።'

2፥24 15፥15፤ ኤፌ1፥20፤ ቈላ2፥12፤ ዕብ13፥20፤ 1ጴጥ1፥21 2፥27 ቁሮ31፤ ሐሥ13፥35
2፥28 መዝ16፥8-11

"2፥23 ወይም ሕግ በሌላቸው ሰዎች (አሕዛብን ያመለክታል?

ላይ መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈሰሰበት ወቅት ጅማሬው እንደ ሆነ ይህም በክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንደሚያበቃ ገልጾአል (ማር 1፥15፤ ሉቃ 4፥18-21፤ ዕብ 1፥1-2 ይመ)። ይህ የተሰየ ጊዜ በክፉ ላይ የፍርድ ዘመን፣ በአጋንንት ላይ የእግዚአብሔር ሥልጣን፣ ለሰው ዘር ሁሉ ድኅነትና የእግዚአብሔር መንግሥት ሀልዎት እንደሚገለጥ የሚያመለክት ነው።

(ሀ) ይህ "የመጨረሻው ቀን" በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚከናወኑ ነገሮችን የያዘ ነው (ማቴ 12፥28)።

(ለ) "የመጨረሻው ቀን" የእግዚአብሔር ኀይል በክርስቶስ አማካይነት በሰይጣንና በኀጢአት ግዛት ላይ የሚያደርገውን ወረራ የሚያካትት ነው። ነገር ግን ውጊያው ተጀመረ እንጂ ገና በድል አልተጠናቀቀም፤ ክፋትና ሰይጣናዊ ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ አሁንም ይሠራሉና (ኤፌ 6፥10-18)። የክፉውን ኀይል እንዲያበቃ የሚያደርገውና የመጨረሻውን ቀን ወደ ፍጻሜ የሚያመጣው የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ብቻ ነው (ዘጸአ 1፥3-5፤ ከራእ 19 ጋር ያነጻጽሩ)።

(ሐ) "የመጨረሻው ቀን" ሰው ሁሉ ንስሓ እንዲገባ፣ በክርስቶስ እንዲያምንና የመንፈስ ቅዱስን ሙላት እንዲለማመድ (1፥8፤ 2፥4፤38-40፤ ኢሌ 2፥28-32) የሚያደርግ ትንቢታዊ የምስክርነት ጥሪ ያለው ነው። የእግዚአብሔርን የፀሎጣ ቀን (ሮሜ 2፥5) ማለትም "ታላቅና ክቡር የሆነውን የጌታ ቀን" (2፥20) እየተጠባበቅን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል አማካይነት የክርስቶስን የማዳን ሥራ ማወጅ አለብን። በክርስቶስ ያገኘነው ቤዛነት ፍጹም የሚሆንበትንና ክርስቶስ ለሕዝቡ የሚመለስበትን ጊዜ በመጠባበቅ በየዕለቱ በንቃት ልንኖር ይገባናል (ዮሐ 14፥3፤ 1ተሰ 4፥15-17)።

(መ) "የመጨረሻው ቀን" ኀይልን ሁሉ ይዞ አሁን የሚመሰከውን የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚጀምርበት ነው (ሉቃ 11፥20 እና ማብ እንዲሁም (በገጽ 1443 ላይ፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። መንፈሳዊ ውጊያ ሲገጥመንና (2ቆሮ 10፥3-5፤ ኤፌ 6፥11-12) ከጽድቅ የተነሣም መከራ ሲደርስብን (ማቴ 5፥10-12፤ 1ጴጥ 1፥6-7) የዚያን ኀይል ሙላት መለማመድ ይኖርብናል።

2፥17 ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ጴጥሮስ በሌሎች ልሳኖች መናገርን (ሥ 4፥11) ከትንቢት ጋር (ሥ 17-18) አያይዞታል። ስለዚህ በሌሎች ልሳኖች መናገር ትንቢት የመናገር አንዱ መንገድ እንደሆነ ይቈጠራል። ትንቢት መናገር ማለት በመንፈስ ቅዱስ ቀጥተኛ አነሣሽነት የራስን ድምፅ ለእገልግሎትና ለእግዚአብሔር ክብር ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ (1) 120 ዎቹ "ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፣ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር" (2፥4)፣ (2) መንፈስ ቅዱስ በቆርኔሌዎስና በቤተሰቡ ላይ ወረደ፣ ጴጥሮስም፣ "በልሳን ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ሰማ (10፥44-47)፣ (3) በኤፌሶን ያሉት ደቀ መዛሙርት፣ "... መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፣ በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ" (19፥6) ይላል።

2፥18 በወንዶችና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ፣ በኢዩኤል ትንቢት መሠረት ጴጥሮስ ተግባራዊ እንዳደረገው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ላሉት ሰዎች ነው ማለትም ለእግዚኖች ወይም ለወንድና ሴት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሰዳኑት፣ ዳግም ልደት ላገኙትና የእግዚአብሔር ለሆኑት የሚሰጥ ማለት ነው።

2፥18 በዚያ ጊዜ፤ ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢዩኤልን በመጥቀስ እግዚአብሔር መንፈሱን በዚያን ጊዜ እንደሚያፈስ ተናግሮአል። የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስና አብረውት የሚከሡቱት ዲቡ ተፈጥሮአዊ ምልክቶች "በአንዱ" የጸንጤ ቄስጤ ዕሰት ብቻ ሊመሰኑ አይችሉም። የመንፈስ ቅዱስ ኀይልና በረከት እያንዳንዱ አማን በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ ሊኖረውና ሊለማመደው የሚገባ ነው፣ ይህም ዘመን ክርስቶስ በመጀመሪያና ዳግም በሚመጣበት ዘመን መካከል ያለው አጠቃላይ ጊዜ ነው (ራእ 19-20፤ ሐሥ 2፥39 እና ማብ ይመ)።

29 "ወንድሞች ሆይ፤ ከቀደምት አባቶች
ዳዊት ሞቶ እንደ ተቀበረ፣ መቃብሩም
እስከ ዛሬ ድረስ በመካከላችን እንደሚገኝ
በድፍረት መናገር እችላለሁ። 30 ነቢይ በመ
ሆኑም፣ ስላዚአብሔር ከዘሮቹ አንዱን በዙፋኑ
ላይ እንደሚያስቀምጥ በመሐላ ቃል የገባ
ለት መሆኑን ዐወቀ። 31 ይህንን አስቀድሞ
በማየቱ እርሱ በሲኦል እንደማይቀርና ሥጋ
ውም እንደማይበሰብስ ስለክርስቶስ ትንሣኤ
ተናገረ። 32 ይህን ኢየሱስን፣ እግዚአብሔር
ከሞት አስነሣው፤ እኛም ሁላችን ለዚህ
ነገር ምስክሮች ነን። 33 ስለዚህ በእግዚአብሔር
ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ፣ የመንፈስ ቅዱስን
ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና
የምትሰሙትን አፈሰሰው። 34 ዳዊት ወደ
ሰማያት አልወጣምና፤ እርሱ ራሱ ግን
እንዲህ ብሎአል፤
"'ጌታ ጌታዬን፣
35 "ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስከ
ማደርግልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ" አለው።'
36 "እንግዲህ እግዚአብሔር ይህን
እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፣ ጌታም

2፥29 1ነገ2፥10፤ 1ዜና29፥28፤ ሐሥ7፥8-9፤ 13፥36፤ 22፥5
2፥30 ማቴ1፥1
2፥31 መዝ16፥10
2፥32 ቁ.24፤ ሉቃ24፥48
2፥33 ማር16፥19፤ ዮሐ7፥39፤ 14፥26፤ 15፥26፤ ሐሥ1፥4፤ 10፥45፤ ፊል2፥9
2፥35 መዝ110፥1፤ ማቴ22፥44
2፥36 ማቴ28፥18፤ ሉቃ2፥11
2፥37 ሉቃ3፥10-12፥14፤ ሐሥ16፥30
2፥38 ቁ.41፤ ኤር36፥3፤ ማር1፥4፤ ሉቃ24፥47፤ ዮሐ20፥22፤ ሐሥ3፥19፤

ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን
ሁሉ ይረዳ!"
37 ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው
እጅግ ተነካ፤ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም
ሐዋርያት፣ "ወንድሞች ሆይ፤ ታዲያ ምን
እና ድርግ?" አሏቸው።
38 ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፤ "ንስሓ ግቡ፤ ጎጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። 39 የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ ለምሳክኝ ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፣ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና።" ሐሥ 4፥8
40 በሌላ ብዙ ቃል እየመሰከረላቸው፣ "ከዚህ ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን

2፥37 ሐሥ8፥12፥16፤ 36፥38፤ 9፥18፤10፥48፤ 16፥15፤33፤ 19፥5፤ 22፥16፤ ቁላ2፥12 2፥39 ኢሳ44፥3፤ 57፥19፤ 65፥23፤ ሐሥ10፥45፤ ኤፌ2፥13 2፥40 ዘዳ32፥5፤ ፊል 2፥15

2፥31 ወይም *መሲሕ*፤ በግሪክ ክርስቶስ፤ በዕ ብራይስጥ መሲህ ማለት ቀተባው ማለት ነው፤ አንዲሁም በሦ 36

2፥33 **በእግዚአብሔር ቀኝ**፤ በኢየሱስ አማካይነት የተፈጸመው የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ኢርሱ በእውነት ከፍ ከፍ ያለው መሲሕ እንደ ሆነ፣ አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር ቀኝ እንደ ተቀመጠና በምድር ላሉት ተወካዮቹ እንደሚማልድ ያረጋግጣል (ዕብ 7፥25)። (1) ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ መሆኑን ማለትም በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ መሆኑን (ከሉቃ 3፥21-22፤ 4፥1፤14፤18-19 *ጋር ያነጻጽሩ*) በማረጋገጥ በሙሳት በእርሱ ላይ ነበር። አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ሆኖ በመኖር በእርሱ በሚያምኑት ላይ ያንኑ መንፈስ ቅዱስ ያፈሳል (በገጽ 1559 ላይ፣ "*ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (2) ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ሲያፈስ ዐሳማው መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ህልዎት ለአማኞች እንዲያስተላልፍና እርሱ በምድር ሳለ ያደረገውን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ ኀይልን እንዲታጠቁ ነው።

2፥38 **ንስሓ ግቡ** ... **ተጠመቁ**፤ ንስሓ መግባት፣ የኀጢአትን ይቅርታ ማግኘትና የውሃ ጥምቀትን ሥርዐት መፈጸም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ከመቀበል በፊት የሚደረጉ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። ይሁን እንጂ ጴጥሮስ አድማጮቹን የአብን ተስፋ (ከ1፥4-8 *ጋር ያነጻጽሩ*) ከመቀበላቸው በፊት በውሃ መጠመቅ አለባቸው ሲል፣ መጠመቅ የግድ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ፍጹም አስፈላጊ ነው ወይም የውሃ ጥምቀት ሥርዐት ሲፈጸም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አብሮ የሚከሠት ነው ማለቱ አይደለም።

(1) በዚህ ሁኔታ ጴጥሮስ የውሃ ጥምቀት አብ የሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ ከመቀበል በፊት እንዲሆን የፈለገው በአይሁድ አድማጮች ዘንድ የተምቀት ሥርዐት የሚፈጸመው ማንኛውንም የሕይወት ለውጥ ውሳኔ ያደረገ ሰው የሚያከናውነው የተለመደ ነገር ስለ ነበር ነው። ይሁን እንጂ በ9፥17-19 (ሐዋርያው ጳውሎስ) እና በ10፥44-48 (በቆርኔሌዎስ ቤ ተሰብ) እንደተጠቀሰው የውሃ ጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አልቀደመም።

(2) አያንዳንዱ አማኝ ኀጢአቱን ከተናዘዘና ኢየሱስ

አድኑ" በማለት አስጠነቀቃቸው። 41ቃሉን የተቀበሉትም ተጠመቁ፤ በዚያ ቀንሦስት ሺህ ያህል ሰዎች በቊጥራቸው ላይ ተጨመሩ።

የአማኞች የኅብረት ኑሮ

42እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት፣ እንጀራውንም በመቍረስና በጸሎት ይተጉ ነበር። 43በሐዋርያት እጅ ብዙ ድንቅና ታምራት ይደረግ ስለ ነበር፣ ሰው ሁሉ ፍርሀት አደረበት። 44የመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ አደ ረጉ። 45ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ያህል ይሰጡት ነበር። 46በየዕለቱ በቤተ መቅደስ በአንድነት እየተገናኙ፣ በቤታቸውም እንጀራ እየ3ረሱ በደስታና በቀና ልብ ይመገቡ ነበር፤ 47እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፤ ጌታም የሚድኑትን በቊጥራቸው ላይ ዕለት በዕለት ይጨምር ነበር።

ሮሜ 15፥5-11

ጴጥሮስ ሽባውን ለማዳን ፈወሰ

3 አንድ ቀን ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ ይ3ውም ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት፣ ወደ ቤተ መቅደስ ይወጡ ነበር። 2ወደ ቤተ መቅደስ ከሚገቡት ሰዎች ምጽዋት እንዲለምን፣ ሰዎች በየዕለቱ ተሸክመው 'ውብ' በተባለው የቤተ መቅደስ መግቢያ በር ላይ የሚያስቀምጡት አንድ ከተወለደ ጀምሮ ሽባ የሆነ ሰው ነበረ፤ 3እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ ሊገቡ አይቶ ምጽዋት ለመናቸው። 4ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ወደ እርሱ ትኵር ብሎ እየውና፣ "እስቲ ወደ እኛ ተመልከት" አለው። 5ሰውየውም፣ ከእነርሱ አንድ ነገር ለማግኘት አስቦበት ዙረት ተመለከታቸው።

6ጴጥሮስ ግን፣ "እኔ ብርና ወርቅ የለኝም፤ ነገር ግን ያለኝን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ በእግርህ ተመላለስ" አለው፤ 7ቀኝ እጁንም ይዞ አስነሣው፤ ወዲያውም እግሩና ቊርጭምጭሚቱ በረታ፤ 8ዘሎም ቀጥ ብሎ ቆመ፤ መራመድም ጀመረ፤ ወዲህ ወዲያ እየሄደና እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ

2፥41 ሥ47፤ ሐሥ4፥4፤ 5፥14፤ 6፥1፣7፤ 9፥31፤35፣42፤ 11፥21፣24፤ 14፥1፣21፤ 16፥5፤ 17፥12
2፥42 ማቴ14፥19፤ 28፥20፤ ሐሥ1፥14
2፥43 ሐሥ5፥12
2፥44 ሐሥ4፥32
2፥45 ማቴ19፥21፤ ሉቃ12፥33፤ 18፥22፤ ሐሥ4፥34፣35፤ 6፥1
2፥46 ሥ42፤ ማቴ14፥19፤ ሉቃ24፥53፤ ሐሥ3፥1፤ 5፥21፣42
2፥47 ሥ41፤ ሮሜ14፥18
3፥1 መዝ55፥17፤ ሉቃ22፥8፤ ሐሥ2፥46፤ 10፥30
3፥2 ሉቃ16፥20፤ ዮሐ9፥8፤ ሐሥ14፥8
3፥6 ሥ16፤ ማር1፥24
3፥8 ኢሳ35፥6፤ ሐሥ14፥10
3፥9 ሐሥ4፥16፣21
3፥10 ሥ2
3፥11 ሉቃ22፥8፤ ዮሐ10፥23፤ ሐሥ5፥12
3፥13 ዘፀ3፥6፤ ማቴ27፥2፤ ሉቃ23፥4፤ ሐሥ2፥23፤ 5፥30፤ 7፥32፤ 22፥14
3፥14 ማር1፥24፤ 15፥11፤ ሉቃ23፥18-25፤ ሐሥ3፥27፤ 7፥52
3፥15 ሥ24፣48፤ ሐሥ2፥24
3፥16 ሥ6

አደባባይ ገባ። 9ሕዝቡም ሁሉ እየተራመደና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ ባዩት ጊዜ፣ 10ይህ ሰው ቀድሞ ሲል 'ውብ' በተባለው የቤተ መቅደስ መግቢያ በር ላይ ተቀምጦ ምጽዋት ይለምን የነበረው እርሱ መሆኑን ዐወቁ፤ በእርሱ ላይ ከተፈጸመውም ነገር የተነሣ በመደነቅና በመገረም ተሞሉ።

ጴጥሮስ ለማኙ ሲፈወስ ላየው ሕዝብ ንግግር አደረገ

11የተፈወሰውም ለማኝ ከጴጥሮስና ዮሐንስ ጋር ጥብቅ ብሎ አብሮአቸው ሳለ፣ ሕዝቡ ሁሉ በመገረም እነርሱ ወደ ነበሩበት 'የሰሎ ሞን መመላለሻ' ወደ ተባለው ሰፍራ እየሮጡ መጡ። 12ጴጥሮስም ይህን ባየ ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ በዚህ ለምን ትደነቃላችሁ? ደግሞም በእኛ ኀይል ወይም በእኛ ጽድቅ ይህ ሰው ድኖ እንዲመላለስ እንዳደረግ ነው በመቊጠር፣ ለምን ወደ እኛ አትኵራችሁ ትመለከታላችሁ? 13የአባቶቻችን አምላክ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው፤ እናንተ ግን እንዲሞት አሳልፋችሁ ሰጣ ችሁት፤ ኢላማስ ሊፈታው ቢፈልግም እና ንተ በእርሱ ፊት ካዳችሁት፤ 14ቅዱሱንና ጻድቁን ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩ እንዲፈታላ ችሁ ለመናችሁ፤ 15የሕይወት መገኛ የሆ ነውን ገደላችሁት፤ እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው፤ እኛም ለዚህ ምስክሮች ነን። 16ይህ የምታዩትና የምታውቁት ሰው የበረታው በኢየሱስ ስም በማመን ነው፤ ሁላችሁም እንደምታዩት ፍጹም ፈውስ እንዲያገኝ ያደረገው የኢየሱስ ስምና በእርሱ አማካይነት የሚገኘው እምነት ነው።

17"አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ እናንተ ይህን ያደረጋችሁት እንደ አለቆቻችሁ ሁሉ ባለማወቅ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። 18እግዚአብሔር ግን የእርሱ የሆነው ክርስቶስ[ሰ] መከራን እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያቱ ሁሉ አፍ የተናገረውን ፈጽሞአል። 19እንግዲህ

3፥17 ሉቃ23፥34፤ ሐሥ13፥27፤ 22፥5 3፥18 ማቴ1፥22፤ ሉቃ24፥27፤ ሐሥ2፥23፤ 17፥2፣3፤ 26፥22፣23
3፥19 መዝ51፥1፣ ኢሳ43፥25፤ 44፥22፤ ሐሥ2፥38
ሰ3፥18 ወይም መሲሕ፤ እንዲሁም በቊ 20

2፥42 **በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት፣ እንጀራውንም በመቍረስና በጸሎት፤** 12፥5 እና ዐሥራ ስድስቱን የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ባሕርያት በተመለከተ የተጻፈውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

3፥6 **በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ በእግርህ ተመላለስ፤** የሽባው ለማኝ ፈውስ እውን የሆነው በሐዋርያቱ ውስጥ በሠራው በክርስቶስ ኀይል ነበር። በእርሱ ለሚያምኑት የእርሱ ተከታዮች ኢየሱስ የሚከተለውን ተናገረ፤ "በስሜ ... እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወሳሉ" (ማር 16፥17-18)። ቤተ ክርስቲያን ለፈቃዱ በመታዘዝ የኢየሱስን የፈውስ አገልግሎት ማከናወን ቀጠለች። ይህ ታምራት የተሠራው፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" በማመንና በጴጥሮስ በኩል በተፈጸመው፣ "የመፈወስ ስጦታዎች" ነበር (1ቆሮ 12፥1፡9)።

ጴጥሮስ ብር ወይም ወርቅ እንደሌለው ተናገረ፤ ይሁን እንጂ ለሽባው ለማኝ የበለጠ ጠቃሚ ነገር እንደሚሰጠው ገለጸ። በቂ የሆነ ምድራዊ ብልጥግና ያላቸው ዐብያተ ክርስቲያናት እዚህን የጴጥሮስን ቃላት በጥልቀት ማሰብ ይኖርባቸዋል። ዛሬ ብዙ ዐብያተ ክርስቲያናት፣ "ብርና ወርቅ የለኝም" ማለትን ትተዋል፤ ወይም "በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ በእግርህ ተመላለስ" ማለት ያቃታቸው ይመስላል።

3፥19 **ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ** ...፤ መንፈስ ቅዱስን በማፍሰስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊባርክበት የመረጠው መንገድ

ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤ ከመንግዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ የመታደስ ዘመን ይመጣላችኋል፤ 20ደግሞም አስቀድሞ ለእናንተ የተመደበውን ክርስቶስን እርሱም ኢየሱስን ይልክላችኋል። 21እንዘአስብሔር አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ እንደተናገረ፣ ሁሉን ነገር እስከሚያድስበት ዘመን ድረስ እርሱ በሰማይ ይ3ይ ዘንድ ይገባል። 22ሙሴም እንዲህ ብሎ አለ፤ 'ጌታ አምላካችሁ ከእናንተው መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል፤ እርሱ የሚነግራችሁን ሁሉ ስሙት፤ 23ይህን ነቢይ የማትሰማ ነፍስ ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይታ ትጥፋ።' 24"በርግጥም ከሳሙኤል ጀምሮ የተነሡት ነቢያት ሁሉ ስለ እነዚህ ጊዜያት ተናግረዋል። 25እናንተም የነቢያት ልጆች ናችሁ፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ 'በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ' ብሎ የገባው ኪዳን ወራሾች ናችሁ። 26እግዚአብሔር ብሳቴናውን ባስነሣ ጊዜ፣ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ መልሶ ይባርካችሁ ዘንድ አስቀድሞ ወደ እናንተ ላከው።"

3፥20 ሉቃ2፥11
3፥21 ማቴ17፥11፤ ሉቃ1፥70፤ ሐሥ1፥6፡11
3፥22 ዘዳ18፥15፡18፤ ሐሥ7፥37
3፥23 ዘዳ18፥19
3፥24 ሉቃ24፥27
3፥25 ዘፍ12፥3፤ 22፥18፤ 26፥4፤ 28፥14፤ ሐሥ2፥39፤ ሮሜ9፥4፡5
3፥26 ቈላ2፥22፤ ሐሥ2፥24፤ 13፥46፤ ሮሜ1፥16

4፥1 ማቴ3፥7፤ 16፥1፡6፤ 22፥23፡34፤ ሉቃ22፥4፤ ሐሥ5፥17፤ 23፥6-8
4፥2 ሐሥ17፥18
4፥3 ሐሥ5፥18
4፥4 ሐሥ2፥41
4፥5 ሉቃ23፥13
4፥6 ማቴ26፥3
4፥8 ቈላ2፥9

ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት

4 ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሕዝቡ እየተናገሩ ሳሉ፣ ካህናትና የቤተ መቅደሱ ጥበቃ ኀላፊ እንዲሁም ሰዱቃውያን ድንገት ወደ እነርሱ መጡ። 2እነርሱም ሐዋርያት ሕዝቡን በማስተማራቸውና በኢየሱስ ስለተገኘው ትንሣኤ ሙታን በመስበካቸው እጅግ ተ3ጡ። 3ጴጥሮስና ዮሐንስን ያዟቸው፤ ጊዜውም ምሽት ስለ ነበረ እስኪነጋ ድረስ ወህኒ ቤት አሳደሯቸው። 4ይሁን እንጂ ቃሉን ከሰሙት መካከል ብዙዎቹ አመኑ፤ የወንዶቹም ቍጥር ወደ አምስት ሺህ ከፍ አለ።

5በማግስቱም አለቆቻቸውና ሽማግሌዎቻቸው እንዲሁም ጸሓፍት በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። 6ሊቀ ካህናቱ ሐና፣ ቀያፋ፣ ዮሐንስ፣ እስክንድሮስና የሊቀ ካህናቱ ቤተ ዘመዶች ሁሉ በዚያ ተገኝተው ነበር። 7እነርሱም ጴጥሮስንና ዮሐንስን በመካከል አቁመው፣ "ይህን ያደረጋችሁት በምን ኀይል ወይም በማንስም ነው?" ብለው ጠየቋቸው።

8በዚህ ጊዜ፣ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ የሕዝብ

4፥8 ሉቃ1፥15፡ 23፥13

ንስሓ ብቻ ነው። ይኸውም ከኀጢአትና በአካባቢ ካለ ከጠማማ ትውልድ ያለተቀደሰ መንገድ ዘወር ማለት ነው። ይህም ወደ እግዚአብሔር መመለስ፣ ነቢዩ ክርስቶስ የሚናገራቸውን ሁሉ መስማት (ቊ 22-32)፣ እንዲሁም ምንጊዜም በቅንነት ለክርስቶስ ትእዛዝ እሺ ባይ መሆን ነው (ከ2፥38-41፤ 5፥29-32 ጋር ያንጻጽሩ)።

3፥19 የመታደስ ዘመን፤ በዚህ ባለንበት ዘመንና ክርስቶስ እስኪመጣ ባለው ጊዜ ውስጥ ንስሓ በመግባት ለተለወጡት ሁሉ እግዚአብሔር "የመታደስን ዘመን" ይልካል፤ ይህም የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ነው። በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ እጅግ የከፋ ጊዜ የሚመጣና ከአምነት የሚፈግፈግ ሁኔታ የሚከሠት ቢሆንም (2ተሰ 2፥3፤ 2ጢሞ 3፥1)፣ እግዚአብሔር አሁንም በታማኞቹ ላይ የመኖቃቅትንና የመጽናናትን ዘመን እንደሚልክ ቃል ገብቶአል። የክርስቶስ ሀልዎት፣ መንፈሳዊ በረከቶች፣ ታምራትና የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በታማኝነት እርሱን በሚሹት እንዲሁም ዓለምን፣ ኀጢአተኛ ተፈጥሮንና የሰይጣንን የበላይነት ባሸነፉት ትሩፋን ላይ ይመጣሉ (ከ26፥18 ጋር ያንጻጽሩ)።

3፥21 ሁሉን ነገር እስከሚያድስበት ዘመን ድረስ፤ ክርስቶስ ከሰማይ ተመልሶ በመምጣት ክፋትን ይደመስሳል፤ ከኀጢአት ሁሉ ነጻ የሆነን የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ይመሠርታል። በመጨረሻ እንደሚታደሱ በብሉይ ኪዳን በትንቢት የተነገሩ ነገሮች ሁሉ (ከዘካ 12-14፤ ከሉቃ 1፥32-33 ጋር ያንጻጽሩ) ይታደሳሉ። ክርስቶስ ፍጥረትን ሁሉ ይዋጃል፤ ያድሳል (ሮሜ 8፥18-23)፤ በአካልም በመገኘት በምድር ሁሉ ላይ ይገዛል (ራእ 20—21 ይመ)። በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሳይሆኑ፣ ክርስቶስና የሰማይ ሰራዊት የእግዚአብሔርንና የመንግሥቱን ድል እንደሚያመጡ ልብ ይበሉ (ራእ 19፥11—20፥9)።

3፥22 ነቢይ፤ ሙሴ በዘዳ 18፥18-19 "እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ" ብሎ እግዚአብሔር ተናገረን ያለው ትንቢት ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ ነበር። ኢየሱስ ሙሴን የመሰለው በምን መንገድ ነበር? (1) ሙሴ በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ነበር (ዘኍ 11፥17)፤ ኢየሱስም ሠንጌልን ይሰብክ ዘንድ የጌታ መንፈስ በላዩ ላይ ነበር (ሉቃ 4፥18-19)፣ (2) ሙሴ ብሉይ ኪዳንን እንዲጀምር እግዚአብሔር ተጠቀመበት፤ ኢየሱስ አዲስ ኪዳንን አመጣ፤ (3) ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ አውጥቶ ወደ ሲና መራ፤ ከእግዚአብሔርም ጋር ያለውን ኪዳናዊ ግንኙነት መሠረተ፤ ክርስቶስ ደግሞ ሕዝቡን ከኀጢአትና ከሰይጣን አስራት በመዋጀት፣ ወደ እግዚአብሔር ሀልዎት የሚገቡበትን አዲስና ሕያው ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር መሠረተ፤ (4) ሙሴ በብሉይ ኪዳን ሕጎች ቤዛነትን የሚያመጣውን የመሥዋዕቱን በግ አመለከተ፤ ክርስቶስ ራሱ ለሚቀበሉት ሁሉ ድነትን የሚሰጥ የእግዚአብሔር በግ ሆነ፤ (5) የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል ትእዛዛቱን መጠበቅ እንደሚገባ ሙሴ በታማኝነት ሕጉንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ግዴታ አመለከተ፤ የእግዚአብሔርን በረከትና የዘላለም ሕይወትን ለመቀበል እንዲሁም የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም የሚያስችለው የእግዚአብሔር መንገድ እርሱ ራሱና መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደ ሆነ ክርስቶስ አመለከተ።

3፥26 ከክፋታችሁ መልሶ፤ ጴጥሮስ እንደ ገና በክርስቶስ ለማመንና በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ ከኀጢአት ዘወር ማለትና ከክፉ መለየት አስፈላጊ እንደ ሆነ በአጽንዖት ተናገረ (2፥38፡40 ማብ፡ 3፥19 ማብ፡ 8፥21 ማብ ይመ)። በመጀመሪያው ሐዋርያዊ መልእክት፣ ከቅድስና ውጪ በረከት እንደሚኖር የተሰጠ ተስፋ የለም።

4፥8 ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣ ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን እውነት ያውጅ ዘንድ የሚያስችል ድንገተኛ ኀይልን፣ ዋበብንና ድፍረትን የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አኖኘ። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የአንድ ጊዜ ልምምድ ሳይሆን፣ በተደጋጋሚ

ሐሥ 4፡31 አለቆችና ሽማግሌዎች ሆይ፤ ⁹ዛሬ ለዚህ
ሽባ ሰው ስለ ተደረገው በጎ ሥራ፣ እንዴት
እንደዳነ የምትጠይቁን ከሆነ፣ ¹⁰እናንተ
በሰቀላችሁት፣ ነገር ግን ከሙታን
ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
መዳኑንና ፈታችሁ መቆሙን እናንተም
ሆናችሁ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ይህን
ይወቅ። ¹¹እርሱም፣

"'እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፣
የማእዘን ራስ የሆነው ድንጋይ' ነው።

ሐሥ 13፡38-39 ¹²ድነት በሌላ በማንም አይገኝምና፤ እንድንበት
ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር
ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና።"

¹³ሰዎቹም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዲህ
በድፍረት ሲናገሩ ባዩአቸው ጊዜ፣ ያልተማሩ
ተራ ሰዎች መሆናቸውን ተረድተው ተደነቁ፤
ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩም ተገነዘቡ።
¹⁴የተፈወሰውን ሰው እዚያው ከእነርሱ ጋር
ቆሞ ስላዩት የሚናገሩበትን ሰበብ አጡ።
¹⁵ስለዚህ ከሸንጎው እንዲያወጧቸው አዘዙ፤
ከዚያም በአንድነት ተሰብስበው ተመካከሩ፤
¹⁶እንዲህም ተባባሉ፤ "እንግ ዲህ እነዚህን
ሰዎች ምን እናድርጋቸው? በኢየሩሳሌም
የሚኖር ሁሉ በነርሱ እጅ የተደረገውን
ድንቅ ታምር ዐውቆአል፣ ስለዚህ ይህንን
ማስተባበል አንችልም፤ ¹⁷ይሁን እንጂ፣
ይህ ነገር ከእንግዲህ በሕዝቡ መካከል
ይበልጥ እንዳይስፋፋ፣ እነዚህም ሰዎች
ዳግመኛ በዚህ ስም ለማንም እንዳይናገሩ
እናስጠንቅቃቸው።"

¹⁸ከጠሯቸውም በኋላ፣ በኢየሱስ ስም
ፈጽሞ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ
አዘዟቸው። ¹⁹ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን
መልሰው እንዲህ አሏቸው፤ "ከእግዚአብሔር
ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት
ይገባ እንደሆነ እስቲ እናንተው ፍረዱ፤
ሐሥ 4፡33 ²⁰እኛስ ያየነውንና የሰ ማነውን ከመናገር
ወደ ኋላ አንልም።"

²¹እነዚ ግና ከዛቱባቸው በኋላም
4፡9 ሐሥ3፥6
4፡10 ማር11፥24፣ ሐሥ2፥24
4፡11 መዝ118፥22፣ ኢሳ28፥16፣ ዘዳ10፥14፣ ማቴ21፥42፣ ኢፌ2፥20፣ 1ጴጥ2፥7
4፡12 ማቴ1፥21፣ ዮሐ14፥6፣ ሐሥ10፥43፣ ሮሜ11፥14፣ 1ጢሞ2፥5
4፡13 ማቴ11፥25፣ ማር3፥14፣ ሉቃ22፥8
4፡15 ማቴ5፥22
4፡16 ዮሐ11፥47፣ ሐሥ3፥6-10
4፡18 ኤር7፥13፣ ሥር5፥40
4፡19 ሐሥ5፥29
4፡20 ኢዩ32፥18፣ ኤር20፥9፣ አሞ3፥8፣ ሉቃ24፥48
4፡21 ሐሥ5፥26፣ ማቴ9፥8
4፡24 ነህ9፥6፣ ኢዮ41፥11፣ ኢሳ37፥16፣ ሐሥ1፥1
4፡25 ሐሥ1፥16
4፡26 መዝ2፥1-2፣ ዳን9፥25፣ ሉቃ4፥18፣ ሐሥ10፥38፣ ዕብ1፥9
4፡27 ቊ30፣ ማቴ14፥1፣ 27፥2፣ ሉቃ23፥12፣ ሐሥ3፥13-14
4፡28 ሐሥ2፥23
4፡29 ቊ13፥31፣ መዝ138፥3፣ ለቀቋቸው፤ ምክንያቱም ሕዝቡ ሁሉ ስለ
ሆነው ነገር ክብረ በሉ ያመሰግኑ ስለ ነበር
ሊቀጧቸው አልቻሉም፤ ²²በዚህ ታምር
የተፈወሰውም ሰው ዕድሜው ከአርባ ዓመት
በላይ ነበርና።

የአማኞች ጸሎት

²³ጴጥሮስና ዮሐንስም ከተፈቱ በኋላ
ወደ ወገኖቻቸው ተመልሰው የካህናት
አለቆችና ሽማግሌዎች ያሏቸውን ሁሉ
ነገሯቸው። ²⁴እነ ርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ
ድምፃቸውን በአን ድነት ወደ እግዚአብሔር
ከፍ አድርገው እንዲህ አሉ፤ "ልዑል
ጌታ ሆይ፤ አንተ ሰማይንና ምድርን፣
ባሕርንም፣ በውስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ
ፈጥረሃል፤ ²⁵በመንፈስ ቅዱስም አማካይነት
በአገልጋይህ በአባታችን በዳዊት አፍ
እንዲህ ብለህ ተናግረሃል፤

"'አሕዛብ ለምን በቀሩባ ተነሣሡ?
ሕዝቡስ ለምን በከንቱ አሤሩ?
²⁶የምድር ነገሥታት ተሰለፉ፤
ገዦችም በአንድነት ተሰበሰቡ፤
በጌታ ላይ፣
በተቀባውም ላይ ተነሣቡ።'

²⁷በርግጥም ሄሮድስና ጳንጥዮስ ጲላጦስ
ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚህች
ከተማ እንተ በቀባሽው በቅዱሱ ብላቴናህ
በኢየሱስ ላይ ለማሤር ተሰበሰቡ፤ ²⁸ይህም
የሆነው የአንተ ክንድና ፈቃድ ጥንት የወሰኑት እንዲፈጸም ነው። ²⁹አሁንም ጌታ
ሆይ፤ ዛቻቸውን ተመልከት፤ ባሪያዎችህም
ቃልህን በፍጹም ድፍረት መናገር እንዲችሉ አድርጋቸው። ³⁰ለመፈወስ እጅህን
ዘርጋ፤ በቅዱሱ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም
ድንቅና ታምራት አድርግ።"

4፡29 ሐሥ9፥27፣ 13፥46፣ 14፥3፣ 28፥31፣ ኤፌ6፥19፣ ፊል1፥14 4፡30 ቊ27፣ ዮሐ4፥48

*4:11 ወይም የማእዘን ድንጋይ
*4:26 ወይም ክርስቶስ ወይም መሲሕ ማለት ነው።

የሚከሠት መሆኑ በሥነ መለኮት ረገድ ተቀባይነት ያለው
ጕዳይ ነው። ይህ ድርጊት ኢየሱስ በሉቃ 12፡11-12
ላይ የገባው ተስፋ ፍጻሜ ነው፡ አዲስ መሳትን
በተመለከተ የተጠቀሱ ሁኔታዎችን በሐሥ 7፡55 እና
13፡9 ላይ ማግኘት ይቻላል።

4፡12 ድነት በሌላ በማንም፣ ደቀ መዛሙርት
ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ ነው ብለው የሚያምኑት
ከኀጢአትና ከእግዚአብሔር ቊጣ አምልጠ ድነትን
ማግኘት ነው፤ ይህም ፍላጎት በኢየሱስ ክርስቶስ
ካልሆነ በቀር በማንም ሊሟላ እንደማይችል ሰብኩ።
ይህ እውነት የወንጌልን ልዩ ባሕርይና ቤተ ክርስቲያን
ለሁሉም ሰው ወንጌልን እንድትሰብክ የተጣለባትን
ታላቅ ኀላፊነት ይገልጻል። ለድነት ሌሎች መንገዶች
ቢኖሩ ኖሮ ለቤተ ክርስቲያን ኀላፊነቱ ቀላል በሆነላት
ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ራሱ በተናገረው መሠረት
(ዮሐ 14፡6) ማንኛውም ሰው ድነትን በክርስቶስ ካላገኘ
በቀር ሌላ ተስፋ የለውም (ከ10፡43፣ ከ1ጢሞ 2፡5-6
ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ የወንጌል መልእክተኛ እንድሆን
ለተሰጠን ትእዛዝ መሠረት ነው።

4፡20 ከመናገር ወደ ኋላ አንልም፣ መንፈስ
ቅዱስ በሐዋርያት ውስጥ ወንጌልን ለመስበክ የሚያነሣሣ
ከፍተኛ ፍላጎትን ጨመረባቸው። በሐዋርያት ሥራ
ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አማኞች ወንጌልን ለሌሎች
እንዲያደርሱ አነሣሣቸው (1፡8፣ 2፡14-41፣ 3፡12-26፣
8፡25፡35፣ 9፡15፣ 10፡44-48፣ 13፡1-4)።

4፡29 በፍጹም ድፍረት መናገር እንዲችሉ፣
ስለ ክርስቶስ እንዲመሰክሩና እንዲናገሩ ደቀ መዛሙርት
የተለየ ድፍረት ያስፈልጋቸው ነበር። በክርስትና ሕይወት
ውስጥ እኛም ከእፍረት፣ ከንቀት፣ ከነቀፋ ወይም
ከስደት የተነሣ የሚመጣውን ፍርሃት ማሸነፍ እንድንችል
መጸለይ ያስፈልገናል። በመንፈስ ቅዱስ መሳት
የሚገኘው የእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ኢየሱስ በድፍረት
እንድንናገር ይረዳናል (ከማቴ 10፡32 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፡30 ለመፈወስ ... ድንቅና ታምራት አድርግ፤
ስብከትና ታምራትን ማድረግ በአንድነት የሚከናወኑ
ነገሮች ናቸው (3፡1-10፡ 4፡8-22፡29-33፡ 5፡12-16፡
6፡7-8፡ 8፡6...፡ 15፡12፡ 20፡7...)። ከታምራት መፈጸም
ጋር የክርስቶስን የምስክርነት ቃል የሚያጸኑ ምልክቶች
ይታያሉ (14፡3 ይመ፡ ከማር 16፡20 ጋር ያነጻጽሩ)።
(1) "ታምራዊ ምልክቶች" በአጠቃላይ የመለኮታዊ

31ከጸለዩም በኋላ የነበሩበት ስፍራ ተና
ወጠ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤
የእግዚአብሔርንም ቃል በድፍረት
ተናገሩ።

የአማኞች ማኅበራዊ አኗኗር

32ያመኑትም ሁሉ በአንድ ልብና በአንድ
ሐሳብ ተስማምተው ነበር፤ ያላቸውም
ሁሉ የጋራ ነበር እንጂ የራሱ የሆነውን
ሀብት እንኳ እንደ ማሉ የሚ3ዋር ማንም
አልነበረም። 33ሐዋርያትም ስለ ጌታ ኢየሱስ
ትን ሣሌ በታላቅ ኀይል መመስከራቸውን
ቀጠሉ፤ በሁላቸውም ላይ ታላቅ ጸጋ
ነበር። 34ከመካከል ላቸውም አንድ ችግረኛ
አልነበረም፤ ምክንያ ቱም መሬትም ሆነ
ቤት የነበራቸውን ሁሉ እየሸጡ ዋጋውን
አምጥተው፤ 35በሐዋርያት እግር ሥር
በማስቀመጥ ለእያንዳንዱ በሚ ያስፈልገው
መጠን ያካፍሉት ነበር።

36በቆጵሮስ የሚኖር ዮሴፍ የሚባል
አንድ ሌዋዊ ነበረ፤ ሐዋርያትም 'በርናባስ'
ብለው ጠሩት፤ ትርጕሙም 'የመጽናናት
ልጅ' ማለት ነው፤ 37እርሱም መሬቱን ሸጠ፣
ገን ዘቡን አምጥቶ በሐዋርያት እግር ሥር
አስ ቀመጠ።

ሐናንያና ሰጲራ

5 ሐናንያ የተባለ ሰው፣ ከሚስቱ ከሰጲራ
ጋር መሬት ሸጠ፤ 2ሚስቱም በሚገባ
እያወቀች ከሽያጩ የተወሰነ ገንዘብ በማ
ስቀረት የተረፈውን አምጥቶ በሐዋርያት
እግር ሥር አስቀመጠ።

3ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለ፤ "ሐናንያ
ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ከመሬቱ
ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን ልብህን

4፥31 ቊ29፤ ሉቃ1፥15፤ ሐሥ2፥2፤ ዕብ4፥12
4፥32 ሐሥ2፥44
4፥33 ሉቃ24፥48፤ ሐሥ1፥22፤ ሮሜ3፥24
4፥34 ማቴ19፥21፤ ሐሥ2፥45
4፥35 ቊ37፤ ሐሥ2፥45፤ 5፥2፤ 6፥1
4፥36 ሐሥ9፥27፤ 11፥22፣30፤ 13፥2፣ 14ቊ9፥6፣ 19፤2፥1፣9፤13
4፥37 ቊ35፤ ሐሥ5፤2
5፤2 ኢሱ7፥11፤ ሐሥ4፤35፣37
5፤3 ቊ9፤ ዘጸ23፥21፤ ማቴ4፥10፤ ዮሐ13፥2፣27

ኀይልን መናር ለማሳየት፣ ማስጠንቀቂያን ለመስጠት ወይም እምነትን ለማነሣሣት የተፈጸሙ ድርጊቶችን የሚያመለክቱ ናቸው። (2) "ድንቅ" ተመልካችን የሚያስገርም ያልተለመደን ሁኔታ የሚያሳይ ነው። ፈውስ፣ ታምራዊ ምልክቶችና ድንቆች እንዲፈጸሙ በ ተ ክርስቲያን መጸለያሞን ልብ ይበሉ። ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻውን ዘመን ፈታኝ ሁኔታዎች እየተጋፈጠች ሳለ፣ እግዚአብሔር ወንጌልን በታላቅ ኀይል፣ በታምራትና በተትረፈረፈ ጸጋ (ቊ33) እንዲያጸናላት በትጋት መጸለይ ያስፈጋታል። ይህን የጠፋውን ትውልድ ወደ ክርስቶስ ማምጣት የምንችለው ወንጌልን በአዲስ ኪዳን የምስክርነት ኀይል ስናውጅ ብቻ ነው።

4፥31 ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ አያሌ አስፈላጊ እውነቶች በዚህ ስፍራ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል፤ (1) "በመንፈስ ቅዱስ" ወይም "በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ተጠመቁ" የሚለው ሐረግ (1፥5 እና ማቤ ይመ) አማኝን ለምስክርነት ወደሚያበቃው መለኮታዊ ኀይል ውስጥ እንዲገባ የሚያነሣሣውን የመንፈስ ቅዱስን የመቀደስ ሥራ ይገልጻል። "ሙሞላት"፣ "መልበስ"፣ "ኀይልን መታጠቅ" የሚሉት ቃላት መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ለአገልግሎት የሚያስታጥቅበትን ሁኔታ ያመለክታሉ (2፥4፤ 4፥8፣31፤ 9፥17፤ 13፥9፣52)። አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ "መሞላት" ሊደጋገም ይችላል።

(2) "መንፈሴን አፈላለሁ" (2፥17-18፤ 10፥45)፣ "የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ" (2፥38፤ 8፥15)፣ "መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው" (8፥16፤ 10፥44፤ 11፥15፤ 19፥6) የሚሉት ሐረጎች አማኞች በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉበት ጊዜ (2፥4፤ 4፥31፤ 9፥17) ሁኔታውን ለመግለጽ የተነገሩ የተለያዩ መግለጫዎች ናቸው።

(3) ቀደም ሲል የተሞሉት (2፥4)፣ ሐዋርያትን ጨምሮ አማኞች ሁሉ ቀጣዩን የአይሁድ ተቃውሞ (ቊ 29) ለመቋቋም በአዲስ ሁኔታ ይሞላሉ። አዲስ የመንፈስ ቅዱስን መላት መቀበል የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ሳገኙ ሁሉ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ፈቃድና በረከት ክፍል ነው (ቊ 8 እና ማብ፣ 13፥52 ጋር ያነጻጽሩ) እነዚህን አዳዲስ መላቶች መናፈቅና መፈለግ አለብን።

(4) በዚህ ስፍራ መንፈስ ቅዱስ የጉበኘው ጉባኤውን በሙሉ ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያለባቸው ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ (ቊ 8፥ 9፥17፣ 13፥9)፣ ጉባኤው በሙሉ (2፥4፣ 4፥31፣ 13፥53) የተሰየ ፍላጎት ሲኖረውና ፈታኝ ሁኔታዎች ሲገጥሙት በተደጋጋሚ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ይኖርበታል።

(5) እግዚአብሔር በአዲስ የመንፈስ ቅዱስ መላት በመላው ጉባኤ መከከል ሲንቀሳቀስ ለመመስከር ድፍረትና ኀይልን፣ የርስ በርስ ፍቅርንና ለሁሉን የተትረፈረፈ ጸጋ ያወርዳል።

4፥31 የእግዚአብሔርንም ቃል በድፍረት ተናገሩ። በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት የተነሣ ወደ አማኝ ሕይወት የሚመጣው የመንፈስ ቅዱስ ኀይልና የእግዚብሔር ሀልዎት አማኙን ሌሎችን ከመናገራት ነጻ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ በድፍረት በኀይል ስለ እግዚአብሔር እንዲናገር ይረዳዋል።

4፥33 ታላቅ ኀይል፣ "ታላቅ ኀይል" የሚለው ሐ ረግ ሐዋርያዊ ስብከትና ምስክርነትን (ከ1፥8 ጋር ያነጻጽሩ) ተለይቶ የሚታወቅበት ባሕርይ ሲሆን፣ ይህም በሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች ነው፤ (1) የሐዋርያት ምስክርነት በእግዚአብሔር ቃልና (ቊ 29)፣ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሚያስገኘው እምነት ላይ የተመሠረተ ነው (በገጽ 1941 ላይ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር አስተምሩስ መሆኑና ያለው ሥልጣን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (2) ደቀ መዛሙርት ከሞት በተነሣው ጌታ በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሳና ሥልጣን እንደተሰጣቸው ያመቁ ነበር፤ (3) መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርት አማካይነት (ቊ 31) የግል ኀጢአትን፣ የክርስቶስን ጽድቅና የእግዚአብሔርን ፍርድ በተመለከተ (ዮሐ 16፥8 እና ማብ ይመ) የተነገረውን መንጌል የሰሙ እንዲያምኑ አደረገ።

5፥3 መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና፤ ከዘራታንና ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ ሐናንያና ሰጲራ ባደረጉት ስጦታ ቤተ ክርስቲያንን ዋሽ። ይህንን ውሸት እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ላይ ከባድ ጥፋት እንደመፈጸም አድርጎ ቈጠረው። የሐናንያና የሰጲራ ሞት ዳግም ተወልደናል፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል በሚሉ አማኞች መከከል ለሚገለጥ አታላይ ልብ ማስጠንቀቂያ የሚሆን ቋሚ ምሳሌ ነው። መንፈስ ቅዱስን መዋሸት እግዚአብሔርን መዋሸት እንደ ሆነ ልብ ይበሉ (ቊ 3-4፤ ራእ 22፥15 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1679 ላይ፣ "የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

ለምን ሞላው? 4ሳትሸጠው በፊት የአንተው
አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ ቢሆን
ገንዘቡ በእጅህ አልነበረምን? ለመሆኑ ይህን
ነገር እንዴት በልብህ አሰብህ? የዋሸኸው
እኮ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም።"
5ሐናንያም ይህን እንደ ሰማ ወድቆ
ሐሥ 16፥16-18 ሞተ፤ ይህን የሰሙትም ሁሉ ታላቅ ፍርሀት
ያዛቸው።
6ጕልማሶችም ተነሥተው አስ ከሬኑን
ገነዙት፤ ወስደውም ቀበሩት።
7ሦስት ሰዓት ያህልም ካለፈ በኋላ፣
ሚስቱ የሆነውን ሳታውቅ መጥታ ገባች።
8ጴጥሮስም፣ "እስቲ ንገሪኝ፤ መሬታችሁን
የሸጣችሁት በዚህ ዋጋ ነውን?" አላት።
እርሷም፣ "አዎን፤ በዚሁ ዋጋ ነው"
አለች።
9ጴጥሮስም፣ "የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ
ዘንድ እንዴት እንዲህ ተስማማችሁ?
እነሆ፤ ባልሽን የቀበሩት ሰዎች ተመልሰው
እግራቸው ደጃፍ ላይ ነው፤ አንቺንም ይዘው
ይወጣሉ" አላት።
10እርሷም ወዲያውኑ እግሩ ሥር ወድቃ
ሞተች፤ ጕልማሶቹም ሲገቡ ሞታ አገኟት፤
አውጥተውም በባሏ አጠገብ ቀበሯት።
11መላዪቱን ቤተ ክርስቲያንና ይህን
የሰሙትን ሁሉ፣ ታላቅ ፍርሀት ያዛቸው።

በሐዋርያት እጅ ብዙ ሰው ተፈወሰ

12ሐዋርያትም በሕዝቡ መካከል ብዙ
ታምራዊ ምልክቶችንና ድንቅ ሥራዎችን
አደረጉ፤ አማኞቹም ሁሉ 'የሰሎሞን
ደጅ' በተባለው መመላለሻ ይሰበሰቡ
ነበር። 13ከእነርሱ ጋር ሊቀላቀል የደፈረ
ማንም አልነበረም፤ ሆኖም ሕዝቡ እጅግ
ያከብሯቸው ነበር፤ 14ብዙ ወንዶችና
ሴቶችም ከጊዜ ወደ ጊዜ በጌታ እያመኑ ወደ
እነርሱ ይጨመሩ ነበር። 15ከዚ ህም የተነሣ፣
ጴጥሮስ በዚያ ሲያልፍ፣ ቢያንስ ጥላው
እንኳ በጥቂቶች ላይ እንዲያርፍባቸው
በማለት ሕመምተኞችን ወደ ውጭ እያወጡ
በዐልጋና በቃሬዛ በመንገድ ላይ ያስተኙ
ነበር። 16በኢየሩሳሌም አካባቢ ከሚገኙ
ከተሞች፣ ሕመምተኞችንና በርኩ ሳን[a]
መናፍስት የሚሠቃዩትን ይዘው የሚ
መጡት ሰዎች አካባቢውን ያጨናንቁት
ነበር፤ የመጡትም ሁሉ ይፈወሱ ነበር።

ሐዋርያት መከራና ስደት ደረሰባቸው

17ከዚህም የተነሣ ሊቀ ካህናቱና አብረውት
የነበሩት የሰዱቃውያን ወገን ሁሉ በቅናት
ተሞሉ፤ 18ሐዋርያትንም ይዘው ማረፊያ
ቤት ከተቷቸው። 19ይሁን እንጂ የጌታ
መልአክ በሌሊት የእስር ቤቱን ደጆች ከፍቶ
አወጣቸውና፣ 20"ሂዱ፤ በቤተ መቅደሱም
አደባባይ ቁሙ፤ የዚህንም ሕይወት ቃል
ሁሉ ለሕዝብ ንገሩ" አላቸው።
21እንደ ነጋም፣ በተነገራቸው መሠረት፣
ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ ገብተው
ሕዝቡን ማስተማር ጀመሩ።
ሊቀ ካህናቱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
መጥተው የአይሁድን ሸንጎና የእስራኤልን
ሽማግሌዎች ጉባኤ በሙሉ በአንድነት

5፥4 ዘሌ 6፥2፤ ዘዳ 23፥22
5፥5 ቍ 10፡11፤ መዝ 5፥6
5፥6 ዮሐ 19፥40
5፥8 ቍ 2
5፥9 ቍ 3
5፥10 ቍ 5፡6
5፥11 ቍ 5፤ ሐሥ 19፥17
5፥12 ዮሐ 4፥48፤ 10፥23፤ ሐሥ 2፥43፤ 3፥11፤ 4፥32
5፥13 ሐሥ 2፥47፤ 4፥21
5፥14 ሐሥ 2፥41
5፥15 ሐሥ 19፥12
5፥16 ማቴ 8፥16፤ ማር 16፥17
5፥17 ሐሥ 4፥1፤ 15፥5
5፥18 ሐሥ 4፥3
5፥19 ዘፍ 16፥7፤ ዘፀ 3፥2፤ መዝ 34፥7፤ ማቴ 1፥20፤ 2፥13፡19፤ 28፥2፤ ሉቃ 1፥11፤ 2፥9 ዮሐ 20፥12፤ ሐሥ 8፥26፤ 10፥3፤ 12፥7፡23፤ 16፥26፤ 27፥23
5፥20 ዮሐ 6፥63፡68
5፥21 ቍ 27፡34፡41፤ ማቴ 5፥22፤ ሐሥ 4፥5፡6

[a]5፥16 ወይም በክፉ

5፥4 ለመሆኑ ይህን ነገር እንዴት በልብህ አሰብህ? የሐናንያና የሰጲራ ኀጢአት መሠረቱ የገንዘብ ፍቅርና ሌሎች እንዲያከብሯቸው መፈለጋቸው ነው። ይህ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስን እንዲያሳዝኑ አደረጋቸው (ቍ 9)። የገንዘብ ፍቅርና ከሰዎች ሙገሳን የማግኘት ፍላጎት አንድ ጊዜ ልብን ከወረሰ፣ የማንም ሰው መንፈስ ሰይጣናዊ ለሆነ ክፉ አሠራር የተከፈተ ይሆናል (1ጢሞ 6፥10)። ሰው በአንድ ጊዜ ገንዘብንና እግዚአብሔርን መውደድ እንዲሁም ማገልገል አይችልም (ማቴ 6፥24፤ ዮሐ 5፥41-44)።

5፥5 ሐናንያም ... ወድቆ ሞተ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሊኖር በማይገባው አታላይነትና ታማኝ አለመሆን ሁሉ ላይ ያለውን ጥላቻ ለመግለጽ፣ እግዚአብሔር ሐናንያንና ሰጲራን በኀይል መትቶ ጣላቸው (ቍ 5፡10)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ አስጸያፊ ከሆኑት ኀጢአቶች አንዱ ከክርስቶስ ጋር ስላለን ግንኙነት፣ ለእርሱም ስለምንሠራው ሥራ እንዲሁም ስለ አገልግሎታችን ስሩት የእግዚአብሔርን ሰዎች የምናታልልበት ውሸት ነው። በዚህ ዐይነቱ ግብዝነት ውስጥ መገኘት የፈሰሰውን የክርስቶስ ደም በሌሎች ሰዎች ፊት ራሳችንን ለማክበር መጠቀም ማለት ነው። ይህ ኀጢአት ክርስቶስ የተሠቃየበትንና የሞተበትን ዋና ዐላማ (ኤፌ 1፥4፤ ዕብ 13፥12) ዋጋ ያሳጣል፤ እግዚአብሔርን መፍራትም በሕይወታችን እንደሌለ ያመለክታል (ቍ 5፡11) እንዲሁም ለመንፈስ ቅዱስ አክብሮትና ቦታ እንደሌለን ያሳያል፤ ይህም የእግዚአብሔርን ጻድቅ ፍርድ የሚያስከትል ይሆናል።

5፥11 መላዪቱ ቤተ ክርስቲያንና ... ታላቅ ፍርሀት ያዛቸው፤ በሐናንያና በሰጲራ ላይ የወረደው የእግዚአብሔር ፍርድ ትሕትና፣ ድንጋጤና ፍርሀት እንዲበዛ አደረገ። ቅዱሱን እግዚአብሔርንና በኀጢአትም ላይ ያለውን ቍጣ በሚገባ አለመፍራት የእግዚአብሔር ሕዝብ ርኩስ ወደሆነው የዓለም መንገድ ዘወር እንዲል፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልምምድ እንዳይለቀቅለትና የእግዚአብሔር ታምራዊ ሀልዎት እንዲቀርበት እንዲሁም የእግዚአብሔር ጸጋ መፍሰስ እንዲቋረጥበት ያደርገዋል። እግዚአብሔርን መፍራት በአዲስ ኪዳን እምነትና በዛሬው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው (በገጽ 291 ላይ፣ *"እግዚአብሔርን መፍራት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

5፥16 ሁሉም ይፈወሱ ነበር፤ ሐዋርያት ጌታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ያደርግ እንደ ነበረው አደረጉ፤ ይኸውም በርኩሳን መናፍስት የሚሠቃዩትን መፈወስ ነበር (ማር 1፥34 ይመ)። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት በታላቅ ኀይል በሕዝቡ መካከል መገለጡን የሚያሳይ ላቅ ያለ ምልክት ነው (በገጽ 1499 ላይ፣ *"በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሕመምና በአጋንንት እየተሠቃዩ ላሉት መልካም ለማድረግና እነርሱም ይፈወሱ ዘንድ መጸለይ ፍጹም ስሕተት አይደለም (4፥30 እንዲሁም በገጽ 1433 ላይ፣ *"መለኮታዊ ፈውስ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ

ሐሥ 5፥3-4 "ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለ፦ "ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ትዋሸ ዘንድ ሰይጣን ልብህን ለምን ሞላው? ሳትሸጠው በፊት የአንተው አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ ያልነበረምን? ለመሆኑ ይህን ነገር እንዲት በልብህ አሰብህ? የዋሸኸው እኮ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም።"

በእግዚአብሔር ቤዛነትን የመሰጠት ዐላማ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን አስፈላጊ ሥራ አማኞች መረዳት ይኖርባቸዋል። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዓለም ባይኖር ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ብዙ ክርስቲያኖች አልተረዱም። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኀይል ፍጥረት፣ ፍጥረተ ዓለም እንዲሁም የሰው ዘር (ዘፍ 1፥2፣ ኢዮ 33፥4) አይኖርም ነበር። ያለመንፈስ ቅዱስም መጽሐፍ ቅዱስ (2ጴጥ 1፥21)፣ አዲስ ኪዳን (ዮሐ 14፥26፣ 15፥26-27፣ 1ቆሮ 2፥10-14)፣ ወንጌልን ለማወጅ የሚያስችል ኀይል (ሐሥ 1፥8) አይኖርም። ያለ መንፈስ ቅዱስ እምነት፣ አዲስ ልደት፣ ቅድስና አውን አይሆንም እንዲሁም ክርስቲያኖች በዓለም ውስጥ አይኖሩም ነበር። ይህ የትኩረት ጽሑፍ ስለ መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ መሠረታዊ ትምህርቶች እንድንረዳ ያስችለናል።

የመንፈስ ቅዱስ አካል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ የግል ማንነት እንዳለው ተገልጾአል (2ቆሮ 3፥17-18፣ ዕብ 9፥14፣ 1ጴጥ 1፥2)። እርሱ ልክ እንደ እግዚአብሔር አብና እንደ እግዚአብሔር ወልድ መለኮታዊ ማንነት አለው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ስሜት አለማሽ ወይም ኀይል ብቻ አይደለም። የራሱ የሆነ ባሕርይ አለው፣ ያስባል (ሮሜ 8፥27)፣ ስሜት አለው (ሮሜ 15፥30)፣ ፈቃድ አለው (1ቆሮ 12፥11) እንዲሁም ኀብረትን የመውደድና በኀብረትም ደስ የመሰኘት ችሎታ አለው። አማኞች ከኢየሱስ ጋር ወደ ቀረበ ህልምትና ኀብረት ውስጥ ይገቡ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር አብ ተልኮአል (ዮሐ 14፥16-18፥26 እንዲሁም በገጽ 1559 ላይ፣ "ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ከእነዚህ እውነቶች አንጻር መንፈስ ቅዱስን እንደ አንድ አካል በመቀጠርና በልባችን ውስጥ የሚኖር ዘላለማዊ ሕያው አምላክ እንደ ሆነ በማሰብ አምልኮአችን፣ ፍቅራችንና መዝሙራችን ለእርሱ እንደሚገባው ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል (በማር 1፥11 ላይ ስለ ሥላሴ የተጠቀሰውን ማብ ይመ)።

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፣ (1) በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ራሱን የገለጠበት ሥራ። መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የሠራውን ዝርዝር ሥራ ለመረዳት በገጽ 1314 ላይ፣ "መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

(2) በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ራሱን የገለጠበት ሥራ። (ሀ) መንፈስ ቅዱስ ስለ በደል የሚወቅስ (ዮሐ 16፥7-8)፣ ስለ ኢየሱስ ያለውን እውነት የሚገልጥ (ዮሐ 14፥16:26)፣ አዲስ ልደትን የሚሰጥ (ዮሐ 3፥3-6)፣ ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ እንድንገባ የሚያደርግ የድኅነት ኀይል ነው። በክርስቶስ እምነን ስንለወጥ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን (ዮሐ 3፥3-6፣ 20፥22)፣ የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይም እንሆናለን (2ጴጥ 1፥4 እንዲሁም በገጽ 1646 ላይ፣ "የደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(ለ) መንፈስ ቅዱስ መቀደስን የሚያመጣ ኀይል ነው። በክርስቶስ አምነው በሚለወጡ ብት ጊዜ አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆናሉ፣ ከዚያም በእርሱ የመቀደስ ተግባር ሥር ይሆናሉ (ሮሜ 8፥9፣ 1ቆሮ 6፥19)። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሲኖር፣ የሚሠራውን ሥራ ልብ በሉ። እርሱ ይቀድሰናል፣ ይኸውም ያነጻናል፣ ኩነኒአት ባርነት ነጻ በማውጣትም (ሮሜ 8፥2-4፣ ገላ 5፥16-17፣ 2ተሰ 2፥13) በቅዱስ ኑሮ እንድንመራ ያደፋፍረናል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆንን ይነግረናል (ሮሜ 8፥16)፣ እግዚአብሔርን በምናመልክበት ጊዜ (ሐሥ 10፥46) እና በጸሎት ሕይወታችን ያግዘናል፣ ወደ እግዚአብሔርም በምንጮኽበት ጊዜ ይማልድልናል (ሮሜ 8፥26-27)። ክርስቶስን እናከብር ዘንድ የክርስቶስ የሆኑትን የጸጋ ባሕርያት በውስጣችን ይፈጥርልናል (ገላ 5፥22-23፣ 1ጴጥ 1፥2)። እርሱ ኢየሱስን ለእኛ በመግለጥ፣ ከኢየሱስ ጋር የቀረበ ኀብረትና አንድነት እንዲኖረን በማድረግ (ዮሐ 14፥16-18፣ 16፥14)። ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን መለኮታዊ አስተማሪያችን ነው (ዮሐ 16፥13፣ 14፥26፣ 1ቆሮ 2፥9-16)። ባለማቋረጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር ወደ እኛ ያስተላልፋል (ሮሜ 5፥5)፣ ደስታን መጽናናትንና ርዳታን ይሰጠናል (ዮሐ 14፥16፣ 1ተሰ 1፥6)።

(ሐ) መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ለአገልግሎትና ለምስክርነት የሚያስታጥቅ የአገልግሎት ጎይል ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቅ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት ጋር የተያያዘ ነው (በገጽ 1664 ላይ፣ "በመንፈስ ፈቅዱስ መጠመቅ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በመንፈስ ቅዱስ ስንጠመቅ፣ ለክርስቶስ ለመመስከር እንዲሁም በቤተ ክርስቲያንና በዓለም ፊት ውጤታማ ሥራ ለመሥራት የሚያስችለንን ጎይል እንቀበላለን (ሐሥ 1፥8)። የእግዚአብሔርን ቃል እንድንናገርና (ሐሥ 1፥8፣ 4፥31) ታምራትን እንድናደርግ (ሐሥ 2፥43፣ 3፥2-8፣ 5፥15፣ 6፥8፣ 10፥38) የሚያስችለንን በደቀ መዛሙርትና (ሐሥ 2፥4፣ 1፥5 ይመ) በክርስቶስ (ዮሐ 1፥32-33) ላይ የወረደውን ዐይነት መለኮታዊ ቀባት እንቀበላለን። በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ እንዱጠመቁ ሚድረግ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያሰበው ዐሳማ ነው (ሐሥ 2፥39)። በአገልግሎት ረገድ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ግለሰብ አባላት ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ወይም ለማጠንከር የሚያስችሉአቸውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ይሰጣቸዋል (1ቆሮ 12-14)። እነዚህ ስጦታዎች መንፈስ ቅዱስ በግለሰብ አማኞች ሕይወት ውስጥ የሚገለጥባቸው ምልክቶች ሲሆኑ፣ የክርስቶስ ሀልዎት፣ ፍቅር፣ እውነትና ጻድቅ መለኪያዎች ለጋራ ጥቅም (1ቆሮ 12፥7-11) በአማኞች ጎብረት ውስጥ እውን እንዲሆኑ የሚያደርጉ ናቸው።

(መ) መንፈስ ቅዱስ አማኞች በአንዱ በክርስቶስ አካል ውስጥ እንዲተባበሩ የሚያደርግ ጎይል ነው (1ቆሮ 12፥13)፣ እርሱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይኖራል (1ቆሮ 3፥16)፣ ቤተ ክርስቲያንን ይገነባል (ኤፌ 2፥22)፣ የቤተ ክርስቲያንን አምልኮ ያንቀሳቅሳል (ፊል 3፥3)፣ ተልእኮዋን ይመራል (ሐሥ 13፥2፡4)፣ ሠራተኞቿን ይሾማል (ሐሥ 20፥28)፣ ለቤተ ክርስቲያን ስጦታን ይሰጣል (1ቆሮ 12፥1-11)፣ ሰባኪዎቿን ይቀባል (ሐሥ 2፥4፣ 1ቆሮ 2፥4)፣ ወንጌልን ይጠብቃል (2ጢሞ 1፥14)፣ የጽድቅንም ሕይወት እንዲሰፋፋ ያደርጋል (ዮሐ 16፥8፣ 1ቆሮ 3፥16፣ 6፥18-20)።

(3) የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች እርስ በርስ የሚደጋገፉ እንጂ የሚቃረኑ አይደሉም። እንደዚሁም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ልዩ ልዩ ገጽታዎች እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው፣ ፈጽሞም ሊለያዩ አይችሉም። ስለዚህ (ሀ) በክርስቶስ ያለውን የአዲስ ሕይወት ሙላትን፣ (ለ) ጽድቅን የኑሮ መርሕ ማድረግን፣ (ሐ) ለጌታችን የመመስከር ጎይል መቀበልን ወይም (መ) በአካሉ ውስጥ ያለንን አንድነት ቦቲናቦል መለማመድ አንችልም። ለምሳሌ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣ መንፈስ ቅዱስ ጽድቅን በውስጣችን ለማፍራት ከሚሠራው ሥራ እንዲሁም ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በመምራትና ራሳችንን እንድንሰጥ በማድረግ ከሚፈጽመው ሥራ ተለይቶ በዘላቂነት ሊጠበቅ አይችልም።

ሰበሰበ፤ ሐዋርያትንም እንዲያመጡ ሰዎችን ወደ እስር ቤት ላኩ። 22የተላኩትም ወደ እስር ቤቱ ሄደው በዚያ አላገኟቸውም፤ ተመልሰ ውም እንዲህ አሏቸው፤ 23"እስር ቤቱ በሚገባ ተልፎ፣ ጠባቂዎቹም በበሩ ላይ ቆመው አገኘን፤ ከፍተን ስንገባ ግን በውስጡ ማንም አልነበረም።" 24የቤተ መቅደሱ ጥበቃ ሹምና የካህናት አለቆችም ይህን በሰሙ ጊዜ በነገሩ ተገረሙ፤ ግራም ተጋቡ።

25በዚህ ጊዜ አንድ ሰው መጥቶ፣ "እነሆ፤ እስር ቤት ያስገባችኋቸው ሰዎች በቤተ መቅደሱ አደባባይ ቆመው ሕዝቡን እያስተማሩ ናቸው" አላቸው። 26የጥበቃ ሹሙም ከወታደሮቹ ጋር ሄዶ፣ ይዞ አመጣቸው፤ ያመ ጣቸው ግን ሕዝቡ በድንጋይ እንዳይወግሯቸው ስለ ፈሩ በኀይል ላያስገድዱ ነበር።

27ሐዋርያትንም እምጥተው በሸንጎው ፊት አቆሟቸው፤ ሊቀ ካህናቱም እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፤ 28"በዚህ ሰም እንዳታስተ ምሩ በጥብቅ አስጠንቅቀናችሁ ነበር፤ እናንተ ግን ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞላችኋት፤ ደግሞም እኛን ለዚህ ሰው ደም ተጠያቂዎች ልታደርጉን 3ርጣችሁ ተነሣችሁ"

29ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያትም መልሰው እንዲህ አሉ፤ "ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል! 30እናንተ በዕን ጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን፣ የአባቶቻችን አምላክ ከሙታን አስነ ሣው፤ 31እርሱም ለእስራኤል ንስሓንና የኀ ጢአትን ስርየት ይሰጥ ዘንድ፣ እግዚአብሔር የሁሉ ራስና አዳኝ አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው። 32እኛም ለእነዚህ ነገሮች ምስክር ነን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው።"

33ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ክፉኛ ተ3ጡ፤ ሊገድሏቸውም ፈለጉ። 34ነገር ግን በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ የተከበረ አንድ የሕግ መምህር፣ እርሱም ገማልያል የሚሉት ፈሪሳዊ ተነሥቶ በሸንጎው መካከል ቆመና ሐዋርያትን ወደ ውጭ አውጥተው ለጥቂት ጊዜ እንዲያዩአቸው አዘዘ፤ 35ለሸንጎውም እንዲህ አለ፤ "የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ በእነዚህ ሰዎች ላይ ልታደርጉ ስላሰባችሁት ነገር በጥንቃቄ ልታጤኑ ይገባችኋል።

36ከዚህ ቀደምም ቴዎ ዳስ ራሱን ትልቅ አድርጎ በመቍጠር ተነ ሥቶ፣ አራት መቶ ያህል ሰዎች ተባበሩት፤ ነገር ግን እርሱም ተገደለ፤ ተከታዮቹም ሁሉ ተበታተኑ፤ ነገሩም እንዳልነበር ሆነ። 37ከእርሱም በኋላ በሕዝብ 3ጠራው ወቅት ገሊላዊው ይሁዳ ተነሥቶ ብዙ ሕዝብ እሽ ፈተ፤ ተከታይም አግኝቶ ነበር፤ እርሱም ጠፋ፤ ተከታዮቹም ተበተኑ። 38ስለዚህ አሁንም የምላችሁ፦ እንዚህን ሰዎች ተዉአቸው፤ አትንኳቸው፤ ሐሳባቸው ወይም አድራጎታቸው ከሰው ከሆነ ይጠፋልና፤ 39ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን ልት ገድቸው አትችሉም፤ እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ትገኙ ይሆናል።"

40እነርሱም ምክሩን ተቀብለው፤ ሐዋርያትን አስጠርተው አስገረፏቸው፤ ዳግመኛም በኢየሱስ ስም እንዳይናገሩ አዘው ለቀቂቸው።

41ሐዋርያትም፣ ስለ ስሙ ውርደትን ለመቀበል በመብቃታቸው ደስ እያላቸው ከሸንጎው ወጥተው ሄዱ፤ 42በየዕለቱም፣ በቤተ መቅደስም ሆነ በየቤቱ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ከማስተማርና ከመስበክ ከቶ ወደ ኋላ አላሉም ነበር።

የሰባቱ ዲያቆናት መመረጥ

6 የደቀ መዛሙርት ቍጥር እየጨመረ በሄደበት በዚህ ወቅት፣ ከግሪክ አገርየመጡ አይሁድ ብይሁዳ ይኖሩ በነበሩት አይሁድ ላይ አጒረመረሙ፤ ምክንያቱም በየዕለቱ በሚከናወነው ምግብ የማደል አሠራር ላይ ከእነርሱ ወገን የሆኑት መበለቶች ችላ ተብለው ነበር። 2ስለዚህ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሌሎችን ደቀ መዛሙርት በአንድነት ሰብስበው እንዲህ አሉ፤ "እኛ የማእዱን አገልግሎት ለማስተናገድ ስንል የእግዚአ ብሔርን ቃል አገልግሎት መተው አይገባንም። 3ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ መካከል በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸውን

*5፡42 ወይም መሲሕ

5፡22 ሐሥ12፡18፡19
5፡24 ሐሥ4፡1
5፡26 ሐሥ4፡21
5፡27 ማቴ5፡22
5፡28 ማቴ23፡35፤ 27፡25፤ ሐሥ2፡23፡36፤ 3፡14፡15፤ 4፡18፤ 7፡52
5፡29 ዘፀ1፡17፤ ሐሥ4፡19.
5፡30 ሐሥ2፡24፤ 3፡13
5፡31 ማቴ1፡21፤ ማር1፡4፤ 16፡19፤ ሉቃ2፡11፤ 24፡47፤ ሐሥ2፡38፤ 3፡19፤ 10፡43
5፡32 ሉቃ24፡48፤ ዮሐ15፡26.
5፡33 ሐሥ2፡37፤ 7፡54
5፡34 ሉቃ2፡46፤ 5፡17፤ ሐሥ22፡3
5፡37 ሉቃ2፡1፡2
5፡38 ማቴ15፡13.
5፡39 2ዜና13፡12፤ ምሳ21፡30፤ ኢሳ46፡10፤ ሐሥ7፡51፤ 11፡17
5፡40 ማቴ10፡17
5፡41 ማቴ5፡12፤ ዮሐ15፡21
5፡42 ሐሥ2፡46፤ 9፡22፤ 13፡32
6፡1 ሐሥ2፡41፤ 4፡35፤ 9፡29፡39፡41፤ 1ጢሞ5፡3
6፡2 ሐሥ11፡26፤ ዕብ4፡12
6፡3 ዘፀ18፡21፤ ነህ13፡13፤ ሉቃ1፡15፤ ሐሥ1፡16

5፥29 ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል፦ በማንኛውም አማኝ ፊት ትልቁ ዋያቄ፣ "ለሰዎች የሚጠቅም፥ የሚመች፣ ደስ የሚያሰኝ ወይም የሚወደድ ነው ወይ?" ማለት ሳይሆን፣ "በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛው የቱ ነው?" የሚለው መሆን አለበት (ከገላ 1፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥32 ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ፦ እውነተኛ የሆነ መታዘዝ ለክርስቶስ ካልተገለጠ ወይም በእውነት የመንግሥቱን ጽድቅ የመሻት ፍላጐት ከሌለ (ማቴ 6፥33፣ ሮሜ 14፥17)፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን ለማግኘት መጠባበቅ ዋጋ የለውም። የክርስቶስ ጌትነት በሕይወታችን ላይታይ እንጒ ቄስጢ የማይቻል ነው (ክ2፥38-42 ጋር ያነጻጽሩ)። "በእምነት አማነይኖት ወደሚገኘው መታዘዝ" ውስጥ በመግባት ለሚኖሩ መንፈስ ቅዱስ ከነሙሉ ኀይሉ ይሰጣልና (ሮሜ 1፥5 እንዲሁም (በገጽ 1694 ላይ፣ "እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

6፥3 በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ፦ ሐዋርያት አጥብቀው የጠየቁት ሰባቱ ሰዎች በታማኝነት በመንፈስ ቅዱስ ስለ መመራታቸው የተመሰከረላቸው መሆኑ እንዲረጋገጥላቸው ነበር። ሐዋርያት ሁሉም አማኞች በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን ጠበቀው አይዘልቁም የሚል ግምት እንደ ነበራቸው ግልጽ ነው። በሌላ አነጋገር በመንፈስ ቅዱስ በመኖር ጸንተው መቆም የማይችሉ (ገላ 5፥16-25)፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ይቋረጥባቸዋል ማለት ነው። "በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ" እና "በመንፈስ ቅዱስ መሞላት" የሚሉትን ሐረጎች

ሐሥ 7፡55 ሰባት ሰዎች ምረጡ፤ ይህን ጎላፊነት ለእነርሱ እንሰጣለንና። ⁴እኛ ግን በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት እንተጋለን።"

⁵አባባሉ ሁላቸውን ደስ አሰኘ፤ በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላውን እስጢፋኖስን፣ እንዲሁም ፊልጶስን፣ ጵሮኮሮስን፣ ኒቃኖርን፣ ጢሞናን፣ ጰርሜናንና ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን እንጾኪያዊውን ኒቆላውስን መረጡ። ⁶እነዚህንም አምጥተው ሐዋርያት ፊት አቀረቡአቸው፤ እነርሱም ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው።

ሐሥ 14፡9-10

⁷የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፤ የደቀ መዛሙርቱም ቍጥር በኢየሩሳሌም እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙዎቹ ለእምነት የታዘዙ ሆኑ።

የእስጢፋኖስ መያዝ

ሐሥ 11፡27-28 ⁸በዚህ ጊዜ እስጢፋኖስ ጸጋንና ኀይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅ ነገሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን ያደርግ ነበር። ⁹"የነጻ ወጪዎች ምኵራብ" ተብሎ የሚጠራው

6፡4 ሐሥ 1፡14
6፡5 ቍ 8፤ ሉቃ 1፡15፤ ሐሥ 7፡55-60፤ 8፡5-40፤ 11፡19፤ 21፡8፤ 22፡20
6፡6 ዘኍ 8፡10፤ 27፡18፤ ማር 5፡23፤ ሐሥ 1፡24፤ 9፡17፤ 19፡6፤ 28፡8፤ 1ጢሞ 4፡14
6፡7 ሐሥ 2፡41፤ 12፡24፤ 19፡20
6፡8 ዮሐ 4፡48
6፡9 ማቴ 27፡32፤ ሐሥ 2፡9፤ 15፡23፤ 41፤ 22፡3፤ 23፡34
6፡10 ሉቃ 21፡15
6፡11 1ነገ 21፡10፤ ማቴ 26፡59-61
6፡12 ማቴ 5፡22
6፡13 ዘዳ 23፡1፤ ምኵራብ አባላት የሆኑ ከቀሬናና ከእስክንድርያ እንዲሁም ከኪልቅያና ከእስያ አውራጃዎች የመጡ ሰዎችም ተቃውሞ አስነሥተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ጀመር፤ ¹⁰ይሁን እንጂ ይናገርበት የነበረውን ጥበብና መንፈስ መቋቋም አልቻሉም።

¹¹ስለዚህ፣ "እስጢፋኖስ በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ሲሰነዝር ሰምተናል" የሚሉ ሰዎችን በስውር አዘጋጁ።

¹²በዚህ ሁኔታ ሕዝቡን፣ የአገር ሽማግሌዎቹንና የሕግ መምህራኑን በማነሣሣት፣ እስጢፋኖስን አስይዘው በአይሁድ ሸንጎ ፊት አቀረቡት፤ ¹³እንዲህ ብለው የሚመሰክሩ የሐሰት ምስክሮችንም አቆሙበት፤ "ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ የስድብ ቃል መናገሩን በፍጹም አልተ ወምኘ ¹⁴ምክንያቱም ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ስፍራ

6፡13 መዝ 27፡12፤ ማቴ 24፡15፤ ሐሥ 7፡48፤ 21፡28
6፡14 ዮሐ 2፡19፤ ሐሥ 15፡1፤ 21፡21፤ 26፡3፤ 28፡17

በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ማለት ይገባል፥

(1) "በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ" (ከ6፡5፡ 11፡24 ጋር ያነጻጽሩ) የሚለው ሐረግ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚታየውን ቀጣይነት ያለውን ባሕርይ፤ የሕይወት ብልጫን ወይም ሁኔታን የሚገልጽ ሲሆን፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙሳትን ከመለማመድ የሚመነጭ ነው፡ ይህም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንዲያገለግሉና መንፈስ ቅዱስም በሰጣቸው ሙጠን ችንቢታዊ መልእክት እንዲያስተላልፉ ያስችላቸዋል።

(2) "በመንፈስ ቅዱስ መሞላት" የሚለው ሐረግ በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ተገልጸአል፡ (ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን መቀበልን ለማመልከት (1፡5፤ 2፡4፤ 9፡17፤ 11፡16)፥ (ለ) አማኞች በአንድ ልዩ ሁኔታ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ግፊት ለመናገር የሚያስችልን ኀይል መታጠቃቸውን ለማመልከት ነው (4፡8፡ 13፡9፡ ሉቃ 1፡41-45፡67-79)። (ሐ) የአገልግሎቱን ጊዜ ለይቶ ሳይገልጽ በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና ቅባት የሚፈጸመውን ትንቢታዊ አገልግሎት በአጠቃላይ ለማመልከት ነው (4፡31-33፡ 13፡52፡ ሉቃ 1፡15)።

(3) የመጀመሪያውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከተቀበሉበትና የሥጋን ሥራ በመግደል (ሮሜ 8፡13-14) ቢታማኝነት በመንፈስ የሚመላለሱ አማኞች፣ "በመንፈስ የተሞሉ" ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ፥ ይህም በውስጣቸው በሙላት የሚያደረውን መንፈስ ቅዱስን እንደያዙ የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ ከሰባቱ ሰዎች አስጢፋኖስ ቍ 3፡5፡ 7፡55 ወይም በርናባስ 11፡24)። በተጨማሪም የመንፈስ ቅዱስ ሙሳትን አጥብቀው የያዙ ለተለየ ዐላማ ወይም ሥራ አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ሙሳትን ሊቀበሉ ይችላሉ፤ ይህም በመንፈስ ቅዱስ ግፊት መናገር የሚያስችል ከመለኮት የሚሰጥ ልዩ ችሎታ ነው።

6፡4 በጸሎትና ... እንተጋለን፤ ውጤታማ ለሆነ ክርስቲያናዊ መሪነት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን መቀበል ብቻውን በቂ አይደለም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባለማቋረጥ ለጸሎትና ቃሉን ለመስበክ ራሳቸውን መስጠት ይኖርባቸዋል። እንተጋለን የሚለው ግሥ (በግሪክ፡ ፕሮስካርቴርኦ) ጽኑና ፍጹም እምነትን እንዲሁም ለአንድ ለተወሰነ ድርጊት ብዙ ጊዜ መስጠትን የሚያመለክት ነው። ሐዋርያት ጸሎትና ቃሉን ማገልገል የክርስቲያን መሪዎች ታላቅ ሥራ እንደ ሆነ ተረድተዋል። ጸሎትን በተመለከተ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተከታታይ የተገለጸውን ልብ ይበሉ (1፡14፡24፤ 2፡42፤ 4፡24-31፡ 6፡4፡6፡ 9፡40፤ 10፡2፡4፡9፡31፡ 11፡5፤ 12፡5፡ 13፡3፡ 14፡23፤ 16፡25፡ 22፡17፡ 28፡8)።

6፡6 እጃቸውን ጫኑባቸው፤ በአዲስ ኪዳን እጅ መጫን በሚከተሉት አምስት መንገዶች ሥራ ላይ ውሎአል፡ (1) ከፈውስ ታምራት ጋር በተያያዘ መልክ (28፡8፤ ማቴ 9፡18፡ ማር 5፡23፤ 6፡5)፡ (2) ሌሎችን ለመባረክ (ማቴ 19፡13፡15)፡ (3) ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር በተያያዘ ሁኔታ (8፡17፡19፡ 19፡6)፡ (4) ለተለየ ሥራ አገልጋዮችን ሾሞ ለመላክ (ቍ 6፡ 13፡3)፡ (5) በሽማግሌዎች አማካይነት ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎችን እንዲቀበሉ ለማድረግ (1ጢሞ 4፡14)። እግዚአብሔር ስጦታዎቹንና በረከቶቹን ለሌሎች ከሚያስተላልፍባቸው መንገዶች አንዱ በመሆኑ፣ እጅ መጫን የዋንት ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አስተምህሮ ሆኖአል (ዕብ 6፡2)። እጅ መጫን ከጸሎት የተለየ ሆኖ ሊታይ አይገባም፤ ጸሎት የሚያመለክተው የጸጋ፣ የፈውስ ስጦታዎች ወይም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚገኘው ከእግዚአብሔር እንጂ አገልግሎቱን ከሚፈጽሙ ሰዎች አለመሆኑን ነው።

ሰባቱን ሰዎች በዚህ ስፍራ መቀደስ ወይም መሾም በመሠረቱ የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች የሚያመለክት ነው፡ (1) እነዚህ ሰባት ሰዎች እግዚአብሔርን በመፍራትና በታማኝነት ጸንተው ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ራሳቸውን የሰጡ ለመሆናቸው በሕዝብ ፊት በቤተ ክርስቲያን ምስክርነት መስጫ ነው (ከ1ጢሞ 3፡1-10 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) ሰዎቹ ለእግዚአብሔር ሥራ የተለዩ መሆናቸውን የሚያመለክትና የእግዚአብሔርን ጥሪ ጎላፊነት ለመቀበል ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ምስክርነት ነው።

6፡8 እስጢፋኖስ ጸጋንና ኀይልን ተሞልቶ፤ እስጢፋኖስ፣ "በሕዝቡ መካከል ድንቅ ነገሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን" እንዲያደርግ መንፈስ ቅዱስ ኀይልን አስታጠቀው፡ ወንጌልን ሲሰብክም ተቃዋሚዎቹ ሊቋቋሙት የማይችሉትን ታላቅ ጥበብን ሰጠው (ቍ 10 ይመ፡ ከዘፀ 4፡15፤ ከሉቃ 21፡15 ጋር ያነጻጽሩ)።

እንደሚያጠፋና ከሙሴ የተቀበልነውን ወግ እንደሚለውጥ ሲናገር ሰምተነዋል።"
15በሸንጎው ተቀምጠው የነበሩትም ሁሉ እስጢፋኖስን ትኵር ብለው ሲመለከቱት ፊቱ የመልአክ ፊት መስሎ ታያቸው።

እስጢፋኖስ በሸንጎው ፊት ያደረገው ንግግር

7ሊቀ ካህናቱም፣ "ይህ የቀረበብህ ክስ እውነት ነውን?" አለው።
2እስጢፋኖስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ወንድሞችና አባቶች ሆይ፤ አድምጡ"! አባታችን አብርሃም ወደ ካራን ከመምጣቱ በፊት፣ ገና በመስጴጦምያ ሳለ፣ የክብር አምላክ ተገልጦለት፤ 3"ከአገርህና ከወገንህ ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ አለው።
4"እርሱም ከከለዳውያን ምድር ወጥቶ በካራን ተቀመጠ። ከአባቱም ሞት በኋላ፣ አሁን እናንተ ወደምትኖሩበት ወደዚህ አገር አመ ጣው። 5በዚህም ስፍራ አንዲት ጫማ ታህል እንኳ ርስት አልሰጠውም፤ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ምንም ልጅ ሳይኖረው፣ እርሱና ከእርሱም በኋላ ዘሩ ምድሪቱን እንደሚወርሱ ተስፈ ሰጠው። 6ዳግሞም እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ 'ዘርህ በባዕድ አገር መጻተኛ ይሆናል፤ አራት መቶ ዓመትም በባርነት ቀንበር ሥር ይማቅቃል። 7ሆኖም በባርነት የሚገዛቸውን ሕዝብ እኔ ደግሞ እቀጣዋለሁ። ከዚያም አገር ወጥተው በዚህች ስፍራ ያመልኩኛል።' 8ከዚያም የግዝረትን ኪዳን ሰጠው፤ አብርሃምም ይስሐቅን ወለደ፤ በስምንተኛውም ቀን ገረዘው። ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ዐሥራ ሁለቱን የነገድ አባቶች ወለደ።
9"የነገድ አባቶችም በዮሴፍ ቀንተው በባርነት ወደ ግብፅ ሸጡትና እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ስለ ነበር፣ 10ከመከራው ሁሉ አወጣው፤ በግብፅም ንጉሥ በፈርዖን ፊት ሞገስና ጥበብን አጐናጸፈው፤ ፈርዖንም በግብፅና በቤተ መንግሥቱ ሁሉ ላይ ገዣ አድርጎ ሾመው።
11"በዚያ ጊዜም በግብፅና በከነዓን አገር ሁሉ፣ ታላቅ መከራን ያስከተለ ራብ መጣ፤ አባቶቻችንም የሚበሉትን አጡ። 12ያዕቆብም እህል በግብፅ መኖሩን በሰማ ጊዜ፣ አባቶቻችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ግብፅ ላካቸው፤ 13ለሁለተኛ ጊዜ ሲሄዱ ደግሞ ዮሴፍ ማንነቱን ለወንድሞቹ ገለጠ፤ ፈርዖንም ስለ ዮሴፍ ዘመዶች ተረዳ። 14ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ልከ አባቱን ያዕቆብንና ሰባ አምስት ነፍስ የሚሆኑ ቤተ ዘመዶቹን በሙሉ አስመጣ። 15ያዕቆብ ወደ ግብፅ ወረደ፤ እርሱም አባቶቻችንም በዚያ ሞቱ። 16አስከሬናቸውም ወደ ሴኬም ተወሰዶ፣ አብርሃም ከዔሞር ልጆች ላይ በዋሪ ብር በገዛው መቃብር ተቀበረ።
17"እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል የሚፈጸምበት ጊዜ ሲቃረብም፣ በግብፅ የነበረው የሕዝባችን ቍጥር እየበዛ ሄደ። 18ከዚያ በኋላ ዮሴፍን የማያውቅ ሌላ ንጉሥ በግብፅ ነገሠ። 19እርሱም ሕዝባችንን በተን ኰሉ አስጨነቃቸ፤ ገና የተወለዱ ሕፃናታቸ ውም ይሞቱ ዘንድ ወደ ውጭ አውጥተው እንዲጥሏቸው አስገደዳቸው።
20"በዚህ ጊዜ ሙሴ ተወለደ፤ እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘ ሙብ ሕፃን ነበር። በአባቱም ቤት ሦስት ወር በእንክብካቤ አደገ። 21ወደ ውጭ በተጣለም ጊዜ የፈርዖን ልጅ አግኝታ ወሰደችውና እንደ ራሷ ልጅ አድጋም አሳደገችው። 22ሙሴም የግብፃውያን ጥበብ ሁሉ ተማረ፤ በንግግሩና በተግባሩም ብርቱ ሆነ።
23"ሙሴ አርባ ዓመት በሆነው ጊዜ፣ ወንድሞቹን የእስራኤልን ልጆች ሊጐበኝ በልቡ አሰበ። 24አርሱም፣ አንድ ግብፃዊ ከወንሮቹ አንዱን በደል ሲያደርስበት አይቶ ግብፃዊ ውንም ገደለ፤ ለተገፋውም ወገኑም ተበቀለ። 25ወገኖቹም እግዚአብሔር በእርሱ እጅ ነጻ እንደሚያወጣቸው የሚያስተውሉ መስሎት ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም። 26በማግ ስቱም ዳግሞ ሁለት እስራኤላውያን ሲጣሉ ደረሰ፤ ሊያስታርቃቸውም ፈልጎ፣ 'ሰዎች፤ እናንተ እኮ ወንድማማቾች ናችሁ፤ እንዴት እርስ በርሳችሁ ትጐዳዳላችሁ?' አላቸው።
27"በባልንጀራው ላይ በደል ሲያደርስ የነበረው ሰው ግን፣ ሙሴን ገፈተረውና እንዲህ አለ፤ 'እንትን ገና ፈራጅ አድርጎ በእኛ ላይ የሾመህ ማን ነው? 28ወይስ ትናንት ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው እኔንም ልትገድለኝ ትፈልጋልህን?' 29ሙሴም ይህን እንደ ሰማ ሸሽቶ በምድያም አገር መጻተኛ ሆኖ ተቀመጠ፤ በዚያም ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ።

*7፥20 ወይም ተራ ልጅ አልነበረም

6፥15 ማቴ5፥22
7፥2 ዘፍ11፥31፣ 15፥7፣ መዝ29፥3፣ ሐሥ22፥1
7፥3 ዘፍ12፥1
7፥4 ዘፍ12፥5
7፥5 ዘፍ12፥7፣ 17፥8፣ 26፥3፣ ዕብ11፥13
7፥6 ዘፀ1፥8-11፥ 12፥40
7፥7 ዘፍ15፥13-14፥ ዘፀ3፥12
7፥8 ዘፍ17፥9-14፣ 21፥2-4፣ 25፥26፣ 29፥31-35፣ 30፥5-13፣ 17-24፣ 35፥16-18፣22-26
7፥9 ዘፍ37፥4፣11፣28፥ 39፥2፣21፣23፥ መዝ105፥17፣ ሐሌ2፥4
7፥10 ዘፍ41፥37-43፣ መዝ105፥20-22
7፥11 ዘፍ41፥54
7፥12 ዘፍ42፥1፣2
7፥13 ዘፍ45፥1-4፥16
7፥14 ዘፍ45፥9፣10፣ 46፥26፣27፥ ዘፀ1፥5፣ ዘዳ10፥22
7፥15 ዘፍ46፥5-7፥ 49፥33፣ ዘፀ1፥6
7፥16 ዘፍ23፥16-20፣ 33፥18፣19፥ 50፥13፥ ኢሱ24፥32
7፥17 ዘፀ1፥7፥ መዝ105፥24
7፥18 ዘፀ1፥8
7፥19 ዘፀ1፥10-22
7፥20 ዘፀ2፥2፣ ዕብ11፥23
7፥21 ዘፀ2፥3-10
7፥22 1ነገ4፥30፥ ኢሳ19፥11
7፥27 ዘፍ19፥9፣ ዘጥ16፥13
7፥29 ዘፀ2፥11-15

7፥2 ወንድሞችና አባቶች ሆይ አድምጡኝ፤

ከቍ 2-53 ይመልከቱ። እስጢፋኖስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት የተናገረው ንግግር በክርስቶስና በሐዋርያት የተሰበከው እምነት የሚደግፍና ተቃዋሚዎቹ ላቀረቡበት ክስ መከላከያ ቃል ነበር። እርሱም መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት የሚቃወሙትን ወይም የሚያጣሙትን በመከላከል የመጀመሪያው ሰው ሲሆን፣ በዚሁ ምክንያት ሰማዕትነትን ተቀብሏል በመሞትም የመጀመሪያው ሰው ነበር። እስጢፋኖስን ይቀበል ዘንድ ኢየሱስ በሰማይ ባለው በአባቱ ፊት በመቆም እርሱ የወሰደውን እርምጃ አጸደቀለት (ቊ 55 እና ማብ)። እስጢፋኖስ ለእውነት ያለው ፍቅርና ይህንንም እውነት ለመጠበቅ ሕይወቱን ይሰጥ ዘንድ መፍቀዱ፣ "ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለተሰጠው እምነት እንድትጋደሉ" (ይሁዳ 3) የሚለውን ምክር ችላ ከማሉ እንዲሁም በዓቅር፣ በስሜትና በመቻቻል ስም የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችንና ክርስቶስ የሞተለትን ንጹሕ የሆነውን የወንጌል እውነት የሚያጣሙ መሪዎችን ለመቃወም ምንም ስሜት ከሌላቸው ሰዎች ድርጊት ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሚያስገርም ነው (ገላ 1፥9 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1716 ላይ፣ "የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

30 "ከአርባ ዓመት በኋላ፣ በሲና ተራራ አካባቢ፣ ባለው ምድረ በዳ፣ በሚነድ ቍጥቋጦ
ነበ ልባል ውስጥ መልአክ ተገለጠለት።
31 ሙሴም ባየው ነገር ተደነቀ፤ ነገሩን
ለማጣራት ወደዚያ ሲቀርብ የጌታ ድምፅ፤
32 'እኔ የአባቶችህ አምላክ፣ የአብርሃም፣
የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ' ሲል ሰማ።
ሙሴም በፍርሀት ተዋጠ፤ ለመመልከትም
አልደፈረም።
33 "ጌታም እንዲህ አለው፤ 'የእግርህን
ጫማ አውልቅ፤ የቆምህባት ስፍራ
የተቀደሰች ምድር ናትና።
34 በግብፅ ያለውን
የሕዝቤን መከራ በርግጥ አይቻለሁ፤ የሚጮኽ
ጩኸታቸውን ሰምቻለሁ፤ ላድናቸውም
ወርጃለሁ። አሁንም ና፤ ወደ ግብፅ መልሼ
እልክሃለሁ።'
35 "እንግዲህ እነዚያ፣ 'ገዥና ፈራጅ
አድርጎ የሾመህ ማን ነው?' ብለው የናቁትን
ይህንን ሙሴ እግዚአብሔር በቍጥቋጦው ውስጥ
በታየው መልአክ አማካይነት ገዥና ታዳጊ
አድርጎ ወደ እነርሱ ላከው።
36 እርሱም
መርቶ ከግብፅ አወጣቸው፤ በግብፅ፣ በቀይ
ባሕርና በምድረ በዳ አርባ ዓመት ድንቅ
ነገሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን አደረገ።
37 "የእስራኤልንም ሕዝብ፣ 'እግዚአብሔር
እንደ እኔ ያለ ነቢይ ከመካከላችሁ
ያስነሣላችኋል' ያላቸው ይኸው ሙሴ ነበር።
38 እርሱም በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክ
ጋር በምድረ በዳ በሕዝቡ
ጉባኤ መካከል ነበር፤ የሕይወትንም ቃል

7:31 ዘፀ3:1-4
7:32 ዘፀ3:6፣ ሐሥ3:13
7:33 ዘፀ3:5፣ ኢሳ6:15
7:34 ዘፀ3:7-10
7:35 ቍ.27
7:36 ዘፀ11:10፣ 12:41፣ 14:21፣ 15:25፣ 17:5፣6፣ 33:1፤ ዮሐ6:48
7:37 ዘዳ18:15፣18፤ ሐሥ3:22
7:38 ቍ.53፣ ዘፀ19:17፤ ዘሌ27:34፣ ዘዳ32:45-47፣ ሮሜ3:2፣ ዕብ4:12
7:39 ዘኍ14:3፣4
7:40 ዘፀ32:1፣23
7:41 ዘፀ32:4-6፣ መዝ106:19፣20፣ ራእ9:20
7:42 ኢሴ24:20፣ ኢሳ63:10፣ ኤር19:13
7:43 አሞ5:25-27
7:44 ዘፀ25:8፣9፣40፣ 38:21፣ ዘኍ1:50፣ 17:7

ወዳ እኛ ለማስተላለፍ ተቀበለ።
39 "አባቶቻችን ግን ተቃወሙት፤ እንጂ
ሊታዘዙት ስላልፈለጉ በልባቸው ወደ ግብፅ
ተመለሱ።
40 አሮንንም፣ 'ፊት ፊታችን
የሚ ሄዱ አማልክት አብጅልን፤ ከግብፅ
ምድር መርቶ ያወጣን ያ ሙሴ ምን እንደ
ደረሰበት አናውቅምና' አሉት።
41 በዚያን
ጊዜ የጥጃ ምስል ሠርተው፣ ለጣዖቱ
መሥዋዕት አቀረቡ፤ በእጃቸውም ሥራ
ተደሰቱ፤ ፈነጠዙም።
42 እግዚአብሔር ግን
ከእነርሱ ዘወር አለ፤ ያመልኳቸውም ዘንድ
ለሰማይ ከዋክብት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም
በነቢያት መጽሐፍ እንዲህ ተብሎ በተጻፈው
መሠረት ተፈጸመ፤

"'እናንት የእስራኤል ቤት ሆይ፤ አርባ
ዓመት
በምድረ በዳ በነበራችሁ ጊዜ፣
መሥዋዕትንና መባን ለእኔ
አቀረባችሁልኝን?
43 ይልቁንም ልታመልኳቸው
የሠራችኋቸውን፣
የሞሎክን ድንኳንና የጣዖታችሁን፣
የራምፋንን ከከብ ከፍ ከፍ አድርጋችሁ
ያዛችሁ።
ስለዚህ እኔም እንድትጋዙ
አደርጋለሁ፤
ከባቢሎንም ወዲያ እሰዳችኋለሁ።'
44 "እግዚአብሔር ለሙሴ ባሳየው ንድፍና
ባዘዘው መሠረት የተሠራችው የምስክር
ድንኳን፣ ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ

7:38 በምድረ በዳ በሕዝቡ ጉባኤ፤ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው እስራኤላውያን እንደ አንድ ማኅበር የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናቸውን ነው። በዕብራይስጥ፣ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል የተተረጐመው "ቃሐል" በሚለት ሲሆን፣ በግሪኩ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ግለትም በሰባ ሊቃናት ትርጉም "ኤክሌሺያ" ተብሎአል፤ ይህም "ጉባኤ" ወይም "ቤተ ክርስቲያን" ማለት ነው። (1) ሙሴ የብሉይ ኪዳኑን ቤተ ክርስቲያን እንደ መሪ፣ ክርስቶስ ደግሞ የአዲስ ኪዳኑን ቤተ ክርስቲያን ይመራል። "የአብርሃም ዘር" (ገላ 3፥29 ይመ፤ ክሮሜ 4፥11-18 ጋር ያነጻጽሩ) እና "የእግዚአብሔር እስራኤል" (ገላ 6፥16) በሚል የተሰየመው የአዲስ ኪዳኑ ቤተ ክርስቲያን፣ የብሉይ ኪዳኑ ቤተ ክርስቲያን ቀጣይ እንቅስቃሴ ነው። (2) ልክ እንደ ብሉይ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን፣ የአዲስ ኪዳኗም ቤተ ክርስቲያን "በምድረ በዳ" ትገኛለች፤ ይኸውም ገና ወደ ተስፋዪቱ ምድር ያልደረሰችና በጉዞ ላይ ያለች ቤተ ክርስቲያን መሆኗ ነው (ዕብ 11፥6-16)። ከዚህም የተነሣ በዚህ ምድር ባለው ሕይወት በብዙ ምኞት በመንደላቀቅ ወደ ተስፋዪቱ ምድር የምናደርገውን ጉዞ መዘንጋት የለብንም።

7:42 እግዚአብሔር ... አሳልፎ ሰጣቸው፤ የእስጢፋኖስ ቃሎች በእግዚአብሔር ቃልና በቤዛነት ታሪክ ላይ በሚገባ የተመሠረተን መርሕ ያንጸባርቃሉ። እግዚአብሔርን ዐመፅን የሚጸኑ ለክፋት፣ ለስይጣንና ለኢንብረገብዊነት አልፈው ይሰጣሉ (ክሮሜ 1፥24፣28 ጋር ያነጻጽሩ)። አስደናቂ ትምህርት ቢሰጥም በእኛ በኩል የራሳችንን ድርሻ ካልተወጣን እግዚአብሔር ፍቅሩንና ይቅርታውን በመቀጠል ምሕረቱን አያሳየንም። በእሥራኤል ንስሓና በፍጹም ታዛዥነት ልባቸውን ወደ እርሱ ለሚመልሱ ምሕረቱን እንዲሁም ፍቅሩን ይገልጽላቸዋል። ልባቸውን የሚያደነድኑ፣ መንፈስ ቅዱስን የሚቃወሙና የእግዚአብሔርን ድኅነት ሊቀበሉ የማይሹ ሰዎችማ ይጸረጋሉ (ሮሜ 2፥4-6:8)።

7:44 ንድፍ ... መሠረት፤ እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊከተለው የሚገባ መለኮታዊ መመሪያ ምን ጊዜም ይኖረዋል። (1) እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን መለኪያ ሆኖ የሚያገለግል መመሪያ ለሙሴ ሰጥቶት ነበር። (ሀ) እግዚአብሔር በዘፀአት 12 ላይ በግብፅ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሚከበረው ፋሲካ ለየት ያለ መመሪያ ለሙሴ ሰጠው፤ ይህም መመሪያ ቀጣዩ የእስራኤል ትውልድ ሁሉ በምሳሌነት ሊከተለው የሚገባ ነበር። (ለ) በዘፀአት 20 ቀጣዩ ትውልድ ሊከተለው የሚገባው መመሪያና ማዕረገ-ገዥ መለኪያ እንዲሆን እግዚአብሔር ለሙሴ ሀሥርቱን ትእዛዛት ሰጠው። (ሐ) እግዚአብሔር በምድር ላይ በጌታ በእየሱስ አማካይነት ሊፈጽም ላቀደው የሰማያዊ ነገሮችና የቤዛነት ጥላ እንዲሁም ቅጂ እንዲሆን በዘፀአት 25 ላይ እግዚአብሔር ሙሴን ማደሪያ ድንኳኑን እንዲተክል አዘዘው። ሙሴ ማደሪያ ድንኳኑንና በውስጡ ያሉትን ዕቃዎች ሁሉ እግዚአብሔር ባሳየው ዕቅድ መሠረት (ዘፀ 25፥9:40 ይመ፤ ከዕብ 8፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ) በጥንቃቄ ሠራ።

(2) በእርግጥ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለነበረው ማደሪያ ድንኳን መመሪያ እንደ ነበረው ሁሉ፣ በአዲስ ኪዳን ላለችው ቤተ ክርስቲያንም መመሪያ አለው። የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እንዴት መመራት እንዳለባት በዘፈቀደ አይወስኑም ነበር። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በመንጌሎች፣ በሐዋርያት

ነበረች። 45አባቶቻችንም ድንኳንዋን ከተቀበሉ በኋላ፣ እግዚአብሔር በኢያሱ መሪነት ያሳደዳቸውን የአሕዛብን አገር በወረሱ ጊዜ ይዘዋት ገቡ፤ እስከ ዳዊትም ዘመን ድረስ በምድሪቱ ተቀመጠች፤ 46ዳዊትም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ በማግኘቱ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያ ያዘጋጅ ዘንድ ለመነ፤ 47ነገር ግን የማደሪያውን ቤት የሠራለት ሰሎሞን ነበር።

48"ይሁን እንጂ፣ ልዑል የሰው እጅ በሠራው ቤት ውስጥ አይኖርም፤ ይህም ነቢዩ እንዲህ ባለው መሠረት ነው፤

49" 'ሰማይ ዙፋኔ ነው፤
ምድርም የእግሬ ማሳረፊያ ናት፤
ታዲያ ምን ዐይነት ቤት ትሠሩልኛላችሁ?
ይላል ጌታ፤
ወይንስ ማረፊያ የሚሆነኝ የትኛው
ቦታ ነው?
50ይህን ሁሉ የሠራው እጄ አይደለምን?'

51"እናንት ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ፣ አንገተ ደንዳኖች ልክ እንደ አባቶቻችሁ መንፈስ ቅዱስን ሁልጊዜ ትቃወማላችሁ። 52ከነቢያት መካከል አባቶቻችሁ ያሳደዱት ማን አለ? የጻድቁን መምጣት አስቀድመው የተናገሩትን እንኳ ገድለዋል፤ እናንተም አሁን አሳልፋችሁ ሰጣችሁት፤ ገደላችሁትም፤ 53በመላእክት አማካይነት የተሰጣችሁንም ሕግ ተቀበላችሁ እንጂ አልጠበቃችሁትም።"

7፥45 ኢሱ3፥14-17፣ 18፥1፣ 23፥9፣ 24፥18፣ 2ሳሙ7፥2፡6፣ መዝ44፥2 7፥46 2ሳሙ7፥8-16፣ 1ነገ8፥17፣ መዝ132፥1-5 7፥47 1ነገ6፥1-38 7፥48 1ነገ8፥27፣ 2ዜጊ2፥6፣ ማር5፥7 7፥49 ማቴ5፥34፡35 7፥50 ኢሳ66፥1፡2 7፥51 ዘፀ32፥9፣ 33፥3፡5፣ ዘሌ26፥41፣ ዘዳ10፥16፣ ኤር4፥4፣ 9፥26 7፥52 ማቴ5፥12፣ ሐሥ3፥14፣ 1ተሰ2፥15 7፥53 ቈላ2፥15 ዕብ2፥2

7፥54 ሐሥ5፥33 7፥55 ማር16፥19፣ ሉቃ22፥69 7፥56 ማቴ3፥16፣ 8፥20 7፥58 ዘሌ24፥14፡16፣ ዘዳ17፥7፣ ሉቃ4፥29፣ ሐሥ8፥1፣ 22፥20 7፥59 መዝ31፥5፣ ሉቃ23፥46

የእስጢፋኖስ መወገር

54በሸንጎው ስብሰባ ላይ የነበሩትም ይህን በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቆጡ፤ ጥርሳቸውንም አፋጨቱበት። 55እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመለከት፣ የእግዚአብሔርን ክብርና እንዲሁም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፤ 56"እነሆ፤ ሰማያት ተከፍተው፣ የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ" አለ።

57በዚህ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፍነው እርሱ ወደ አለበት በአንድነት ሮጡ፤ 58ይዘውም ከከተማው ውጭ ጣሉት፤ በድንጋይም ይወግሩት ጀመር። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በዚያ የነበሩ ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በተባለ ጕልማሳ እግር አጠገብ አስቀመጡ።

59እስጢፋኖስም እየወገሩት ሳለ፣ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፤ ነፍሴን ተቀበላት" ብሎ ጸለየ፤ 60ከዚያም ተንበርክኮ፤ በታላቅ ድምፅ፣ "ጌታ ሆይ! ይህን ኀጢአት አትቍጠርባቸው" ብሎ ጮኸ፤ ይህን ካለ በኋላም አንቀላፋ።

8 ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስማምቶ ነበር።

የአማኞች መሰደድና መበተን

በዚያ ቀን በኢየሩሳሌም በነበረችው

ሐሥ 8፥14 17

7፥60 ማቴ5፥44፣ 9፥24፣ ሉቃ22፥41፣ ሐሥ9፥40 8፥1 ቍጥ፡ ሐሥ7፥58፣ 9፥31፣ 11፥19

7፥46 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የያዕቆብ ቤት ይላሉ።

ሥራ፣ በመልእክቶችና ለሰባቱ ዐበይት ክርስቲያናት በተጻፉት መልእክቶች (ራእ 2-3) እንደ ተጻፈው ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነው ሐዋርያዊ መመሪያ የተመሠረተው በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ ነበር።

(3) እጅግ በጣም የሚያሳዝነው ነገር ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ቤተ ክርስቲያን በባሕልና በአደረጃጀት ረገድ ራሷን ከሰው ምድራዊ ሐሳብ ጋር በማስማማት ከመለኮታዊው መነሻዋ በመለየት፣ የእግዚአብሔርን ሰማያዊ መመሪያ ማሻሻል መጀመሯ ነው። ይህም በቤተ ክርስቲያን አሠራር ውስጥ ሰው ሠራሽ መመሪያዎች እንዲበዙ አደረገ።

(4) የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሙሉ ዕቅድ፣ ጎደልና ሀልዎት እንደ ግና እንዲኖራት ከተፈለገ ከራስዋ መንገድ ዘወር በማለት የአዲስ ኪዳንን ሐዋርያዊ መመሪያ እግዚአብሔር ያለጊዜ ገደብ ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጠው መርሐ እንደ ሆነ አድርጋ መቀበል ይኖርባታል።

7፥51 **መንፈስ ቅዱስን ሁልጊዜ ትቃወማላችሁ፤** የእስራኤል ታሪክ በተደጋጋሚ አምላኩን የማይታዘዝና የተገለጠውን ቃሉን የሚቃወም ሕዝብ ታሪክ ነው። አዋቂው ሕዝቡን ለመታዘዝ ከመፈለግ ይልቅ፣ ልባቸው በዙሪያቸው ያሉት እግዚአብሔርን የማያመልኩ ሕዝቦች ወደሚከተሉት መንገድና የኑሮ ዘይቤ ዘወር አለ። ስለ ክርስቶስ መምጣት የሚናገሩትንና የንስሓ ጥሪ የሚያቀርብላቸውን ነቢያት ገደሉ (ሥ 52-53)። *መንፈስ ቅዱስን መቃወም* ማለት ይህ ነው።

በአዲስ ኪዳን የክርስቶስ እስራኤል የሆኑትም እንዲሁ በብሉይ ኪዳን የነበሩ አስራኤላውያን ከኖሩት ዐይነት ኑሮ ራሳቸውን በጥንቃቄ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። የክርስቶስ ዐበይት ክርስቲያናት ከክርስቶስና ከቃሉ ዘወር ሊሉና የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ መታዘዝንም ሊቃወሙ ይችላሉ፤ ይህ በሚሆንበትም ጊዜ የእግዚአብሔር ፍርድ በራሳቸው ላይ እንዲመጣ ማድረጋቸው ነው። ይኸውም የእግዚአብሔር *መንግሥት* ከእነርሱ ይወሰዳል ማለት ነው (ሮሜ 11፥20-22፤ ራእ 2—3 ይመ)።

7፥55 **ኢየሱስ ... ቆሞ አየና፤** መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ እንደተቀመጠ ይናገራል (2፥34፤ ማር 14፥62፤ ሉቃ 22፥69፤ ቈላ 3፥1)። ነገር ግን በዚህ ስፍራ ኢየሱስ የቆመው የመጀመሪያ ሰማዕቱን ወደ እርሱ ሲመጣ ለመቀበል ነው። እስጢፋኖስ በሰዎች ፊት ስለ ኢየሱስ ተናገረ፣ ስለ እምነቱም ቆመ። አሁን ደግሞ ክርስቶስ አገልጋዩን በማክበር በሰማያዊ አባቱ ፊት ይመሰክርለታል። ወደ ሞት ለቀረቡ ታማኝ አማኞች ሁሉ፣ አዳኙ አማላጅና ጠበቃ በመሆን ቆሞ ለመቀበል ዝግጁ ነው (ከማር 8፥38፤ ከሉቃ 12፥8፤ ከሮሜ 8፥34፤ ከ1ዮሐ 2፥1 *ጋር* ያነጻጽሩ)።

8፥1 **ታላቅ ስደት፤** በዜተ ክርስቲያን ላይ በመጀመሪያ ለደረሰው መጠነ ሰፊ ስደት ሳውል መሪ የነበረ ይመስላል (ቍጥ 1-3፣ 9፥1)። ስደቱም ከባድና አስጨናቂ ነበር። ክርስቲያን ወንድሞችና እኅቶች ወደ ውኃኒ ተጣሉ (ቍጥ 3)፤ ተደብደቡ (22፥19)፤ ብዙዎችም ተገደሉ (22፥20፤ 26፥10-11)። ይሁን እንጂ ይህን ስደት ቤተ ክርስቲያን ታላቁን የወንጌል አገልግሎት እንድትጀምር እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል (ቍጥ 4)።

በተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፤ ከሐዋርያትም በስተቀር እማኞች በሙሉ በይሁዳና በሰማርያ አውራጃዎች ሁሉ ተበተኑ፤ ²ለመንፈሳዊ ነገር የተጉ ሰዎችም እስጢፋኖስን ቀበሩት፤ ደግሞም እጅግ አለቀሱለት። ³ሳውል ግን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ታጥቆ ተነሣ፤ ከቤት ወደ ቤት በመግባትም ወንዶችንና ሴቶችን ጐትቶ እያወጣ ወህኒ ቤት ያስገባቸው ነበር።

8፥3 ሐሥ 7፥58፤ 9፥1፤ 13፥21፤ 22፥4፤ 19፥ 26፥10፤ 11፤ 1ቆሮ 15፥9፤ ገላ 1፥13፤ 23፤ ፊል 3፥6፤ 1ጢሞ 1፥13

ፊልጶስ በሰማርያ

ሐሥ 8፥26-40

⁴የተበተኑትም በሄዱበት ሁሉ ቃሉን ሰበኩ፤ ⁵ፊልጶስም ወደ አንዲት የሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው። ⁶ብዙ ሕዝብም ፊልጶስ የተናገረውን ሲሰሙና ያደረገውንም ታምራዊ ምልክቶች ሲያዩ፤ አንድ ልብ ሆነው ያዳምጡት ነበር። ⁷ርኩሳን፣ መናፍስትም እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ወጡ፤ ብዙ ሽባዎችና አንካሶችም ተፈወሱ፤ ⁸ስለዚህ የተነሣም በከተማዪቱ ታላቅ ደስታ ሆነ።

8፥4 ሐሥ 5፥36፤ 13፥6 8፥10 ሐሥ 14፥11፤ 28፥6 8፥12 ማቴ 3፥2፤ ሐሥ 2፥38 8፥13 ቍ 6፤ ሐሥ 19፥11

ጠንቋዩ ሲሞን

⁹ነገር ግን ከዚህ ቀደም ሲል በከተማዪቱ ውስጥ እየጠነቈለ የሰማርያን ሰዎች ሁሉ ያስገረመ፣ ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው ነበር፤ እርሱም ራሱን እንደ ታላቅ ሰው ይቈጥር ነበር። ¹⁰ካታናሽ እስከ ታላቅ ያለው ሰው ሁሉ፣ "ይህ ሰው 'ታላቁ ኀይል' በመባል የሚታወቀው መለኮታዊ ኀይል ነው" በማለት ከልብ ያዳምጡት ነበር፤ ¹¹ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በጥንቈላ ሥራው ስላስገረማቸው ውም ትኵረት ሰጥተው ይከተሉት ነበር። ¹²ነገር ግን ፊልጶስ ስለ ስማዕበሐይ መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሰበከላቸውን አምነው በመቀበላቸው ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፤ ¹³ራሱ ሲሞን እንኳ ሳይቀር አምኖ ተጠመቀ፤ ፊልጶስንም ተከትሎ ሄደ፤ የሚደረገውን ምልክትና ታላቅ ታምራት

ሐሥ 19፥11-12

⁹8፥5 ወይም መሲሕ
⁹8፥7 ወይም ክፉ

8፥5 ፊልጶስም ወደ አንዲት የሰማርያ ከተማ ወርዶ፤ ከቍ 5-24 ይመልከቱ። በሰማርያ አማኞች ላይ መንፈስ ቅዱስ ከመውረዱ በፊት በተካታታይ የተደረጉ ቀጥሎ ያሉ ሁኔቶችን ልብ ይበሉ። (1) ፊልጶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ሰበከ፤ እግዚአብሔርም ቃሉን በታምራዊ ምልክቶች አጸና (ቍ 5-7)።

(2) አብዛኞቹ የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበሉ (ቍ 14)፤ በኢየሱስ አመኑ (ቍ 12)፤ ተፈወሱ እንዲሁም ከክፉ መናፍስት ነጻ ወጡ (ቍ 7)፤ ከዚያም በውሃ ተጠመቁ (ቍ 12-13)። ስለዚህ ድኅነትን በማግኘት፣ መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ለመስጠት የሚሠራውን ሥራና የእግዚአብሔርን መንግሥት ኀይል ተለማመዱ (ቍ 12 እና ማብ ይመ)።

(3) ይሁን እንጂ በክርስቶስ አምነው ከተለመጡና የውሃ ጥምቀት ከመሰዱ በኋላ "መንፈስ ቅዱስ በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር" (ቍ 16)።

(4) የሰማርያ ሰዎች በክርስቶስ አምነው ከተለመጡ ከተቂት ቀናት በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ሰማርያ መጡ፤ የሰማርያ ሰዎችም መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው (ቍ 14-15)። ክርስቶስን አምነው በተቀበሉበት ጊዜና በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁበት ጊዜ መካከል ግልጽ የሆነ የጊዜ ክፍተት አለ (ቍ 16-17 ይመ፣ ከ2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። በሌላ አነጋገር የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ሁኔታ ደቀ መዛሙርት በጸንጤ ቄስጤ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁበትን መንገድ የተከተለ ነው (በገጽ 1646 ላይ፣ *"የደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል"* በሚል ርእስና በገጽ 1664 ላይ፣ *"በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ"* በማል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)።

(5) ያለጥርጥር በሌሎች ልሳኖች የመናገርና ትንቢትን መናገር የመሳሰሉ ውጭአዊ ምልክቶች መንፈስ ቅዱስን ከመቀበል ጋር ተከትለው የመጡ መሆን አለባቸው።

8፥6 ያደረገውንም ታምራዊ ምልክቶች፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስብከት የሚያጸኑ ታምራዊ ምልክቶች ክርስቶስ ለሐዋርያት ብቻ የሰጣቸው ስጦታዎች አልነበሩም (ማር 16፥15-18፤ እንዲሁም በገጽ 1527 ላይ፣ *"አማኞች ሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በደቀ መዛሙርት አገልግሎት የተሰወጠ ማለትም "የሚያምኑ ሁሉ" ኢጋንንትን ማውጣትን (ማር 16፥17) እና በሽተኞችን መፈወስን (ማር 16፥18) የመሰሰሉትን ምልክቶች በኢየሱስ ስም እንደሚፈጽሙ ጌታ ተስፋ ሰጥቶአል። ፊልጶስ ያደረገውም ይህንኑ ነበር።

8፥12 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ... አምነው፤ የሰማርያ ሰዎች ለድነት የሚያስፈልገውን መሠረታዊ ነገር ሙሉ በሙሉ በሚሚላታቸው፣ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ከመውረዱ በፊት ክርስቲያኖች ሆነዋል። (1) ፊልጶስ የሰበከላቸውን "አምነው በመቀበላቸው ... ተጠመቁ"፣ የሰማርያ ሰዎች እምነት በትክክል ለድነት የሚያበቃ መሆኑን የሚያመለክቱ የሚከተሉት ሁለት ማስረጃዎች አሉ፡ (ሀ) ፊልጶስና (ቍ 12) ሐዋርያት (ቍ 14) የሰማርያ ሰዎች እምነት ትክክለኛ እንደ ሆነ አረጋግጠዋል፡ (ለ) የሰማርያ ሰዎች ማመናቸውን ራት ለፊት ለመመስከር የውሃ ጥምቀትን ሥርዐት በመፈጸም ራሳቸውን ለክርስቶስ ሰጡ። መጽሐፍ ቅዱስም፣ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" (ማር 16፥16) በማለት ያረጋግጣል። ስለዚህ የሰማርያ ሰዎች ዳግም ልደትን ያገኙና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆኑ ነበሩ (ሮሜ 8፥9)።

(2) ከአያሌ ቀናት በኋላ መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው (ቍ 17) ለድነት አልነበረም። ነገር ግን ደቀ መዛሙርት በጸንጤ ቄስጤ ዕለት የተቀበሉትን መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው ነበር። ይኸውም ለአገልግሎትና ለምስክርነት የሚረዳ ኀይልን ለማስታጠቅ ነበር (1፥8፤ 2፥4)። ሉቃስ በመሠረቱ፣ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ከአዲስ ልደት ወይም ከዳግም ልደት አንጻር ሳይሆን፣ ኀይልን በማስታጠቅ አንጻር ነበር (1፥8፤ 2፥38፤ 8፥17፤ ፤10፥47፤ 19፥2፤) እንዲሁም (በገጽ 1606 ላይ፣ *"ዳግም ልደት"* በሚል ርእስ፣ በገጽ 1646 ላይ፣ *"የደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል"* በማል ርእስና በገጽ 1664 ላይ፣ *"በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ"* በማል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)።

(3) አንዳንድ ሰዎች የሰማርያ ሰዎች እምነት ለድነትና ለዳግም ልደት የሚያበቃ እምነት አልነበረም ብለው ያስባሉ፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞላው ፊልጶስ (6፥3-5) እምነታቸው ትክክለኛ ያልሆነን ሰዎች ያጠምቃል፣ ይፈውሳል፣ አጋንንትም

አይቶም ተገረመ።

14በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላቸውን በሰሙ ጊዜ፣ ጴጥሮስንና
የሐንስን ወደ እነርሱ ላካቸው። 15እነርሱም
ሰማርያ በደረሱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን
እንዲቀበሉ ለሰማርያ ሰዎች ጸለዩላቸው፤
16ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በጌታ ኢየሱስ
ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ ገና መንፈስ
ቅዱስ በአንዳቸውም ላይ አልወረደም
ነበር። 17ስለዚህ ጴጥሮስና የሐንስ
እጃቸውን ጫኑባቸው፤ እነርሱም መንፈስ
ቅዱስን ተቀበሉ።

18ሲሞንም ሐዋርያት እጃቸውን
በሚጭኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰዋ
አይቶ፣ ገንዘብ አመጣላቸውና እንዲህ አላ
ቸው፤ 19"እጄን የምጭንበት ሰው ሁሉ
መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን
ለእኔም ስጡኝ።"

20ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፤

8፥14 ቍ·1፣ ሥ·22፥8፣ ዕብ4፡12
8፥15 ዮሐ20፡22
8፥16 ማቴ28፡19፣ ሐሥ2፡38፣ 10፡44፣ 19፡2
8፥17 ዮሐ20፡22፣ ሐሥ6፡6
8፥20 2ነገ5፡16፣ ጾን5፡17፣ ማቴ10፡8፣ ሐሥ2፡38
8፥21 ነህ2፡20፣ መዝ78፡37
8፥22 ሐሥ2፡38
8፥24 ዘፀ8፡8፣ ዘኍ21፡7፣ 1ነገ13፡6፣ ኤር42፡2
8፥25 ቍ·40፣ ሐሥ13፡48

"የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት
አስበሃልና፣ አንተም ገንዘብህም አብራችሁ
ጥፋ! 21ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ቅን
ስላልሆነ፣ አንተ በዚህ አገልግሎት ድርሻ
ወይም ዕድል ፈንታ የለህም። 22አሁንም
ስለዚህ ክፋትህ ንስሓ ግባ፤ ወደ ጌታም
ጸልይ፤ ምናልባት ይህን የልብህን ሐሳብ
ይቅር ይልህ ይሆናል፤ 23ምክንያቱም
በመራራነት ተሞልተህ፣ በዐመፅ ሰንሰለት
ተይዘህ አይሃለሁና።"

24ሲሞንም መልሶ፣ "ከተናገራችሁት
ምንም ነገር እንዳይደርስብኝ ጌታን
ለምኑልኝ" አላቸው።

25ጴጥሮስና የሐንስም የጌታን ቃል
ከመሰከሩና ገልጠው ከተናገሩ በኋላ፣ በብዙ
የሰማርያ መንደሮች ወንጌልን እየሰበኩ፣
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

ያመጣላቸዋል ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም።

8፥16 በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር፤ በጸንጤ ቊስጥ፡ ዕለት በአማኞች ላይ የወረደው መንፈስ ቅዱስ በተመሳሳይ መንገድ ገና በእነርሱ ላይ አልወረደም ነበር (2፥4)። አብ በሰጠው ተስፋ መሠረት (1፥4)፣ ክርስቶስም "በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" ብሎ አስቀድሞ በተናገረው መሠረት (1፥5) እርሱ ገና በእነርሱ ላይ አልወረደም ነበር። በተሰፋ የሚጠበቁትን መንፈሳዊ መገለጦች በተለይም መለከታዊ የሆኑ መንፈሳዊ ንግግሮችን በገልጽ አልተለማመዱም ነበር (ቍ· 5-24 እና ማቴ፡ ቍ፡ 18 ማቴ ይመ)።

8፥17 መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡ እጆችን በመጫን አገልግሎት አማካይነት በጸንጤ ቄስጤ ዕለት እንደ ሆነው የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (1፥8፡ 2፥4)።

የሰማርያ ሰዎች "ሁለት ደረጃ" ያለው ልምምድ ማለትም በመጀመሪያ ማመን ቀጥሎም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የሚያሳየው በጸንጤ ቄስጤ ዕለት አማኞች ያከናወኑት "ሁለት ደረጃ" ያለው ልምምድ ያልተለመደ ነገር ነው ተብሎ እንዲገመት አያደርገንም። ሐዋርያው ጳውሎስ በ9፥5-17 ላይ እና የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት በ19፥1-6 ላይ የነበራቸው ልምምድ የሰማርያ ሰዎች ከተለማመዱት ልምምድ ጋር አንድ ዐይነት ነበር። በመጀመሪያ ክርስትናን ጌታ አድርገው ተቆበሉት፣ ከዚያ በኋላም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። ይሁን እንጂ ቂጣሪያ በነበሩት አሕዛብ ላይ እንደተፈጸመው ለድነት በሚያበቃው እምነትና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መካከል ይህን ያህል የጊዜ መራዘም መኖር የለበትም (ምዕ 10)።

8፥18 ሲሞንም ... አይቶ፤ መንፈስ ቅዱስ በሰማርያ ሰዎች ላይ በወረደ ጊዜ የተከሠቱ ውጭአዊ ምልክቶች ለጠንቋዩ ለሲሞን እንኳ በግልጽ የሚታዩ ነበሩ። በዚህ ጊዜ የታዩት ውጭአዊ ምልክቶች በጸንጤ ቄስጤ ዕለት በቀደሙት ደቀ መዛሙርት ላይ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ በግልጽ ከታዩት ሁኔታዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው ብሎ ማጠቃለል ተገቢ ነው፡ ይኸውም በሌሎች ልሳኖች መናገር ነው (2፥4፡ 10፥45-46፡ 11፥15 እና ማብ፡ 19፥6 እንዲሁም በገጽ 1669 ላይ፣ "በልሳን መናገር" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህ ክሥተት ለሰማርያ ሰዎችም ሆነ ለሐዋርያት በእጹስ አማኞች ላይ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደ የሚያሳይ ማረጋገጫ ምልክት ሆነ።

8፥21 ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ስላልሆነ፤ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተፈጸመው ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ለመሆን ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው። (1) የመንፈስ ቅዱስን ኀይልና ስጦታ እንዲሁም ስጦታውን ለማስተላለፍ የሚያስችለውን ሥልጣን ለማግኘት የፈለገውን ሲሞንን (ቍ· 19)፣ እግዚአብሔር ተቃውመው፡ ይኸውም ሲሞን ልቡ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ስላልሆነ እንዲሁም በክፋትና በኀጢአት አስራት ውስጥ ስለሆነ ነበር (ቍ· 22-23)። ትክክለኛው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚወርደው እግዚአብሔርን ለሚፈሩና ጽድቅን ለሚያደርጉ ብቻ ነው (10፥35 ይመ፡ ከ10፥44-48 ጋር ያንጻጽሩ፡ 5፥32 ይመ)።

(2) ከጸንጤ ቄስጤ ዕለት በፊትም ሆነ በኋላ የክርስቶስ ተከታዮች ራሳቸውን ከሞት ለተነሣው ጌታ ሙሉ በሙሉ ሰጡ (1፥2-14፡ 2፥32)፡ ባለማቋረጥም በጸሎት ይተጉ ነበር (1፥14፡ 6፥4)። ኮነኒኢትና ከዓለም የመለየት ኑሮን ኖሩ (2፥38-40)፡ ለሐዋርያትም ትምህርት ታዘዙ (2፥42፡ 6፥4)። ተከታታይ የሆነ ወይም አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ሙሳት ከኀጢአትና ከክፋት መንገድ ዘወር በማለት ለክርስቶስ የመታዘዝን ኑሮ ለሚኖሩ አማኞች ብቻ ተሰጠ (ከ2፥42፡ 3፥1፡19፥22-26፡ 4፥8፡19-35፡ 5፥29-32፡ 6፥4፡ 8፥14-21፡ 9፥1-19፡ 10፥34-47፡ 19፥1-6፡ 24፥16 ጋር ያንጻጽሩ)። በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መመላለስና በእርሱም ምሪት መራመድ ምንጊዜም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ባሕርይ ነው (ገላ 5፥16-25፡ ኤፌ 5፥18 ይመ)።

(3) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ጸሐ ተፈጥሮአዊ ልምምድ የነኒኢተኛ ተፈጥሮን መንገዶች ተከትሎ በማኖር ሰው ሕይወት ውስጥ ቢከሠት፣ ክሥተቱ ከክርስቶስ አይደለም (ከ1ዮሐ 4፥1-6 ጋር ያንጻጽሩ)። ይህ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም ተመሳሳሉ የተገለጠ የመንፈስ አሠራር ሲሆን፣ ከእጋንንታዊ ኀይልና ስጦታዎችም ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል (ማቴ 7፥21-23፡ 2ተሰ 2፥7-10 እንዲሁም በገጽ 1694 ላይ፣ "እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ

8፥26 ሐሥ5፥19፤ 6፥5
8፥27 1ነገ8፥41-43፤ መዝ68፥31፤ 87፥4፤ ኢሳ56፥3-5፤ ሶፎ3፥10፤ ዮሐ12፥20
8፥29 ሐሥ10፥19፤ 11፥12፤ 13፥2፤ 20፥23፤ 21፥11
8፥33 ኢሳ53፥7፤8
8፥35 ማቴ5፥2፤ ሉቃ24፥27፤ ሐሥ13፥32፤ 17፥2፤ 18፥28፤ 28፥23
8፥36 ሐሥ2፥38፤ 10፥47
8፥39 1ነገ18፥12፤ 2ነገ2፥16፤ ሕዝ3፥12፡14፤ 8፥3፤ 11፥1፡24፥ 43፥5፤
2ቆሮ12፥2፤ 1ተሰ4፥17፤ ራእ12፥5
8፥40 ቀሥ25፥ ሐሥ10፥1፡24፥ 12፥19፤ 21፥8፡16፥ 23፥23፡33፥ 25፥1፡4፡6፡13
9፥1 ሐሥ8፥3
9፥2 ኢሳ17፥1፤ ኤር49፥23፤ ሐሥ19፥9፡23፥ 22፥4፤ 24፥14፡22
9፥3 1ቆሮ15፥8
9፥4 ኢሳ6፥8
9፥6 ቀሥ16፥ ሕዝ3፥22
9፥7 ዳን10፥7፤ ዮሐ12፥29
9፥8 ቀሥ18
9፥10 ሐሥ10፥3፡17፡19፤ 12፥9፤ 16፥9፡10፥ 18፥9
9፥11 ቀሥ30፥ ሐሥ11፥25፥ 21፥39፥ 22፥3

[26]የጌታም መልአክ ፊልጶስን፣ "ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ በሚያወርደው በምድረ በዳው መንገድ ሂድ" አለው። [27]እርሱም ተነሥቶ ሄደ። እነሆ የኢትዮጵያ ንግሥት የህንደኬ ባለሟልና የሀብት ንብረቷ ሁሉ አዛዥ የሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አገኘ። ይህም ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር። [28]ሲመለስም በሠረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር። [29]መንፈስም ፊልጶስን፣ "ሂድና ወደዚህ ሠረገላ ቅረብ" አለው።

[30]ፊልጶስም ፈጥኖ ወደ ሠረገላው ሄደና ጃንደረባውም የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰምቶ፣ "ለመሆኑ፣ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" አለው።

[31]ጃንደረባውም፣ "የሚያስረዳኝ ሰው ሳይኖር እንዴት አድርጌ አስተውላለሁ" አለውና፣ እርሱም ወደ ሠረገላው ወጥቶ አብሮት እንዲቀመጥ ፊልጶስን ለመነው።

[32]ጃንደረባው ያነብ የነበረው የመጽሐፍ ክፍል ይህ ነበር፤

"እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤
የበግ ጠቦት በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል፣
እንዲሁ አፉን አልከፈተም።
[33]ፈርዱን በማዋረዱም ፍትሕን ተነፈገ፤
ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፣
ስለ ትውልዱ ማን ሊናገር
ይችላል?"

[34]ጃንደረባውም መልሶ ፊልጶስን፣ "ነቢዩ ይህን የሚናገረው ስለ ማን ነው? ስለ ራሱ ነው፣ ወይስ ስለ ሌላ ሰው? አባክህ ንገረኝ" አለው። [35]ፊልጶስም አፉን ከፈተ፤ ከዚህም መጽሐፍ ክፍል ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት።

[36]በመጓዝ ላይ ሳሉም ውሃ ካለበት ስፍራ ደረሱ፤ ጃንደረባውም፣ "እነሆ፤ ውሃ አለ፤ ይጠይቀኝ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምን ነገር አለ?" አለው። [37]ፊልጶስም፣ "በፍጹም ልብህ ካመንህ መጠመቅ ትችላለህ" አለው። ጃንደረባውም፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ" ሲል መለሰለት። [38]ሠረገላውም እንዲቆም አዘዘ። ከዚያም ሁለቱ አብረው ወደ ውሃው ወረዱ፤ ፊልጶስም ጃንደረባውን አጠመቀው። [39]ከውሃውም በወጡ ጊዜ፣ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጥቆ ወሰደው፤ ጃንደረባውም ከዚህ በኋላ አላየውም፤ ሆኖም ደስ እያለው ጕዞውን ቀጠለ። [40]ከዚያ በኋላ ግን ፊልጶስ በአዛጦን ታየ፤ ቂሳሪያም እስኪደርስ ድረስ፣ በሚያልፍባቸው ከተሞች ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።

የሳውል ጥሪ

9፡1-19 ተዛ ምብ — ሐሥ 22፡3-16፤ 26፡9-18

9 ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት ለመግደል አሁንም እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናቱ ሄደ፤ [2]የጌታን መንገድ የሚከተሉትን ወንዶችንም ሆኑ ሴቶችን በዚያ ካገኘ አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ እንዲችል፣ በደማስቆ ለነበሩት ምኩራቦች ደብዳቤ እንዲሰጠው ሊቀ ካህናቱን ለመነው።

[3]ደማስቆ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ብርሃን ከሰማይ ድንገት በዙሪያው አንጸባረቀበት፤ [4]እርሱም በምድር ላይ ወደቀ፤ በዚያ ጊዜም "ሳውልኤ፤ ሳውልኤ፤ ለምን ታሳድደኛለህ?" የሚል ድምፅ ሰማ።

[5]ሳውልም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?" አለው።

እርሱም እንዲህ አለው፤ "እኔማ አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ። [6]አሁንም ተነሥተህ ወደ ከተማዪቱ ግባ፤ ማድረግ የሚገባህም ይነገርሃል።"

[7]ከሳውል ጋር ይጓዙ የነበሩትም ሰዎች ድምፁን እየሰሙ ማንንም ባላዩ ጊዜ፣ እጓቸውን ይዘው ቆሙ። [8]ሳውልም ከወደቀበት ተነሥቶ ዐይኑን ሲገልጥ ምንም ማየት አልቻለም፤ ስለዚህ ሰዎቹ እጁን ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አስገቡት። [9]ሦስት ቀንም ታውረ፤ እህል ውሃም አልቀመሰም።

[10]በደማስቆ ሐናንያ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበር፤ ጌታም በራእይ፣ "ሐናንያ" ብሎ ጠራው።

እርሱም፣ "ጌታ ሆይ፤ እነሆኝ" አለ።

[11]ጌታም እንዲህ አለው፤ "ተነሣና 'ቀጥተኛ ጐዳና' በተባለው መንገድ ይሁዳ ወደ ተባለ ሰው ቤት ሂድና፤ አዚያም ሳውል

^8፡38 አንዳንድ ቅጆች ይህን ቊጥር አይጨምሩም። ከአንዳንድ የቅርብ ጊዜ ቅጆች የተመለደ ነው።

9፡3-19፤ በዚህ ክፍል ጳውሎስ እንዴት በክርስቶስ እንዳመነ ተገልጾአል፤ በተለይም ከቊ 3-9 ጳውሎስ ከደማስቆ ከተማ ውጪ እንዴት በክርስቶስ እንዳመነ ተመቅሶአል (ከ22፡3-16፡ 26፡9-18 ጋር ያንጻጽሩ)። በክርስቶስ ማመኑ በኋላ በይሁዳ ቤት (ቊ 11) ሳይሆን፣ በዚህ ስፍራ ለመሆኑ በሚከተሉት ሐሳቦች ተገልጾአል፤ (1) ጳውሎስ የክርስቶስን መመሪያ ታዝዘ (ቊ 6፡ 22፡10፡ 26፡15-19)፤ የወንጌል "አገልጋይና ምስክር" ለመሆን ራሱን አሳልፎ ሰጠ (26፡16)፤ ለአሕዛብም የወንጌል መልእክተኛ ሆነ (26፡17-19)፤ ራሱንም ለጸሎት አሳልፎ ሰጠ (ቊ 11)፤ (2) ሐናንያ ሐዋርያው ጳውሎስን፣ "ወንድሜ ሳውል" ብሎ ጠራው (ቊ 17)። ጳውሎስ አዲስ ልደትን ያገኘ አማኝ እንደሆነ (ዮሐ 3፡3-6)፤ ለክርስቶስና ለእግዚአብሔር ተልእኮ ራሱን የሰጠ፤ ከመጠመቅ በላይ ምንም የማያስፈልገው፣ ወይኑ ሊበራለትና በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላ (ቊ 17-18፡ 9፡17 እና ማብ ይመ) የሚገባው ሰው መሆኑን ሐናንያ ተረድቶ ነበር።

9፡11 እየጸለየ ነውና፤ ጳውሎስ ከኢየሱስ ጋር ከተገናኘና እርሱንም ጌታውና መሲሑ አድርጎ ከተቀበለው በኋላ ምራት ያገኘ ዘንድ በጸምና በጸሎት በፍጹም ልብ በእግዚአብሔር ፊት ይተጋ ነበር። ለድነት የሚያበቃው እምነትና ይህንንም ተከትሎ የሚመጣው አዲስ ልደት ምንጊዜም አማኞች ከአዲሱ ጌታቸውና አዳኛቸው ጋር ኅብረት ይኖራቸው ዘንድ እንዲናፍቁ ያደርጋቸዋል።

ሮሚ ባል አንድ የጠርሴስ ሰው እየጸለየ
ነውና ፈልገው፤ 12ምክንያቱም ሐናንያ
የሚባል ሰው እርሱ ወዳለበት መጥቶ እጁን
እንደ ሚጭንበትና ዐይኑ እንደሚበራለት
በራእይ አይቶአል።" 13ሐናንያም መልሶ
እንዲህ አለው፤ "ጌታ ሆይ፤ ይህ ሰው እኩ
በኢየሩሳሌም ባሉ ቅዱሳንህ ላይ ምን ያህል
ጕዳት እንዳደረሰ ከብዙ ሰው ሰምቻለሁ፤
14ወደዚህም የመጣው ስምህን የሚጠሩትን
ሁሉ ለማሰር ከካህናት አለቆች ሥልጣን
ተቀብሎ ነው።"

15ጌታም እንዲህ አለው፤ "ሂድ፤ ይህ
ሰው በአሕዛብና በነገሥታት ፊት እንዲሁም
በእስራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም
የተመረጠ ዕቃዬ ነውና፤ 16እኔም ስለ
ስሜም ያህል መከራ መቀበል እንዳለበት
አሳየዋለሁ።"

17ሐናንያ ሄዶ ወደተባለውም ቤት ገባ፤
በላውልም ላይ እጁን ጭኖ፣ "ወንድሜ
ሳውል ሆይ፤ ወደዚህ ስትመጣ በመንገድ
ላይ የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ፣ ዐይንህ
እንዲበራና፣ በመንፈስ ቅዱስም እንድት
ሞላ እኔን ልኮኛል" አለው። 18ወዲያውም

9፥12 ግሪ5፥23
9፥13 ሮሜ32፥
ሐሥ8፥3፤
26፥10፤ ሮሜ1፥7፤
15፥25፡26፡31፤
16፥2፡15፤
ኤፌ1፥1፤ ፊል1፥1
9፥14 ቈላ2፥21
ሐሥ2፥21
9፥15 ሐሥ13፥2፤
25፥22፡23፤
26፥1፤ ሮሜ1፥1፤
11፥13፤
15፥15፡16፤
ገላ1፥15፡16፤
2፥7፡8፤
1ጢሞ1፥12
9፥16 ሐሥ20፥23፤
21፥11፤
2ቆሮ6፥4-10፤
11፥23-27፤
2ጢሞ1፥8፤
2፥3፡9
9፥17 ሉቃ1፥15፤
ሐሥ6፥6
9፥18 ሐሥ2፥38

9፥19 ሐሥ11፥26፤
26፥20

ከሳውል ዐይን ላይ ቅርፊት የመሰለ ነገር
ወደቀ፤ እንደ ገና ማየት ቻለ፤ ተነሥቶም
ተጠመቀ፤ 19ምግብም በልቶ በረታ።

ሳውል በደማስቆና በኢየሩሳሌም

ሳውል በደማስቆ ከነበሩት ደቀ
መዛሙርት ጋር አያሌ ቀን ተቀመጠ።
20ወዲያውም፣ ኢየሱስ የክርስቶስ ልጅ
መሆኑን በየምኵራቦቹ መሰበክ ጀመረ።
21የሰሙትም ሁሉ በመገረም፣ ይህ ሰው
"በኢየሩሳሌም ይህን ስም የሚጠሩትን
ሲያጠፋ የነ በረ አይደለምን? ደግሞም
ወደዚህ የመ ጣው እንርሱን አስሮ ወደ
ካህናት አለቆች ሊወስዳቸው አልነበረምን?"
አሉ። 22ሳውል ግን እየበረታ ሄደ፤ በደማስቆ
ለሚኖሩትም አይሁድ ኢየሱስ እርሱ
ክርስቶስ መሆኑን ማስረጃ እያቀረበ
አፋቸውን ያስይዛቸው ነበር።

9፥20 ማቴ4፥3፤ ሐሥ13፥5፡14፤ 14፥1፤ 17፥2፡10፡17፤
18፥4፡19፤ 19፥8 9፥21 ቍ14፤ ሐሥ8፥3
9፥22 ሉቃ2፥11፤ ሐሥ5፥42፤ 17፥3፤ 18፥5፡28
ግ9፥22 ወይም መሲሕ

9፥13 ቅዱሳንህ፤ በአዲስ ኪዳን ያሉ አማኞች "ቅዱሳን" ተብለው ተጠርተዋል (ክ26፥10፤ ኮሮሜ 1፥7፤ ክ1ቆሮ 1፥2፤ ክራእ 13፥7፤ 19፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) በመሠረቱ "ቅዱስ" (ግሪክ፡ ሃግዮስ) የሚለው ቃል ትርጉም ከክብሉት ወጥቶ ለእግዚአብሔር መለየትን የሚያመለክት ነው። በሌላ አነጋገር ቅዱሳን "ለእግዚአብሔር የተለዩ" ወይም "ለእግዚአብሔር የተቀደሱ" ናቸው፤ ይህ የሚያመለክተው በመንፈስ ቅዱስ መመራትንና መቀደስን (ሮሜ 8፥14፤ 1ቆሮ 6፥11፤ 2ተሰ 2፥13፤ 1ጴጥ 1፥2) እንዲሁም ኢየሱስን ለመከተል ጀርባን በዓለም ላይ ማዞርን ነው (ዮሐ 17፥15-17፤ እንዲሁም በገጽ 2000 ላይ፣ "መቀደስ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ይህን እንጂ "ቅዱስ" የሚለው ቃል አማኙ ፍጹም ወይም ኀጢአት መሥራት የማይችል ነው ማለት አይደለም። (2) አማኞችን "የዳኑ ነጢአተኞች" ብሎ መጥራት የአዲስ ኪዳን ልምምድ አይደለም፤ አማኞችን ሁሉ በተመለከተ "ቅዱስ" ለሚለው ቃል የተለመደው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባል የሚከተሉትን የሚያካትት ነው፤ (ሀ) አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፕ የጽድቅ መንገድ መከተላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግዴታ መሆኑ (ኤፌ 5፥3) እና (ለ) የክርስቶስ ለሆኑት ሁሉ ቅድስና የውስጥ ማንነትን የሚገልጽ አስፈላጊ እውነታ መሆኑ ነው (1ቆሮ 1፥30)።

9፥16 ስለ ስሜ ... መከራ መቀበል እንዳለበት፤ የጳውሎስ መለወጥና ድነትን ማግኘት ወንጌልን ለመስበክ መልእክተኛ መሆን ብቻ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ መከራን ለመቀበል መጠራትንም ይጨምራል። ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ብዙ መከራን እንደሚቀበል ከመጀመሪያውኑ ተነግሮት ነበር። በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ ስለ ስሙ መከራን መቀበል የእግዚአብሔርን ከፍተኛ ክብር የሚያገኙት ምልክት (14፥22፤ ማቴ 5፥11-12፤ ሮሜ 8፥17፤ 2ጢሞ 2፥12) እና ፍሬያማ አገልግሎት የሚሰጥበት መንገድ ነው (ዮሐ 12፥24፤ 2ቆሮ 1፥3-6)፤ በመንግሥተ ሰማያትም ብዙ ሽልማትን ያስገኛል (ማቴ 5፥12፤ 2ጢሞ 2፥12)። የእግዚአብሔር ሕይወት ከእነርሱ አልፎ ለሌሎች ይፈስ ዘንድ ሞት በአማኞች መሥራት አለበት (ሮሜ 8፥17-18፡36-37፤ 2ቆሮ 4፥10-12)። የጳውሎስን መከራ የሚያመለክቱ ተጨማሪ ምንባቦች በ20፥23፤ 2ቆሮ 4፥8-18፤ 6፥3-10፤ 11፥23-27፤ ገላ 6፥17፤ 2ጢሞ 1፥11-12፤ 2ቆሮ 1፥4 እና ማብ 11፥23 እና ማብ ላይ ይመልከቱ።

9፥17 ወንድሜ ሳውል ሆይ፤ ቍ 3-19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

9፥17 በመንፈስ ቅዱስም እንድትሞላ፤ ጳውሎስ በክርስቶስ አምኖ ከተለወጠ ከሦስት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ። የጳውሎስ ተሞክሮ ደቀ መዛሙርት በጸንጒ ቂስጤ ዕለት ከተቀበሉት ጋር ተመሳሳይ ነበር (በገጽ 1664 ላይ፣ "በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። በመጀመሪያ ዳግመኛ መወለድ ድነትን አገኘ (ቍ 3-19 እና ማብ ይመ)፡ ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ።

ጳውሎስ የጸንጒ ቂስጤን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲቀበል በልሳን የመናገሩን ሁኔታ ሉቃስ ለይቶ ባይጠቅስም በሚከተሉት ምክንያቶች ጳውሎስ በልሳን መናገሩን ማመን ተገቢ ነው፤ (1) በአዲስ ኪዳን የተለመደው አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ወዲያውኑ በልሳን መናገር መጀመሩ ነው (2፥4፤ 10፥45-46፤ 19፥6፤ 11፥5 እና ማብ ይመ)፤ (2) ጳውሎስ ራሱ በተደጋጋሚ በልሳን እንደተናገረ ለመግለጽ፣ "ከሁላችሁ የበለጠ በልሳን ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ" (1ቆሮ 14፥18) በማለት መስክሮአል።

9፥18 ተጠመቀ፤ ሉቃስ በዋነኛነት ትኵረት የሰጠው የጳውሎስ በልሳን የመናገር ጉዳይ ሳይሆን፣ በተከበረ በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቁ ሁኔታ ነበር (ቍ 17)። የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን የመሻት ጕዳይ ማእከል ሚያደረግ ያለበት ውጭአዊ ምልክቶችን ሳይሆን ራሱን መንፈስ ቅዱስን መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን የሚጠባበቁ አማኞች ሁሉ ለመምጣቱ ምልክት የሆኑትን ውጭአዊ ክሥተቶችንም መሻት ይገባቸዋል (2፥4፤17)።

23ከብዙ ቀንም በኋላ፣ አይሁድ ሳውልን ለመግደል አሢሩ፤ 24እርሱ ግን ዕቅዳቸው ውን ዐውቆ ነበር፤ እነርሱም ሊገድሉት የከተማዋን በር ቀንና ሌሊት ይጠብቁ ነበር፤ 25የእርሱ ተከታዮች ግን በሌሊት በከተማዋ ቅጥር ቀዳዳ አሽልከው በቅርጫት አወረዱት።

26ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ፣ ከደቀ መዛሙርት ጋር ለመቀላቀል ሞከረ፤ እነርሱ ግን በርግጥ ደቀ መዝሙር መሆኑን ስላላመኑ ሁሉም ፈሩት። 27ይሁን እንጂ ባርናባስ ወስዶ ወደ ሐዋርያት አመጣው፤ ሳውልም በጕዞው ላይ ሳለ ጌታን እንዴት እንዳየው፣ ጌታም እንዴት እንደ ተናገረው እንዲሁም በደማስቆ የጌታን ስም እንዴት በድፍረት እንደ ሰበከ ነገራቸው። 28ስለዚህ ሳውል አብሮአቸው ተቀመጠ፤ በኢየሩሳሌም ምም በመዘዋወር በጌታ ስም በድፍረት ይናገር ነበር። 29ከግሪክ አገር ከመጡት አይሁድ ጋር እየተነጋገረ፣ ይከራከር ነበር፤ እነርሱ ግን ሊገድሉት ጥረት ያደርጉ ነበር። 30ወንድሞችም ይህን ባወቁ ጊዜ፣ ወደ ቂሳርያ አውርደው ወደ ጠርሴስ ሰደዱት።

31በዚህ ጊዜ በይሁዳ፣ በገሊላና በሰማርያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በሰላም መኖር ጀመረች፤ ተጠናከረችም። ደግሞም ስጧዚአብሔርን በመፍራት እየተመላለሰችና በመንፈስ ቅዱስ እየተጽናናች በቍጥር እየበዛች ሄደች።

ኤንያና ዶርቃ

32ጴጥሮስም ከአገር ወደ አገር በሚዘዋ ወርበት ጊዜ፣ በልዳ የሚኖሩትን ቅዱሳን ለመጐብኘት ወረደ። 33በዚያም ኤንያ የተ ባለ፣ ስምንት ዓመት የዐልጋ ቍራኛ የነበረ አንድ ሽባ ሰው አገኘ። 34ጴጥሮስም፣ "ኤንያ ሆይ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃልኧ ተነ ሣና መንጋህን አንጥፍ" አለው። ኤንያም ወዲያውኑ ብድግ አለ። 35በልዳና በሰሮና የሚኖሩትም ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ተመለሱ።

36በኢዮጴ ጣቢታ የተባለች አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች፤ የስሟም ትርጓሜ ዶርቃ ማለት ነው። እርዐም ዘወትር በት ጋት በጎ ነገር እያደረገችና ድኾችን እየረዳች ትኖር ነበር። 37በዚያ ጊዜም ታማ ሞተች፤ ሰዎችም አስከሬኗን አጥበው በሰገ ነት ላይ ባለው ክፍል አስቀመጡት። 38ልዳ ለኢዮጴ ቅርብ ስለ ነበረች፣ ደቀ መዛሙርትም ጴጥሮስ በልዳ መሆኑን በሰሙ ጊዜ፣ ሁለት ሰዎች ልከው፣ "እባክህ ፈጥነህ ወደ እኛ ና" ሲሉ ለመኑት።

39ጴጥሮስም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ሄደ፤ እዚያ በደረሰ ጊዜም ሰገነት ላይ ወዳለው ክፍል አወጡት። መበለቶቹም ሁሉ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር በነበረችበት ጊዜ ያደረገቻቸውን ቀሚሶችና ልብሶች እያሳዩት ዙሪያውን ከበው ያለቅሱ ነበር።

40ጴጥሮስም ሁሉንም ከክፍሉ አስወጥቶ ተንበርክኮ ጸለየ፤ ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ፣ "ጣቢታ፤ ተነሺ" አለ። እርሷም ዐይኗን ገለ ጠች፤ ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ቀና ብላ ተቀመጠች፤ 41እርሱም እጁን ይዞ አስነሣት፤ አማኞችንና መበለቶቹንም ጠርቶ ከነሕይ ወቷ አስረከባቸው። 42ይህም ነገር በመላው ኢዮጴ ታወቀ፤ ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ። 43ጴጥሮስም ስምዖን ከተባለ ከአንድ ቍርበት ፋቂ ጋር በኢዮጴ ብዙ ቀን ተቀመጠ።

ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን አስጠራ

10 በቂሳርያ 1የኢጣሊያ ክፍለ ጦር በሚባለው ሰራዊት ውስጥየመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ። 2እርሱም ከመላው ቤተ ሰቡ ጋር በመንፈሳዊ ነገር የተጋና ስጧዚአብሔርን የሚ ፈራ፣ ለሰዎች እጅግ ምጽዋት የሚሰጥ፣ አዘውትሮ ወደ ስጧዚአብሔር የሚጸልይ ነበር። 3አንድ ቀን፣ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ የስጧዚአብሔር መልአክ በራእይ ወደ እርሱ መጥቶ፣ "ቆርኔሌዎስ ሆይ!" ሲለው በግልጽ አየ።

4ቆርኔሌዎስም በድንጋጤ ትኵር ብሎ እያየው፣ "ጌታ ሆይ፤ ምንድን ነው?" አለው። መልአኩም እንዲህ አለው፤ "ጸሎትህና ምጽዋትህ ለመታሰቢያነት ወደ ስጧዚአብሔር ፊት አርጎልሃል። 5አሁንም ሰዎች ወደ

23ከብዙ ቀንም በኋላ፣ አይሁድ ሳውልን ለመግደል አሢሩ፤ 24እርሱ ግን ዕቅዳቸው ውን ዐውቆ ነበር፤ እነርሱም ሊገድሉት የከተማዋን በር ቀንና ሌሊት ይጠብቁ ነበር፤ 25የእርሱ ተከታዮች ግን በሌሊት በከተማዋ ቅጥር ቀዳዳ አሽልከው በቅርጫት አወረዱት።

26ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ፣ ከደቀ መዛሙርት ጋር ለመቀላቀል ሞከረ፤ እነርሱ ግን በርግጥ ደቀ መዝሙር መሆኑን ስላላመኑ ሁሉም ፈሩት። 27ይሁን እንጂ ባርናባስ ወስዶ ወደ ሐዋርያት አመጣው፤ ሳውልም በጕዞው ላይ ሳለ ጌታን እንዴት እንዳየው፣ ጌታም እንዴት እንደ ተናገረው እንዲሁም በደማስቆ የጌታን ስም እንዴት በድፍረት እንደ ሰበከ ነገራቸው። 28ስለዚህ ሳውል አብሮአቸው ተቀመጠ፤ በኢየሩሳሌ ምም በመዘዋወር በጌታ ስም በድፍረት ይናገር ነበር። 29ከግሪክ አገር ከመጡት አይሁድ ጋር እየተነጋገረ፣ ይከራከር ነበር፤ እነርሱ ግን ሊገድሉት ጥረት ያደርጉ ነበር። 30ወንድሞችም ይህን ባወቁ ጊዜ፣ ወደ ቂሳ ርያ አውርደው ወደ ጠርሴስ ሰደዱት።

31በዚህ ጊዜ በይሁዳ፣ በገሊላና በሰማርያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በሰላም መኖር ጀመረች፤ ተጠናከረችም። ደግሞም ስጧዚአብሔርን በመፍራት እየተመላለሰችና በመንፈስ ቅዱስ እየተጽናናች በቍጥር እየበዛች ሄደች።

ኤንያና ዶርቃ

32ጴጥሮስም ከአገር ወደ አገር በሚዘዋ ወርበት ጊዜ፣ በልዳ የሚኖሩትን ቅዱሳን ለመጐብኘት ወረደ። 33በዚያም ኤንያ የተ ባለ፣ ስምንት ዓመት የዐልጋ ቍራኛ የነበረ አንድ ሽባ ሰው አገኘ። 34ጴጥሮስም፣ "ኤንያ ሆይ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃልኧ ተነ ሣና መንጋህን አንጥፍ" አለው። ኤንያም ወዲያውኑ ብድግ አለ። 35በልዳና በሰሮና የሚኖሩትም ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ተመለሱ።

36በኢዮጴ ጣቢታ የተባለች አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች፤ የስሟም ትርጓሜ ዶርቃ ማለት ነው። እርዐም ዘወትር በት ጋት በጎ ነገር እያደረገችና ድኾችን እየረዳች ትኖር ነበር። 37በዚያ ጊዜም ታማ ሞተች፤ ሰዎችም አስከሬኗን አጥበው በሰገ ነት ላይ ባለው ክፍል አስቀመጡት። 38ልዳ ለኢዮጴ ቅርብ ስለ ነበረች፣ ደቀ መዛሙርትም ጴጥሮስ በልዳ መሆኑን በሰሙ ጊዜ፣ ሁለት ሰዎች ልከው፣ "እባክህ ፈጥነህ ወደ እኛ ና" ሲሉ ለመኑት።

39ጴጥሮስም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ሄደ፤ እዚያ በደረሰ ጊዜም ሰገነት ላይ ወዳለው ክፍል አወጡት። መበለቶቹም ሁሉ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር በነበረችበት ጊዜ ያደረገቻቸውን ቀሚሶችና ልብሶች እያሳዩት ዙሪያውን ከበው ያለቅሱ ነበር።

40ጴጥሮስም ሁሉንም ከክፍሉ አስወጥቶ ተንበርክኮ ጸለየ፤ ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ፣ "ጣቢታ፤ ተነሺ" አለ። እርሷም ዐይኗን ገለ ጠች፤ ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ቀና ብላ ተቀመጠች፤ 41እርሱም እጁን ይዞ አስነሣት፤ አማኞችንና መበለቶቹንም ጠርቶ ከነሕይ ወቷ አስረከባቸው። 42ይህም ነገር በመላው ኢዮጴ ታወቀ፤ ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ። 43ጴጥሮስም ስምዖን ከተባለ ከአንድ ቍርበት ፋቂ ጋር በኢዮጴ ብዙ ቀን ተቀመጠ።

ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን አስጠራ

10 በቂሳርያ 1የኢጣሊያ ክፍለ ጦር በሚባለው ሰራዊት ውስጥየመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ። 2እርሱም ከመላው ቤተ ሰቡ ጋር በመንፈሳዊ ነገር የተጋና ስጧዚአብሔርን የሚ ፈራ፣ ለሰዎች እጅግ ምጽዋት የሚሰጥ፣ አዘውትሮ ወደ ስጧዚአብሔር የሚጸልይ ነበር። 3አንድ ቀን፣ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ የስጧዚአብሔር መልአክ በራእይ ወደ እርሱ መጥቶ፣ "ቆርኔሌዎስ ሆይ!" ሲለው በግልጽ አየ።

4ቆርኔሌዎስም በድንጋጤ ትኵር ብሎ እያየው፣ "ጌታ ሆይ፤ ምንድን ነው?" አለው። መልአኩም እንዲህ አለው፤ "ጸሎትህና ምጽዋትህ ለመታሰቢያነት ወደ ስጧዚአብሔር ፊት አርጎልሃል። 5አሁንም ሰዎች ወደ

9፥23 ሐሥ20፥3
9፥24 ሐሥ20፥3፤19፥ 23፥16፤30
9፥25 1ኅሙ19፥12፤ 2ቆር11፥32፤33
9፥26 ሐሥ22፥17፤ 26፥20፤ ገላ1፥17፤18
9፥27 ቍ3-6፤20፥22፤ ሐሥ4፥36
9፥29 ሐሥ6፥1፤ 2ቆር11፥26
9፥30 ቍ11፤ ሐሥ11፥25፤ 8፥40
9፥31 ሐሥ2፥41፤ 8፥1
9፥32 ቍ13
9፥34 ሐሥ3፥6፤16፤ 4፥10
9፥35 ዘዳ5፥16፤ 27፥29፤ መሐ2፥1፤ ኢሳ33፥9፤ 35፥2፤ 65፥10፤
ሐሥ2፥41
9፥36 ኢሳ19፥46፤ 2ዜና2፥16፤ ዕዝ3፥7፤ ዮና1፥3፤ ሐሥ10፥5፤ 1ጢሞ2፥10፤ ቲቶ3፥8
9፥37 ሐሥ1፥13፤ 20፥8
9፥38 ሐሥ11፥26
9፥39 ሐሥ6፥1፤ 1ጢሞ5፥3
9፥40 ማቴ9፥25፤ ሉቃ7፥14፤ 22፥41፤ ሐሥ7፥60
9፥42 ሐሥ2፥41
9፥43 ሐሥ10፥6
10፥1 ሐሥ8፥40
10፥2 ቍ22፥35፤ ሐሥ13፥16፥26
10፥3 መዝ55፥17፤ ሐሥ3፥1፤ 5፥19፤ 9፥10
10፥4 መዝ20፥3፤

10፥4 ማቴ10፥42፤ 26፥13፤ ራእ8፥4 10፥5 ሐሥ9፥36
ግ9፥36 ጣቢታ በአረማይክ ሲሆን ዶርቃ ደግሞ በግሪክ ነው፤ ትርጕሙም ፈቆ ማለት ነው።

9፥31 **እግዚአብሔርን በመፍራት**፣ ሉቃስ፣ "እግዚአብሔርን መፍራት" የሚለውን ታላቅ ቃል በወንጌሉም (ሉቃ 1፥50፣ 18፥2፣ 23፥40) በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉም በአጽንዖት ጠቅሶአል። በምዕራፍ 10 እንደ ተጠቀሰው ወደ አሕዛብ ለተላከው የወንጌል መልእክት መጀመሪያ የሆኑት እግዚአብሔርን የሚፈሩ ማለትም የአይሁድን እምነት የሚያከብሩ አሕዛብ ነበሩ (10፥2፤22፥35፤ 13፥16፤26)። እግዚአብሔርን መፍራት ከክፋት መራቅን ጨምሮ እምነትንና መታዘዝን ያመጣል (ኢዮ 28፥28፣ መዝ 111፥10፣ ምሳ 1፥7)። ይህ ምላሽ በራሱ የመንፈስ ቅዱስ መጽናናትን ያስገኛል። ይህን ሐሳብ ይበልጥ ለመረዳት በገጽ 291 ላይ፣ "እግዚአብሔርን መፍራት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

9፥36 **ዶርቃ ... በጎ ነገር እያደረገች**፣ እግዚአብሔር በጴጥሮስ በኩል ፈውስንና (ቍ. 33-35) ሙታን ማስነሣትን (ቍ. 40) እንዳከናወነ ሁሉ፣ በደርቃም እንዲሁ የቸርነት ሥራንና ፍቅርን ገልጸአል። እንደ ታምራት፣ እንደ ምልክትና እንደ ድንቅ ሁሉ በችግር ላይ ያሉትን በመርዳት የሚደረግ ሥራም የመንፈስ ቅዱስ ምልክት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን እውነት በ1ቆሮ 13 ላይ በአንጽንያት ተናግሮአል (ከ1ጴጥ 4፥10-11 *ጋር ያነጻጽሩ*)።

10፥4 **ጸሎትህና ... ለመታሰቢያነት ወደ እግዚአብሔር ፊት**፣ እግዚአብሔር ጸሎታችንን በእምነትና በታማኝነት ወደ እርሱ በጽናት መጣራታችን እንደሆነበመቀኖጠር ወደ እርሱ የሚያርግ መሥዋዕት አድርጎ ይቀበለዋል (መዝ 141፥2፣ ዕብ 13፥15-16 ይመ)።

ኢዮጴ ልክህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን አስመጣው፤ ⁶እርሱም በባሕሩ አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድነት ወርፎአል።"

⁷ቆርኔሌዎስም፣ ያነጋገረው መልአክ ተለይቶት ከሄደ በኋላ፣ ከአገልጋዮቹ ሁለቱን፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ነገር የተጋና ለእርሱ ታማኝ" የሆነውን አንዱን ወታደር አስጠራ፤ ⁸የሆነውንም ነገር ሁሉ ከነገራቸው በኋላ ወደ ኢዮጴ ላካቸው።

ጴጥሮስ ያየው ራእይ

10፥9-32 ማቍ — ሐሥ 11፥5-14

⁹የተላኩትም ሰዎች በማግስቱ ወደ ከተማዪቱ እንደ ተቃረቡ፣ ጴጥሮስ እኩለ ቀን ገደማ ሲሆን፣ ለመጸለይ ወደ ሰገነት ወጣ። ¹⁰በዚያን ጊዜም ስለ ተራበ የሚበላ ነገር ፈለገ፤ ምግብ እየተዘጋጀ ሳለም አሸለበውና በተመሰጠ ውስጥ ሆነ፤ ¹¹ሰማይም ተከፍቶ አንድ ትልቅ ጨርቅ የሚመስል ነገር በአራቱ ማእዘን ተይዞ ወደ ምድር ሲወርድ አየ። ¹²በጨርቁም ላይ አራት እግር ያላቸው የተለያዩ እንስሳት፣ በምድር የሚሳቡ ፍጥረታትና በአየር የሚበሩ አዕዋፍ ነበሩ በት። ¹³በዚህ ጊዜ፣ "ጴጥሮስ ሆይ፤ ተነሣ፤ እነዚህን ዐርደህ ብላ" የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ።

¹⁴ጴጥሮስ ግን "ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይ ሆንምና፤ እኔ ያልተቀደሰ ወይም ርኩስ ነገር ፈጽሞ በልቼ አላውቅምና" አለ።

¹⁵ያም ድምፅ እንደ ገና ለሁለተኛ ጊዜ ወደ እርሱ መጥቶ፣ "እግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገውን አንተ እንደ ርኩስ አትቍጠረው" አለው።

¹⁶ይህም ሦስት ጊዜ ተደጋገመ፤ ጨርቁም ወዲያውኑ ወደ ሰማይ ተወሰደ።

¹⁷ጴጥሮስም ስላየው ራእይ ትርጒም እጅግ ተጨንቆ በማሰላሰል ላይ ሳለ፣ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች የስምዖንን ቤት ፈልገው ካገኙ በኋላ መጥተው በሩ ላይ ቆሙ፤ ¹⁸ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን እዚያ ይኖር እንደ ሆነ ጠየቁ።

¹⁹ጴጥሮስ የራእዩን ነገር በማሰላሰል ላይ ሳለ፣ መንፈስ እንዲህ አለው፤ "እነሆ፤ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤ ²⁰ስለዚህ ተነ

10፥6 ሐሥ9፥43
10፥8 ሐሥ9፥36
10፥9 ማቴ24፥17
10፥10 ሐሥ22፥17
10፥11 ማቴ3፥16
10፥14 ዘሌ11፥4-8፤13-20፤ 20፥25፣ ዘዳ14፥3-20፤ ሕዝ4፥14፣ ሐሥ9፥5
10፥15 ቍ28፣ ዘፍ 9፥3፤ ማቴ15፥11፤ ሉቃ11፥41፤ ሐሥ11፥9፣ ሮሜ14፥14፤ 17:20፣ 1ቆሮ10፥25፣ 1ጢሞ4፥3፣4፤ ቲቶ1፥15
10፥17 ቍ7፣8፤ ሐሥ9፥10
10፥19 ሐሥ8፥29፣ 9፥10
10፥20 ሐሥ15፥7-9

*10፥19 አንድ የጥንት ቅጅ ሁለት ይላል፤ ሌሎች የጥንት ቅጆች ይህ ቍጥር የላቸውም።

10፥9 **ጴጥሮስ ... ለመጸለይ ወደ ሰገነት ወጣ፤** የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊ የሆነው መንፈስ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ዕብዙ ጸሎት ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች መሆናቸውን ገልጾአል። በቀን ውስጥ በሚደረግ የተቀጠ ደቂቃ ጸሎት የእግዚአብሔር መንግሥት በሙሉ ኀይሉ እንደማይገለጥ ተረድተው ነበር (1፥14፤ 2፥42፤ 3፥1፤ 6፥4፤ ኤፌ 6፥18፤ ቈላ 4፥2)። (1) ማንኛውም ሃይማኖተኛ አይሁዳዊ በቀን ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ይጸልያል (ከመዝ 55፥17፤ ከዳን 6፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። ለክርስቶስ ተከታዮች በተለይም ለሐዋርያት (6፥4) በተመሳሳይ ሁኔታ ተግቶ መጸለይ የተለመደ ነበር። ጴጥሮስና ዮሐንስ፣ "በጸሎት ጊዜ" (3፥1) ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ወጡ፣ ሉቃስና ጸውሎስም ያደረጉት ይህንኑ ነበር (16፥16)። ጴጥሮስ ሳያቋርጥ እኩለ ቀን ላይ ይጸልይ ነበር፤ ቆርኔሌዎስ የጸሎት ጊዜውን በታማኝነት ስለጠበቀ እግዚአብሔር አከበረው (ቍ. 30...)።

(2) ቅዱሳት መጻሕፍት አማኞች በታማኝነት ጸሎታቸውን መቀጠል እንዳለባቸው እንደሚከተለው አጥብቀው ያሰስባሉ (ሮሜ 12፥12)፤ ሁልጊዜ ጸልዩ (ሉቃ 18፥1)፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ (1ተሰ 5፥17)፤ በሁሉም በታ ጸልዩ (1ጢሞ 2፥8)፤ በጸሎትና በልመና ሁሉ በማንኛውም ሁኔታ ጸልዩ (ኤፌ 6፥18)፤ በትጋት ጸልዩ (ቈላ 4፥2) እና ጎይልን ተሞልታችሁ ጸልዩ (ያዕ 5፥16)። እነዚህ ምክሮች ከንጠአት፣ ከሰይጣንና ከዓለም ጋር በምናደርገው ጦርነት ወይም የጠፉትን ለመመለስ በምናደርገው ጥረት በየዕለቱ በትጋት ሳንጸልይ ትክክለኛው የእግዚአብሔር መንግሥት ጎይል ሊገለጥ እንደማይችል ያመለክታሉ (በገጽ 528 ላይ፣ "መልስ የሚያስገኝ ጸሎት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልመና መሠረት ደቀ መዛሙርት፣ "አንዲት ሰዓት እንኳ" (ማቴ 26፥38-41) ተግተው ቢጸልዩ እንዲሁም የምንኖርበት የመጨረሻው ዘመን አስቸኳይነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ እንዲስፋፋና ከዚህ ጋር የተያያዘው ነገር ሁሉ ለእኛ እንዲጨመር (ማቴ 6፥10፤33) እያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ ቢያንስ በየዕለቱ አንድ ሰዓት ያህል ለጸሎትና ቃሉን ለማንበብ ራሱን ቢሰጥ እግዚአብሔርን የቱን ያህል ያስደስተው ነበር።

(4) የአንድ ሰዓት የጸሎት ጊዜ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡ (ሀ) ውዳሴ (ለ) ለጌታ መዘመር (ሐ) ምስጋና ማቅረብ (መ) እግዚአብሔርን በትዕግሥት መጠበቅ (ሠ) ቃሉን ማንበብ (ረ) መንፈስ ቅዱስን ማዳመጥ (ሰ) የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል እንዳለ በመድገም እያሰላሰሉ መጸለይ (ሸ) ውድቀትን መናዘዝ (ቀ) ለሌሎች መማለድ (በ) ለሚያስፈልገን ነገር ልመናን ማቅረብ እና (ተ) በልሳን መጸለይ።

10፥19 **መንፈስ እንዲህ አለው፤** መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ሁሉ ድኅነትን እንዲያገኙ ይፈልጋል (ማቴ 28፥19፤ 2ጴጥ 3፥9)። ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀበሉ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይፈልጋሉ። ከእንግዲህ ድኅነት ለእስራኤል ብቻ የተወሰነ ለምን እንደማይሆን በሥጋዊ አእምሮአቸው ባይረዱትም ነገር ግን ድኅነት አሁን እንደሚታየው ለማንኛውም ወገን ሁሉ ነው (ቍኗ 34-35)። ቤተ ክርስቲያንን ሰፋ መዳሰ ራእይ ያመጣት መንፈስ ቅዱስ ነበረ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለመንጌል ተልእኮ ድርጅት ጎይል በመስጠት ቤተ ክርስቲያንን ወደ አዳዲስ የምስክርነት ስፍራዎች የሚመራት መንፈስ ቅዱስ ነው (8፥29፣39፤ 11፥11-12፤ 13፥2፣4፤ 16፥6፤ 19፥21)። የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስና ወንጌልን የማሠራጨት ተልእኮ ግዴታ ምንጊዜም አብረው የሚጓዙ ጒዳዮች ናቸው (ከ1፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። ዛሬም ቢሆን ብዙ አማኞች መንፈስ ቅዱስ ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ያለውን የማዳን ተልእኮ ዕቅማ ሙሉ በሙሉ ባለመረዳት የራሳቸው ማኅበረሰብ ብቻ እንዲድንላቸው ይመኛሉ (ማቴ 28፥19 እና ማቀ፡ ሉቃ 24፥47 እና ማብ ይመ)።

ሥተህ ውረድ፤ የላክኋቸውም እኔ ስለ ሆንሁ ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ።"
21ጴጥሮስም ወርዶ፣ "እነሆ፤ የምትፈልጉት ሰው እኔ ነኝ፤ የመጣችሁበት ጕዳይ ምንድን ነው?" አላቸው።
22እነርሱም፣ "የመጣነው ቆርኔሌዎስ ከተባለው መቶ አለቃ ዘንድ ነው፤ እርሱም ጻድቅና እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ በአይሁድም ሕዝብ ሁሉ ዘንድ የተከበረ ሰው ነው። አንተን ወደ ቤቱ እንዲያስመጣና የምትለውን እንዲ ሰማ ቅዱስ መልአክ ነግሮታል" አሉት። 23ጴጥሮስም ሰዎቹን ሊያስተናግዳቸው ወደ ቤት አስገባቸው።

ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት

ጴጥሮስም በማግሡቱ ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ሄደ፤ ከኢዮጴ የመጡ አንዳንድ ወንድሞችም አብረውት ሄዱ፤ 24በሚቀጥለው ቀን ቂሳርያ ገባ። ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹን ሰብስቦ ይጠብቃቸው ነበር። 25ጴጥሮስም ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተቀበለው፤ እግሩም ላይ ወድቆ ሰገደለት። 26ጴጥሮስ ግን፣ "እኔም እንዳንተው ሰው ነኝና ተነሥ!" ብሎ አስነሣው።
27ጴጥሮስም ኢያነጋገረው አብሮት ሲገባ ብዙ ሰው ተሰብስቦ አገኘ፤ 28እንዲህም አላቸው፤ "አንድ አይሁዳዊ ከሌላ ወገን ጋር እንዲተባበር ወይም እንዲቀራረብ ሕጋችን እንደማይፈቅድ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እኔ ማንንም ርኩስ ወይም ያልተቀደሰ ነው እንዳልል እግዚአብሔር አሳይቶኛል፤ 29ስለዚህም በተጠራሁ ጊዜ፣ እነሆ ሳላመነታ መጣሁ፤ እንግዲህ፣ ለምን እንደጠራችሁኝ ማወቅ እፈልጋለሁ።"
30ቆርኔሌዎስም እንዲህ አለው፤ "ከአራት ቀን በፊት በዚህ ጊዜ ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት በቤቴ ሆኜ እጸልይ ነበር፤ ድንገትም ብሩህ ልብስ የለበሰ ሰው መጥቶ በፊቴ ቆመና 31እንዲህ አለኝ፤ 'ቆርኔሌዎስ ሆይ፤ ጸሎ ትህ ተሰምቶልሃል፤ ምጽዋትህም ለመታሰቢያነት በእግዚአብሔር ፊት ደርሶአል። 32ሰው ችን ወደ ኢዮጴ ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን አስመጣ፤ እርሱም በባሕር አጠ ገብ ባለው በቀሩርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድነት ዐርፎአል።' 33እኔም ወዲያው ላኩብህ፤ አንተም በመምጣትህ መልካም አድርገሃል። እንግዲህ እኛ ሁሳችን ጌታ ያዘዘህን ስትነግረን ለመስማት በእግዚአብሔር ፊት አለን።

34ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ፤ "እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ በር ግጥ ተረድቻለሁ፤ 35ነገር ግን እርሱን የሚ ፈሩትንና ጽድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆኑ ይቀበላቸዋል። 36እግዚአብሔር የሁሉ ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የላከውም የሰላም የምሥ ራች መልእክት ይኸው ነው። 37ዮሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ ከገሊላ ጀምሮ በመላው ይሁዳ የሆነውን ታውቃላችሁ፤ 38እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል ቀባው፤ እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያብሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ።
39"እርሱ በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ላደረገው ሁሉ እኛ ምስክሮች ነን፤ ደግ ሞም ሰዎች እርሱን በዕንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። 40እግዚአብሔር ግን በሦስተኛው ቀን ከሙታን አስነሣው፤ እንዲታይም አደ ረገው፤ 41የታየውም ለሁሉ ሰው ሳይሆን፣ ከሙታን ከተነሣ በኋላ አብረነው ለበላንና ለጠጣን፣ እግዚአብሔርም አስቀድሞ ለመረጠን ለእኛ ለምስክሮቹ ነው። 42ለሕዝቡ እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታንም ላይ እንዲፈርድ እግዚአብሔር የሾመው እርሱ መሆ ኑን እንድንመስክር እርሱ ራሱ አዘዘን፤ 43በእርሱም የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።"
44ጴጥሮስ ይህን እየተናገረ ሳለ፣

10፥22 ቊ2፤ ሐሥ11፥14
10፥23 ቊ45፤ ሐሥ15፥16፤ 11፥12
10፥24 ሐሥ8፥40
10፥26 ሐሥ14፥15፤ ራእ19፥10፤ 22፥8፣9
10፥27 ቊ24
10፥28 ቊ14፥15፤ ዮሐ4፥9፤ 18፥28፤ ሐሥ11፥3፤ 15፥8፣9
10፥30 ዮሐ20፥12
10፥34 ዘዳ10፥17፤ 2ዜና19፥7፤ ኢዮ34፥19፤ ማር12፥14፤ ሮሜ2፥11፤ ገላ2፥6፤ ኤፌ6፥9፤ ቈላ3፥25፤ ያዕ2፥1፤ 1ጴጥ1፥17
10፥35 ሐሥ15፥9
10፥36 ማቴ28፥18፤ ሉቃ2፥14፤ ሐሥ13፥32፤ 1ዮሐ1፥5
10፥38 ማቴ4፥23፤ ዮሐ3፥2፤ ሐሥ4፥26
10፥39 ቊ41፤ ሉቃ24፥48፤ ሐሥ5፥30
10፥40 ሐሥ2፥24
10፥41 ሉቃ24፥43፤ ዮሐ14፥17፣22፤ 21፥13፤ ሐሥ1፥4
10፥42 ማቴ28፥19፣20፤ ዮሐ5፥22፤ ሐሥ17፥31፤ ሮሜ14፥9፤ 2ቆሮ5፥10፤ 2ጢሞ4፥1፤ 1ጴጥ4፥5
10፥43 ኢሳ53፥11፤ ሉቃ24፥27፤ ዮሐ3፥15፤ ሐሥ15፥9፤ 26፥22
10፥44 ሉቃ1፥15፤ ሐሥ8፥15፣16፤ 11፥15፤ 15፥8፤ 19፥6

10፥34 **እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ፤** እግዚአብሔር አድልዎ የሚያደርግለት ሕዝብ ወይም ዘር የለውም፤ እንዲሁም በአገሩ፣ በትውልዱ ወይም በኑሮ ባለው ሥልጣን ምክንያት የሚያዳላለት ግለሰብ የለም (ከያዕ 2፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። ከማንኛውም ሕዝብ መካከል ከጎጢአት ዘመር ለሚሉት፣ በክርስቶስ ለሚያምኑትና እግዚአብሔርን በመፍራት በጽድቅ ለሚኖሩት እግዚአብሔር ያዳላል እንጂሁም ይቀበላቸዋል (ቊ. 35፤ ከሮሜ 2፥6-11 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ዐይነት የሕይወት መንገድ ጸንተው ለሚኖሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍቅርና ክብር ይጠበቅላቸዋል (ዮሐ 15፥10)።

10፥38 **በዲያብሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ፤** በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣንና በኢጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

10፥44 **በ ... ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤** አሕዛብ የሆኑት የቆርኔሌዎስ ቤተ ሰዎች ሁሉ ለድነት በማይበቃ እምነት ቃሉን ሰሙ፣ ተቀበሉም (ቊ. 34-48፤ 11፥14)። (1) ክርስቶስን ከመቀበላቸው የተነሣ ዳግም ልደትን በሚሰጠው የክርስቶስ ሕይወት እንዳመኑና ያንንም እንደ ተቀበሉ ምስክር ይሆኑላቸው ዘንድ እግዚአብሔር ወዲያውኑ በላያቸው ላይ መንፈስ ቅዱስን አፈሰሰላቸው (ከ11፥17፤ 15፥8-9 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) *መንፈስ ቅዱስ* በቆርኔሌዎስ ቤተ ሰዎች ላይ የመጣበት ዐላማ በእንጨ ቄስጤ ዕለት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በደቀ መዛሙርት ላይ ሲወርድ ከነበረው ዐላማ ጋር ተመሳሳይ ነው (ከ1፥8፤ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ጊዜ የተከሠተው የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የእግዚአብሔርን የዳግም ልደት ሥራ የሚገልጽ ሳይሆን፣ ኀይልን ሊሰጣቸው መምጣቱን የሚያመለክት ነው። በዚህ ጊዜ የተከሠተው ነገር በእንጨ ቄስጤ ዕለት ከነበረው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ለመግለጽ በኋላ ጴጥሮስ በአጽንኦት የተናገረውን ልብ ይበሉ (11፥15፣17)።

(3) በእርግጥ *ማንም* ሰው ለድነት የሚያበቃውን እምነት ካገኘ በኋላ ወዲያውኑ *በመንፈስ ቅዱስ ሊጠ*

ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። 45ከትውልዳቸው ጋር የመጡት፤ ከተገረዙት ወገን የሆኑት አማኞችም፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ፤ 46ይሸሙም በልሳን ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ሰሙ።

በዚያ ጊዜ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤ 47"እነዚህ ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀበሉ፣ እንግዲህ በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማን ነው?" 48ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛቸው። ከዚህ በኋላ፣ ጴጥሮስ ጥቂት ቀን ከእነርሱ ጋር እንዲቀመጥ ለመኑት።

ጴጥሮስ አሕዛብ ቤት ለምን እንደገባ አስረዳ

11 ሐዋርያትና በይሁዳ የነበሩት ወንድሞች አሕዛብ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ተቀበሉ ሰሙ፥ 2ስለዚህ ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ፣ ከተገረዙት ወገን የነበሩ አማኞች ነቀፉት፤ 3እንዲህም አሉት፤ "ወዳልተገረዙ ሰዎች ገብተህ ከእነርሱ ጋር በላህ።"

4ጴጥሮስ ግን እንዲህ ሲል ነገሩን በቅ ደም ተከትል ያስረዳቸው ጀመረ፤ 5"በኢዮጴ ከተማ ስጸልይ በተመሰጠ ውስጥ እያለሁ ራእይ አየሁ፤ ትልቅ ፈጌርቅ የሚመስል ነገር፣ በአራት ማእዘን ተይዞ ከሰማይ እኔ ወደ ነበርሁበት ቦታ ሲወርድ አየሁ። 6እተ ሁራም ይህን ነገር ስመለከት አራት እግር ያላቸው እንስሳት፣ የዱር አራዊት፣ በምድር የሚሳቡ ፍጥረታትና በሰማይ የሚበሩ አሰ ዋፍ አየሁ። 7በዚህ ጊዜ፣ 'ጴጥሮስ ሆይ፤ ተነሣና ዐርደህ ብላ' የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ።

8"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይሆንም፤ እኔ ርኩስ ወይም ያልተቀደሰ ነገር ፈጽሞ ወደ አፌ ገብቶ አያውቅም' አልሁ።

9"ዳም ድምፅ ዳግመኛ፣ 'ከእግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገውን አንተ እንደ ርኩስ አትቍጠረው' ሲል ከሰማይ ተናገረኝ። 10ይህም ሦስት ጊዜ ተደጋገመ፤ ከዚያ ሁሉም እንደ ገና ወደ ሰማይ ተወሰደ።

11"ልክ በዚያው ሰዓት፣ ሦስት ሰዎች ከቂሳርያ ወደ እኔ ተልከው መጥተው እኔ ባለሁበት ቤት ደጅ ላይ ቆሙ፤ 12መንፈስ ቅዱ ስም ምንም ሳላወላውል ከእነርሱ ጋር እንድ ሄድ ነገረኝ። እነዚህም ስድስት ወንድሞች ከእኔ ጋር ሄዱ፤ ወደ ሰውየውም ቤት ገባን። 13እርሱም መልአክ በቤቱ ውስጥ ቆሞ እንደ ታየውና እንዲህ እንዳለው ነገረን፤ 'ወደ ኢዮጴ ሰው ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖ ንን አስጠራ፤ 14እርሱም አንተና የቤትህ ሰዎች ሁሉ የምትድኑበትን ቃል ይነግርሃል።'

15"እኔም ገና መናገር ስጀምር፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ። 16በዚህ ጊዜ፣ 'ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን በመ ንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ' ሲል ጌታ የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ። 17እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ

10:45 ቍ.23፤ ሐሥ 2:33፤ 38፤ 11:18፤ 15:8
10:46 ማር 16:17
10:47
የሐ 20:22፤ ሐሥ 8:36፤ 11:17
10:48 ሐሥ 2:38
11:1 ሐሥ 1:16፤ ዕብ 4:12
11:2 ሐሥ 10:45
11:3 ሐሥ 10:25-28፤ ገላ 2:12
11:5 ሐሥ 9:10፤ 10:9-32
11:9 ሐሥ 10:15
11:11 ሐሥ 8:40
11:12 ቍ.1፤ 29፤ ሐሥ 1:16፤ 8:29፤ 15:9፤ ሮሜ 3:22
11:13 ሐሥ 5:19
11:14 ዮሐ 4:53፤ ሐሥ 10:36፤ 16:15፤ 31-34፤ 18:8፤ 1ቆሮ 1:11፤ 16
11:15 ሐሥ 2:4፤ 10:44
11:16 ማር 1:8፤ 11:17 ሐሥ 2:38፤ 10:45፤ 47

*10:46 ወይም በሌላ ቋንቋዎች

መቅ ይችላል (ቍ. 46 እና ማብ ይመ፣ ከ11:17 ጋር ያነጻጽሩ)።

10:45 **መንፈስ ቅዱስ**፣ በአማኝ ሕይወት ላይ ያለውን የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴ መሠረታዊ አስፈላጊነት ለመረዳት በገጽ 1679 ላይ፣ "**የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

10:46 **በልሳን ሲናገሩ**፣ ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቁ ማረጋገጫ ምልክት መሆኑን ተረድተው ነበር። ይሸሙም እግዚአብሔር በጸንጠ ቄስጠ ዕለት በልሳን መናገርን ለመንፈስ ቅዱስ መውረድ ማረጋገጫ ምልክት አድርጎ እንደ ገለጠ (2:4)፣ አሕዛብ የነበሩትም የቆርኔሊዎስ ቤተ ሰዎች ሁሉ በልሳን እንዲናገሩ በማድረግ ለጴጥሮስና ለሌሎቹ አይሁድ አማኞች ማረጋገጫ ምልክት ሰጣቸው በገጽ 1669 ላይ፣ "**በልሳን መናገር**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ።

11:15 **መንፈስ ቅዱስ፣ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ**፤ በጸንጠ ቄስጠ ዕለት የመንፈስ ቅዱስ መውረድ (2:4)፣ ከዚያ በኋላ ላለው መንፈስ ቅዱስን የመቀበል ሁኔታ መመሪያ ሆነ። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መከሠቱ ግለሰቡ በሚታይ መንገድ በመለወጡ፣ በደስታው ብዛት፣ በመንፈስ ቅዱስ በተመራው ንግግሩና ለመመስከር ባለው ድፍረቱ (2:4፣ 4:31፣ 8:15-19፣ 10:45-47፣ 19:6) ይታወቃል። ስለዚህ ጴጥሮስ ለሐዋርያትና በኢየሩሳሌም ላሉት ወንድሞች የቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች መንፈስ ቅዱስ በወረደባቸው ጊዜ በልሳን እንደ ተናገሩ ሲጠቅሰላቸው (ከ10:45-46 ጋር ያነጻጽሩ)፣ እግዚአብሔር ለአሕዛብም በክርስቶስ ያለውን ድኅነት እንደሰጣቸው አመኑ (ቍ. 18)። ዛሬም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በልሳን መናገርን የመሰሰሉት ተጨባጭ ምልክቶች ከሌለብት ፈጽሞ ሙሳቱ አልተከናወነም ለማለት ያስደፍራል። በሐ ዋርያት ሥራ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ ሰው በክርስቶስ ባመነ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ልምምድ አንደ ሆነ አልተጠቀሰም (8:12፡16 እና ማብ፡ 10:44 እና ማብ፡ 19:6 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1669 ላይ፣ "**በልሳን መናገር**" በሚልና በገጽ 1694 ላይ፣ "**እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን**" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)።

11:17 **ስናምን ለእኛ**፣ የሚለው ቃል በተለይም በግሪኩ ከዋናው ግስ በፊት ካለው ድርጊት ቀደም ብሎ አንድ ድርጊት መፈጸሙን የሚያመለክት የኋላ ጊዜ ቦዝ አንቀጽ ነው። ስለዚህ ሁኔታው "ከመኑ በኋላ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠንን ስጦታ ለእነርሱም ሰጣቸው" ተብሎ ቃል በቃል ሊተረጐም ይችላል። ይህ ሐቅ ከጸንጠ ቄስጠ በፊት ደቀ መዛሙርት በኢየሱስ አምነውና በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን አግኝተው ነበር ከሚለው ታሪካዊ እውነታ ጋር የሚስማማ ነው (በገጽ 1646 ላይ፣ "**የደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘን

ሐሥ 10፥44-45 "ጴጥሮስ ይህን እየተናገረ ሳለ፣ ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። ከጴጥሮስ ጋር የመጡት፣ ከተገረዙት ወገን የሆኑት አማኞች፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ።"

ከመንፈስ ቅዱስ የሆኑ ናቸው የተባሉትን ነገሮች በሙሉ ከመቀበላቸው በፊት አማኞች መፈተንና መመዘን እንደሚገባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ያሳስባሉ (1ተሰ 5፥19-21 ይመ፣ ከ1ቆሮ 14፥29 ጋር ያነጻጽሩ)። "መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር መሆናቸውን መርምሩ" (1ዮሐ 4፥1)። የሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖች ተከሥቷል የተባለው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆኑን የምንፈትንባቸው መንገዶች ናቸው፣

(1) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እግዚአብሔር አብንና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከበፊቱ የበለጠ እንድንወድ፣ ከፍ ከፍ እንድናደርግና እንድናከብር ያደርገናል (ዮሐ 16፥13-14፣ ሐሥ 2፥11፤36፤4፥12፤7፥55-56፣10፥44-46)። በልባችን ውስጥ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር እንዲበዛና እንዲያድግ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው (ሮሜ 5፥5)። በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ከሥተት አክብሮታችንን ከእግዚአብሔርና ከጌታ ኢየሱስ ይልቅ ለሌላ ነገር ወይም ለሰው እንድንሰጥ የሚያደርግ ከሆነ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር አይደለም።

(2) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከሰማያዊ አባታችን ጋር ያለንን ግንኙነት በሚገባ እንድናውቅ ያደርገናል (ሐሥ 1፥4፣ ሮሜ 8፥15-16)፣ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ የክርስቶስ ሀልዎት ከእኛ ጋር መሆኑን በይበልጥ እንድናውቅ ይረዳናል (ዮሐ 14፥16፡23፣ 15፥26)፣ እንዲሁም "አባ፣ አባት" ብለን ከልብ የምንጮኽበትን መንፈስ ያበዛልናል (ሮሜ 8፥15፣ ገላ 4፥6)። በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ከሥተት ከክርስቶስና ከእግዚአብሔር ከአባታችን ጋር እጅግ የጠበቀ ግንኙነትና ኅብረት እንድንፈጥር የማያደርግ ከሆነ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር አይደለም።

(3) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቅዱሳት መጻሕፍትን በእጅጉ እንድንወድና እንድናደንቅ ያደርገናል። ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲጻፉ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ (2ጢሞ 3፥16፣ 2ጴጥ 1፥20-21) ማለትም የእውነት መንፈስ (ዮሐ 14፥17) ለእግዚአብሔር ቃል እውነት ያለንን ፍቅር ጥልቅ እንዲሆን ያደርገዋል (ዮሐ 16፥13፣ ሐሥ 2፥42፣ 3፥22፣ 1ዮሐ 4፥6)። በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ከሥተት የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ያለንን ረሀብ የሚያጠፋብን ከሆነ መንፈስ ፈጽሞ ከእግዚአብሔ ር አይደለም (ከዮሐ 8፥31፣ 15፥4-7 ጋር ያነጻጽሩ)።

(4) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ያለንን ፍቅርና በጎ ሐሳብ የበለጠ ጥልቀት እንዲኖረው ያደርጋል (ሐሥ 2፥42-47፣ 4፥31-37)። ክርስቲያናዊ ኅብረትና አንድነት እውን ሊሆን የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (2ቆሮ 13፥14)። በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ከሥተት ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ በማድረግ በእውነት ሊከተሉት ለሚሹት ሁሉ ሊኖረን የሚገባውን ፍቅር የሚቀንስ ከሆነ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር አይደለም (ሮሜ 5፥5ን ከ1ዮሐ 4፥21 ጋር ያወዳድሩ)።

(5) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመከሠቱ በፊት ከኀጢአት ዘወር ማለትንና ክርስቶስን በታማኝነት መታዘዝን ማስቀደም ይገባናል (ሐሥ 2፥38፣ 8፥15-24)፣ ጥምቀቱም በሕይወታችን ጸንቶ ሊቆይ የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ የመቀደስ ሥራ በሕይወታችን እንዲቀጥል ሳንፈቅድ (ሐሥ 2፥40፣ 3፥26፣ 5፥29-32፣ 8፥21፣ 26፥18፣ ገላ 5፥16-25)፣ ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ ስንገድልና በእግዚአብሔር መንፈስ ስንመራ ብቻ ነው (ሮሜ 8፥13-14 ይመ፣ ከገላ 5፥24 ጋር ያነጻጽሩ)። በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ከሥተት ከኀጢአት ነጻ ባልወጣና በኀጢአተኛ ተፈጥሮ ልምምድ መሠረት በሚኖር ሰው ላይ ያረፈ ከሆነ ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም (ሐሥ 2፥38-40፣ 8፥18-23፣ ሮሜ 6፥22-23፣ 8፥2-15)። በዚያ ሰው ላይ የተገለጠው ኀይል ምንጩ ሌላ ነው፣ ይኸውም የሰይጣን የማታለል ድርጊት ነው (ከመዝ 4፥4-5፣ ከ2ቆሮ 11፥13-15፣ ከ2ተሰ 2፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

(6) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በዚህ ዓለም ኀጢአት መደሰትንና ፈሪሃ እግዚአብሔር በሌለበት ነገር ተድላ ደስታ ማድረግን እንድንጠላ ያደርጋል፣ እንዲሁም በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ ምድራዊ ብልጥግናንና ዝናን ያጠፋል (ሐሥ 4፥32-37፣ 8፥14-24፣ 20፥33፣ 1ዮሐ 2፥15-17)።


በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ክሥተት የዓለምን መንግድና ፍልስፍና እንድንቀበል የሚያደርግ ከሆነ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር አይደለም፣ "ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና" (1ቆሮ 2፥12) ስለሚል።

(7) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራ በተመለከተ መመስከር እንድንችል የሚያደርገንን ታላቅ ፍላጎትና ኀይል ይሰጠናል (ከሉቃ 4፥18፣ ከሐሥ 1፥4-98፣ 2፥1-4:37-42፣ 4፥8-33፣ ሮሜ 9፥1-3፣ 10፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ክሥተት ሌሎች ወደ ክርስቶስ የማዳን ግንኙነት ውስጥ እንዲገቡ ጥልቅ መሻትና ፍላጎት እንዲኖረን የማያደርግ ከሆነ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር አይደለም (ሐሥ 4፥20 እና ማቅ ይመ)።

(8) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራና በግል ሕይወታችንም ውስጥ የሚገልጣቸውን ስጦታዎች በተለይም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የመጀመሪያ ውጭአዊ ምልክት የሆነውን በልሳን መናገርን የበለጠ እንድንቀበል ያደርገናል (ሐሥ 2፥4:16-18:43፣ 4፥29-30፣ 5፥12-16፣ 6፥8፣ 8፥5-7፣ 10፥38:44-46፣ 1ቆሮ 12-14፣ ገላ 3፥5፣ (በገጽ 1669 ላይ፣ "በልሳን መናገር" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በአንጻሩ፣ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ክሥተት በሕይወታችን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የማይገልጥ ከሆነ የአዲስ ኪዳን አማኞችን የሕይወት ተመክሮ በጎሐድ ሙተውና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከቀረበው የተለመደ አሠራር ሆን ብሎ መራቅ ነው (ሐሥ 2፥4:18፣ 10፥45-46፣ 19፥6)።

(9) እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ፣ ምሪትና ሀልዎት የበለጠ ልብ እንድንል ያደርገናል። የመንፈስ ቅዱስ ሙሳትን ከተቀበሉ በኋላ የአዲስ ኪዳን አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ሀልዎት፣ ኀይልና ምሪት ሁል ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንደ ሆነ በሚገባ መረዳት ችለዋል (ሐሥ 2፥4:16-18፣ 4፥31፣ 6፥5፣ 9፥31፣ 10፥19፣ 13፥2:4:52፣ 15፥28፣ 16፥6-7፣ 20፥23)። በአንጻሩ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም ክሥተት የመንፈስ ቅዱስን ሀልዎት የበለጠ ልብ እንዳንል የሚያደርግ፣ ምሪቱን ለመታዘዝ ያለንን ፍላጎት የማያበረታታ፣ እርሱን ባለማሳዘን ወይም እሳቱን ባለማጥፋት በተጋቻቸ መኖር እንደሚገባን እንድንኖር ያለንን የሕይወት ግብ የማያጠናክር ከሆነ (ኤፌ 4፥30፣ 1ተሰ 5፥19) ፈጽሞ ከእግዚአብሔር አይደለም።

የፊልጶስና የጴጥሮስ የወንጌል ተልእኮ ጉዞዎች



© 1989 The Zondervan Corporation

ስናምን ለእኛ የሰጠንን ስጦታ ለእነርሱም ከሰጣቸው፣ ታዲያ፣ እግዚአብሔርን መቋቋም እችል ዘንድ እኔ ማን ነኝ?"
ሐሥ 13፥9

18 ይህን በሰሙ ጊዜም የሚሉትን አጥተው እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ "ይህማ ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን ሰጥቷቸዋል ማለት ነው።"

በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን

19 በእስጢፋኖስ ላይ በተነሣው ስደት ምክ ንያት የተበተኑት አማኞች ቃሉን ለአይሁድ ብቻ እየተናገሩ እስከ ፊንቄ፣ እስከ ቆጵሮስና እስከ አንጾኪያ ድረስ ዘለቁ። 20 ከቆጵሮስና ከቀሬና የመጡት አንዳንዶች ሰዎች ግን ወደ አንጾኪያ ሄደው ለግሪኮችም ጭምር በመንገር የጌታን የኢየሱስን ወንጌል ሰበኩላቸው። 21 የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ ብዙ የሆኑ ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ተመለሱ።

22 ወሬውም በኢየሩሳሌም ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጆሮ ደረሰ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱም በርናባስን ወደ አንጾኪያ ሰከችው። 23 እርሱም እዚያ ደርሶ እግዚአብሔር በጸጋው የሠራውን ባየ ጊዜ ደስ አለው፤ ሁሉም በፍጹም ልብ በጌታ በመታመን እንዲጸኑ መከራቸው። 24 እርሱም መንፈስ ቅዱስንና እምነትን የተሞላ ደግ ሰው ነበረ፤ ቍጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመረ።

25 ከዚህ በኋላ በርናባስ፣ ሳውልን ለመፈለግ ወደ ጠርሴስ ሄደ፤ 26 ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። ሁለቱም እዚያ ካሉትም ቤተ ክርስቲያን ጋር በመሆን አንድ ዓመት ሙሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ አስተማሩ፤ ደቀ

11፥18
ሮሜ10፥12-13፣ 2ቆሮ7፥10
11፥19 ቍ.26፥27፣ ሐሥ8፥1-4፣ 13፥1፣ 14፥26፣ 18፥22፣ ገላ2፥11
11፥20 ቍ.19፣ ማቴ27፥32፣ ሐሥ4፥36፣ 13፥32
11፥21
ሉቃ1፥66፣ ሐሥ2፥41
11፥22 ሐሥ4፥36
11፥23
ሐሥ13፥43፣ 14፥22፣26፣ 15፥40፣ 20፥24
11፥24
ሉቃ1፥15፣ ሐሥ2፥41
11፥25 ሐሥ9፥11
11፥26 ቍ.29፣ ሐሥ6፥1፣2፣ 9፥19፣26፣38፣ 13፥52፣ 26፥28፣ 1ጴጥ4፥16
11፥27 ሐሥ13፥1፣ 15፥32፣ 1ቆሮ11፥4፣ 12፥28፣29፣ 14፥29፣32፣37፣ ኤፌ4፥11
11፥28
ማቴ24፥14፣ ሐሥ18፥2፣ 21፥10
11፥29
ቍ.1፣12፣26፣ ሐሥ1፥16፣ ሮሜ15፥26፣ 2ቆሮ8፥1-4፣ 9፥2
11፥30 ሐሥ4፥36፣ 12፥25፣ 14፥23፣ 15፥2፣22፣ 20፥17፣ 1ጢሞ5፥17፣ ቲቶ1፥5፣ ያዕ5፥14፣ 1ጴጥ5፥1፣ 2ዮሐ1፣1
12፥1 ማቴ14፥1
12፥2 ማቴ4፥21፣ ማር10፥39
12፥3 ዘፀ12፥15፣ 23፥15፣ ሐሥ20፥6፣ 24፥27፣ 25፥9
12፥4 ዮሐ11፥55
12፥5 ሐሥ1፥14፣ ሮሜ15፥30፣31፣ ኤፌ6፥18

መዛሙርትም ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ 'ክርስቲያን' ተብለው ተጠሩ።

27 በዚህ ጊዜ አንዳንድ ነቢያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ፤ 28 ከእነርሱም አንዱ አጋቦስ የተባለው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ እንደሚሆን መንፈስ ቅዱስ አስመልክቶት ተናገረ፤ ይህም በቀላውዴዎስ ቂሳር ዘመን ተፈጸመ። 29 ደቀ መዛሙርትም እያንዳንዳቸው ዐቅማቸው በፈቀደ መጠን አዋጥተው በይሁዳ የሚኖሩትን ወገ ድሞች ለመርዳት ወሰኑ፤ 30 ሪዳታውንም በበርናባስና በሳውል እጅ ለሽማግሌዎቹ በመላክ፣ ይህንኑ አደረጉ።

ጴጥሮስ ከእስር ቤት በታምር ወጣ

12 በዚያ ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላትን እያሳደደ ያስጨንቅ ነበር፤ 2 የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ አስገደለ። 3 ይህ አድራጎቱ አይሁድን ደስ እንዳሰኛቸው ባየ ጊዜ፣ ጴጥሮስን ደግሞ አሰያዘው፤ ይህም የሆነው በቂጣ በዓል ሰሞን ነበር። 4 ጴጥሮስን ወህኒ ቤት ካስገባው በኋላ፣ አራት አራት ወታደሮች እየሆኑ እንዲጠብቁት በአራት ፈረቃ ለተመደቡ ወታደሮች አስረከበው፤ ይህን ያደረገውም የፋሲካ በዓል ካለፈ በኋላ ሕዝብ ፊት አውጥቶ ሊያስፈርድበት አስቦ ነው።

5 ጴጥሮስም በዚህ መሠረት እስር ቤት

11፥29 2ቆሮ8፥1-4፣ 9፥2 11፥30 ሐሥ4፥36፣ 12፥25፣ 14፥23፣ 15፥2፣22፣ 20፥17፣ 1ጢሞ5፥17፣ ቲቶ1፥5፣ ያዕ5፥14፣ 1ጴጥ5፥1፣ 2ዮሐ1፣1 12፥1 ማቴ14፥1 12፥2 ማቴ4፥21፣ ማር10፥39 12፥3 ዘፀ12፥15፣ 23፥15፣ ሐሥ20፥6፣ 24፥27፣ 25፥9 12፥4 ዮሐ11፥55 12፥5 ሐሥ1፥14፣ ሮሜ15፥30፣31፣ ኤፌ6፥18

11፥18 **ይህን በሰሙ ጊዜም**፣ የጴጥሮስ ንግግር በዚያ የነበረውን ተቃውሞ ሁሉ ጸጥ አደረገ (ቍ. 4-18)። እግዚአብሔር አሕዛብን በመንፈስ ቅዱስ አጠመቃቸው (10፥45)፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ ሁሉም እንዲቀበሉት ማረጋገጫ ምልክት የሆነው በሊሎች ልሳኖች መናገራቸው ነው (10፥46)። የሚፈጠረውም ምልክት ይህ ብቻ ነበር፣ ያለምንም ጥርጥር ሁሉም ተቀበሉት።

11፥23 **በጌታ በመታመን እንዲጸኑ**፣ የአዲስ ኪዳን ደቀ መዛሙርት የእግዚአብሔርን ጸጋ የተቀበሉ ሁሉ ወዲያውኑ በጌታ በመታመን ጸንተው ለመቆም እንደሚችሩ ያምኑ ነበር፣ ምክንያቱም ዮኀኪአት፣ የኅሊምና የሰይጣን ፈተና አዲስን አማኝ በክርስቶስ ከተገኘ የድነት መንገድ ዘወር ሊያደርግ ይችላል። በርናባስ አዲስ አማኞች እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ጥሩ ምሳሌ ሆኖናል፣ ይኸውም ዋናው ፍላጎታችን አዲስ አማኞች ከክርስቶስና ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር በእምነት፣ በፍቅርና በጉበረት እንዲጸኑ መርዳትና ማበረታታት ነው (ከ13፥43፣ 14፥22 ጋር ያነጻጽሩ)።

11፥26 **ደቀ መዛሙርትም ... ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ**፤ "ክርስቲያን" (ግሪክ፡ 'ክርስቲያኖስ') የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው (11፥26፣ 26፥28፣ 1ጴጥ. 4፥16)። በመጀመሪያ ይህ ቃል የሚያመለክተው የክርስቶስን አገልጋይና ተከታይ ነበር። ዛሬ ግን የመጀመሪያውን የአዲስ ኪዳን ትርጉም ባጆ በማጅረግና በማዛባት አለአቅላይ መጠሪያ ሆኖአል። ይህም ማመልከት የሚገባው የቤተኝንን ስም (ሮሜ 3፥24)፣ ከክርስቶስ ጋር ያለንን የቅርብ ግንኙነት (ሮሜ 8፥38-39)፣ ጌታችን አድርገን እርሱን የመቀበላችንን ሁኔታ (ሮሜ 5፥1) እና የዘላለም ድነት ምንጭ መሆኑን ነው (ዕብ 5፥9)። "ክርስቲያን" በሚለው ስም መጠራት ክርስቶስና በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠው ቃሉ በእኛ ላይ ከፍተኛ ባለሥልጣን እንደሆኑና እነርሱም የወደፊቱ ተስፋችን ምንጭ እንደ ሆኑ ያመለክታል (1ቆላ 1፥5፣27)።

11፥27 **ነቢያት**፣ ነቢያት በዘመኑ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸው የአገልግሎት ስፍራ በሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ተጠቅሶአል (በገጽ 1866 ላይ፣ "*የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

12፥2 **ያዕቆብን ... አስገደለ**፤ እግዚአብሔር የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን (ከማቴ 4፥21 ጋር ያነጻጽሩ) እንዲሞት ሲፈቅድ፣ ነገር ግን ጴጥሮስን ለማዳን መልአኩን ላከ (ቍ. 3-17)። ያዕቆብ ሞቶ ጴጥሮስ ለበለጠ አገልግሎት በሕይወት መቅረቱ እግዚአብሔር በልጆቹ ሕይወት የሚያደርገው ምስጢራዊ አሠራር ነው። ያዕቆብ የሰማዕትነትን ሞት ለመሞት ከሐዋርያት መካከል የመጀመሪያውን ክብር አገኘ። ለእግዚአብሔር ዕቅዳ ጌታው እንደ ሞተ እርሱም ሞተ (ከማር 10፥36-39 ጋር ያነጻጽሩ)።

12፥5 **ቤተ ክርስቲያኒቱ**፣ ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንዲሁም ከሌሎች የአዲስ ኪዳን ምንባቦች

ተማለደ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን ስለ እርሱ አጥብቃ ወደ እግዚአብሔር ተጸልይ ነበር።

12፥6 ሐሥ21፥33

ሄሮድስም ጴጥሮስን ሕዝቡ ፊት ሊያቀርበው አስቦ ሳለ፣ ጴጥሮስ በዚያው ሊሊት

ለአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የተመደበውን መመዘኛ ወይም ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣትን ሥልጣን ቀጥሎ የተጠቀሰው ነው፤ (1) ከሁሉም በፊት ቤተ ክርስቲያን በአንድ አጥቢያ ጉባኤ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ያቀፈች ስትሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ አንድ በመሆን ከእግዚአብሔርና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በታማኝነት የጋል ግንኙነትን በትጋት ለመፍጠር የሚሹ ምእመናን ያሉባት ናት (13፥2፤ 16፥5፤ 20፥7፤ ሮሜ 16፥3-4፤ 1ቆሮ 16፥19፤ 2ቆሮ 11፥28፤ ዕብ 11፥6 እና ማብ)።

(2) በጎይል ከተሞላው ምስክርነት የተነሣ ጉዟቸውን ይድናሉ፤ ዳግም ይወለዳሉ። በውሃ ውስጥ ዘልቀመቀ በጌሳ የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ይጨመራሉ፣ የጌታን እራት ይካፈላሉ። የክርስቶስንም ዳግም ምጽአት በናፍቆት ይጠባበቃሉ (2፥41-42፤ 4፥33፤ 5፥14፤ 11፥24፤ 1ቆሮ 11፥26)።

(3) የመንፈስ ቅዱስ ቋሚት አስፈላጊነት ለአዳዲስ አማኞች ተሰብኩ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ ይደራጋል (2፥39 እና ማብ ይመ)፤ የመንፈስ ቅዱስ ሀልዎትና ጎይልም ይገለጣል።

(4) ድንቆችን፣ ታምራዊ ምልክቶችንና ፈውሶችን (2፥18፡43፤ 4፥30፤ 5፥12፤ 6፥8፤ 14፥10፤ 19፥11፤ 28፥8፤ ማር 16፥18) ጨምሮ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተግባር የሚገለጡ ይሆናሉ (ሮሜ 12፥6-8፤ 1ቆሮ 12፥4-11፤ ኤፌ 4፥11-12)።

(5) እግዚአብሔር ቅዱሳንን ለአገልግሎት ለማስታጠቅ በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ አምስቱን የአገልግሎት ቢሮዎች ሰጥቶአል (ኤፌ 4፥11-12፤ በገጽ 1866 ላይ፣ «የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ሰጠታዎች» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(6) አማኞች አጋንንትን ያስወጣሉ (5፥16፤ 8፥7፤ 16፥18፤ 19፥12፤ ማር 16፥17)።

(7) ለወንጌል የሚገባ ፍጹም ታማኝነት ይኖራል፤ ይኸውም ለክርስቶስና ለሐዋርያት መሠረታዊ ትምህርት ፍጹም ታዛዥ መሆን ነው (2፥42፤ ኤፌ 2፥20 ማብ ይመ)። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናትና ለመታዘዝ ራሳቸውን የሰጡ ይሆናሉ (6፥4፤ 18፥11፤ ሮሜ 15፥18፤ ቁሳ 3፥16፤ 2ጢሞ 2፥15)።

(8) በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሠረት በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን (20፥7፤ 1ቆሮ 16፥2) የአጥቢያው ጉባኤ ለእምልኮና ርስ በርስ ለመተናነጽ በአንድነት ይሰበሰባሉ (1ቆሮ 12፥7-11፤ 14፥26፤ 1ጢሞ 5፥17)።

(9) ቤተ ክርስቲያን በቅዱሱ እግዚአብሔር ሀልዎት ፊት በፍርሀት፣ በአክብሮትና በትሕትና ያምትቀም ትሆናለች (5፥11)። ሕዝብዋም ስለ ቤተ ክርስቲያን ንጽሕና እጅግ በማሰብ ጎጢአት የሚሠሩትን አባሎችና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነት ታማኞች ያልሆኑትን አስተማሪዎች በመገሠጽ ይቀጣሉ (20፥28፤ 1ቆሮ 5፥1-13፤ ማቴ 18፥15 ማብ ይመ)።

(10) ቅድስና በተሞላ ባሕርይ ጸንተው የሚመላለሱና ሐዋርያት ባስተማሩት ጸድቅ መስፈርት መሠረት የሚኖሩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲመሩና የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት በማሳደግ እንዲጠብቁ ሽማግሌዎች በመሆን ይሾማሉ (ማቴ 18፥15 ማብ፤ 1ቆሮ 5፥1፡5፤ 1ጢሞ 3፥1-7፤ ቲቶ 1፥5-9፤ በገጽ 1716 ላይ፣ «ያቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(11) እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያንን ማኅበራዊና ቍሳቍሳዊ ጕዳዮችን በኀላፊነት እንዲመሩ ዲያቆናት ይሾማሉ (1ጢሞ 3፥8 ማብ ይመ)።

(12) በአባላት መካከል ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ግልጽ ፍቅርና ኅብረት ይኖራል (2፥42፡44-46፤ ዮሐ 13፥34 ማብ ይመ)፤ ይህም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከሚያምኑ ከሌሎች የአጥቢያ ምእመናን ጋርም ይሆናል (15፥1-31፤ 2ቆሮ 8፥1-8)።

(13) ቤተ ክርስቲያን የሚጸልዩና የሚጸልዩ ምእመናን ያሰብት ትሆናለች (1፥14፤6፥4፤12፥5፤13፥2፤ ሮሜ 12፥12፤ ቈላ 4፥2፤ ኤፌ 6፥18)።

(14) አማኞች በስፉት ከተገለጠው የሳለም አመለካከትና በአካባቢያቸው ካለው የባሕል መንፈስ ተጽእኖ ራሳቸውን የለዩ ይሆናሉ (2፥40፤ ሮሜ 12፥2፤ 2ቆሮ 6፥17፤ ገላ 1፥4፤ 1ዮሐ 2፥15-16)።

(15) ከዓለምና ከሥርዐትዋ የተነሣ ሥቃይና መከራ በቤተ ክርስቲያን ላይ ይደርሳል (4፥1-3፤ 5፥40፤ 9፥16፤ 14፥22)።

(16) ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላ አገር የወንጌል መልእክተኞች እንዲላኩ በመርዳት አስፈላጊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች (2፥39፤ 13፥2-4)።

በሕዝቧ መካከል እነዚህ 16 ባሕርይት በሥራ ካልተገለጡ፣ የትኛዋም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን የአዲስ ኪዳን መመሪያን የምትከተል አድርጋ መቍጠር አትችልም፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን የተጠቀሰውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የበለጠ ለመረዳት በገጽ 1453 ላይ፣ «ቤተ ክርስቲያን» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

12፥5 አጥብቃ .... ትጸልይ፤ የአዲስ ኪዳን አማኞች አጥብቆ በመጸለይ ስደትን ይቋቋሙ ነበር፤ ሁኔታው አስቸጋሪ ይመስላል፤ ይኸውም ያሰቆብ ተገድሎአል እንዲሁም ጴጥሮስ በዕሥራ ስድስት የሮሮድስ ወታደሮች ጥበቃ ሥር እንዲሆን ተደርጎአል። ይሁን እንጂ የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን፣ «የጻድቅ ሰው ጸሎት ኀይል አለው፤ ታሳት ነባርም ያደርጋል» (ያዕ 5፥16) በሚለው ቃል ጸንተው በመቆም ጴጥሮስ ቢጋጠመው ችግር ላይ አጥብቀው ባለማቋረጥ ይጸልዩ ነበር፤ ጸሎታቸውም ወዲያውኑ ተመለሰ (ቍሥ 6-17)።

የአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛውን ጊዜ ረዥም የጉበረት ጸሎት ያደርጉ ነበር (1፥14፤ 2፥42፤ 4፥24-31፤ 12፥5፡12፤ 13፥2)። እግዚአብሔርም ትርጉም ላለውና ለዘላቂ ጸሎት ሕዝቡ በአንድነት እንዲሰበሰብለት ይፈልጋል፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል» (ማቴ 21፥13) በማለት የተናገረውን ልብ ይበሉ። የሥነ መለኮት፣ የልምምድና የቲልኢ መሠረታቸውን በሐ ዋርያት ሥራና በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተመ ሠረተው መለኮታዊ መመሪያ አንጻር እንደ ሆነ የሚቈጥሩ አብያተ ክርስቲያናት በአምልኮአቸው ውስጥ እንደ ዐይነተኛ ነባር ሊታዩ የሚገባው ትልቅ ቁዳይ ጥልቅ የሆነ የጉበረት ጸሎት ማድረግ ነው፤ ይኸውም በአንድ የአምልኮ ስብሰባ የአንድ ወይም የኩለት ደቂቃ ጸሎት ማለት አይደለም። በጉንትዋ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔ ር ጎይልና ሀልዎት እንዲሁም የጸሎት ስብሰባዎች የማይነጣጠሉ ጕዳዮች ናቸው። የቱንም ያህል ስብከት፣ ትምህርት፣ ዝማሬ፣ መዚቃ ወይም ሌላ ድርጊት ቢዘጎ አማኞች «ያለማቋረጥ ተግተው ይጸልዩ ነበር» (1፥14) እንደሚለው ያለ የአዲስ ኪዳን ጸሎት እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጎይልና ሀልዎት ሊገለጽ አይችልም።

በሁለት ሰንሰለት ታስሮ፣ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፤ የወህኒ ቤት ጠባቂዎችም አስር ቤቱ በር ላይ ቆመው ነበር። 7የጌታ መልአክም ድንገት ታየ፤ በክፍሉም ውስጥ ብርሃን በራ፤ መልአኩም የጴጥሮስን ጐን መታ አድርጎ ቀሰቀሰውና፣ "ቶሎ ተነሣ!" አለው፤ በዚህ ጊዜ ሰንሰለቶቹ ከእጆቹ ወደቁ።

8መልአኩም፣ "ልብስህን ልበስ፤ ጫማህ ንም አድርግ" አለው። ጴጥሮስም እንደታ ዘዘው አደረገ። መልአኩም ቀጥሎ፣ "መደረቢያህን ከላይ ጣል አድርገህ ተከተለኝ" አለው። 9ጴጥሮስም ተከትሎት ከእስር ቤት ወጣ፤ ነገር ግን ራእይ የሚያይ መሰለው እንጂ መልአኩ የሚያደርገው ነገር በእውን መሆኑን አላወቀም ነበር። 10የመጀመሪያ ውንና ሁለተኛውን ዘብ ዐልፈው ወደ ከተ ማይቱ በሚወስደው መንገድ ላይ ወዳለው የብረት መዝጊያ ዘንድ ደረሱ። መዝጊያ ውም ራሱ ሀውቆ ተከፈተላቸው፤ እነርሱም ወጥተው ሄዱ፤ አንዲት ሰላት መንገድ እንዳለፉም ወዲያው መልአኩ ተለየው።

11ጴጥሮስም ሲረጋጋ፣ "ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና አይሁድ ካሰቡብኝ ሁሉ እንዳወጣኝ አሁን ያለ ጥርጥር ዐወቅሁ" አለ።

12ይህን ከተረዳ በኋላም፣ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው በአንድነት ወደሚጸልዩበት፣ ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት ሄደ። 13እዚያ ደርሶ የውጭ ውን በር ባንኳኳ ጊዜ፣ ሮዳ የተባለች አን ዲት የቤት ሠራተኛ ማን እንደ ሆነ ለማጣራት ወደ በሩ ሄደች። 14የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑንም ባወቀች ጊዜ፣ በጣም ከመደሰቷ የተነሣ በሩን ሳትከፍት ሮጣ በመመለስ፣ ጴጥሮስ በሩ ላይ ቆሞ እንደሚገኝ ተናገረች።

15ሰዎቹም፣ "አብደሻል እንዴ!" አሏትና እርሷ ግን ይህንኑ ደጋግማ በነገረቻቸው ጊዜ፣ "እንግዲያውስ የእርሱ መልአክ ነው" አሉ።

16ጴጥሮስ ግን በር ማንኳኳቱን ቀጠለ፤ እነርሱም በሩን ከፍተው ባዩት ጊዜ ተገረሙ።

12፥7 መዝ107፥14፥ ሐሥ5፥19፥ 16፥26
12፥9 ሐሥ9፥10
12፥10 ሐሥ5፥19፥ 16፥26
12፥11 መዝ34፥7፤ ዳን3፥28፤ 6፥22፥ ሉቃ15፥17፥ 2ቆሮ1፥10፤ 2ጴጥ2፥9
12፥12 ቊ5፥25፥ ሐሥ13፥5፣13፥ 15፥37፣39፥ ቈላ4፥10፤ 2ጢሞ4፥11፥ ፊሞ24፤ 1ጴጥ5፥13
12፥13 ሮሐ18፥16፥17
12፥14 ሉቃ24፥41
12፥15 ማቴ18፥10
12፥17 ሐሥ1፥16፥ 13፥16፤ 15፥13፥ 19፥33፥ 21፥40
12፥19 ሐሥ8፥40፥ 16፥27
12፥20 1ነገ5፥9፣11፥ ሕዝ27፥17፥ ማቴ11፥21
12፥23 1ሳሙ25፥38፤ 2ሳሙ24፥16፣17፥ 2ነገ19፥35፥ ሐሥ5፥19
12፥24 ሐሥ6፥7፥ 19፥20፥ ዕብ4፥12
12፥25 ቊ12፥ ሐሥ4፥36፥ 11፥30
13፥1 ማቴ14፥1፥ 27፥32፥ ሐሥ4፥36፤ 11፥19፣27፥ ኤፌ4፥11
13፥2 ሐሥ8፥29፥

17እርሱም ዝም እንዲሉ በእጁ ጠቅሶ፣ ጌታ ከእስር ቤት እንዴት እንዳወጣው አስረዳቸው፣ "ስለ ሁኔታው ለያዕቆ ብና ለወንድሞች ንገሯቸው" አላቸው፤ ከዚ ያም ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ።

18በማግስቱም ጠዋት ወታደሮቹ፣ "ጴጥ ሮስ የት ገባ?" እያሉ በመካከላቸው ትልቅ ትርምስ ተፈጠረ። 19ሄሮድስም ጴጥሮስን አስፈልጎ ባጣው ጊዜ፣ ዘብ ጠባቂዎቹን በጥ ብቅ ከመረመረ በኋላ እንዲገደሉ አዘዘ።

የሄሮድስ አሟሟት

ከዚያም ሄሮድስ ከይሁዳ ወደ ቂሳርያ ወርዶ እዚያ ተቀመጠ። 20እርሱም ከጢ ሮስና ከሲዶና ሰዎች ጋር ጥለኛ ነበር፤ አገራቸው ምግብ የሚያገኘው ከንጉሡ ግዛት ስለ ነበር፣ የንጉሡን ባለሟል የብላስጦስን ድጋፍ ካገኙ በኋላ፣ አንድ ላይ ሆነው ከን ጉሡ ጋር ለመታረቅ ጠየቁ።

21በቀጠሮውም ቀን ሄሮድስ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ ለሕዝቡም ንግግር አደረገ። 22ሕዝቡም፣ "ይህስ የአምላክ ድምፅ እንጂ የሰው አይ ደለም" ብለው ጮኹ። 23ሄሮድስም ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ የጌታ መልአክ ወዲ ያው መታውና በትልም ተበልቶ ሞተ።

24የእግዚአብሔር ቃል ግን እያደገና እየ ሰፋ ሄደ።

25በርናባስና ሳውልም ተልእኮአቸውን ፈጽመው ከኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ማርቆስ የተ ባለውን የዮሐንስንም ከእነርሱ ጋር ይዘውት መጡ።

በርናባስና ሳውል ተሳኩ

13 በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲ ያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም፦ በርናባስ፣ ኔጌር የተባለው ስም ዖንን፣ የቀሬናው ሉክዮስ፣ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስ አብሮ አደግ የነበረው ምና ሔና ሳውል ነበሩ። 2እነዚህም ጌታን እያመ

13፥2 9፥15፤ 14፥26፣ 22፥21፥
*12፥25 እንዳንድ ቅጆች ወደ ኢየሩሳሌም ይላሉ።

12፥7 **መልአክም፡** መላእክት "መዳንን የሚወርሱትን ለማገልገል የሚላኩ አገልጋይ መናፍስት" ናቸው (ዕብ 1፥14 እንዲሁም በገጽ 372 ላይ፡ "*መላእክትና የእግዚአብሔር መልአክ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

13፥2 **እያመለኩና እየጾሙ፡** በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ክርስቲያኖች በተለይም በጸሎትና በጾሙት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ለማድመጥ የተዘጋጁ ናቸው (ማቴ 6፥16 ማብ ይመ)። በዚህ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ የመጣው መልእክት ምናልባት በትንቢት ሳይሆን አይቀርም (ከሥ 1 ጋር ያነጻጽሩ)።

13፥2 **እኔ ለጠራኋቸው ሥራ፡** ጳውሎስና በርናባስ የተጠሩት ለወንጌል አገልግሎት ሲሆን፣ ተልእኮው የተሰጣቸውም በአንጾኪያ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ነበር። የዚህ ሥራ ባሕሪይ በ9፥15፣ 13፥5፣ 22፥14-15፣21 እና 26፥16-8 ተዘርዝሮ ተገልጾአል፡ (1) ጳውሎስና በርናባስ የተጠሩት መንጌል ለመስበክ ሲሆን፣ ይህም ወንዶችንና ሴቶችን ወደ ክርስቶስ ኅብረት በማምጣት እንዲድኑ ማድረግ ነው። የወንጌል መልእክተኞች ወደ ዓለም የሚላኩት ማኅበረሰዊ ወይም ፖለቲካዊ ሥራ ለመሥራት ይኸውም ወንጌልን ለመስበክና ቤተ ክርስቲያንን ለመመሥረት በማንኛውም በተጠናከረ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብቶ ለሮም መንግሥትና ሕዝብ ጥቅም ለመሥራት እንደ ሆነ የሚያመለክት ሐሳብ በአዲስ ኪዳን በየትኛውም ስፍራ ፈጽሞ አይገኝም። ግባቸው ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት (16፥31፣ 20፥21)፣ ከሰይጣን ኀይል ነጻ ማውጣት (26፥18)፣ መንፈስ ቅዱስ እንዲመርድጣቸው መርዳት (19፥6) እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲደራጁ ማድረግ ነው። በእነዚህ

ለኩና እየጸሙ ሳሉ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ "በርናባስንና ሳውልን እኔ ለጠራኋቸው ሥራ ለዩ

13፥3 ሐሥ6፥6፣ 14፥26

ልኝ" አለ። ³እነርሱም ከጸሙና ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጭነው አሰናበቷቸው።

አዳዲስ ክርስቲያኖች ላይ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ራሱን በፍቅር ገለጠላቸው፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሰጣቸው (1ቆሮ 12-13)፣ ሕያው ለሆነው አምላካቸው ሕይወታቸው ክብርን ያመጣ ዘንድ የውስጥ ሰውነታቸውን ለወጠ።

(2) ዛሬም ቢሆን የወንጌል መልእክተኞች ተመሳሳይ ለሆነ አገልግሎት ራሳቸውን መስጠት ይኖርባቸዋል፤ ይኸውም የወንጌል ምስክሮችና አገልጋዮች መሆን፣ ሰዎችን ከሰይጣን ግዛት ነጻ በማውጣት ወደ ክርስቶስ ማምጣት (26፥18)፣ ደቀ መዛሙርት ማድረግ፣ መንፈስ ቅዱስንና ስጦታዎቹን እንዲቀበሉ ማደፋፈር (2፥38፣ 8፥17)፣ ክርስቶስ ያዘዛቸውን ሁሉ እንዲፈጽሙ ማስተማር ነው (ማቴ 28፥19-20)። ከዚህ ጋር አብሮ ምልክትና ድንቅ፣ የበሽተኞች መፈወስና በኢጋንንት የታሰሩትን ነጻ ማውጣት ሊኖር ይገባል (2፥43፣ 4፥30፣ 8፥7፣ 10፥38፣ ማር 16፥17-18)። ይሁን እንጂ ወንጌልን የመስበክ ከፍተኛ ሥራ በችግር ላይ ላሉት ቸርነትንና ፍቅርን ማሳየት ሊያካትት ይገባል (ከገላ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ መንገድ የወንጌል ምስክሮች እንዲሆኑ የተጠሩ ሁሉ በአገልግሎታቸው ያሏቸውን አርአያነት መከተል ይኖርባቸዋል (ሉቃ 9፥2 ማብ ይመ)።

13፥3 **አሰናበቷቸው**፤ በዚህ ቃል መሠረት "እስከ ምድር ዳርም" (1፥8) ድረስ የሚደርሰው ታላቁ የወንጌል አገልግሎት ይጀምራል። የወንጌል መልእክተኞችን ለሚልኩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚጠቅመው በምዕራፍ 13 የተዘረዘሩት የወንጌል መልእክተኞነት መርሖች የሚከተሉት ናቸው፣

(1) የወንጌል መልእክተኞነት ሥራ ለጌታና ለመንግሥቱ ራሳቸውን በእውነት በሰጡ፣ እርሱንም በጸምና በጸሎት በሚፈልጉ መንፈሳዊ መሪዎች አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ የሚነሣሣ ነው (ቍሥ 2)።


(2) ቤተ ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት፣ ለትንቢታዊ አገልግሎትና ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ልቧን የከፈተች ልትሆን ይገባል (ቍሥ 2)።

(3) የወንጌል መልእክተኞች ለአገልግሎት የሚመጡት መንፈስ ቅዱስ ወደ እነርሱ ባመጣው ልዩ ጥሪና ፈቃድ መሠረት መሆን አለበት (ቍሥ 2ለ)።

(4) ሳታቋርጥ በጸምና በጸሎት እየተጋች ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ጋር ለመስማማት በመፈለግ (ቍሥ 3-4)፣ ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል አገልግሎት እግዚአብሔር የጠራቸውን አንዳንድ ግለሰቦች ለይታ ታውጣለች። ዐላማው ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ስለሥራው የሰየቸውን ሰዎች እንድትልክ ማድረግ ነው።

(5) እጆችን በመጫንና የወንጌል መልእክተኞችን በመላክ፣ ቤተ ክርስቲያን ወደ አገልግሎት ለሚላኩት ሰዎች ያላትን ድጋፍና ማበረታቻ ትገልጻለች። መልእክተኞችን የምትልከው ቤተ ክርስቲያን ጎላፊነት መልእክተኞችን በመንገዳቸው በፍቅር መላክና እግዚአብሔር ያን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ መሸኘትን (3ዮሐ 1፥6)፣ ለእነርሱ መጸለይን (13፥3፣ ኤፌ 6፥18-19)፣ የገንዘብ እርዳታ ማድረግን (ሉቃ 10፥7፣ 3ዮሐ 1፥6-8)፣

የጳውሎስ የመጀመሪያ የወንጌል ጉዞ



© 1989 The Zondervan Corporation

በርናባስና ሳውል በቆጵሮስ

1 በርናባስና ሳውልም በመንፈስ ቅዱስ
ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፤ ከዚያም
በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ። 5 ስልማና በደረሱም ጊዜ በአይሁድ ምኵራቦች የእግዚአብሔርን
ቃል ሰበኩ፤ ዮሐንስም አብሮአቸው ሆኖ
ይረዳቸው ነበር።

6 በቆጵሮስን ደሴት ከዳር እስከ ዳር አቋ
ርጠው ጳፉ በደረሱ ጊዜ፣ በርያሱስ የተባለ
አንድ አይሁዳዊ ጠንቋይና ሐሰተኛ ነቢይ
አገኙ፤ 7 እርሱም ሰርግዮስ ጳውሎስ ከተ
ባለው አስተዋይ አገረ ገዥ ጋር ነበረ። ይህ
አገረ ገዥ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት
ፈልጎ በርናባስንና ሳውልን አስጠራቸው።
8 ጠንቋዩ ኤልማስ ግን፣ የስሙ ትርጒም
እንዲህ ነበርና፣ አገረ ገዥ እን ዳያምን
ለማደናቀፍ ስለ ፈለገ ተቃወማ ቸው።
9 ጳውሎስ የተባለውም ሳውል በመ ንፈስ
ቅዱስ ተሞልቶ፣ ትኵር ብሎ ተመ ለከተውና
እንዲህ አለው፤ 10 "አንተ የድያቆ ሁሉ
ጠላት፣ ተንኰልንና ክፋትን ሁሉ የተሞላህ
የዲያብሎስ ልጅ የጌታን ቀና መንገድ
ከማጣመም አታርፍምን? 11 አሁንም የጌታ
እጅ በአንተ ላይ ነው፤ ዕውር ትሆናለህ፤
ከእንግዲህ የፀሓይን ብርሃን ለአ ንድ አፍታ
እንኳ አታይም።"

ወዲያውም ጭጋግና ጨለማ በላዩ ወረደ፤
እጁን ይዞ የሚመራውንም ሰው ለመፈለግ
ወዲያ ወዲህ ይል ጀመር። 12 አገረ ገዥም
የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ፣ በጌታ ትምህርት
በመደነቅ አመነ።

በርናባስና ጳውሎስ በጲስድያ

13 ጳውሎስና ጓደኞቹ ከጳፉ ተነሥተው
በጵንፍልያ ወደምትገኘው ወደ ጴርጌን
ሄዱ፤ ዮሐንስም ከእነርሱ ተለይቶ ወደ
ኢየሩሳ ሌም ተመለሰ። 14 እነርሱ ግን

13፡4 ሥሥ2፡3፣ 4፡36
13፡5 ሐሥ9፡20፣ 12፡12፣ ዕዝ4፡12
13፡6 ማቴ7፡15፣ ሐሥ8፡9
13፡7 ሥሥ8፡12፣ ሐሥ18፡12፣ 19፡38
13፡8 ሥሥ7፤ ኢሳ30፡11፣ ሐሥ6፡7፤ 8፡9
13፡9 ሉቃ1፡15
13፡10 ሆሴ14፡9፣ ማቴ13፡38፣ ዮሐ8፡44
13፡11 ዘፍ19፡10፡11፣ ዘፀ9፡3፣ 1ሳሙ5፡6፡7፤ 2ነገ6፡18፣ መዝ32፡4
13፡12 ሥሥ7
13፡13 ሥሥ6፣ ሐሥ2፡10፣ 12፡12
13፡14 ሥሥ27፡42፡44፣ ሐሥ9፡20፣ 14፡19፡21፣ 16፡13፣ 18፡4
13፡15 ሐሥ15፡21
13፡16 ሐሥ12፡17
13፡17 ዘፀ6፡6፡7፣ ዘዳ7፡6-8
13፡18 ዘኍ14፡33፣ ዘዳ1፡31፣ መዝ95፡10፣ ሐሥ7፡36
13፡19 ዘዳ7፡1፣ ኢሱ19፡51፣ መዝ78፡55፣ ሐሥ7፡45
13፡20 መሳ2፡16፣ ከጴርጌን ተነሥተው በጲስድያ ሙስዋ
ወዳለችው ወደ አንጾኪያ ሄዱ፤ በሰንበት
ቀንም ወደ ምኵራብ ገብተው ተቀመጡ።
15 የሕግና የነቢያት መጻሕፍት ከተነበቡ
በኋላ፣ የምኵራብ አለቆች፣ "ወንድሞች
ሆይ፤ ሕዝቡን የሚመክር ቃል ካላችሁ
ተናገሩ" ሲሉ ላኩባቸው።

16 ጳውሎስም ተነሥቶ በእጁ በመቅረስ
እንዲህ አለ፤ "የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤
ደግሞም እናንት እግዚአብሔርን የምትፈሩ
ሁሉ፤ አድምጡ። 17 የዚህ የእስራኤል ሕዝብ
አም ላክ፣ አባቶቻችንን መረጣቸው፤ በግብፅ
ምድር እያሉም ከፍ ከፍ አደረጋቸው፤ በ
ያል ክንዱም ከዚያ አወጣቸው። 18 አርባ
ዓመት ያህልም በበረሓ ታገሣቸው፤ 19 በከነዓን ምድር የነበሩትንም ሰባት
መንግሥታት አጥፍቶ፣ ምድሪቱን ለገዛ
ሕዝቡ ርስት አድርጎ አወረሳቸው። 20 ይህም
ሁሉ የተፈጸመው በአራት መቶ አምሳ
ዓመት ያህል ጊዜ ውስጥ ነበር።

"ከዚህ በኋላ እስከ ነቢዩ ሳሙኤል
ዘመን ድረስ መሳፍንትን ሰጣቸው።
21 ከዚያም ሕዝቡ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው
ለመኑት፤ እግዚአብሔርም ከብንያም ወገን፣
የቂስን ልጅ ሳኦልን ሰጣቸው፤ እርሱም
አርባ ዓመት ገዛቸው። 22 ሳኦልንም ከሻረው
በኋላ፣ ዳዊትን አነገሣቸው፤ ስለ እርሱም፣
'እንደ ልቤ የሆነና እኔ የምሻውን ሁሉ
የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ'
ሲል መሰከረለት።

23 እግዚአብሔርም በገባው ቃል መሠረት
ከዘሪህ ሰው ዘር አዳኝ የሆነውን ኢየሱስን

13፡20 1ሳሙ3፡19፡20፣ ሐሥ3፡24 13፡21 1ሳሙ8፡5፡19፡ 9፡1፡2፡ 10፡1 13፡22 1ሳሙ13፡14፣ 15፡23፡26፡ 16፡13፣ መዝ89፡20፣ ኢሳ44፡28፣ ኤር3፡15 13፡23 ሥ32፣ 2ሳሙ. 7፡11፣ 22፡51፣ ኤር30፡9፣ ማቴ1፡1፡21፣ ሉቃ2፡11

*ሃ13፡18 አንዳንድ ቅጆች ተንከባከባቸውም ይላሉ።

ለሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ የፍቅር ስጦታ መላ
መላክን ይጨምራል (ፊል 4፡10፡14-18)። የመንፈል
መልእክተኞች የምትልከው ቤተ ክርስቲያን ዋና ዐላማ፣
ትኵረትና ተልእኮ ከሆኑት አንደ አንዱ ክፍል መቈጠር
አለባቸው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለእውነት የሚሠሩ
(3ዮሐ 1፡8 ይመ፣ ከፊል 1፡5 ጋር ያነጻጽሩ) ምእመናን
ያለብት ትሆናለች።

(6) የመንፈል መልእክተኞች ሆነው የሚመጡ
አገልጋዮች ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሕይወታቸውን
መሥዋዕት አድርገው ለመስጠት ፈቃደኞች ሊሆኑ
ይገባል (15፡26)።

13፡8 ጠንቋዩ፤ ይህ ጠንቋይ ምናልባት አይሁዳዊ
ከነብ ቈጣሪ ሳይሆን አይቀርም። ከነብ ቈጣሪዎች
የእያንዳንዱ ግለሰብ እድል ፈንታ በሰማይ አካላት
ሁኔታ ይወሰናል ብለው ያስተምራሉ። የከዋክብትንና
የፕላኔቶችን አቀማመጥ በመመርመር የወደፊቱን
መናገር ይቻላል ብለው ያምናሉ። ጥንቈላ ወይም
ኰከብ ቈጠራ ሁሉ የሰይጣንና የአጋንንት ሥራ ስለሆነ፣
የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የሚቃወም ነው (ሥሥ 10፡
ዘዳ 18፡9-11 ማብ ይመ)።

13፡9 ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፤
ማንም ሰው ጳውሎስ እንደተጠመቀው በመንፈስ ቅዱስ
ሊጠመቅ ይችላል (9፡17)፣ ይሁን እንጂ አስፈላጊ
በሚሆንበት በልዩ ጊዜ ደግሞ አዲስ የመንፈስ ቅዱስ
ሙላትን ሊቀበል ይችላል። እንዲህ ዐይነቱ ተደጋጋሚ
የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልገው በሚከተሉት
ምክንያቶች ነው፡ (1) ወንጌል የሚቃወመውን ኀይል
ለመቋቋም (4፡8-12)፣ (2) ወንጌልን ለማስፋፋት
(4፡8፡31)፣ (3) የሰይጣንን እንቅስቃሴ በቀጥታ
ለመቋቋም (13፡9፡50-52)። በመንፈስ ቅዱስ የተጠ
መቁ አማኞች ሁሉ ተደጋጋሚ የሆኑ የመንፈስ ቅዱስ
ሙላቶችን የሕይወታቸው ልምምድ ሊያደርጉ ይገባል።

13፡11 ዕውር ትሆናለህ፤ ታምራት በአዲስ
ኪዳን ብዙውን ጊዜ ፈውስ ብቻ ሳይሆን ይችላል፤
አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ኤልማስን በዚህ
ስፍራ እንደተቈጣበት (ቊጥ 8-11) እና ሄሮድስን
እንደቀሠፈበት (12፡20-23) ዐይነት የእግዚአብሔር ፍርድ
አርሱን በማይፈሩ ግለሰቦች ላይ የሚገለጥበት ሁኔታም
አለ። በሐናንያና በሰጲራ ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር
ቊጣ (5፡1-11)፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለ ነጠላት
ላይ ለሚገለጥ ታምራዊ ፍርድ ምሳሌ ነው።

ለእስራኤል አመጣ። 24ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት፣ ዮሐንስ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ንስሓ ገብተው እንዲጠመቁ ሰብክላቸው ነበር። 25ዮሐንስ ተልእኮውን በማጠናቀቅ ላይ ሳለ፣ 'እኔ ማን መሰልኋችሁ? እኔ እኮ እርሱ አይደለሁም፤ ነገር ግን የእግሩን ጫማ እንኳ መፍታት የማይገባ ከእኔ በኋላ ይመጣል' ይል ነበር።

26"እናንት ከአብርሃም ዘር የተወለዳችሁ ወንድሞች፤ ደግሞም በመካከላችሁ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ፤ ይህ የድነት መልእክት የተላከው ለሁላችንም ነው። 27የኢየሩሳሌም ሰዎችና አለቆቻቸው ኢየሱስን አላወቁትም፤ ይሁን እንጂ በየሰንበቱ የሚነበበው የነቢያት ቃል እንዲፈጸም በእርሱ ፊረ ዳበት። 28ለሞት የሚያበቃው አንድም ምክ ንያት ቢያገኙበትም እንኳ ጲላጦስ የሞት ፍርድ እንዲፈርድበት ተማጸኑት። 29ስለ እርሱ የተጻፈውን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ ከተ ሰቀለበት ዕንጨት አውርደው በመቃብር ውስጥ አስገቡት። 30እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው። 31ከገሊላ ጀምሮ እስከ ኢየ ሩሳሌም ከእነርሱ ጋር ለነበሩትም ብዙ ቀን ታያቸው፤ እነርሱም አሁን ለሕዝቡ ምስክሮቹ ናቸው።

32"እኛም እግዚአብሔር ለአባቶች ቃል የገ ባውን የምሥራች ቃል ለእናንተ እንሰብ ክለን፤ 33ኢየሱስንም ከሙታን በማስነሣቱ ለእነርሱ የገባውን ቃል ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞአል፤ ይኸውም በሁለተኛው መዝሙር እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤

" 'አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወለድሁህ።' "

34ደግሞም፣ እርሱ እንዳልበሰበሰና እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው ለማረጋገጥ እንዲህ ብሎአል፤

" 'የተቀደሰውንና የታመነውን፣
የዳዊትን በረከት እሰጣችኋለሁ።'

13፥24 ማር1፥4
13፥25 ማቴ3፥11፤ ዮሐ1፥20፣27፤ ሐሥ20፥24
13፥26 ሉቃ3፥8፤ ሐሥ4፥12፤ 22፥5፣ 28፥28
13፥27 ማቴ1፥22፤ ሉቃ24፥27፤ ሐሥ3፥17
13፥28 ማቴ27፥20-25፤ ሐሥ3፥14
13፥29 ማቴ1፥22፤ ሉቃ18፥31፤ 23፥53፤ ሐሥ5፥30
13፥30 ማቴ16፥21፤ 28፥6፤ ሐሥ2፥24
13፥31 ማቴ28፥16፤ ሉቃ24፥48
13፥32 ኢሳ40፥9፤ 52፥7፤ ሐሥ5፥42፤ 8፥35፤ 10፥36፤ 14፥7፣15፣21፤ 17፥18፤ 26፥6፤ ሮሜ1፥2፤ 4፥13፤ 9፥4
13፥33 መዝ2፥7፤ ማቴ3፥17፤ ሐሥ2፥24
13፥34 ኢሳ55፥3
13፥35 መዝ16፥10፤ ሐሥ2፥27
13፥36 2ሳሙ7፥12፤ 1ነገ2፥10፤ 2ዜና 29፥28፤ ማቴ9፥24፤ ሐሥ2፥29
13፥37 ሐሥ2፥24

35ስለዚህ በሌላም ስፍራ፤

" 'ቅዱስህ መበስበስን እንዲያይ
አትፈቅድም' ይላል።

36"ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካገለገለ በኋላ እንቀላፍቶአል፤ ከአ ባቶቹም ጋር ተቀብሮ ሥጋው በስብሶአል። 37እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሣው እርሱ ግን መበስበስን አላየም።

38እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ የኀጢአት ይቅርታ የሚገኘው በኢየሱስ በኩል መሆኑ እንደ ተሰበከላችሁ ዕወቁ፤ 39በእርሱ የሚ ያምን ሁሉ በሙሴ ሕግ በኩል ሚገኘ ት ያልተቻለውን ጽድቅ ያገኛል። 40ስለዚህ ነቢያት እንዲህ ብለው የተናገሩት እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ፤ ሮሜ 1፥16

41" 'እናንት ፈዘኞች፤ ተመልከቱ፤
ተደነቁ፤ ጥፋም፤
ማንም ቢነግራችሁ፣
የማታምኑትን ሥራ፣
እኔ በዘመናችሁ እሠራለሁና።' "

42ጳውሎስና በርናባስ ከምኵራብ ሲወጡ፣ ሰዎቹ ስለዚህ ነገር በሚቀጥለው ሰንበት እንዲነግሯቸው ለመኗቸው። 43ጉባኤው ከተ በተነ በኋላም፣ ብዙ አይሁድና ወደ ይሁዲ ሃይማኖት ገብተው በመንፈሳዊ ነገር የበረቱ ሰዎች፣ ጳውሎስንና በርናባስን ተከተሏቸው፤ እነርሱም አነጋገሯቸው፤ በእግዚአብሔርም ጸጋ ጸንተው እንዲኖሩ መከሯቸው።

44በሚቀጥለውም ሰንበት የከተማው ሕዝብ፣ ጥቂቱ ሰው ብቻ ሲቀር፣ በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ተሰበሰቡ። 45አይሁ ድም ብዙ ሕዝብ ባዩ ጊዜ፣ በቅናት ተሞሉ፤ የጳውሎስንም ንግግር እየተቃወሙ ይሰድቡት ነበር።

13፥38 ሉቃ24፥47፤ ሐሥ2፥38
13፥39 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ3፥28 13፥41 ዕን1፥5
13፥42 ቊ14 13፥43 ሐሥ11፥23፤ 14፥22፤ ሮሜ3፥24
13፥45 ሐሥ18፥6፤ 1ተሰ2፥16፤ 1ጴዋ4፥4፤ ይሁ10

†13፥33 ወይም አባትህ ሆንኩ

13፥31 ለሕዝቡ ምስክሮቹ ናቸው፤ ምስክር (ግሪክ፡ ማርተስ) "እውነትን በድርጊት ወይም በቃል የሚመሰክር" ማለት ነው። ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራ በቃል፣ በድርጊት፣ በኑሮ አስፈላጊም ከሆነ በሞት የሚመሰክሩና የሚያረጋግጡ ናቸው። ይህ እውነታ የሚከተሉትን ሰባት መርሖች የሚያካትት ነው፡

(1) ክርስቲያናዊ ምስክርነት ከአማኞች ሁሉ የሚጠበቅ ግዴታ ነው (1፥8፤ ማቴ 4፥19፤ 28፥19-20)።

(2) ክርስቲያን መስካሪዎች ወደ ሕዝቦች ሁሉ የመሄድና የእግዚአብሔርን የድነት ስሙታ ወደ ምድር ዳርቻ ሁሉ የማድረስ የወንጌል መልእክተኝነት አስተሳሰብ ሊኖራቸው ይገባል (11፥18፤ 13፥2-4፤ 26፥16-18፤ ማቴ 28፥19-20፤ ሉቃ 24፥47)።

(3) ክርስቲያን መስካሪዎች በመሠረቱ የሚናገሩት የክርስቶስን ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤ፣ የማዳን ኀይሉንና ተስፋ የተገባውን የመንፈስ ቅዱስን ትርጒም መሆን አለበት (2፥32፣38-39፤ 3፥15፤ 10፥39-41፣43፤ 18፥5፤ 26፥16፤ 1ቆሮ 15፥1-8)።

(4) ክርስቲያን መስካሪዎች ኀጢአትን፣ ጽድቅንና ፍርድን በተመለከተ ለውጥን ማምጣት አለባቸው (2፥37-40፤ 7፥51-54፤ 24፥24-25፤ ዮሐ 16፥8 ግብ ይመ)። በእንደዚህ ዐይነት መስካሪዎች አማካይነት ሰዎች ለድነት ወደሚያበቃው እምነት ይደርሳሉ (2፥41፤ 4፥33፤ 6፥7፤ 11፥21)።

(5) ክርስቲያን መስካሪዎች አንዳንድ ጊዜ ሥቃይ ሊደርስባቸው ይችላል (7፥57-60፤ 22፥20፤ 2ቆሮ 11፥23-29)። ሰማዕት በሚል የተተረጐመው የእንግሊዝኛ ቃል የተወሰደው ምስክር የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ከተተረጐመበት ከግሪኩ ቃል ነው። ደቀ መዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ ምንም ይሁን ምን ሙሉ በሙሉ ልብ መስጠትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

(6) ክርስቲያናዊ ምስክርነት ከዓለም መለየትን (2፥40)፣ የጽድቅ ሕይወት መኖርን (ሮሜ 14፥17) እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንፈስና ኀይል መግለጥ የሚያስችለውን (1ቆሮ 2፥4) በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የመደገፍን ሕይወት (4፥29-33) ማስከተል አለበት።

(7) ክርስቲያናዊ ምስክርነት አስቀድሞ በትንቢት የተነገረ ነው (2፥17) እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚደረግና (1፥8) የሚነሣሣ (2፥4፤ 4፥8) ነው።

46ጳውሎስና በርናባስም በድፍረት እንዲህ አሏቸው፤ “የእግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያ ለእናንተ መነገር አለበት፤ እናንተ ግን ናቃችሁት፤ በዘላለም ሕይወት እንደማ ይገባችሁ በራሳችሁ ላይ ስለ ፈረዳችሁ፣ እኛም ወደ አሕዛብ ዞር ለማለት እንገደዳ ለን። 47ጌታም እንዲህ ብሎ አዞናል፤

“ ‘ድነትን እስከ ምድር ዳርቻ ታደርስ ዘንድ፣
ለአሕዛብ ብርሃን አደርጌሃለሁ።’ ”

48አሕዛብ ይህን በሰሙ ጊዜ ደስ አላቸው፤ በእግዚአብሔርም ቃል ክብርን ሰጡ፤ ለዘላለም ሕይወት የተዘጋጁትም ሁሉ አመኑ።

49የጌታም ቃል በአካባቢው ባለው አገር ሁሉ ተሰፋፋ። 50አይሁድ ግን በመንፈሳዊ ነገር የተጉትንና በኑሮ የከበሩትን ሴቶች አንዲሁም የከተማውን ታላላቅ ወንዶች ቀስ ቅሰው በጳውሎስና በበርናባስ ላይ ስደትን አስነሡ፤ ከአገራቸውም አስወጧቸው። 51ጳውሎስና በርናባስም ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ የእግራቸውን ትቢያ አራግፈው ወደ ኢቆንዮን ሄዱ። 52ደቀ መዛሙርቱም በደስታና በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ።

ጳውሎስና በርናባስ በኢቆንዮን

14 በኢቆንዮንም ጳውሎስና በርናባስ አብረው ወደ አይሁድ ምኵራብ ገቡ፤ በዚያም በሚገባ ስላስተማሩ፣ ከአይሁዶችም ከግሪክም እጅግ ብዙ ሰዎች አመኑ። 2ያላመኑት አይሁድ ግን፣ አሕዛብን አነሣሥተው ወንድሞችን እንዲጠሉ አደረጓቸው። 3ጳውሎስና በርናባስም ስለ ጌታ በድፍረት እየተናገሩ ብዙ ጊዜ አዚያው ቈዩ፤ ጌታም የሚናገሩትን የጸጋውን ቃል በታምራዊ ምልክትና በድንቅ ሥራ እየደገፈ ያረጋግጣላቸው ነበር። 4የከተማውም ሕዝብ ተከፋፈለ፤ ግሚሉ ከአይሁድ ጋር፣ ግሚሉም ከሐዋርያት ጋር ሆነ። 5በዚህ ጊዜ አሕዛብና አይሁድ ከመሪዎቻቸው ጋር ተባብረው ሊያንገላቷቸውና በድንጋይ ሊያስወግሯቸው ሞከሩ። 6እነርሱ ግን ይህን እንዳወቁ ልስጥራንና ደርቤን ወደ ተባሉት ወደ ሊቃኦንያ ከተሞችና በዙሪያቸው ወዳለው አገር ሸሹ፤ 7በዚያም ወንጌልን መስበክ ቀጠሉ።

ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራና በደርቤ

8በልስጥራንም፣ እግሩ አንካሳ የሆነና ከተወለደ ጀምሮ ፈጽሞ በእግሩ ሄዶ የማያውቅ ሽባ ሰው ተቀምጦ ነበር። 9ይህም ሰው ጳውሎስ ሲናገር ያደምጥ ነበር። ጳውሎስም ወደ እርሱ ትኵር ብሎ ተመለከተና ለመዳን እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ

14:8 ሐሥ 3:2 14:9 ማቴ 9:28,29፤ 13:58

13:46 ቍ 26፤ ማቴ 21:41፤ ሐሥ 3:26፤ 18:6፤ 22:21፤ 26:20፤ 28:28፤ ሮሜ 11:11፤ 13:47 ኢሳ 49:6፤ ሉቃ 2:32 13:48 ቍ 49፤ ሐሥ 8:25፤ 15:35,36፤ 19:10,20 13:49 ቍ 48 13:50 1ተሰ 2:16 13:51 ማቴ 10:14፤ ሐሥ 14:1፤ 19:21፤ 16:2፤ 2ጢሞ 3:11 13:52 ሉቃ 1:15፤ ሐሥ 11:26 14:1 ሐሥ 2:41፤ 9:20፤ 13:51 14:2 ሐሥ 1:16 14:3 ዮሐ 4:48፤ ሐሥ 4:29 14:4 ሐሥ 17:4,5፤ 28:24 14:5 ቍ 19፤ ሐሥ 20:3 14:6 ማቴ 10:23 14:7 ቍ 15:21፤ ሐሥ 13:32፤ 16:10

ገሠገሠ፤ 5 ዘዳ 25:5

13:47 ታደርስ ዘንድ የሚለው በግሪኩ ካለ ሞቷር ነው።

13:48 **ለዘላለም ሕይወት የተዘጋጁትም፤** አንዳንዶች ይህን ጥቅስ ድነትን በሚመለከት አስቀድሞ የመወሰንን ትምህርት በዘፈቀደ የሚያስተምር እንደ ሆነ አድርገው ይቈጥራሉ። ነገር ግን በውዱም ሆነ ሐሳቡ የተመለሰበት ቃል (ግሪክ፡ “ቴታግሜናይ”፣ “ታሶ” ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው) አስቀድሞ የመወሰንን ትርጕም እንድንሰጥ አይፈቅድልንም። (1) ቍ 46 እያንዳንዱ ሰው የዘላለም ሕይወትን የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት እንዳለው በግልጽ ያመለክታል። ስለዚህ “ቴታግሜናይ” ለሚለው ቃል የተሻለው ትርጕም “ፈቃደኞች ነበሩ” የሚለው ነው። ይኸውም “የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ፈቃደኞች የሆኑ ሁሉ አመኑ” ማለት ነው። ይህ ትርጓሜ በ1ጢሞ 2፡4፣ ዕብ 2፡11፣ በ2ጴጥ 3፡9 ካሉት ማረጋገጫዎች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ ነው (በግሪ 1860 ሳይ፣ “ምርጫና አሰቀድሞ መወሰን” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) ። (2) ከዚህም በተጨማሪ ሐዋርያው ጳውሎስ ማንም ሰው ያለምንም ዐይነት ቅድመ ሁኔታ ለዘላለም ሕይወት እንደማይመረጥ ያስተምረናል (ሮሜ 11፡20-22)።

13:52 **በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤** “ተሞሉ” ለሚለው የግሪኩ ግስ በጎላ ጊዜ የተፈጸመ የማያቋርጥ ድርጊትን የሚያመለክት ቦዝ ያልሆነ አንቀጽ ነው። ደቀ መዛሙርት በየዕለቱ ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ይሞሉና በነይልም ይታጠቁ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የአንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ የሚቆም የመጀመሪያ ከሥተት አይደለም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ለሆኑ ፍላጎቶችና በሳማዎች በታዩበ መሳት የሚኖርበት ሕይወት ነው (ከኤፌ 5፡18 ጋር ያነጻጽሩ)።

14:3 **በታምራዊ ምልክትና በድንቅ ሥራ፤** የወንጌልን እውነት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የወንጌል ስብከት ታምራዊ ምልክቶች እንዲከተሉት የእግዚአብሔር ዐላማ ነው (ከማር 16፡20 ጋር ያነጻጽሩ እንዲሁም በግእ 1527 ሳይ፣ “አማኞች ሮሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር አብሮ ሠራ፤ የመልእክታቸውን እውነተኛነት መሰከረ። የእግዚአብሔር ጸጋ በምልክቶችና በድንቆች የማረጋገጥ በት እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ “በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ጊዜ እንደሚመጣ” የተባለውን ፈት ለፌት የጌጠምንዝት ለዘራው ጊዜ በእጅጉ የሚያስፈልግ ነው (1ጢሞ 4፡1፣ 2ጢሞ 3፡1-13 ይመ)።

14:4 **ከሐዋርያት፤** ጳውሎስና በርናባስ ሁለቱም ሐዋርያት ተብለው ተጠርተዋል፤ “ሐዋርያ” የሚለው ስም አጠቃላይ መጠሪያ በመሆን የአዲስ ኪዳንን መልእክት ለመስበክ በዜተ ክርስቲያን የተሳኩትን የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞች የሚያመለክት ነበር (ቍ 4:14)። “ሐዋርያ” የሚለው ቃል ልዩ መጠሪያ በመሆን፣ የዋሰው የመጀመሪያውን መልእክትና ራእይ ተቀብለው ተግባራዊ ለማድረግ በቀዋታ ከክርስቶስ ተልእኮን ያገኙትን ለማመልከት ነው (ኤፌ 2፡20 እና ግብ ይመ)። ጳውሎስ በዚህኛው ልዩ ዋሪ ሐዋርያ በመሆን የተሸመ ነበር።

14:9 **ለመዳን እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ፤** ሽባ የነበረው ሰው እምነት እንዳለው መለየት የተቻለው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። ጳውሎስ የዚህን ሰው እምነት ያደሩፈረው ቀጥ ብሎ እንዲቆም በማዘዝ ነበር። የእግዚአብሔር ጸጋና ፈውስ የሚስፈልጋቸውን ግለሰቦች እምነት ለይቶ ለማወቅ፣ እግዚአብሔር መንፈሳዊ መረዳትን እንዲሰጣቸው አማኞች መጸለይ ይገባቸዋል።

[10]በታላቅ ድምፅ "ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም!" አለው፤ በዚህ ጊዜ ዘሎ ተነሣና መራመድ ጀመረ።

[11]ሕዝቡም ጳውሎስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ፣ በሊቃኦንያ ቋንቋ፣ "አማልክት በሰው ተመ ስለው ወደ እኛ ወርደዋል!" ብለው ጮኹ፤ [12]በርናባስን 'ድያ' አሉትና፤ ጳውሎስም ዋና ተናጋሪ ስለ ነበር 'ሄርሜን' አሉት። [13]ከከተማው ጠባ ብሎ የነበረውና የድያ ቤተ መቅደስ ካህንም ኰርማዎችንና የአበባ ጕንጕኖችን ወደ ከተማው መግቢያ አምጥቶ፣ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ ሊሠዋላቸው ፈለገ።

[14]ሐዋርያቱ በርናባስና ጳውሎስ ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል ሮጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አደርገው እንዲህ አሉ፤ [15]"እናንተ ሰዎች፤ ለምን ይህን ታደርጋላችሁ? እኛም እኒ እንደ እናንተው ሰዎች ነን። እናንተም ደግሞ ከዚህ ከንቱ ነገር ርቃችሁ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም በውስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር እንድትመለሱ ወንጌልን እንሰብክላችኋለን። [16]እርሱ ባለፉት ትው ልዶች፣ ሕዝቦች ሁሉ በገዛ መንገዳቸው እንዲሄዱ ተዋቸው፤ [17]ይሁን እንጂ ዝናብን ከሰማይ እንዲሁም ፍሬያማ ወቅቶችን በመ ስጠቱ፣ ደግሞም ልባችሁን በመብልና በደ ስታ በማርካቱ መልካም በማድረግ ራሱን ያለ ምስክር አልተወም።" [18]ይህን ሁሉ ተናግረው እንኳ፣ ሕዝቡ እንዳይሠዋላቸው ያስተዉት በብዙ ችግር ነበር።

[19]አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጥተው፣ ሕዝቡን አግባብተ፤ ጳውሎስንም በድንጋይ ከወገሩት በኋላ፣ የሞተ መስሎ

14፥10 ሐዋ2፥1፡ ሐሥ3፥8
14፥11 ሐሥ8፥10፡ 28፥6
14፥12 ዘፀ7፥1
14፥14 ማር14፥63
14፥15 ሮ7፥21፡ ዘፍ1፥1፡ 1ሳሙ12፥21፡ መዝ146፥6፡ ማቴ16፥16፡ ሐሥ10፥26፡ 13፥32፡ 1ተሰ1፥9፡ ራእ14፥7
14፥16 መዝ81፥12፡ ሚክ4፥5፡ ሐሥ17፥30
14፥17 ዘዳ11፥14፡ ኢዮ5፥10፡ መዝ4፥7፡ 65፥10፡ ሮሜ1፥20
14፥19 ሐሥ13፥45፡51፡ 2ቆሮ11፥25፡ 2ጢሞ3፥11
14፥20 ቈሮ22፥28፡ ሐሥ11፥26
14፥21 ሐሥ2፥41፡ 13፥32፡51
14፥22 ዮሐ16፥33፡ ሐሥ11፥23፡ 13፥43፡ 1ተሰ3፥3፡ 2ጢሞ3፥12
14፥23 ሐሥ11፥30፡ 13፥3፡ 20፥32
14፥24 ሐሥ2፥10

እቸው ጐትተው ከከተማው ወደ ውጭ አወጡት። [20]ሆኖም ደቀ መዛሙርት ከዙት እንዳሉ ተነሣ፤ ወደ ከተማም ገባ። በማግስቱም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ሄዱ።

ጳውሎስና በርናባስ በሶርያ ወዳለችው አንጾኪያ ተመለሱ

[21]ጳውሎስና በርናባስ በደርቤን የምሥራቹን ቃል ሰብከው፣ ብዙ ደቀ መዛሙርትም ካፈሩ በኋላ፣ ወደ ልስጥራን፣ ወደ ኢቆንዮንና ወደ አንጾኪያ ተመለሱ። [22]የደቀ መዛሙርቱንም ልብ በማበረታታትና በእም ነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር፣ "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን" አሏቸው። [23]ከዚያም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ፣ በጸምና በጸሎት ላመኑበት ጌታ ዐደራ ሰጧቸው። [24]በጲስድያም ዐል ፈው ወደ ጵንፍልያ መጡ፤ [25]በጴርጌንም ቃሉን ከሰበኩ በኋላ፣ ወደ ኢጣልያ ወረዱ።

[26]ከአጣልያም፣ እስካሁን ላከናወኑት ሥራ፣ ለእግዚአብሔር ጸጋ በዐደራ ወደ ተሰጡባት ከተማ ወደ አንጾኪያ በመርከብ ተመለሱ። [27]እዚያም በደረሱ ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያንን በአንድነት ሰብስበው፣ እግዚአብሔር በእነርሱ አማካይነት ያደረገውን ሁሉ፣ ደግሞም ለአሕዛብ እንዴት የእምነትን በር እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ። [28]በዚያም ከደቀ መዛሙርት ጋር ብዙ ጊዜ ተቀመጡ።

14፥26 ሐሥ11፥19፡23፥ 13፥1፡3 14፥27 ሐሥ15፥4፡12፡ 21፥19፡ 1ቆሮ16፥9፡ 2ቆሮ2፥12፡ ቈላ4፥3፡ ራእ3፥8
14፥28 ሐሥ11፥26

14፥19 **ጳውሎስንም በድንጋይ ከወገሩት፤** ጥንት በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር አገልጋዮቹን ሁል ጊዜ ከጉዳት አይጠብቃቸውም ነበር። ይህ እውነት ከወንጌል ጋር አብሮ ያለና ባሬም ቢሆን በተከበረ የሚፈጸም ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር መንግሥት ሊስፋፋ የሚችለው የእግዚአብሔር አገልጋዮች በሚከፍሉት ከፍተኛ ዋጋ በመሆኑ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በኋላ ይህን ሥቃይ፣ "አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ" (2ቆሮ 11፥25፣ ሐሥ 9፥16 እና ማብ ይመ) በማለት ገልጾታል፤ ወደ ገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ፣ "እኔ የኢየሱስን ምልክት በሥጋዬ ተሸክሜአለሁ" (ገላ 6፥17፣ 2ቆሮ 11፥23 እና በሐ ዋርያው ጳውሎስ መከራ ላይ የተጠቀሰውን ማብ ይመ) ሲልም ምናልባት ይህንኑ ሁኔታ በአእምሮው በማሰብ ሊሆን ይችላል።

14፥22 **በብዙ መከራ፤** ለክርስቶስ ጌትነት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ የሰጡና በመጨረሻም የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚወርሱ፣ በመንገዳቸው "ብዙ መከራ" ሊቀበሉ ይገባል። ለጳት በሆነችው በዚህች ዓለም ውስጥ ሲኖሩ፣ ከኀጢአትና ከሰይጣን ኀይል ጋር መንፈሳዊ ውጊያ ማድረግ ይኖርባቸዋል (ኤፌ 6፥12 ይመ፤ ከሮሜ 8፥17፣ ከ2ተሰ 1፥4-7፣ ከ2ጢሞ 2፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) ለክርስቶስ፣ ለቃሉና ጻድቅ የሆነው መንገዱ ታማኞች የሆኑ በዚህ ዓለም መከራ ሊያጋጥ ማቸው ይችላል (ዮሐ 16፥33)። በዚህ ዓለም ሰላምና ምቾት ሊያጋጥመው የሚችለው ለብ ያለ ወይም አስመሳይ "አማኝ" ብቻ ነው (ከራእ 3፥14-17 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) የአሁኑ ክፉ ዓለምና ሐሰተኛ አማኞች፣ ጌታ ኢየሱስ ዳግም መጥቶ የነሰምን ክፉ ሥርዐት እስኪያስወግድ ድረስ የክርስቶስ መንጌል ተቃዋሚዎች በመሆን ይቈያሉ (ራእ 19-20)። እስከዚያ ድረስ የአማኞች ተስፋ፥ "በሰማይ ተዘጋጅቶ" ይቀመጣል (ቈላ 1፥5)፤ "በመጨረሻውም ዘመን" ይገለጣል (1ጴጥ 1፥5)። ተስፋቹው በምድራዊ ሕይወት ወይም በዓለም አይደለም፤ ነገር ግን ወደ ራሱ ሊመለዳቸው በሚገለጠው በአዳኛቸው ነው (ዮሐ 14፥1-3፣ 1ዮሐ 3፥2-3) አንዲሁም (በገጽ 824 ላይ፣ "*መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

14፥23 **ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው፤** ሽማግሌዎችን (ኤጲስ ቆጶሶችን ወይም እረኞችን) የመሾም ሁኔታ የሚፈጸመው በጸሎትና በጸሎት የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ በመፈለግ ብቻ ሳይሆን ባሕርይን፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን፣ በሰዎች ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነትና የሰዎቹን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በመፈተንም ጭምር ነው (1ጢሞ 3፥1-10)። በሕይወታቸው የሚነቀፉበት ምንም ነገር ከሌለ፣ ለማገልገል ይሾማሉ (በገጽ 1925 ላይ፣ "*የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

የኢየሩሳሌም ጉባኤ

15 አንዳንድ ሰዎችም ከይሁዳ ወደ አንጾኪያ ወረዱና፣ "በሙሴ ሥርዐት መሠረት ካልተገረዛችሁ ልትድኑ አትችሉም" በማለት ወንድሞችን ማስተማር ጀመሩ። [2]ይህም ጳውሎስንና በርናባስን ከእነርሱ ጋር ወደ ከረረ ጠብና ክርክር ውስጥ ከተታቸው። ስለዚህ ጳውሎስና በርናባስ ከሌሎች አንዳንድ ምእምናን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተው ስለዚህ ጕዳይ ሐዋርያት ንና ሽማግሌዎችን እንዲጠይቁ ተወሰነ። [3]ቤተ ክርስቲያኒቱም እግረ መንገዳቸውን በፊንቄና በሰማርያ በኩል እንዲያልፉ ሳከቻቸው፤ እነርሱም በእነዚህ ቦታዎች ለነበ ሩት የአሕዛብን መመለስና ማመን ነገር ቸው፤ ወንድሞችም ሁሉ በዚህ እጅግ ደስ አሳቸው። [4]ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜም፣ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት እንዲሁም ሽማ ግሌዎች ተቀበሏቸው፤ የተሳኩትም ነገሮች ሁሉ ከእነርሱ ጋር ሆኖ የሠራውን ነገሯቸው።

[5]ከፈሪሳውያን ወገን ያመኑት አንዳንዶቹ ተነሥተው በመቆም፣ "አሕዛብ እንዲገረዙና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ማድረግ አስፈላጊ ነው" አሉ።

[6]ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም ይህንኑ ጕዳይ ለማጤን ተሰበሰቡ። [7]ከብዙ ክርክር በኋላ ጴጥሮስ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው፤ "ወንድሞች ሆይ፤ ከጥቂት ጊዜ በፊት በእናንተ መካከል እኔን መርጦ፣ አሕዛብ የወንጌልን ቃል ከእኔ አንደበት ሰምተው እንዲያምኑ ማድረጉን ታውቃላችሁ። [8]ልብን የሚያውቅ አምላክ ለእኛ እንደ ሰጠን ሁሉ፣ ለእነርሱም መንፈስ ቅዱ ስን በመስጠት የተቀበላቸው መሆኑን መሰክረላቸው፤ [9]ልባቸውንም በእምነት በማንጻት በእኛና በእነርሱ መካከል ምንም ልዩነት አላደረገም። [10]እንግዲህ፣ አባቶቻችንም እኛም ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀን በር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን ለምን አሁን እግዚአብሔርን ትፈታተኑታላችሁ? [11]እኛም የዳንነው ልክ እንደ እነርሱ በጌታ በኢየሱስ ጸጋ መሆኑን እናምናለን።"

[12]ጕባኤውም በሙሉ ዝም ብሎ፣ በርናባስና ጳውሎስ እግዚአብሔር በእነርሱ አማካይነት በአሕዛብ መካከል ስላደረጋቸው ታም ራዊ ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች ሲናገሩ ያዳምጣቸው ነበር። [13]እነርሱም ተናግረው ሲጨርሱ፣ ያዕቆብ ተነሥቶ በመቆም እንዲህ አለ፤ "ወንድሞች ሆይ፤ ስሙኝ፤ [14]ስምዐንሐዘ ከአሕዛብ ወገን ለእርሱ የሚሆነውን ሕዝብ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምዖን አስረድቶናል። [15]እንዲህ ተብሎ የተጻፈው የነቢያቱም ቃል ከዚህ ጋር ይስማማል፤

[16] "'ከዚህ በኋላ እመለሳለሁ፤
የፈረሰውን የዳዊትን ቤት
እገነባለሁ።
ፍርስራሹን መልሼ አቆማለሁ፤
እንደ ገናም እሠራዋለሁ፤
[17]ይኸውም የቀሩት ሰዎች ጌታን እንዲ
ፈልጉ፣
ስሜን የተሸከሙ አሕዛብም
እንዲሹኝ ነው፤
እነዚህን ያደረገ ጌታ እንዲህ
ይላል፤'

[14] 15:14 እርሱም ጴጥሮስ ነው።
[16-17] 15:16-18 እንኖንድ ቅጆች ... ለጌታ ከዮንት ጀምሮ የታወቀው የራሱ ሥራ ነው ይላሉ።

15:1 ሥሥ 15:24፤ ሐሥ 11:16፤ 6:14፤ ገላ 2:12፤ 5:2፤3 15:2 ሐሥ 11:30፤ ገላ 2:2 15:3 ሐሥ 11:19፤ 14:27 15:4 ሥሥ 12:1 ሐሥ 14:27፤ 21:19 15:5 ሥሥ 1:3 ማቴ 3:7፤ ሐሥ 5:17 15:7 ሐሥ 10:1-48 15:8 ሐሥ 10:44-47፤ ራእ 2:23 15:9 ሐሥ 10:28,34፤ 43፤ 11:12 15:10 ማቴ 23:4፤ ሐሥ 5:9፤ ገላ 5:1 15:11 ሮሜ 3:24፤ ገላ 2:16፤ ኤፌ 2:5-8 15:12 ዮሐ 4:48፤ ሐሥ 14:27፤ 21:19 15:13 ሐሥ 12:17፤ 21:18፤ 1ቆሮ 15:7፤ ገላ 1:19፤ 2:9,12 15:14 2ጴጥ 1:1 15:17 አሞ 9:11-12

15:8 ልብን የሚያውቅ አምላክ፤ እግዚአብሔር የአሕዛብን ልብ ማለትም የቆርኔሌዎስንና የቤተሰቦቹን ልብ ማወቁ በውስጣቸው ያለውን ለድኅት የሚያቤቃውን እምነት ማየቱን ያመለክታል። እግዚአብሔር የእምነታቸውን ትክክለኛነት የመሰከረላቸው፣ (1) በውስጣቸው ዳግም ልደትን በሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ልባቸውን በማንጻት (ቊጥ 9) እና (2) በኋላም ምልክቱ በልሳን መናገር በሆነው በመንፈስ ቅዱስ በማጥመቅ ነው (10:44-46፣ 11:15-18)።

15:11 በጌታ በኢየሱስ ጸጋ፤ በኢየሩሳሌም ጉባኤ የተነሣው ዋነኛ ጥያቄ ግርዘትና ለሙሴ ሕግ መታዘዝ ለድኅት አስፈላጊ መሆን አለመሆናቸውን በተመለከተ ነው። የጉባኤው አባላት የሰጡት አጠቃላይ ውሳኔ፣ አሕዛብ ድኅትን ያገኙት ምሕረትን በሰጣቸውና አዲስ ፍጥረት ባደረጋቸው በጌታ ኢየሱስ ጸጋ መሆኑን ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኲረት ጽሑፍ ይመ)። ጸጋ ወደ አንድ ሰው የሚመጣው፣ ያ ሰው ንስሓ በመግባት ክርስቶስን ጌታውና አዳኙ አድርጉ ሲያምን ነው (2፥38-39)። ይህ ሰው ለእግዚአብሔር ጸጋ የሚሰጠው ምላሽ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የሚያስችል ኀይል እንዲቀበል ያደርገዋል (ዮሐ 1፥12)።

15:14 ከአሕዛብ ወገን ... ሕዝብ፤ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ያለው ዓላማ ለስሙ የተለየለትን ሕዝብ ከወገኖች ሁሉ መካከል መውሰድ ነው። ከአሁኑ ዓለም ሥርዐት ተለይታ የመጣችው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ራሷን የክርስቶስ ሙሽራ በማድረግ ታዘጋጃለች (ራእ 19፥7-8)።

15:16 የፈረሰውን የዳዊትን ቤት፤ የጌታ ወንድም የነበረው ያዕቆብ በዚህ ጊዜ ለማስረዳት ያቀረበው ሐሳብ የክርስቶስ የቤዛነት ተልእኮ አይሁድንና አሕዛብን ሁለቱንም የሚያጠቃልል መሆኑን ያመለክታል። "የፈረሰውን የዳዊትን ቤት" (አሞ 9፥11-15 እና ግብ ይመ) የሚለው ሐረግ ከእግዚአብሔር ፍርድ ያመለጠውን የእስራኤል ትሩፋ የሚያመለክት ነው። (1) የአሞጽ ትንቢት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያመለክታል፣ (ሀ) በንጢአት የተሞሉትን እስራኤላውያንን እግዚአብሔር ይቀጣል፣ ነገር ግን ሁሉንም አይደለም፣ (ለ) በያዕቆብ ቤት ውስጥ ያሉትን ንጢአተኞች በሙሉ ያጠፋል (አሞ 9፥10)፣ (ሐ) እርሱን የማይፈሩትን አያዙድ ካጠፋ በኋላ እግዚአብሔር "የፈረሰውን የዳዊትን ቤት" ይገነባል (አሞ 9፥11)። (2) የነጻው የአይሁድ ትሩፋ ድኅትን ማግኘት አሕዛብ እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ ያደርጋል (ቊጥ 17)። በሌላ በኩራ ሐዋርያው ጳውሎስ የአይሁድ ትሩፋ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቁ ለአሕዛብ በረከት ይሆናሉ በማለት ሲናገር ተመሳሳይ ነገር ማመልከቱ ነው (ሮሜ 11፥11-15፣25-26)።

[18]እነርሱም ከጥንት ጀምሮ የታወቁ
ናቸው።'
[19]"ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን
አሕዛብ እንጸናስፈሌንታቸው ይህ የእኔ
ብያኔ ነው። [20]ይልቁን በጣዖት ከረከሰ
ነገር፣ ከዝሙት ርኵሰት፣ ታንቆ የሞተ
እን ስላ ሥጋ ከመብላትና ደም ከመመገብ
እንዲርቁ ልንጽፍላቸው ይገባልፀ [21]የሙሴ
ሕግማ ከጥንት ጀምሮ በየሰንበቱ በምኵራብ
ሲነበብና በየከተማው ሲሰበክ ኖሮአልና።"

ላሙኑት አሕዛብ ከጉባኤው የተላከ ደብዳቤ

[22]በዚህ ጊዜ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች
ከመላው ቤተ ክርስቲያን ጋር ሆነው
ከመካከላቸው አንዳንድ ሰዎችን መርጠው፣
ከጳውሎስና ከበርንባስ ጋር ወደ አንጾኪያ
ለመላክ ወሰኑ፤ ከወንድሞችም መካከል
ዋነኛ የነበሩትን በርስያን የተባለውን
ይሁዳንና ሲላስን መረጡ፤ [23]በእነርሱም
እጅ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ላኩ፤

ወንድሞቻችሁ ከሆኑት ከሐዋርያትና
ከሽማግሌዎች፤

ከአሕዛብ ወገን እምነው በአንጾኪያ፣
በሶሪ ያና በኪልቅያ ለሚገኙ ወንድሞች፤

ሰላምታችን ይድረሳችሁ።

[24]አንዳንድ ሰዎች ያለ እኛ ፈቃድ ከእኛ
ዘንድ ወጥተው በንግግራቸው ልባችሁን
እንዳወኩና እንዳናወዟችሁ ሰምተናል።
[25]ስለ ዚህ ጥቂት ሰዎች መርጠን
ከተወዳጆቹ ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር ወደ
እናንተ ለመላክ ሁላችንም ተስማምተናል፤
[26]በርናባስና ጳውሎስም ስለ ጌታችን ስለ
ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሕይወታቸውን
አሳልፈው የሰጡ ናቸው። [27]ስለዚህ እኛ
የጻፍነውን በቃል እንዲያረጋግጡላችሁ፣
እነሠ፤ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል።
[28]ከእነዚህ እስፈላጊ ነገሮች በስተቀር
ሌላ ተጨማሪ ሸክም እንዳ ንጭንባችሁ፣
ለመንፈስ ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ
ታይቶናል፤ ይኸውም፦ [29]ለጣዖት ከተሠዋ
ነገር፣ ከደም፣ ታንቆ ከሞተ እንስሳ ሥጋ
እንዲሁም ከዝሙት ርኵሰት እንድትርቁ
ነው። ከእነዚህ ዐይነት ነገሮች ብትርቁ
ለእናንተ መልካም ነው።

ደኅና ሁኑ።

[30]የተላኩትም ሰዎች ከተሰናበቱ
በኋላ ወደ አንጾኪያም ወረዱ፤ በዚያም
የምእመናኑን ጉባኤ በአንድነት ሰብስበው
ደብዳቤውን ሰጧቸው። [31]ሕዝቡም ካነበቡት
በኋላ አበረታታች በሆነው ቃሉ ደስ ተሰኙ።
[32]ይሁዳና ሲላስም ራሳቸው ነቢያት ስለነበሩ፣ ¶ ሐሥ 21፥9-12
ወንድሞችን ብዙ ንግግር በማድረግ
መከሯቸው፤ አበረታቷቸውም። [33]በዚያም
ጥቂት ጊዜ ከ3ዩ በኋላ፣ ከወንድሞች በሰ ላም
ተሰናብተው ወደ ላኳቸው ሰዎች ተመለሱ።
[34]ሲላስ ግን እዚያው ለመቅረት ወሰነ።
[35]ጳውሎስና በርናባስም ከሌሎች ብዙ ሰዎች
ጋር ሆነው የጌታን ቃል እያስ ተማሩና
እየሰበኩ በአንጾኪያ ተቀመጡ።

ጳውሎስና በርናባስ በሐሳብ ተለያዩ

[36]ጳውሎስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በርናባስን፣
"ተነሣና የጌታን ቃል ወደ ሰበክንባቸው
ከተሞች ሁሉ እንሂድና በዚያ ያሉ ወንድሞ
ችም በምን ሁኔታ እንዳሉ ለማወቅ
እንጐብኛቸው" አለው። [37]በርናባስም
ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ አብሮአቸው
እንዲሄድ ፈለገ፤ [38]ጳውሎስ ግን እርሱን ይዞ
ለመሄድ አልፈለገም፤ ምክንያቱም፣ ቀደም
ሲል ማርቆስ ከእነርሱ ተለይቶ በጵንፍልያ
ስለ ቀረና ወደ ሥራ አብሮአቸው ስላልሄደ
ነበር። [39]እንዲህ የከረረ አለመግባባት
በመካከላቸው ስለ ተፈጠረ እርስ በርስ
ተለያዩ፤ ስለዚህ በርናባስ ማርቆስን ይዞ
በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ። [40]ጳውሎስ ግን
ሲላስን መረጠ፤ ወንድሞችም ለጌታ ጸጋ
ዐደራ ከሰጡት በኋላ ተለይቶአቸው ሄደ፤
[41]አብያተ ክርስቲያናትንም እያበረታታ
በሶርያና በኪልቅያ በኩል ዐለፈ።

15፥37 ሐሥ 12፥12 15፥38 ሐሥ 13፥13 15፥40 ቊ 22፡
ሐሥ 11፥23 15፥41 ቊ 23፣ ሶፎ 2፥2፣ ሐሥ 6፥9፣ 16፥5

15፥18 ኢሳ 45፥21
15፥20 ቊ 29፣
ዘፍ 9፥4፣
ዘሌ 3፥17፣
7፥26፣ 17፥10-13፣ 19፥26፣
ዘዳ 12፥16-23፣
1ቆሮ 8፥7-13፣
10፥7፡8፡14-28፣
ራእ 2፥14፣20
15፥21
ሐሥ 13፥15፣
2ቆሮ 3፥14፡15፣
15፥22
ቊ 27፡32-40፣
ሐሥ 11፥19-30፣
16፥19፡25-29፣
2ቆሮ 1፥19፣
1ተሰ 1፥1፣
2ተሰ 1፥1፣
1ጴጥ 5፥12
15፥23 ቊ 1፡41፣
ሶፎ 2፥2፣
ሐሥ 6፥9፣ 11፥19፣
23፥25፡26፣
ያዕ 1፥1
15፥24 ቊ 1፣
ገላ 1፥7፣ 5፥10
15፥26
ሐሥ 9፥23-25፣
14፥19፣
1ቆሮ 15፥30
15፥27 ቊ 22
15፥28 ሐሥ 5፥32
15፥29 ቊ 20፣
ሐሥ 21፥25

15፥32 ቊ 22፣
ሐሥ 11፥27
15፥33
1ሳሙ 1፥17፣
ማር 5፥34፣
ሶፎ 7፥50፣
ሐሥ 16፥36፣
1ቆሮ 16፥11
15፥35 ሐሥ 8፥4፣
13፥48
15፥36
ሐሥ 13፥4፡13፣
14፡48፡51፣
14፥1፡6፡24፡25

15፥28 ለመንፈስ ቅዱስ ... መልካም መስሎ ታይቶናል፤ የኢየሩሳሌም ጉባኤ ምሪትን የተቀበለው ከመንፈስ ቅዱስ ነበር። ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ቃል ገብቶ ነበር (ዮሐ 16፥13)። በዚኑ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሰዎች ሐሳብ ብቻ የተደገፉ መሆን የለባቸውም፤ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጸም በጸሎት እንዲሁም የእግዚአብሔር ፈቃድ በግልጽ እስኪለይላቸው ድረስ ለቃሉ ራሳቸውን በመስጠት የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መሻት አለባቸው (ከ13፥2-4 ጋር ያነጻጽሩ)። ቤተ ክርስቲያን በእርግዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከሆነች፣ መንፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን መስማት አለባት (ከራእ 2፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

15፥29 እንድትርቁ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ (ቊ 28) አይሁድ ክርስቲያኖች ከአሕዛብ ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው ጋር በእንዴት ዐይነት መንገድ ተስማምተው መኖር ይችሉ ዘንድ ከእንዳንድ ነገሮች መራቅ እንዳለባቸው በዚህ ስፍራ አመልክቶአል። በሌላም በኩል አሕዛብ፣ አይሁድ ቅር ከሚሰኝባቸው ከእንዳንድ ድርጊቶቻቸው መታቀብ ይኖርባቸዋል። የክርስትና ሕይወት ዕድገት እንዴ መለኪያ እንዳንድ ክርስቲያኖች ትክክል ነው ብለው ከሚያስቡት ሌሎቹ ግን ትክክል አይደለም ብለው ከሚያምኑበትና ከሚሰናከሉበት ነገር ሁሉ ለመታቀብ ፈቃደኛ መሆን ነው (ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 8፥1-11 ዋተናገረውን ይመ)።

15፥39 የከረረ አለመግባባት፤ አንዳንድ ጊዜ ጌታን በሚወዱና እርስ በርሳቸውም በሚዋደዱ አማኞች መካከል አለመግባባት ሊከሠት ይችላል። እንዲህ ዐይነቱ ነገር ሊስተካከል ካልቻለ እግዚአብሔር ፈቃዱን ጕዳዩ በሚመለከታቸው ሰዎች ሕይወት እንዲገልጽ አለመስማማትን በፍቅር ማሳየት ይኻላል። በጳውሎስና በበርናባስ መካከል እንደ ሆነው መለያየትን የሚያመጣ የሐሳብ አለመግባባት፣ መራርነትንና ጥላቻን የሚያስከትል መሆን የለበትም። ጳውሎስና በርናባስ ሁለቱም በእርሱ በረከትና ጸጋ የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራታቸውን ቀጠሉ።

ጢሞቴዎስ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተሰማራ

16 ጳውሎስ ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራን ደረሰ። በዚያም እናቱ አይሁዳዊት ሆና በጌታ ያመነች፣ አባቱ ግን የግሪክ ሰው የሆነ፣ ጢሞቴዎስ የተባለ አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ። 2እርሱም በልስጥራንና በኢቆንዮን በነበሩት ወንድሞች ዘንድ መልካም ምስክርነት ነበረው። 3ጳውሎስም ይህ ሰው ከእርሱ ጋር እንዲሄድ ፈለገ፤ ስለዚህ በዚያ አካባቢ በነበሩ አይሁድ ምክንያት ይህ ገረዘው፤ እነዚህ አይሁድ በሙሉ የጢሞቴዎስ አባት የግሪክ ሰው እንደ ሆነ ያውቁ ነበርና። 4እነርሱም ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው በሚያልፉበት ጊዜ፣ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በኢየሩሳሌም ያሳለፉትን ውሳኔ ተቀብለው እንዲጠብቁ ለምእመናኑ ይሰጡ ነበር። 5አብያተ ክርስቲያናትም በእምነት እየበረቱና ዕለት ዕለትም በቍጥር እየጨመሩ ይሄዱ ነበር።

ጳውሎስ ስለ መቄዶንያው ሰው ያየው ራእይ

6ጳውሎስና ባልደረቦቹ ቃሉን በእስያ እንዳይሰብኩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው፣ በፍርግያና በገላትያ አገር ዐልፈው ሄዱ። 7ወደ ሚስያም በተቃረቡ ጊዜ፣ ወደ ቢታኒያ ሊገቡ ሞክረው ነገር ግን የኢየሱስ መንፈስ አልፈቀዳላቸውም፤ 8ስለዚህ በሚስያ በኩል አድርገው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ። 9ጳውሎስም ሌሊት በራእይ አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ፣ "ወደ መቄዶንያ ተሻግረህ ርዳን" ብሎ ሲለምነው አየ። 10ጳውሎስ ይህን ራእይ ካየ በኋላ፣ እግዚአብሔር ወንጌልን እንድንሰብክላቸው ጠርቶናል ብለን በመወሰን ወዲያው ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ፈለግን።

ልድያ በፊልጵስዩስ በጌታ አመነች

11ከጢሮአዳ በመርከብ ተነሥተን በቀጥታ ተጕዘን ወደ ሳሞትራቄ መጣንና በማግስቱም ጕዞአችንን ወደ ናጵሊ ቀጠልን፤ 12ከዚያም የሮማውያን ቅኝና የአካባቢው የመቄዶንያ ግዛት ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ወደ ፊልጵስዩስ ገባን፤ በዚያም አያሌ ቀን ተቀመጥን።

13በሰንበት ቀንም፣ የጸሎት ስፍራ በመፈለግ፣ ከከተማዪቱ በር ወጥተን ወደ አንድ ወንዝ ወረድን፤ በዚያም ተቀምጠን ተሰብስበው ለነበሩት ሴቶች መናገር ጀመርን። 14ከሚያዳምጡትም ሴቶች መካከል ልድያ የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፤ እርሷም ከሸዚአብሔርን የምታመልክና ከትያጥሮን ከተማ የመጣች የቀይ ሐር ነጋዴ ነበረች። ጌታም፣ ጳውሎስ የሚናገረውን በማስተዋል ትሰማ ዘንድ፣ ልቧን ከፈተላት። 15እርሷና ቤተ ሰዎቿ ከተጠመቁ በኋላም፣ "በጌታ ማመኔን በርግጥ ከተረዳችሁልኝ ወደ ቤቴ መጥታችሁ ዋቂት ተቀመጡ" በማለት አቀብቃ ለመነችን።

ጳውሎስና ሲላስ በወህኒ ቤት

16አንድ ቀን ወደ ጸሎት ስፍራ ስንሄድ፣ በዋንጫላ መንፈስ ትንቢት የምትናገር አንዲት የቤት አገልጋይ አገኘችን፤ እርሷም በዚህ የዋንጫላ ሥራዋ ለአሳዳሪዎችዋ ብዙ ገንዘብ ታስገኝላቸው ነበር። 17ይህችው አገልጋይ ጳውሎስንና እኛን እየተከተለች፣ "እነዚህ ሰዎች የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ፣ የልዑል እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው!" በማለት ትረግፕ ነበር። 18ይህንም ብዙ ቀን ደጋገመችው። ጳውሎስ ግን በዚህ እጅግ በመታወኩ ዘወር ብሎ ያን መንፈስ፣ "ከእርሷ እንድትወጣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ" አለው። መንፈሱም በዚያው ቅጽበት ወጣላት።

19አሳዳሪዎቿም የገንዘብ ማግኛ ተስፋቸው ወጥቶ መሄዱን በተረዱ ጊዜ፣ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው እየጐተቱ ባለ ሥልጣኖች ወዳሉበት ወደ ገበያ ቦታ አመጧቸው። 20ገዦቹም ፊት አቅርበዋቸው እንዲህ አሉ፤ "እነዚህ ሰዎች አይሁድ ሆነው ሳሉ፣ ኩሬማችንን አውከዋል፤ 21ደግሞም እኛ ሮማውያን መቀበል ወይም መፈጸም የማይገባንን ልማድ በሕዝቡ መካከል ይነዛሉ።"

22ሕዝቡም ተባብረው በጳውሎስና በሲላስ ላይ ተነሡባቸው፤ ገዦቹም ልብሳቸው ተገፎ በበትር እንዲደበደቡ

16፥1 ሐሥ14፥6፣ 1ቆሮ4፥17፤ 16፥10፣ 2ቆሮ1፥1፥19፣ ፊል1፥1፣ 2፥19፣ 1ጢሞ1፥2፣ 2ጢሞ1፥2፣ 2፥5፣6፣ 16፥2 ቀሩ40፣ ሐሥ1፥16፣ 13፥51፣ 16፥3 ገላ2፥3፣ 16፥4 ሐሥ11፥30፣ 15፥2፣28፣29፣ 16፥5 ሐሥ2፥41፣ 9፥31፣ 15፥41፣ 16፥6 ሐሥ2፥9-10፣ 18፥23፣ ገላ1፥2፣ 3፥1፣ 16፥7 ሮሜ8፥9፣ ገላ4፥6፣ ፊል1፥19፣ 1ጴጥ1፥11፣ 16፥8 ቀሩ1፣ ሐሥ20፥5፣ 2ቆሮ2፥12፣ 2ጢሞ4፥13፣ 16፥9 ሐሥ9፥10፣ 19፥21፥29፣ 20፥1፣3፣ ሮሜ15፥26፣ 1ቆሮ16፥5፣ 1ተሰ1፥7-8፣ 16፥10 ቀሩ10-17፣ 20፥5-15፣ 21፥1-18፣ 27፥1-28፥16፣ ሐሥ14፥7፣ 16፥11 ቀሩ8፣ 16፥12 ቀሩ9፣ ሐሥ20፥6፣ ፊል1፥1፣ 1ተሰ2፥2፣ 16፥13 ሐሥ13፥14፣ 16፥14 ሉቃ24፥45፣ ራእ1፥11፣ 2፥18፣24፣ 16፥15 ሐሥ2፥38፣ 11፥14፣ 16፥16 ቀሩ13፣ ዘፀ18፥11፣ 1ሳሙ28፥3፣7፣ 16፥17 ማር5፥7፣ 16፥18 ማር16፥17፣ 16፥19 ቀሩ16፣ ሐሥ8፥3፣ 15፥22፣ 17፥6፣ 19፥25፣26፣ 27፥30፣ ያዕ2፥6፣ 16፥20 ሐሥ17፥6፣ 16፥21 ቀሩ12፣ አስ 3፥8፣ 16፥22 2ቆሮ11፥25፣ 1ተሰ2፥2፣

16፥5 **አብያተ ክርስቲያናትም** ... **እየበረቱ፤** የአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ሊኖራቸው ስለሚገባው ቅርጽ በ12፥5 ላይ የተጠቀሰውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

16፥6 **ቃሉን** ... **እንዳይሰብኩ መንፈስ ቅዱስ፤** ማንኛውም የወንጌል ሥርጭትና የወንጌል መልእክተኝነት አገልግሎት በተለይም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጠቀሱት የወንጌል ጉዞዎች የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ውጤቶች ናቸው (1፥8፤ 2፥14-41፤ 4፥8-12፥31፤ 8፥26-29፥39-40፤ 10፥19-20፤ 13፥2፤ 16፥6-10፤ 20፥22)። ምሪቱ በትንቢታዊ መገለጥ፣ በውስጥ ግሬት፣ በውጭአዊ ሁኔታዎች ወይም ራእዮች ሊሆን ይችላል (ቍጥ 6-9)። በሐዋርያት ዘመን አማኞች ወንጌልን ላልዳኑት ለማድረስ በመንፈስ ቅዱስ ግሬት ይንቀሳቀሱ ነበር። ወደ አንዱ አቅጣጫ ሲሄዱ መንፈስ ቅዱስ ሲከለክላቸው፣ የጉዞ ዕቅዳቸውን እንዲያረጋግጥላቸው በመንፈስ ቅዱስ በመታመን ወደ ሌላው አቅጣጫ ይሄዱ ነበር።

16፥16 **በጥንቈላ መንፈስ ትንቢት የምትናገር፤** ይህች የቤት አገልጋይ በኢንንት መንፈስ የምትናገረው ቃል እንደ አምላክ ድምፅ ተደርጐ ይቈጠር ነበር፤ ስለዚህ በጥንቈላ የምትሰጠው አገልግሎት እጅግ ተፈላጊ ነበር። በሐዋርያው ጳውሎስ አማካይነት ክርስቶስ ኀይሉን በክፉው ዓለም ላይ ገለጠ (በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣን በኢንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኲረት ጽሑፍ ይመ)።

አዘዙ። 23ክፉኛ ከተደበደቡ በኋላም ወደ ወህኒ ቤት አስገቧቸው፤ የወህኒ ቤት ጠባቂውም ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት። 24እርሱም ይህን የመሰለ ትእዛዝ ከተቀበለ በኋላ፣ ወደ ወህኒ ቤቱ ውስጠኛ ክፍል አስገብቶ እግራቸውን

16፥23 ማቴ 5:25-26 ሉቃ 12:58-59

ከግንድ ጋር አጣብቆ አሰራቸው።

25እኩለ ሌሊት አካባቢ ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩና እየዘመሩ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ነበር፤ ሌሎቹ እስረኞችም ያዳም ጫቸው ነበር። 26ድንገትም የወህኒ ቤቱን መሠረት

16፥25 ሐሥ 15፥22፤ ኤፌ 5፥19 16፥26 ሐሥ 4፥31፤ 5፥19፤ 12፥7፤10

16፥23 16፥24 ሉቃ 21:12 ዮሐ 13:27፤ 33፥11፤ ኤር 20፥2፡3፤ 29፥26


16፥25 መዝ 119፥55፡62፤

ክፉኛ ከተደበደቡ፤ ግርፋትን በተመለከተ የአይሁድ ሕግ፣ "ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው" (2ቆሮ 11፥24) ነበር። በሮማውያን ባሕል መሠረት ፍርዱ የሚወሰነው በዳኛው ሲሆን፣ እጅግ ጭካኔ የተሞላበት ሊሆን ይችላል። ድብደባው የሚካሄደው በአብዛኛው ዕርቃኑን በሆነ ግላ ላይ ነበር።

16፥25 እየጸለዩና እየዘመሩ፤ ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ውርደት ደርሰባቸው ይውቃዩ ነበር፤ እግራቸው ከግንድ ጋር ተጣብቆ ታስሮአል፤ ጀርባቸውም በጅራፍ ተልሎ ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ ሥቃይ ውስጥ እንዳሉ ጸለዩ እንዲሁም የምስጋና መዝሙር ለእግዚአብሔር ዘመሩ (ከማቴ 5፥10-12 ጋር ያነጻጽሩ)። ከእነርሱ የመንጌል ተልእኮ ተመክሮ የሚከተሉትን እንማራለን፣ (1) የአማኞች ደስታ ከውስጥ የሚመነጭ እንጂ በውጭአዊ ሁኔታ የሚወሰን እንዳይደለ እንዲሁም ስደት ሰላማችንንና ደስታችንን ሊያጠፋ እንደማይችል (ያዕ 1፥2-4)፣ (2) የክርስቶስ ጠላቶች አማኝ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነትና ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ሊያጠፉ እንደማይችሉ (ሮሜ 8፥35-39)፣ (3) እጅግ አስከፊ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር በፈቃዱ ውስጥ ላሉትና ስለስሙ መከራ ለሚቀበሉት በቂ አጋን እንደሚሰጥ (ማቴ 5፥10-12፤ 2ቆሮ 12፥9-10)፣ (4) ስለ ክርስቶስ ስም መከራን ለሚቀበሉ "የክብር መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ" እንደሚያርፍባቸው (1ጴጥ 4፥14)።

16፥26 የውሉም እስራት ተፈታ፤ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በአጠቃላይ ታማኝ በሆኑ አማኞች አማካይነት የሚሰራጨውን የክርስቶስን ወንጌል ምንም ነገር ሊያቆመው እንደማይችል ሉቃስ በእጅግ ተናግሮአል። የመሬት መንቀጥቀጥ ሆኖ በፈጸሰበት እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባቱ ጳውሎስና ሲላስ ነጻ ወጡ። የዚህም ውጤት ወንጌል የበለጠ እንዲሰራጭ ማድረጉ ሲሆን፣ በተለይም የወህኒ ቤቱ ጠባቂና ቤተ ሰዎቹ ድነትን ማግኘታቸው ነው።

የጳውሎስ ሁለተኛው የወንጌል ጉዞ



© 1989 The Zondervan Corporation

የሚያናውጥ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ሆነ፤ ወዲያውም የወህኒ ቤቱ በሮች ተከፈቱ፤ የሁሉም እስራት ተፈታ። 27የወህኒ ቤቱ ጠባቂም ከእንቅልፉ ነቅቶ የወህኒ ቤቱ በሮች ተከፍተው ባየ ጊዜ፣ እስረኞቹ ያመለጡ መስሎት ራሱን ለመግደል ሰይፉን መዘዘ። 28ጳውሎስ ግን ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "እኛ ሁላችን እዚሁ ስላለን፣ በራስህ ላይ ክፉ ነገር አታድርስ!" ብሎ ጮኸ።

29የወህኒ ቤቱ ጠባቂም መብራት ለምኖ ወደ ውስጥ ዘሎ ገባ፤ እየተንቀጠቀጠም በጳውሎስና በሲላስ እግር ላይ ወደቀ፤ 30ይዘአቸው ከወጣ በኋላ፣ "እናንት ሰዎች፤ እድን ዘንድ ምን ላድርግ?" አላቸው።

31እነርሱም፣ "በጌታ በኢየሱስ አመን፤ አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ" አሉት። 32ከዚያም ለእርሱና በቤቱ ላሉት ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ተናገሩ። 33የወህኒ ቤት ጠባቂውም ሊሏት በዚያኑ ሰዓት ወስዶ ቍስላቸውን አጠበላቸው፤ ወዲያውም እርሱና ቤተ ሰቡ ሁሉ ተጠመቁ። 34የወህኒ ቤቱ ጠባቂም ወደ ቤቱ ወስዶ ማእድ አቀረበላቸው፤ ከቤተሰቡም ሁሉ ጋር በእግዚአብሔር በማመኑ በደስታ ተሞላ።

35ሲነጋም፣ ገዦቹ፣ "እነዚያን ሰዎች ፈተህ ልቀቃቸው" ብለው መኰንኖቻቸውን ላኩበት። 36የወህኒ ቤት ጠባቂውም፣ "ገዦቹ እንድትፈቱ አዘዋልኤ፤ ስለዚህ ወጥታችሁ በሰላም ሂዱ" ብሎ ለጳውሎስ ነገረው።

37ጳውሎስ ግን፣ "እኛ የሮም ዜጎች ሆነን ሳለን፣ በሕዝብ ፊት ያለ ፍርድ ደብደበው ወደ እስር ቤት ወረወሩን፤ ታዲያ አሁን በስውር ሊያስወጡን ይፈልጋሉ? ይህማ አይሆንም፤ እነርሱ ራሳቸው መጥተው ያስወጡን!" አላቸው።

38መኰንኖቹም ይህንኑ ቃል ለገዦቹ ነገሯቸው፤ እነርሱም ጳውሎስና ሲላስ የሮም ዜጎች መሆናቸውን ሲሰሙ ደነገጡ፤ 39እነርሱ ራሳቸውም መጥተው ይቅርታ ጠይቀው ከወህኒ ቤቱ አወጧቸው፤ ከተማውንም ለቀው እንዲሄዱ ለመኗቸው። 40ጳውሎስና ሲላስ ከእስር ቤቱ ከወጡ በኋላ ወደ ልድያ ቤት ሄዱ፤ በዚያም ወንድሞችን አግኝተው አበረታቷቸው፤ ከዚያም በኋላ ሄዱ።

16፥27 ሐሥ 12፥19
16፥29 ሐሥ 15፥22
16፥30 ሐሥ 2፥37
16፥31 ዮሐ 3፥15፤ ሮሜ 11፥14፤ ሐሥ 11፥14
16፥33 ቍ 25፤ ሐሥ 2፥38
16፥34 ሐሥ 11፥14
16፥36 ቍ 23፥27፤ ሐሥ 15፥33
16፥37 ሐሥ 22፥25-29
16፥38 ሐሥ 22፥29
16፥39 ማቴ 8፥34፤ ሉቃ 8፥37
16፥40 ቍ 2፥14፤ ሐሥ 1፥16
17፥1 ቍ 11፥13፤ ፊል 4፥16፤ 1ተሰ 1፥1፤ 2ተሰ 1፥1፤ 2ጢሞ 4፥10
17፥2 ሐሥ 8፥35፤ 9፥20፤ 13፥14፤ 18፥28
17፥3 ሉቃ 24፥26፡46፤ ሐሥ 2፥24፤ 3፥18፤ 9፥22
17፥4 ሐሥ 15፥22
17፥5 ቍ 13፤ ሮሜ 16፥21፤ 1ተሰ 2፥16
17፥6 ማቴ 24፥14፤ ሐሥ 1፥16፤ 16፥19፡20
17፥7 ሉቃ 23፥2፤ የሐ 19፥12
17፥9 ቍ 5
17፥10 ቍ 13፤ ሐሥ 9፥20፤ 15፥22፤ 20፥4
17፥11 ቍ 1፤ ዘዳ 29፥29፤ ሉቃ 16፥29፤ ዮሐ 5፥39

ጳውሎስና ሲላስ በተሰሎንቄ

17 ጳውሎስና ሲላስም በአንፊጶልና በአጶሎንያ ዐልፈው ወደ ተሰሎንቄ ሄዱ፤ በዚያም የአይሁድ ምኵራብ ነበር፤ 2ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ ምኵራብ ገባ፤ ሦስት ሰንበትም ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ፤ 3ክርስቶስ መከራን መቀበል እንዳለበትና ከሙታንም መነሣት እንደሚገባው እያስረዳ በማ ረጋገጥ፣ "ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው" አላቸው። 4አይሁድም አንዳንዶቹ የሰሙትን በመቀበል ከጳ ውሎስና ከሲላስ ጋር ተባበሩ፤ ደግሞም ቊጥራቸው ብዙ የሆነ ክንዚአሕዜን የሚፈሩ ግሪኮችና አያሌ ዕውቅ ሴቶች የሰሙትን ተቀብለው ከእነርሱ ጋር ተባበሩ።

5አይሁድ ግን ስለቀኑ ወሰላቶችን ከገዚያ ቦታ አሰባሰቡ፤ ሕዝቡንም አነሣሥተው በከተማው ውስጥ ሁከት ፈጠሩ፤ ጳውሎስንና ሲላስንም አምጥተው ሕዝቡ ፊት ለማቅረብ ወደ ኢያሶን ቤት እየተጣደፉ ሄዱ፤ 6ነገር ግን ሊያገኟቸው አልቻሉምና፤ ስለዚህ ኢያሶንንና ሌሎች ወንድሞችን በከተማው ባለ ሥልጣኖች ፊት እየጐተቷቸው እንዲህ እያሉ ጮኹ፤ "እነዚህ ሰዎች ዓለሙን ሁሉ ሲያውኩ 3ይተው፤ አሁን ደግሞ ወደዚህ መጥተዋል፤ 7ኢያሶንም በቤቱ ተቀብለዎአቸዋል፤ እነዚህም ሁሉ፣ 'ኢየሱስ የሚባል ሌላ ንጉሥ አለ' በማለት የቄሳርን ሕግ የሚጥሱ ናቸው።" 8ሕዝቡና የከተማውም ሹማምት ይህን በሰሙ ጊዜ ተሸበሩ፤ 9ከዚያም ኢያሶንንና ሌሎቹን በዋስ ለቀቋቸው።

ጳውሎስና ሲላስ በቤርያ

10ወንድሞችም ወዲያው ጳውሎስንና ሲላ ስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው፤ እነርሱም እዚያ በደረሱ ጊዜ፣ ወደ አይሁድ ምኵራብ ገቡ። 11የቤርያ ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ አስተዋዮች ነበሩ፤ ምክንያቱም ነገሩ እንደዚህ ይሆንን እያሉ መጻ ሕፍትን በየዕለቱ በመመርመር ቃሉን በታ ላት

ሠ 17፥3 ወይም መሲሕ
ኣ 17፥5 ወይም በሕዝብ ጉባኤ ፊት

16፥30 **እድን ዘንድ ምን ላድርግ?** ይህን ጥያቄ ማንም ሊጠይቀው የሚገባ ዋና ጥያቄ ነው። የሐዋርያት ምላሽ "በጌታ በኢየሱስ አመን" የሚል ነው (ቍ. 31)። (1) በጌታ ኢየሱስ ማመን፣ እምነታችንና ውሳኔአችን በክርስቶስ ማንነት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ነው። ይኸውም እርሱ ከንጪአት የተቤዠን፣ ከእርግማን ያዳነንና የሕይወታችን ጌታ እንደ ሆነ በመረዳት ወደ ሕያው ማንነቱ መመለስ ማለት ነው። እንዲሁም እርሱ በአብ የተላከ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና እርሱ ያለውም ሁሉ በሕይወታችን ውስጥ እውነትና ገዥ እንደሆነ ማመን ማለትም ነው። ከዚህም በተጨማሪ እርሱ ጉዚአታችንን ይቅር ያለን፣ ልጆቹ ያደረገንና፣ መንፈስ ቅዱስን የሰጠን እንደ ሆነ እንዲሁም ምንጊዜም ሊረዳን፣ ሊመራን፣ ሊያጽናንና ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊወስደን አብሮን እንዳለ ማመን ማለት ነው።

(2) ለድነት የሚያበቃ እምነት ስለ ክርስቶስ የተነገሩትን እውነቶች ከማመቅ በላይ ነው። ይኸውም ወደ እርሱ እንድንቀርብ፣ በእርሱ እንድንኖር እንዲሁም እርሱ፣ ቃሉና መንፈስ ቅዱስ በዚህ ምድር ሕይወት እየመሩን ወደ አብ ዘላለማዊ ሀልዎት እንደሚወስዱን ርግጠኛ በመሆን በሕይወታችን ስንጪነቅ ራሳችንን ለእርሱ እንድንሰጥ ያደርገናል ማለት ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

17፥11 **መጻሕፍትን በየዕለቱ በመመርመር**፣ በቤርያ ያሉት ሰዎች ድርጊት ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያስረዱ ሰባኪዎችንና አስተማሪዎችን የሚሰሙ ሰዎች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነው። ማንኛውንም

ጕጕት ተቀብለዋል። 12ስለዚህ ከእነ ርሱ ብዙዎቹ አመኑ፤ ደግሞም ከእነርሱ ጋር ሮማዊቲቱ ከፍተኛ የሆነ ዕውቅ የግ ሪክ ሴቶችና ወንዶችም አመኑ።

13በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድም፣ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል በቤርያ ደግሞ መሰበ ኩን ባወቁ ጊዜ፣ ሕዝቡን ለመቀስቀስና ለማነሣሣት ወደዚያ ደግሞ ሄዱ። 14ባዚህ ጊዜ ወንድሞች ጳውሎስን ቶሎ ብለው ወደ ባሕሩ ዳርቻ ሰደዱት፤ ሲላስና ጢሞቴዎስ ግን እዚያው ቀሩ። 15ጳውሎስን የሸኙት ሰዎችም አቴና አደረሱት፤ ከዚያም ሲላስና ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ በፍጥነት እንዲመጡ የሚል ትእዛዝ ተቀብለው ተመለሱ።

ጳውሎስ በአቴና

16ጳውሎስ በአቴና ሆኖ ሲጠባበቃቸው ሳለ፣ ከተማዪቱ በጣዖት የተሞላች መሆኗን በማየት መንፈሱ ተበሳጨበት። 17ስለዚህ በምኵራብ ሆኖ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ግሪክ ጋር፣ ደግሞም በገበያ ስፍራ ዕለት ዕለት ከሚያገኛቸው ሰዎች ጋር ይነጋገር ነበር። 18ከኤፌቆሮስና ከኢስጦኢክ የፍልስፍና ወገን የሆኑትም ወደ እርሱ መጥተው ይከራከሩት ነበር። አንዳንዶቹ፣ "ይህ ለፍላፊ ምን ለማለት ይፈልጋል?" ይሉ ነበር፤ ሌሎች ደግሞ ስለ ኢየሱስና ስለ ትንሣኤው የምሥራች ሲሰብክ ሰምተው፣ "ስለ አዳዲስ ባዕዳን አማልክት የሚናገር ይመስላል" አሉ። 19ይዘውም አርዮስፋጎስ ወደ ተባለው ስፍራ በመውሰድ እንዲህ አሉት፤ "አንተ የምታስተምረው ይህ አዲስ ትምህርት ምን እንደ ሆነ እንድናውቅ ትፈት ዳለህን? 20ደግሞም በጆሮአችን የምታሰማን እንግዳ ነገር ስለ ሆነብን፣ ምን ማለት እንደ ሆነ ማወቅ እንፈልጋለን።" 21የአቴና ሰዎች በሙሉ እንዲሁም በዚያ የሚኖሩ የውጭ ሰዎች ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ስለ አዳዲስ ነገሮች በማውራትና በመስማት እንጂ በሌላ ጕዳይ አልነበረም።

22ስለዚህ ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፤ "የአቴና ሰዎች ሆይ፤ በማናቸውም ረገድ፣ በጣም ሃይማኖተኞች መሆናችሁን አያለሁ፤ 23እየተዘዋወርሁ ሳለሁ፣ የምታመልኳቸውን ነገሮች ስመለከት፣ 'ለማይታወቅ አምላክ' የሚል ጽሑፍ ያለበት አንድ መሠዊያ አይቻለሁና፤ እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እገልጽላችኋለሁ።

24"ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው፤ ስለዚህም እርሱ የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም። 25እርሱ ለሰዎች ሁሉ ሕይወትንና እስትንፋስን እንዲሁም ሌላውንም ነገር ሁሉ የሚሰጥ ስለ ሆነ፣ የሚጐድ ለው ነገር ባለመኖሩ በሰው እጅ አይገለገልም። 26የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመናቸውን ልክና የመኖሪያ ስፍራቸው ንም ዳርቻ ወሰነላቸው። 27ይኸ ውም ሰዎች እግዚአብሔርን ፈልገው ተመራምረው ምናል ባት ያገኙት እንደ ሆነ ብሎ ነው፤ ይህምቢሆንእርሱ ከእያንዳንዳችን የራቀ ሆኖ አይደለም፤ 28የምንኖረውና የምንንቀሳቀ ሰው፣ ያለነውም በእርሱ ነው። ከራሳችሁ ባለቅኔዎችም እንዳንድ እንዳሉት፣ 'እኛም ደግሞ ልጆቹ ነን።'

29"እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን፣ አምላክ በሰው ሙያና ጥበብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ ይመ ስላል ብለን ማሰብ አይገባንም። 30ቀደም ሲል እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን አለማወቅ በትዕግሥት ዐልፎአል፤ አሁን ግን በየቦታው ያሉ ሰዎች ሁሉ ንስሓ እንዲገቡ ያዛል፤ 31በመረጠው ሰው አማካይነት በዓለም ላይ

17፥12 ሐሥ 2፥4
117፥13 ዕብ 4፥12
17፥14
ሐሥ 9፥30፤
15፥22፤ 16፥1
17፥15
ቍጥ 16፥21፤ 22፥
ሐሥ 18፥1፤ 5፥
1ተሰ 3፥1
17፥17 ሐሥ 9፥20
17፥18 ቍጥ 31፡32፥
ሐሥ 4፡2፤ 13፥32
17፥19 ቍጥ 22፥
ማር 1፥27
17፥21 ቍጥ 15

17፥22 ቍጥ 16፡19
17፥23 ዮሐ 4፥22
17፥24 ዘዳ 10፥14፤
1ነገ 8፥27፥
ኢሳ 42፥5፤
66፥1፡2፥
ማቴ 11፥25፥
ሐሥ 7፥48፤
14፥15
17፥25
መዝ 50፥10-12፤
ኢሳ 42፥5
17፥26 ዘዳ 32፥8፤
ኢዮ 12፥23፥
17፥27 ዘዳ 4፥7፤
ኢሳ 55፥6፥
ኤር 23፥23፡24
17፥28 ዘዳ 30፥20፤
ኤፌ 12፥10፤
ኖኅ 5፥23
17፥29
ኢሳ 40፥18-20፤
ሮሜ 1፥23
17፥30 ቍጥ 23፥
ሉቃ 24፥47፥
ሐሥ 14፥16፤
ሮሜ 3፥25፥
ቲቶ 2፥11፡12፥
1ጴጥ 1፥14
17፥31 መዝ 9፥8፤
96፥13፥ 98፥9፥

17፥31 ማቴ 10፥15፥ ሐሥ 2፥24፥ 10፥42

ትርጓሜ ወይም አስተምህሮ በቀላሉ መቀበል ተገቢ አይደለም። ይልቁን ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥንቃቄ በግል መመርመር ያስፈልጋል። «መመርመር» (ግሪክ፡ «አናክሪኖ») የተተረጐመበት የእንግሊዝኛ ቃል «ወደ ላይና ወደ ታች እያደረጉ ማበመር፣ በጥንቃቄና በትክክል ጥናት ማድረግ» ማለት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ስብከት የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችን ከሰሚዎች የተለዩ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት። የማንኛውም አስተምህሮ እውነት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሊመረመር ይገባዋል (ኤፌ. 2፥20 እና ማብ ይመ)።

17፥16 መንፈሱ ተበሳጨበት፤ ባዕድ አምልኮንና ኢግብረገባዊ የሆነን ነገር ሲመለከት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈሱ እጅግ ተቈጣ፤ ልቡም በሐዘን ተመታ (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)፤ ስለ ጠፋትና ድኅነት ስለሚያስፈልጋቸውም ሰዎች መንፈሱ ተናወጠ። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኀጢአትና ኀጢአትም ስለሚያስከትለው አፍራሽ ሥራ የተሰማውን ሀይነት ሐ ዘን ሐዋርያው ጳውሎስም ተሰምቶታል (ዮሐ 11፥33 እና ማብ ይመ)። የክርስቶስ መንፈስ ያላቸው ሁሉ ኀጢአትንና ኢግብረገባዊነትን በሚያዩበት ጊዜ በውስጣቸው የተቀደሰ ቊጣ እንዲሰማቸው የሚያደርግ ባሕርይ ሊኖራቸው ይገባል። ለክርስቶስ ዐሳማ ለመቆምና የጠፋት ድድኑ ዘንድ ለማድረግ በቅዱሳት መጻሕፍት የተወገዘውን፣ እግዚአብሔ ርን ያስቈጣውን እንዲሁም የሰውን ዘር ሁሉ ለዋ ፋት የሚያደርገውን ኀጢአት የሚጠላ መንፈስ ሊኖረን ይገባል (ከ1ቆሮ 6፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥30 ሁሉ ንስሓ እንዲገቡ ያዛል፤ ባለፉት ዘመናት ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እግዚአብሔርን በመሳት የማወቅ መንገድ ከመገለጹ በፊት እግዚአብሔር አብዛኛውን የሰውን ኀጢአትና እርሱን ያለማወቁን ሁኔታ በትዕግሥት ዐልፎአል (ከሮሚ 3፥25 ጋር ያነጻጽሩ)። አሁን ግን ከክርስቶስ መምጣት ጋር የእግዚአብሔር ሙሉና ፍጹም መገለጥ ሰው ሁሉ ታውቆአል፤ ስለዚህ ሁሉም ሰው ንስሓ እንዲገባና ኢየሱስን ጌታውና አዳኙ አድርጎ እንዲያምን ታዞአል። ምንም ዐይነት ልዩነት የለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔ ር የማንንም ኀጢአት ከእንግዲህ በትዕግሥት ዐያልፍም። ሁሉም ኮነኀጢአት ዘወር ማለት ይገባዋል፤ አለበለዚያ ይፈረድበታል። በሌላ አነጋገር ንስሓ መግባት ለድኅነት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው (ማቴ 3፥2 እና ማብ ይመ)።

17፥31 በዓለም ላይ በጽድቅ የሚፈርድበትን፣

በጸድቅ የሚፈርድበትን ቀን ወስ ኖአልና፤ እርሱንም ከሙታን በማስነሣቱ ለሰዎች ሁሉ ይህን አረጋግጠአል።"

32እነርሱም ስለ ሙታን ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ፣ እንዳንዶቹ አፌዙ፤ ሌሎች ግን "ስለዚህ ጒዳይ ከአንተ ዳግመኛ ለመስማት እንፈልጋለን" አሉት። 33በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ከመካከላቸው ወጥቶ ሄደ፤ 34እንዳንድ ሰዎች ግን ጳውሎስ ባለው በመስማማት ተከተሉት፤ አመኑም፤ ከእነዚህም ዲዮናስዮስ የተባለው የአርዮስፋጎስ ፍርድ ቤት አባል፣ ደማሪስ የተባለች ሴትና ሌሎችም ሰዎች ነበሩ።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ

18 ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ተነሥቶ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። 2በዚያም የጳንጦስ ተወላጅ የሆነውን፣ አቂላ የተባለውን አይሁዳዊ አገኘ፤ እርሱም አይሁድ ሁሉ ከሮም እንዲወጡ ቀላውዴዎስ ባዘዘው መሠረት ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር በቅርብ ጊዜ ከኢጣሊያ የመጣ ነበር። ጳውሎስም ሊያያቸው ወደ እነርሱ ሄደ፤ 3እርሱም እንደ እነርሱ ድንኳን ሰፊ ስለ ነበረ፣ ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ በተመሳሳይ ሥራ ላይ ተሰማራ። 4በየሰንበቱም ከአይሁድና ከግሪክ

17፥32 ሥሥ18፥31
17፥34 ሥሥ19፥22
18፥1 ሐሥ17፥15፣ 19፥1፤ 1ቆሮ1፥2፣ 2 ቆሮ1፥1፣23፣ 2ጢሞ4፥20
18፥2 ሥሥ19፥26፣ ሮሜ16፥3፣ ሐሥ11፥28፣ 1ቆሮ16፥19፣ 2ጢሞ4፥19
18፥3 ሐሥ20፥34፣ 1ቆሮ4፥12፣ 1ተሰ2፥9፣ 2ተሰ3፥8
18፥4 ሐሥ9፥20፣ 13፥14
18፥5 ሐሥ9፥22፣ 15፥22፣ 16፥1፣9፣ 17፥14፣15
18፥6 2ሳሙ1፥16፣ ሕዝ3፥17-19፣ 33፥4፣ ማቴ10፥14፣ ሐሥ13፥45፣46፣ 20፥26
18፥7 ሐሥ16፥14
18፥8 ማር5፥22፣ ሐሥ11፥14፣ 1ቆሮ1፥14
18፥9 ማቴ14፥27፣ ሐሥ9፥10
18፥10 ማቴ28፥20
18፥11 ዕዝ4፥12

ሰዎች ጋር በምኵራብ ውስጥ እየተነጋገረ ሊያሳምናቸው ይሞክር ነበር።

5ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ በወረዱ ጊዜ፣ ጳውሎስ በስብከት እየተጋ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለአይሁድ ይመሰክር ነበር። 6ነገር ግን በተቃወሙትና በሰደቡት ጊዜ ልብሱን አራግፎ፣ "ደማችሁ በራሳችሁ ላይ ይሁን! እኔ ንጹሕ ነኝ፤ ከእን ግዲህ ወደ አሕዛብ እሄዳለሁ" አላቸው።

7ከዚያም ወጥቶ ቲቶስ ኢዮስጦስ ወደ ተባለ፣ ከጎረቤቱ ወደ ሚያመልክ ሰው ቤት ሄደ፤ የዚህም ሰው ቤት በምኵራቡ አጠገብ ነበር። 8የምኵራብ አለቃ የነበረው ቀርስጶስ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ፤ ጳውሎስን ሲናገር የሰሙ ብዙ የቆሮንቶስ ሰዎችም አምነው ተጠመቁ።

9ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን እንዲህ አለው፤ "አትፍራ፤ ተናገር፣ ዝምም አትበል፤ 10እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ማንም በአንተ ላይ ተነሥቶ ሊጐዳህ አይችልምና፤ በዚች ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝና"። 11ስለዚህ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማራቸው አንድ ዓመት ተኩል አብሮአቸው ተቀመጠ።

18፥3 **እንደ እነርሱ ድንኳን ሰፊ ስለነበረ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን እየሰበከ ድንኳን ሰፍቶ ይሸጥ ነበር፤ ሲንገዙም ሆነ በአንድ ስፍራ ሲሰነብት ድንኳን በመስፋት ለኑሮው የሚያስፈልገውን ያገኝ ነበር (20፥34፤ 1ተሰ 2፥9፤ 2ተሰ 3፥8)። ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት መሥራት ያለባቸው አገልጋዮች በሁለተኛ ደረጃ አገልጋይነት መቈጠር እንደሌለባቸው ከሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌነት በግልጽ መረዳት ይቻላል። ራስን እየረዱ በትርፍ ጊዜ ማገልገል መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ ምሳሌነትን መከተል ነው።

18፥9 **አትፍራ፤** ይህ ምንባብ የሐዋርያውን የውስጥ ሰብእዊ ስሜቶችን ያንጸባርቃል። በግልጽ እንደሚታየው ጳውሎስንና ወንጌልን የመቃወምና የመጥላት ሁኔታ እየጨመረ በመምጣቱ፣ ሐዋርያው በመፍራት ቆሮንቶስን ለመተው ወይም ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ዝም ለማለት በማሰብ ጥርጥር ውስጥ ሳይገባ አልቀረም (ከ1ቆሮ 2፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። እንደ ኤልያስ (1ነገ 19፥4) እና እንደ ኤርምያስ (ኤር 15፥15) ባሉት ሰዎች ልብ በግልጽ እንደታየው እንደዚህ ዐይነት ተመሳሳይ ስሜቶች አንዳንድ ጊዜ ታማኝ በሆኑ በእግዚአብሔር ሰዎች ልብ ውስጥ ይታያል። በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታዎች እግዚአብሔር ቅዱሳኑን ያገለግላቸዋል፣ ልባቸውንም ያበረታታል። የእግዚአብሔር ሀልዎት ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን የተሰጠው ተስፋ (ሥሥ 10) ከፍርሀት ነጻ ለማውጣት እንዲሁም እግዚአብሔር በሕይወታቸው ያለውን ፈቃድ ይፈጽም ዘንድ አስፈላጊ የሆነውን ዋስትናንና ሰላምን ለመስጠት በቂ ነው (ሥሥ 10-11)።

18፥10 **እኔ ከአንተ ጋር ነኝና፤** ለጳውሎስ የተነገሩት እነዚህ ቃላት በአጠቃላይ የክርስቶስን በማንኛውም ስፍራ የመገኘቱን ሁኔታ የሚያመለክቱ አይደሉም (ከ17፥26-28፤ ከመዝ 139፤ ከኤር 23፥23-24፤ ከአሞ 9፥2-4 ጋር ያነጻጽሩ)። ነገር ግን ሰብዓዊነት ልጆቹ እርሱ ልዩ በሆነ ሁኔታ ቅርብ መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። የክርስቶስ ቅርብነት ማለት እርሱ ፈቃዱን ለመግለጽ፣ ፍቅሩንና ለእኛ ያለውን ኀብረት ለማሳየት በግል በአጠገባችን ይሆናል ማለት ነው። ብሕይወታችን በሚያጋጥመን በማንኛውም ሁኔታ ሊባርከን፣ ሊረዳን፣ ሊጠብቀንና ሊመራን እርሱ በአጠገባችን አለ።

(1) በብሉይ ኪዳን ምንባቦች ውስጥ "ክርስቶስ ከእኛ ጋር" ከሚለው እግዚአብሔር ከታማኞቹ ጋር መሆኑን ከተናገረበት እውነት አንድ ነገር ልንማር እንችላለን። ሙሴ ወደ ግብፅ ለመመለስ በፊፊ ጊዜ እግዚአብሔር፣ "እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" (ዘፀ 3፥12) አለው። ሙሴ ከሞተ በኋላ ኢያሱ አስራኤልን የመምራ ኀላፊነትን በተቀበለ ጊዜ እግዚአብሔር "... ከአንተም ጋር እሆናለሁ፤ ከቶ አልጥልህም፥ አልተውህም" (ኢሱ 1፥5) በማለት ቃል ገባለት። አስራኤላውያንንም እግዚአብሔር፣ "በውሃ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ... ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ" (ኢሳ 43፥2፡5) በማለት አጽናናቸው።

(2) ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት ዐላማ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ቅርብ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደ ሆነ ማቴዎስ በአዲስ ኪዳን ገልጾአል። ስሙም "አማኑኤል" ነው፥ ትርጒሙም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" (ማቴ 1፥23) ማለት ነው። እንደ ገናም ማቴዎስ በወንጌሉ መጨረሻ ላይ "እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ 28፥20) የሚለውን ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጽፎአል። ማርቆስም በወንጌሉ መጨረሻ፣ "ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር" (ማር 16፥20) በማለት ጽፎአል።

12ጋልዮስ የአካይያ ጥሮ በነበረበት ጊዜ አይሁድ ተባብረው በጳውሎስ ላይ ተነሡ፤ ፍርድ ወንበር ፊት አቅርበውትም፤ 13"ይህ ሰው ሕጉ በማይፈቅደው መንገድ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ እያሳሳታቸው ነው" አሉ።

14ጳውሎስ ሊናገር ገና አፉን ሲከፍት፣ ጋልዮስ አይሁድን እንዲህ አላቸው፤ "የአይሁድ ሰዎች ሆይ፤ ያቀረባችሁት ጕዳይ ስለ በመፅ ወይም ስለ ከባድ ወንጀል ቢሆን ኖሮ ላጸምጣችሁ በተገባኝ ነበር፤ 15ነገር ግን ክርክራችሁ ስለ ቃላትና ስለ ስሞች እንዲሁም ስለ ሕጋችሁ በመሆኑ፣ እናንተው ጨርሱት፤ እኔ በእንዲህ ዐይነት ነገር ፈራጅ ለመሆን አልሻም።" 16ስለዚህ ከፍርድ ወንበር ፊት አስወጣቸው። 17በዚህ ጊዜ ሁሉም የምኵራቡን አለቃ ሶስቴንስን ይዘው በፍርድ ቤቱ ፊት ደበደቡት፤ ጋልዮስ ግን ነገሩ ደንታም አልሰጠውም።

ጵርስቅላ፣ አቂላና አጵሎስ

18ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ብዙ ቀን በቆሮንቶስ ተቀመጠ፤ ከዚያም ወንድሞችን ተሰናብቶ ከጵርስቅላና ከአቂላ ጋር በመርከብ ወደ ሶርያ ሄደ። ስእለትም ስለነበረበት ክን ክራኦስ በተባለ ቦታ ራሱን ተላጨ። 19ኤፌሶን በደረሰ ጊዜም ጵርስቅላንና አቂላን እዚያው ተዋቸው፤ እርሱ ራሱ ግን ወደ ምኵራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋር ይነጋገር ነበር። 20ከእነርሱ ጋር እንዲሰነብት በጠየቁትም ጊዜ ፈቃደኛ አልሆነም፤ 21ነገር ግን ሲለ ያቸው፣ "የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ተመልሼ እመጣለሁ" አላቸው፤ ከኤፌሶንም ተነሥቶ በመርከብ ተንዘ። 22ቂሳርያም በደረሰ ጊዜ፣ ወጥቶ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቀረበ፤ ከዚያም ወደ አንጾኪያ ወረደ።

23በአንጾኪያም ጥቂት ጊዜ ከ3የ በኋላ፣ ከዚያ ተነሥቶ በገላትያና በፍርግያ አገሮች ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ደቀ መዛሙርትን ሁሉ አበረታታ።

24በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ተወላጅ የሆነ አጵሎስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ እርሱም የተማረና ቅዱሳት መጻ ሕፍትን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር። 25ይህ ሰው፣ የጌታን መንገድ የተማረ፣ ስለ ኢየሱስም በትክክል የሚናገርና በመንፈስ እየተቃጠለ የሚያስተምር ነበር፤ ይሁን እንጂ እርሱ የሚያውቀው የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ነበር። 26እርሱም በምኵራብ በድፍረት ይናገር ጀመር፤ ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፣ ወደ ቤታቸው ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ይበልጥ አስተካክለው አስረዱት።

27አጵሎስ ወደ አካይያ ለመሄድ በፈለገ ጊዜ፣ ወንድሞች አበረታቱት፤ በዚያ የነበሩት ደቀ መዛሙርትም እንዲቀበሉት ደብዳቤ ጻፉለት። እዚያም በደረሰ ጊዜ ከጸጋው የተነሣ አምነው ለነበሩት ትልቅ ረዳት ሆናቸው፤ 28ከቅዱሳት መጻሕፍት እያመሳከረ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ከአይሁድ ጋር በጽኑ በመከራከር በሕዝብ ፊት ይረታቸው ነበርና።

ጳውሎስ በኤፌሶን

19አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ፣ ጳውሎስ በላይኛው አገር ዐልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ በዚያም አንዳንድ ደቀ

18፥12 ሥ፳7፤ ሐሥ13፥7-8፤12፤ 19፥38፤ ሮሜ15፥26፤ 1ቆሮ16፥15፤ 2ቆሮ9፥2፤ 1ተሰ1፥7-8

18፥15 ሐሥ23፥29፤ 25፥11፡19

18፥17 ሥ፰1፤ 1ቆሮ1፥1

18፥18 ሥ፲2፡27፤ ዘኍ6፥2፡5፡18፤ ሉቃ2፥21፤ ሐሥ18፥16፤ 21፥24፤ ሮሜ16፥1

18፥19 ሥ፲21፡24፤ ሐሥ19፥1፡17፡26፤ 1ቆሮ15፥32፤ 16፥8፤ ኤፌ1፥13፤ 1ጢሞ1፥3፤ ራእ1፥11፤ 2፥1

18፥21 ሮሜ1፥10፤ 15፥32፤ 1ቆሮ4፥19፤ ያዕ4፥15

18፥22 ሐሥ8፥40፤ 11፥19

18፥23 ሐሥ2፥10፤ 14፥22፤ 15፥32፡41፤ 16፥6 18፥24 ሥ፲19፥1፤ 1ቆሮ1፥12፤ 3፥5፡6፡22፤ 4፥6፤ 16፥12፤ ቲቶ3፥13

18፥25 ማር1፥4፤ ሮሜ12፥11

18፥26 ሥ፲2

23በአንጾኪያም ጥቂት ጊዜ ከ3የ በኋላ፣ ከዚያ ተነሥቶ በገላትያና በፍርግያ አገሮች ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ደቀ መዛሙርትን ሁሉ አበረታታ።

24በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ተወላጅ የሆነ አጵሎስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ እርሱም የተማረና ቅዱሳት መጻ ሕፍትን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር። 25ይህ ሰው፣ የጌታን መንገድ የተማረ፣ ስለ ኢየሱስም በትክክል የሚናገርና በመንፈስ እየተቃጠለ የሚያስተምር ነበር፤ ይሁን እንጂ እርሱ የሚያውቀው የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ነበር። 26እርሱም በምኵራብ በድፍረት ይናገር ጀመር፤ ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፣ ወደ ቤታቸው ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ይበልጥ አስተካክለው አስረዱት።

27አጵሎስ ወደ አካይያ ለመሄድ በፈለገ ጊዜ፣ ወንድሞች አበረታቱት፤ በዚያ የነበሩት ደቀ መዛሙርትም እንዲቀበሉት ደብዳቤ ጻፉለት። እዚያም በደረሰ ጊዜ ከጸጋው የተነሣ አምነው ለነበሩት ትልቅ ረዳት ሆናቸው፤ 28ከቅዱሳት መጻሕፍት እያመሳከረ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ከአይሁድ ጋር በጽኑ በመከራከር በሕዝብ ፊት ይረታቸው ነበርና።

ጳውሎስ በኤፌሶን

19አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ፣ ጳውሎስ በላይኛው አገር ዐልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ በዚያም አንዳንድ ደቀ

18፥27 ሥ፲12፡18፤ ሐሥ1፥16 18፥28 ሥ፲5፤ ሐሥ8፥35፤ 9፥22፤ 17፥2 19፥1 ሐሥ18፥1፡19፡24

ግ18፥25 ወይም በትልቅ ግለት

18፥23 ደቀ መዛሙርትን ሁሉ አበረታታ፤ የጳውሎስ ሦስተኛው የወንጌል ጕዞ በዚህ ይጀምራል (18፥23—21፥15)። የዚህም ጕዞ ዕላማ በመጀመሪያውና (ምዕ 13—14) በሁለተኛው (15፥36—18፥22) የወንጌል ጕዞዎቹ የተመሠረቱትን አብያተ ክርስቲያናት ለመጐብኘት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል የማረካቸውን ሰዎች መልሶ የማይጎበኝበት ጊዜ አልነበረም። አዳዲስ አማኞችን መከታተልና በክርስቶስ መንገድም እንዲበረታቱ ማድረግ ዋነኛ ትኵረቱ ነበር። አዳዲስ አማኞች ሁሉ ወዲያውኑ በብርቱ ክርስቲያኖች ሊያዙ፣ ሊጸለይላቸው፣ የክርስትናን መንገድ እንዲማሩ እንዲሁም ለአምልኮ፣ ለጸሎት፣ ለጋራ ጥቅም የመንፈስ ቅዱስ መገለጫዎችን ለመቀበልና ለቃሉ አገልግሎት ከሌሎች አማኞች ጋር እንዲተባበሩ ሊደረግ ይገባል (2፥42፤ ማቴ 28፥19-20፤ 1ቆሮ 12፥7-11፤ 14)።

18፥25 እርሱ የሚያውቀው የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ነበር፤ አጵሎስ በዚህ ጊዜ ስለ ወንጌል ያለው መረዳት ውሱን ነበር። የዮሐንስን ጥምቀት ተጠምቆ ኢየሱስ የተሰቀለና ከሞት የተነሣ መሲሕ መሆኑን በመቀበል በእርሱ አመነ። ያላወቀው ነገር ቢኖር ኢየሱስ ራሱ አሁን አማኞችን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እያጠመቀ መሆኑን ነው። የኤፌሶን ደቀ መዛሙርትም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ (19፥2፡6)።

19፥1 ኤፌሶን ... እንዳንድ ደቀ መዛሙርት፤ በኤፌሶን የነበሩት እነዚህ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ክርስቲያኖች ነበሩ ወይስ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት? ሁለቱንም ሊሆኑ ይችላሉ። (1) አንዳንዶች በዚህ ስፍራ ደቀ መዛሙርት ተብለው የተጠቀሱት ክርስቲያኖች እንደ ነበሩ ያምናሉ፤ (ሀ) ምክንያቱም ሉቃስ "ደቀ መዛሙርት" ብሎ ይጠራቸዋል፤ ይህም ቃል እርሱ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖችን የሚጠራበት ስም ነበር። ሉቃስ እነዚህን ሰዎች የክርስቶስ ሳይሆን፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ብቻ እንደ ነበሩ ቢያምን ኖሮ በግልጽ በተናገረ ነበር፤ (ለ) ጳውሎስ ስለ እነርሱ የተናገረው አማኞች እንደ ሆኑ በመቀሩጠር ነበር (ቍ. 2)። "ማመን" የሚለው ግስ ቀጥተኛ ተሳቢ ሳይኖረው ቤአዋርያት ሥራ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል። በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ ቃሉ የተጠቀሰበት ወሳድ የሚያመለክተው ለድነት የሚያስፈልገው ነገር በክርስቶስ ማመን ብቻ እንደ ሆነ ነው (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

(2) ሌሎች ደግሞ የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት አሁንም መሲሑን እየተጠባበቁ ያሉ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ነበሩ ብለው ያምናሉ። ስለ ኢየሱስ ከጳውሎስ ከሰሙ በኋላ በትንቢት ቃል መሠረት ሲጠበቅ የነበረው ክርስቶስ እርሱ እንደ ሆነ አምነው በመንፈስ ቅዱስ ጸግሞ ተወለዱ (ቍ. 4-5)።

መዛ ሙርትን አግኝቶ፣ 2"ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" አላቸው።
እነርሱም፣ "አልተቀበልንም፤ እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ አልሰማንም" አሉት።
3ጳውሎስም፣ "ታዲያ፣ ብምን ተጠመቃችሁ?" አላቸው።
እነርሱም፣ "የዮሐንስን ጥምቀት" አሉት።
4ጳውሎስም፣ "የዮሐንስ ጥምቀትማ የንስሓ ጥምቀት ነበር፤ የሐንስም ራሱ ለሰዎች ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ እንዲያምኑ ተናግሮአል" አላቸው።
5እነርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ። 6ጳውሎስም እጁን በላያቸው በጫነ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በልሳኖች ቋንቋዎች፣ ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ። 7ሰዎቹም በአጠቃላይ ዐሥራ

19፥2 ዮሐ20፥22
19፥4 ማር1፥4፣ ዮሐ1፥7
19፥5 ሐሥ2፥38
19፥6 ማር16፥17፣ ሐሥ6፥6፣ 10፥44

19፥8 ማቴ3፥2፣ ሐሥ9፥20፣ 28፥23
19፥9 ቁ.23:30፣ ሐሥ9፥2—11፥26፣ 14፥4
19፥10 ቁ.22:26:27፣ ሐሥ2፥9፣ 13፥48፣ 20፥31
19፥11 ሐሥ8፥13
19፥12 ሐሥ5፥15

ሁለት ያህል ነበሩ።
8ጳውሎስም ወደ ምኵራብ እየገባ፣ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያሳመ ናቸው ሦስት ወር ሙሉ ምንም ሳይፈራ ፊት ለፊት ይናገር ነበር። 9እንዳንዶቹ ግን ግትር በመሆን፣ ለማመን ፈቃደኞች አልነበሩም፤ የጌታንም መንገድ በገሃድ ያዋሳሉ ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ ተቶአቸው ሄደ፤ ደቀ መዛሙርትንም ለብቻቸው ወስዶ በጢራኖስ የትምህርት አዳራሽ ውስጥ በየዕለቱ ያነጋግራቸው ነበር። 10ይህን ማድረጉንም ሁለት ዓመት ስለ ቀጠለ፣ በእስያ አውራጃ ይኖሩ የነበሩት የኢይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት ቻሉ።
11እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ እጅግ የሚያስደንቅ ታምራትን ያደርግ ነበር፤ 12መሐረብ ወይም ሰውነቱን የነካ ጨርቅ

ᵃ19፥2 ወይም ካመናችሁ በኋላ
ᵇ19፥6 ወይም ልሳን

(3) የትኛውም ዐይነት ሁኔታ ይሁን በመንፈስ ቅዱስ የመሞላታቸው ጉዳይ እውን የሆነው ካመኑ፣ ከተጠመቁና እጅ ከተጫነላቸው በኋላ ነበር (ቁ. 5-6)።

19፥2 **መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?** ሐዋርያው ጳውሎስ ያቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ የሚከተሉትን እውነቶች ልብ በሉ፥ (1) የጳውሎስ ጥያቄ በጥብቅ የሚያመለክተው የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት ገና በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ ነገር ግን የተሰወጡና እውነተኛ ክርስቲያኖች የነበሩ እንደ ሆነ ነው።

(2) በዚህ ስፍራ የጳውሎስ ጥያቄ የሚያመለክተው በጸጋዉ ቄስጢ ዕለት እንደ ሆነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነይልን ለመቀበልና አነልግሎትን ለመፈጸም አስፈላጊ መሆኑን ነው (ከ1፥8፣ 2፥4 ጋር ያንጻጽሩ)። ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞች ሁሉ ካመኑበት፣ ከተሰወጡበትና ዳግም ልደትን ከተቀበሉበት ቅጽበት ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው መኖር መጀመሩን (ሮሜ 8፥9) በግልጽ ስለሚያውቅ፣ በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው በአማን ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሀልዎት የሚመለከት አይደለም።

(3) ሐዋርያው ጳውሎስ የጠየቀው ጥያቄ ቃል በቃል ሲተረጉም "ስታምኑ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" የሚል ይሆናል። "ስታምኑ" (ግሪክ፡ "ፒስተውሳንቴስ"፣ "ፒስቲስ" ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው) የሚለው ቃል ከዋናው ግስ በፊት ድርጊቱ መፈጸሙን የሚያመለክት በዝ አንቀጽ ነው። ስለዚህ፣ "ካመናችሁ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" በማለት ልንተረጉመው እንችላለን። ይህ ትርጉም ሙሉ በሙሉ ከወዱ ጋር ይስማማል፡ ለኤፌሶን አማኞችም የሆነው በተክክል እንደዚህ ነው፣ (ሀ) ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ከመኖናኝታቸው በፊት በክርስቶስ አምነው ነበር (ቁ. 1-2)፣ (ለ) ከዚያም ስለ ክርስቶስና ስለ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ የነገራቸውን ሁሉ ሰምተው አመኑ (ቁ. 4)፣ (ሐ) የኤፌሶን አማኞች በክርስቶስ የነበራቸው እምነት እውነተኛና በቂ እንደ ሆነ ጳውሎስ ስለ ተረዳ በጌታ ኢየሱስ ስም አጠመቃቸው (ቁ. 5)፣ (መ) ካመኑና ከተጠመቁ በኋላ ብቻ ነው ጳውሎስ እጁን የጫነባቸው፣ ከዚያም "መንፈስ ቅዱስም ወረደባቸው" (ቁ. 6)። ስለዚህ በክርስቶስ ባመኑበትና መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ በሙሉ ነይሱ በወረደበት ጊዜ መካከል የተወሰነ የጊዜ ክፍተት ነበር።

በዚህ ስፍራ የጳውሎስ ጥያቄ በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቅ በፊት በክርስቶስ "ማመን" እንደሚቻል ማሰቡን ያመለክታል። ይህ ምንባብ አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን ሳይቀበል ክርስቲያን ሊሆን እንደሚችል በመሳኘነት የሚያሳይ ነው (በገጽ 1664 ላይ፣ "*በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

19፥2 **አልሰማንም፤** የኤፌሶን አማኞች ሙልስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጨርሶ አለመስማታቸውን አያመለክትም። ስለ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የተሰጠውን ትምህርት በሚገባ ያውቃሉ። እንዲሁም ክርስቶስ ሊያመጣው ስላለው ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መጥምቁ ዮሐንስ ያስተሳለፈውን መልእክት በእርግጥ ሰምተዋል (ሉቃ 3፥16)። ነገር ግን ገና ያልሰሙት ነገር ቢኖር መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ላይ የመውረዱ ጉዳይ ነው።

19፥5 **ተጠመቁ፤** እነዚህ ሀዥራ ሁለቱ የኤፌሶን ሰዎች (ቁ. 7) በጌታ በኢየሱስ ስም የውሃ ጥምቀት ሥርዐት መፈጸማቸው ለድኅነት የሚያበቃ እምነት እንደነበራቸውና በመንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱ እንደ ሆኑ ይመሰክራል (ቁ. 6)።

19፥6 **መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤** ይህ ሁኔታ እውን የሆነው የመጀመሪያው ጸንጤ ቄስጢ ከተከሠተ ከሃያ አምስት ዓመት በኋላ ነበር (2፥4)፡ ቢሆንም እነዚህ ዐሥራ ሁለት ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን የተቀበለበት መንገድ ሉቃስ ዥቀረበው ከተለመደው መንገድ ጋር ተመሳሳይ ነበር (8፥5-24 ማብ ይመ)።

(1) በኢየሱስ አምነው በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ተወልደዋል (ያዕፈውን ማብ ይመ)።

(2) በውሃ ከተጠመቁ በኋላ (ቁ. 5) ሐዋርያው ጳውሎስ እጁን ጫነባቸው፣ በመንፈስ ቅዱስም ተጠመቁ።

(3) መንፈስ ቅዱስ ሲወርድባቸው በልሳን ተናገሩ፣ ትንቢትም ተናገሩ። ሉቃስ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በእምነት ብቻ በተስፋ ቀሚጠባበቁት ነገር እንደ ሆነ አልገለጸም፣ ነገር ግን እየታወቀና በተጨባጭ ሊገለጽ በሚችል መልኩ በግልጥ የሚለማመዱት ከሥተት እንደ ሆነ አሳይቶአል። በልሳን መናገር ውጭአዊና የሚታይ ሚሪጋግጫ ከመሆኑ የተነሣ መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ በኢየሱስ ተከታዮች ላይ እንደወረደ ያመለክታል (በገጽ 1669 ላይ፣ "*በልሳን መናገር*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

እንኳ ወደ ሕመምተኞች ሲወሰዱ በሽታ
ቸው ይለታቸው ነበርና ርኩሳን መናፍስትም
ይወጡ ነበር።
13 እየዞሩ አጋንንትን የሚወጡ
ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶቹ፣ "ጳውሎስ
በሚሰብከው በኢየሱስ ስም እንድትወጡ
አዛችኋለሁ" እያሉ የጌታን የኢየሱስን
ስም ርኩሳን መናፍስት ባደዟቸው ሰዎች
ላይ ለመጥራት ሞከሩ። 14የእይሁዳዊው
የካህናቱ አለቃ የስኬዋ ሰባት ወንዶች
ልጆችም ይህ ነጉ ያደርጉ ነበር። 15ርኩስ
መንፈሱም፣ "ኢየሱስን ዐውቀዋለሁ፤
ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ፤ አናንተ ግን
እነማን ናችሁ?" አላቸው። 16ከዚያም ርኩስ
መንፈስ ያደረበት ሰው ዘልሎ ያዛቸው፤
በረታባቸውም፤ እጅግ ስላየለባቸውም
ቤቱን ጥለው ዕራቁታቸውን ሸሹ።
17ይህም በኤፌሶን በሚኖሩትና
በአይሁድና ብግሪክ ሰዎች ሁሉ ዘንድ
በታወቀ ጊዜ፣ ሁሉም ፍርሀት ያዛቸው፤
በዚህም የጌታ የኢየሱስ ስም ተከበረ።
18ካመኑትም ሰዎች ብዙዎቹ እየቀረቡ ክፉ
ሥራቸውን በግልጥ ተናዘዙ፤ 19ሲጠነቁሉ
ከነበሩትም መካከል ብዙዎች መጽሐፋቸውን
ሰብስበው በማምጣት በሕዝብ ፊት አቃጠሉ፤
ዋጋቸውም ሲሰላ አምሳ ሺህ ብር ያህል ሆኖ
ተገኘ። 20በዚህ ሁኔታ የጌታ ቃል በኀይል
እያደገና እያሸነፈ ሄደ።
21ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ጳውሎስ በመ
ቄዶንያና በአካይያ በኩል ዐልፎ ወደ ኢየ
ሩሳሌም ለመሄድ በመንፈሱ ወሰነ፣ "እዚያ
ከደረስሁ በኋላ ሮምን ደግሞ ማየት አለብኝ"
አለ። 22ከረዳቶቹም ሁለቱን፣ ጢሞቴዎስንና
ኤርስጦንን፣ ወደ መቄዶንያ ልኮ እርሱ ራሱ
ግን በእስያ አውራጃ ጥቂት ቀን ተቀመጠ።

በኤፌሶን የተነሣው ሁከት

23በዚህ ጊዜ፣ ስለ ጌታ መንገድ ታላቅ
ሁከት ተፈጠረ። 24ድሜጥሮስ የተባለ አንድ
የብር አንጥረኛ የአርጤምስን ቤተ መቅደስ
ምስሎች ከብር ቀጥቅጦ እየሠራ ለሠራተኞቹ
የሚያስገኘው ገቢ ቀላል አልነበረም።
25አርሱም እነዚህን ሠራተኞችና በተመሳሳይ
ሙያ የሚተዳደሩትን ሌሎቹን ሰዎች
በአንድነት ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፤ "ሰዎች
ሆይ፤ ይህ ሥራ ጥሩ ገቢ እንደሚያስገኝልን
ታውቃላችሁ። 26ይህ ጳውሎስ የተባለ ሰው
በኤፌሶን ብቻ ሳይሆን፣ በመላው የእስያ
አውራጃ የሚገኙትን በርካታ ሕዝብ
እያሳመነ እንዳሳታቸው ይኸው የምታዩትና
የምትሰሙት ነገር ነው፤ በሰው እጅ የተሠሩ
አማልክት በፍጹም አማልክት እንዳልሆኑ
ይናገራልና። 27የዘህ የሥራችን መልካም
ስም ከመጒደፉም በላይ፣ መላው እስያና
ዓለም የሚያመልኳት የታላቂ አር ጢምስ
ቤተ መቅደስም ዋጋ ቢስ ይሆናልእ ደግሞም
ገናናው ክብሯ ይዋረዳል።"
28ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ክፉኛ
ተ3ጥተሙ፣ "የኤፌሶና አርጤምስ ታላቅ
ናት!" እያሉ ይጮኹ ጀመር። 29ወዲያ ውም
በከተማው ሁሉ ሁከት ተነሣ፤ ሕዝ በም
አንድ ላይ በማበር የመቄዶንያ ተወ ላጅ
የሆኑትንና ከጳውሎስ ጋር ይጓዙ የነ በሩትን
ጓደኞቹን፣ ጋይዮስንና አርስጥሮኮ ስን
ይዘው ወደ ፊጨዋታ ማሳያው ስፍራ እየሮጡ
ገቡ። 30ጳውሎስም ወጥቶ ሕዝቡ ፊት
ለመቅረብ ፈልጎ ነበር፤ ደቀ መዛሙርት ግን
ከለከሉት። 31ከእውራጃው ባለ ሥልጣኖች
እንዳንድ ወዳጆቹ እንኳ፣ ጳው ሎስ ወደ
ጨዋታ ማሳያው ስፍራ ደፍሮ እንዳይገባ
ሰው ልከው ለመኑት።
32ጉባኤውም ተዘባብቶ፣ አንዱ አንድ
ነገር ሲናገር ሌላውም ሌላ እየተናገረ ይጯ
ጯኽ ነበር፤ አብዛኛውም ሰው ለምን እዚያ
እንደ ተሰበሰበ እንኳ አያውቅም ነበር።
33አይሁድም እስክንድሮስን ከሕዝቡ መካ
ከል ገፍተው ወደ ፊት ባወጡት ጊዜ፤
አን ዳንዶቹ እንዲናገርላቸው ፊጯኽ፤
እርሱም ሊከራከርላቸው ፈልጎ ዝም እንዲሉ
በምልክት ጠቀሳቸው። 34ነገር ግን እርሱ
አይሁዳዊ መሆኑን ባወቁ ጊዜ ሁሉም
በአንድ ድምፅ፣ "የኤፌሶና አርጤምስ ታላቅ
ናት" እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል ፊጯኽ።
35የከተማዪቱም ዋና ጸሐፊ ሕዝቡን ጸጥ
አሰኝቶ እንዲህ አለ፤ "የኤፌሶን ሰዎች
ሆይ፤ የታላቂ የአርጤምስ ቤተ መቅደስና

19:13 ማቴ12:27፣ ማር9:38
19:17 ሐሥ5:5፣11፤ 18:19
19:20 ሐሥ6:7፣ 12:24፣ 13:48
19:21 ሐሥ16:9፤ 18:12፣ 20:16:22፣ 21:4፣12:15፣ ሮሜ15:24፣25:28
19:22 ፍኖ10:26:27፣ ሐሥ2:9፣ 13:5፣ 16:1፣ ሮሜ16:23፣ 2ጢሞ4:20
19:23 ሐሥ9:2
19:25 ሐሥ16:16፣19:20
19:26 ዘዳ4:28፣ መዝ115:4፣ ኢሳ44:10-20፣ ኤር10:3-5፣ ሐሥ2:9፣ 17:29፣ 18:19፣ 1ቆሮ8:4፣ ራእ9:20
19:28
19:29 ሐሥ18:19
19:29 ሐሥ16:9፣ 20:4፣ 27:2፣ ሮሜ16:23፣ 1ቆሮ1:14፣ ቈላ4:10፣ ፊሞ24
19:30 ሐሥ11:26
19:32 ሐሥ21:34
19:33 ሐሥ12:17
19:34 ዘፀ20:4፣
19:35 ሐሥ18:19

19:12 መሐረብ ወይም ... ጨርቅ፣ በኤፌሶን የነበረው ጳውሎስ አገልግሎት ለየት ካለ የፈውስ ታምራትና ከእጋንጉት ነጻ የማውጣት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ነበር። ይኸውም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሙንገድ ሰውነቱን በነካ መሐረብ ወይም ጨርቅ ዩሚከናወን ነበር (በጽንኳን መስፋት ሥራው ውስጥ ሳቡን የሚወርግበት መሐረብ ወይም ጨርቅ ሊሆን ይችላል)። እነዚህ ጨርቆች የታመሙትን ሰዎች ሲነኩ ክፉ መንፈስ የሚርቅ ሲሆን፣ ብሹተኛውም ፈውስን ያገኝ ነበር (ከ5፥15፡ ከማር 5፥27 ጋር ያነጻጽሩ)። ዛሬ ማንኛውም አገልጋይ መሐረቡን ለፈውስ አገልግሎት በማስተዋወቅ የገንዘብ ድጋፉን ለማግኘት ጥረት ቢያደርግ፣ በሐዋርያው ጳውሎስ አስተሳሰብና መንፈስ መሠረት አገልግሎቱን እየፈጸመ አይደለም። ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች ፕንዘብ የማግኛ መንገድ በማድረግ አልተጠቀመባቸውምና። በእርሱ ላይ የነበረውን ፈውስንና ነጻነት የሚሰጠውን ጎይል በግል አማንቶ በእጁ ሊነካቸው ወደማይችል ሰዎች ለማሰራጨትና ብዙ ሰዎች እንዲፈወሱ ለማድረግ ሲል ቀጠቅሞአል።

19:19 ሲጠነቀሉ ከነበሩትም፣ እያለ የጥንቁላ መጻሕፍት በሕዝብ ፊት መቃጠላቸው አዳዲስ አማኞች ፈጥነው ከመተት ሥራ መውጣት እንደሚገባቸው መማራቸውን ያመለክታል። ጥንቁላ፣ አስማት፣ መተት፣ መናፍስት ጠሪነትና ሌሎች ደጅግሞት ሥራዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ከክርስትና እምነት ጋር የማይስማሙ ሰይጣናዊ ድርጊቶች ናቸው። አንድ ሰው ከመናፍስት ጋር እየተገናኘ ወይም ሙታንን እየጠራ የክርስቶስ እውነተኛ አማኝ ሊሆን አይችልም፤ አማዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን ነገር ሁሉ እንደ አስጸያፊ ድርጊት በመቁጠር ያወግዘዋል (ዘዳ፡ 18፥9-13 ማለ ይመ)። አንድ ሰው በመተትና በመናፍስት ጠሪነት ተግባር ውስጥ ቢዘፈቅ ለሰይጣናዊ ጎይል ተጽእኖና በአጋንንት

ከሰማይ የወረደው ምስሏ ጠባቂ የኤፌሶን ከተማ ሕዝብ መሆኑን የማያውቅ ማን አለ? 36ስለዚህ፣ ይህ ሐቅ የማይካድ እንደ መሆኑ መጠን፣ ልትረጋጉና አንዳች ነገር በጥድፊያ ከመፈጸም ልትጠበቡ ይገባችኋል። 37እነዚህን ሰዎች ቤተ መቅደስን ሳይዘርፉ ወይም እምላካችን በሆነችው ላይ የስድብ ቃል ሳይሰነዝሩ ይዛችሁ እዚህ ድረስ እንዲያው አምጥታችኋቸዋል። 38እንግዲህ፣ ድሜጥሮስና ከእርሱ ጋር ያሉት አንጥረኞች በማንም ላይ አቤቱታ ካላቸው፣ ፍርድ ቤቱ ክፍት ነው፤ ዳኞችም አሉ፤ ክስ ማቅረብ ይችላሉ። 39ከዚህ ሌላ ልታቀርቡ የፈለጋ ችሁት ነገር ካለ፣ በሕጋዊ ጉባኤ ይታያል። 40አሰበለዚያ ዛሬ ስለ ሆነው ነገር፣ በሁከት አነሣሽነት እንዳንከሰስ ያሠጋናል፤ አጥጋቢ ምክንያት ስለሌለንም፣ ስለ ሁከቱ ብንጠየ ቅበት መልስ መስጠት እንችልም።" 41ይህን ከተናገረ በኋላም ጉባኤው እንዲበተን አደረገ።

ወደ መቄዶንያና ወደ ግሪክ ጒዞ

20 ሁከቱም እንደ በረደ፣ ጳውሎስ ደቀ መዛሙርትን አስጠርቶ መከራቸውን፤ ተሰናበቶአቸውም ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ተነሣ። 2ባለፈባቸውም ስፍራዎች ሕዝቡን በብዙ ቃል እየመከረ ግሪክ አገር ደረሰ፤ 3በዚያም ሦስት ወር ተቀመጠ። ወደ ሶርያ በመርከብ ለመሄድ ሲዘጋጅም አይሁድ አሢረውበት ስለ ነበር፣ በመቄዶንያ በኩል አድርጎ ለመመለስ ወሰነ። 4የጰይሮስ ልጅ የቤርያው ሱሲጳጥ ሮስ፣ የተሰሎንቄዎቹ አርስጥሮኮስና ሲኮን ዱስ፣ የደርቤኑ ጋይዮስ፣ ከእስያ አውራጃ የመጡት ቲኪቆስና ጥሮፊሞስ፣ እንዲሁም ጢሞቴዎስ አብረውት ሄዱ። 5እነዚህም ሰዎች ወደ ፊት ቀድመውን በጥሮአዳ ጠበቁን። 6እኛ ግን፣ የቂጣ በዓል ካለፈ በኋላ፣ ከፊልጵስዩስ በመርከብ ተነሣን፤ ከአ ምስት ቀንም በኋላ ከሌሎቹ ጋር በጥሮአዳ ተገናኘንን፤ በዚያም ሰባት ቀን ተቀመጥን።

አውጤኪስ በጥሮአዳ ከሞት ተነሣ

7በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመ ቍረስ ተሰብስበን ሳለን፣ ጳውሎስ በማግስቱ ለመሄድ ስላሰበ፣ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፤ ንግግሩንም እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ አራዘመ። 8በተሰበሰብንበትም ሰገነት ላይ ብዙ መብራት ነበር። 9አውጤኪስ የተባለ አንድ ጕበዝም በመስኮት ላይ ተቀምጦ ነበር፤ ጳውሎስ ንግግሩን ባስረዘመ ጊዜ፣ እንቅልፍ እንቅልፍ አለውና ጭልጥ ብሎ ተኛ፤ ከሦስተኛውም ፎቅ ቍልቍል ወደቀ፤ ሞቶም አነሡት። 10ጳውሎስም ወርዶ በላዩ ተጋድሞ ዐቀፈውና፣ "ሕይወቱ በውስጡ ስላለች ሁከት አትፍጠሩ" አላቸው። 11ተመልሶም እንደ ገና ወደ ፎቁ ወጣ፤ እንጀ ራውንም ቈርሶ በላ፤ እስኪነጋም ድረስ ብዙ ከተናገረ በኋላ ተነሥቶ ሄደ። 12ሰዎችም ያን ጕበዝ ሕያው ሆኖ ወሰዱትና፤ በዚህም እጅግ ተጽናኑ።

ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች ተሰናበተ

13እኛ ግን ጳውሎስን ለመቀበል ቀድመን ወደ መርከቡ ሄድንና፤ ከዚያም በመርከብ ወደ አሶን ተጓዝን፤ ይህን ያደረግነውም ጳውሎስ በየብስ በእግሩ ሊሄድ ስላሰበ ነበር። 14በአሶን ከተገናኘንንም በኋላ፣ ተቀብለነው አብረን በመርከብ ወደ ሚጢሊኒ ሄድን። 15በማግስቱም በመርከብ ተጕዘን ከኪዩ ደሴት ተይዩ ደረስን። በሚቀጥለውም ቀን ወደ ሳሞን ተሻገርንና፤ በማግስቱም ሚሊ ጢን ደረስን። 16ጳውሎስም በእስያ አውራጃ ብዙ መቈየት ስላልፈለገ፣ ወደ ኤፌሶን ሳይ ገባ ዐልፎ ለመሄድ ወሰነ፤ ቢቻል በዓለ ኀምሳን በኢየሩሳሌም ለመዋል ቸኵሎ ነበርና።

17ከሚሊጢንም ወደ ኤፌሶን ሰው ልከ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሽማግሌዎች አስጠራ፤ 18በመጡም ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "ወደ እስያ አውራጃ ከገባሁባት ከመጀመሪያዋ ዕለት አንሥቶ ዘወትር ከእናንተ ጋር እን ዴት እንደኖርሁ ታውቃላችሁ። 19ምንም እንኳ ከአይሁድ ሤራ የተነሣ መከራ ቢያደርሱብኝም፣ ጌታን በታላቅ ትሕትናና በእንባ ከማገልገል አልተቈጠብሁም፤ 20በአ ደባባይም ሆነ ከቤት ቤት በመዘዋወር፣ እናንተን ከማስተማርና ይጠቅማችኋል ብዬ ያሰብሁትን ከመስበክ ወደ ኋላ አላልሁም።

19፥37 ሮሜ2፥22
19፥38 ቍጥ24፥ ሐሥ13፥7፤8፥12፤ 18፥12
20፥1 ሐሥ11፥26፤ 16፥9
20፥3 ቍጥ19፥ ሉቃ2፥2፤ ሐሥ9፥23፤24፥ 14፥5፤ 16፥9፥ 23፥12፤15፥30፥ 25፥3፥ 2ቆሮ11፥26፤ 1ጢሞ2፥16
20፥4 ሐሥ2፥9፤ 16፥1፤ 17፥1፥ 19፥29፤ 21፥29፥ ኤፌ6፥21፤ ቈላ4፥7፥ 2ጢሞ4፥20፥ ቲቶ3፥12
20፥5 ሐሥ16፥8፥10
20፥6 ሐሥ16፥8፥12
20፥7 ማቴ14፥19፥ 1ቆሮ16፥2፥ ራእ1፥10
20፥8 ሐሥ1፥13፤ 9፥37
20፥10 1ነገ17፥21፥ 2ነገ4፥34፥ ማቴ9፥23፡24
20፥11 ቍጥ7፥ ማቴ14፥19
20፥15 ቍጥ17፥ 2ጢሞ4፥20
20፥16 ሐሥ2፥1፡9፥ 18፥19፥ 19፥21
20፥17 ቍጥ15፥ ሐሥ11፥30
20፥18 ሐሥ2፥9፤ 18፥19-21፥ 19፥1-41
20፥19 ቍጥ3፥ መዝ6፥6
20፥20 ቍጥ27፥ መዝ40፥10፥ ኤር26፥2፤ 42፥4

እስራት ለመያዝ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል።

20፥19 በእንባ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታን ያገለግል የነበረው "በእንባ" እንደ ሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች ገልጾአል (ቍጥ 31፣ 2ቆሮ 2፥4፣ ፊል 3፥18)። ስኤፌሶን ሽማግሌዎች በጻፈው በዚህ መልእክቱ (ቍጥ 17-38)፣ ለሦስት ዓመት ያህል በየዕለቱ በእንባ እያስጠነቀቃቸው እንደነበር ተናግሮአል (ቍጥ 31)። የሐዋርያው ጳውሎስ እንባ ከደካማነቱ የተነሣ የሆነ አይደለም፤ ነገር ግን የሰው ዘር የመዋፋቱ ጕዳይ፣ ዮነጢአት ክፋት፣ የወንጌልን መልእክት የሚያጣምሙ ሰዎች ሁኔታና ጌታን መቃወማቸው የመሳሰሉት ከባድና አሳዛኝ ችግሮች የሐዋርያው ጳውሎስን ስብከት ሁል ጊዜ ከእንባ ጋር የተያያዘ እንዲሆን አድርገውታል (ከማር 9፥24፤ ከሉቃ 19፥41 ጋር ያነጻጽሩ)።

20፥20 ያሰብሁትን ከመስበክ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሰሚዎቹ ድኑት ይጠቅማል ወይም ያስፈጋል ብሎ የሚያስበውን ሁሉ ይሰብክ ነበር። የወንጌል አገልጋዮች የእግዚአብሔርን የወንጌል እውነት ሁሉ ለመስበክ ታማኞች መሆን አለባቸው። የሕዝብን ፍላጐት ለማሟላት ወይም ሕዝብ የሚቀመውን ለሚድረግ ወይም የራሳቸውን ክብር ለማንጸባረቅ ጥረት ማድረግ የለባቸውም። የተግሣጽን ቃል የሚናገሩ፣ ማስረጃ የሌለውን ተፈጥሮአዊ ክፋትን የሚያጠፋ አስተምህሮን የሚያስተምሩ ወይም ነጢአትኖ ተፈጥሮን የሚቃወሙን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነን ስብከት የሚሰብኩ ቢሆኑም እንኳ፣ ታማኝ ሰባኪዎች ለመንጋው ጤ ንነት ሲሉ እውነትን ሁሉ ማስተላለፍ ይገባቸዋል (ለምሳሌ ገላ 1፥6-10፣ 2ጢሞ 4፥1-5)።

21በንስሓ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና
በጌታችን በኢየሱስ እንዲያምኑ፣
ለአይሁ ድም ለግሪክ ሰዎችም አጥብቄ
መስክሬላቸዋለሁ።
22"አሁንም እዚያ ስደርስ የሚደርስብኝን
ባላውቅም፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሩሳሌም
እንድሄድ ግድ እያለኝ ነው። 23ነገር ግን
በምሄድባቸው ከተሞች ሁሉ አስራትና
መከራ እንደሚጠብቀኝ መንፈስ ቅዱስ
ያመሰክርልኛል። 24ይሁን እንጂ ከጌታ ከኢየ
ሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዬንና የእግዚአብሔርን
የጸጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን
ብፈጽም፣ ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እን
ደማይ[3]ጠር እንደ ከንቱ ነገር ናት።
25"አሁንም ቢሆን፣ በመካከላችሁ ተዘዋ
ውራ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሰበክሁላ
ችሁ፣ እናንተ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲያ
ፊቴን እንደማታዩ በውቃለሁ። 26ስለዚህ
ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኔን በዚች ቀን
እመሰክርላችኋለሁ፤ 27የእግዚአብሔርን ፈቃድ
ሁሉ ለእናንተ ከመግለጽ የተቈጠብሁበት

20፥21
ሐሥ2፥38፤
18፥5፣ 24፥24፤
26፥18፤
ኤፌ1፥15፤
ቈላ2፥5፣ ፊሞ1፥5
20፥22 ቍ16
20፥23
ሐሥ8፥29፤
9፥16፣ 21፥4
20፥24
ሐሥ11፥23፣
21፥13፤
2ቆሮ4፥1፤
ገላ1፥1
2ጢሞ4፥7፤
ቲቶ1፥3
20፥25 ቍ38፤
ማቴ4፥23
20፥26 ሕዝ3፥17-
19፤ ሐሥ18፥6
20፥27 ቍ20

20፥28 ቍ29፤
ዮሐ21፥16፤
ሮሜ3፥25፤
1ቆሮ6፥20፤

ጊዜ የለምና። 28ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ
ኤጲስቆጶሳት" አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ
መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ፤ በገዛ ደሙ የዋጃትን
የእግዚአብሔር[a] ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ። 29እኔ
ከሄድሁ በኋላ፣ ነጣቂ ተኵላዎች መጥተው
በመካከላችሁ ሰርገው እንደሚገቡና
ለመንጋውም እንደማይራሩ ዐውቃለሁ።
30ከእናንተው መካከል እንኳ የራሳቸውን
ደቀ መዛሙርት ለማፍራት እውነትን
የሚያጣምሙ ይነሣሉ። 31ስለዚህ ተጠንቀቁ፤
ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊትና ቀን ምንም
ያህል ሳላቋርጥ በእንባ እያንጻንጻችሁን
እንደ መከርኋችሁ አስታውሱ።
32"አሁንም ለእግዚአብሔር፣ እንዲሁም
ሊያ ንጻችሁና በቅዱሳኑ ሁሉ መካከል
ርስት ሊያወርሳችሁ ለሚችለው ለጸጋው

20፥28 10፥32፤ 1ጢሞ3፥1 20፥29 ቍ28፤ ማቴ7፥15፤
ሕዝ34፥5 20፥30 ሐሥ11፥26 20፥31 ቍ19፤
ሐሥ19፥10 20፥32 ማቴ25፥34፤ ሐሥ14፥23፤ 26፥18፤
ኤፌ1፥14፤ ቈላ1፥12፤ 3፥24፤ ዕብ9፥15፤ 1ጴጥ1፥4

[a]20፥28 ወይም ተመልካች ጠባቂዎች
[b]20፥28 ብዙ የጥንት ቅጆች ጌታን

20፥22 **መንፈስ ቅዱስ ... ግድ እያለኝ ነው፤** ሐዋርያው ጳውሎስ መከራና ሥቃይ እንደሚጠብቀው ዐውቆአል (ቍ. 23)፤ ይሁን እንጂ ወደዚያ መሄዱ የሚያስከትለው ሕይወት ይሁን ሞት መሆኑን ሳያውቅ መንገዱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ (21፥4 እና ግብ ይመ)።

20፥23 **መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል፤** ይህ መከራና አስር እንደሚጠብቀው የሚገልጸው የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ወደ ሐዋርያው ጳውሎስ የመጣው ምናልባት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ነቢያት ወይም በትንቢት አገልግሎት ነው (ከ1ቆሮ 12፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

20፥24 **ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እንደማይቈጠር እንደ ከንቱ ነገር ናት፤** የሐዋርያው ጳውሎስ ዋና ትኩረት የራሱን ሕይወት በምድር የማቈየት ጒዳይ አይደለም፤ ለእርሱ ትልቁ ቁም ነገር ከእግዚአብሔር የተጠራበትን አገልግሎት የመፈጸሙ ጒዳይ ነበር። ሩጫው የትም ቦታ የሚፈጸም ቢሆን፣ የራሱን ሕይወት እንኳ መሥዋዕት እንዲያደርግ ቢጠይቅ፣ "እንደ ወትሮው ሁሉ ዛሬም በሕይወትም ሆነ በሞት ክርስቶስ በሥጋዬ እንዲከበር ሙሉ ድፍረት ይኖረኛል" (ፊል 1፥20) ብሎ በመጸለይ በደስታ ይፈጽመዋል። ለጸዋርያው ጳውሎስ ለክርስቶስ የሆነ ሕይወትና አገልግሎት፣ አንድ ሰው በናዝሬት ታማኝነት ወደ ጌታው እንደሚሮጠው ወይነት ውድድር ይቈጠራል (ከ13፥25፤ ከ1ቆሮ 9፥24፤ ከ2ጢሞ 4፥7፤ ከዕብ 12፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

20፥26 **ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኔን፤** "ደም" የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ ደም ከማፍሰስ ጋር ተያይዞ ይገለጻል፤ ይኸውም ሌላው ሰው እንዲሞት የሚያደርግ ወንጀል ነው (ከ5፥28፤ ዘጸ 23፥35፤ 27፥25 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) በዚህ ስፍራ አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ቢሞትና ለዘላለም ጥፋት የተጸረገ ቢሆን የወንጌል ቃል ሰሰው ሁሉ ስለ ሰበከ ጳውሎስ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ማለት ነው፤ (2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎታቸው ሥር ላሉት ሰዎች መጥፋት ተጠያቂ እንዲሆኑ ከፈሰጉ አስቀድመው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁሉ ሊነግሩአቸው ይገባል።

20፥28 ... **መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ፤** የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በተመለከተ የተጠቀሰውን ይህን የተለመደ ምንባብ በይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1716 ላይ፣ "**የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

20፥29 **ነጣቂ ተኵላዎች፤** የራስን መንግሥት ለመመሥረት ባላቸው የእድገት ምኞት በመነሣሣት ወይም በገንዘብ፣ በሥልጣንና በዝና ፍቅር በመጠ መድ (ለምሳሌ 1ጢሞ 1፥6-7፤ 2ጢሞ 1፥15፤ 4፥3-4፤ 3ዮሐ 1፥9)፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አስመሳዮች የአዲስ ኪዳንን መሠረታዊ ወንጌል በሚከተሉት መንገዶች ያጣምማሉ፡ (1) መሠረታዊ እውነቶችን በመካድ ወይም ችል በማለት፣ (2) የሰውን ሐሳብ፣ ፍልስፍናና የሥነ ልቦና ዕውቀት በመጨመር፣ (3) በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ልምምድ ላይ "የአዲሱን ዘመን" ትምህርቶችን ወይም የሙተና የመናፍስት አሠራርን በመደባለቅ፣ (4) የእግዚአብሔርን ጻድቅ ሕጎች ከሚጻረሩ ኢግዝረባዊ የሕይወት ዘይቤ ዎች ጋር ለመስማማት በመሞከር (1ጢሞ 4፥1 ፊሕ 2—3 እንዲሁም በገጽ 1519 ላይ፣ "**የሐሰት ትምህርት አስቀማሪዎች**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵሬት ጽሑፍ ይመ) እንዲህ ዐይነት ተኵላዎች በመንጋው ውስጥ ገብተው በኢፌሶን የክርሙን ሐ ዋርያዊ አስተምህሮና ልምምድ መሸርሸራቸው በ1ጢሞ 1፥3-4፣18-19፤ 4፥1-3፤ 2ጢሞ 1፥15፤ 2፥17-18፤ 3፥1-8 ላይ በግልጽ ተቀምጠአል። በሐዋርያት ትምህርት ላይ የተነሣው የተቃውሞ ጅማሬ በእስያ አውራጃ በናዝሬት አየተስፋፋ መሄዱን መልክታት ምጋቤ ይገልጣሉ።

20፥31 **ስለዚህ ተጠንቀቁ፤** የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ምንጊዜም በጉባኤያቸው መካከል ለክርስቶስና ለሐዋርያት መሠረታዊ ትምህርት በታማኝነት ሪሳቸውን ያልሰጡትን ሁል ጊዜ በጥንቃቄ ሊከታተሉ ይገባል። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር ሕዝባቸውን በጥንቃቄና በእንባ በመምራት መንጋቸውን ስለሚመጣባቸው አደጋ በማስገንዘብ እንዲሁም የሚያናውጥ መሠረት ወደሆነው ወደ ክርስቶስና ወደቃሉ በማመልከት ቀንና ሌሊት ማስጠንቀቅን ማቋረጥ የለባቸውም።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው

ሐሥ 20፥28 "ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ኤጲስ ቆጶሳት አድርጎ በሳዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ፤ በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ።"

ማንኛዋም ቤተ ክርስቲያን የተሾሙ መሪዎች ከሌሏት ሥራዋን በአግባቡ መፈጸም አትችልም። ስለዚህ ሐዋርያት ሥራ 14፥23 እንደሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ በ1ጢሞ 3፥1-7 እና በቲቶ 1፥5-9 (በገጽ 1925 ላይ፣ "የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) በስጠው የመንፈሳዊ ብቃት መለኪያዎች መሠረት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚሹ አማኞች ጸምና ጸሎት ግለሰቦች ለሽማግሌነት ወይም ለቤተ ክርስቲያን መሪነት ይሾማሉ። ስለዚህ በመጨረሻ አንድን ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው። ለኤፌሶን ሽማግሌዎች የቀረበው የሐዋርያው ጳውሎስ የመጨረሻ መልእክት (ሐሥ 20፥18-35) በምትታየው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሽማግሌዎች እንደ መሪ እንዲት መሥራት እንደሚገባቸው የሚያሳይ የታወቀ መንፈሳዊ መርሕ የቀረበበት ምንባብ ነው። በአዲስ ኪዳን የመሪዎች ኀላፊነት የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ኀላፊነት የመሰለ ነው (በገጽ 1009 ላይ፣ "ነብይ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

እምነትን ማሳደግ፣ (1) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዋና ተግባሮች ከሆኑት አንዱ በጎችን የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር መመገብ ነው። ምንጊዜም ሊያስተውሉት የሚገባቸው ነገር የተሰጣቸው መንጋ እግዚአብሔር በልጁ ክቡር ደም ለራሱ የገዛው ሕዝብ ከመሆን ሌላ ምንም እንዳይደለ ነው (ከሐሥ 20፥28፣ ከ1ቆሮ 6፥20፤ ከ1ጴጥ 1፥19፣ 2፥9፤ ከራእ 5፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) በሐዋርያት ሥራ 20፥19-27 ጳውሎስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ እረኛ ሆኖ እንዳገለገለ በዝርዝር ጽፎአል፣ የኤፌሶንንም ክርስቲያኖች በታማኝነት በማስጠንቀቅና በማስተማር የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሙሉ አስታውቆአቸዋል (ሐሥ 20፥27)። ከዚህም የተነሣ "ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኔን" (20፥26 ማብ ይመ) ብሎ ለመናገር ችሎአል። ዛሬም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሙሉ ለቤተ ክርስቲያኖቻቸው ማስታወቅ ይኖርባቸዋል። ቃሉን መስበክ፣ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ በመሆን በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር ሃሳትና፣ መገሠጽና ማበረታታት ይገባቸዋል (2ጢሞ 4፥2) እንዲሁም ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የሚሹና ሰዎች መስማት የሚፈልጉትን ሁሉ የሚናገሩ ሰባኪዎች መሆን የለባቸውም (2ጢሞ 4፥3)።

እምነትን መጠበቅ፣ እውነተኛ እረኛ በጎቹን ከጠላቶቻቸው በትጋት መጠበቅ አለበት። ሐዋርያው ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን የወደፊት እንቅስቃሴ ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ላይ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ከውስጥ በማስነሣት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ውጪ የሆኑ መላይ ነገሮችን፣ ዓለማዊ ሐሳቦችን፣ የጣዖት አምልኮና የሰው አመለካከቶችን ከውጭ ቀስ በቀስ እንደሚያስገባ ያውቃል፣ እነዚህ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እምነት ያጠፋሉ (በገጽ 1519 ላይ፣ "የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ሐሰተኞች "ነጣቂ ተኵላዎች" ይላቸዋል፣ ይህን ሲልም እነርሱ ብርቱዎች፣ በቀላሉ የማይያዙ፣ ጨካኞችና አደገኞች ናቸው ማለቱ ነው (20፥29 ማብ ይመ፣ ከማቴ 10፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። እንዲህ ዐይነት ግለሰቦች ሰዎችን ከክርስቶስ ትምህርት በማራቅ ወደ ራሳቸውና ወደ ተጣመመው ወንጌላቸው ይስባሉ። የጳውሎስ አስቸኳይ ልመና (ሐሥ 20፥25-31) መሪዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅና ለአዲስ ኪዳን እምነት መሠረታዊ የሆነውን መገለጥ የሚያጣምሙትን መቃወም እንደሚገባቸው የሚያሳይ ታላቅ ግዴታን ያስቀምጣል።

(1) እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኀብረት ጸንተው ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ የሆኑትን ብቻ የምታካትት ናት (በገጽ 1941 ላይ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር አስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በሚገባ

የመጠበቅን ታላቅ ኀላፊነት በተመለከተ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃልና የሐዋርያትን ምስክርነት የሚጻረር ትምህርት በማስተማር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነትን የሚያጣምሙትን (ሐሥ 20፥30) መገሠጽ፣ በፍቅር መናገር (ኤፌ 4፥15) እና አጥብቀው መቃወም (2ጢሞ 4፥1-4፣ ቲቶ 1፥9-11) ይገባቸዋል።

(2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እረኞችና የአስተዳደር ኀላፊዎች በሥራቸው ላሉት ሰዎች ሁሉ ሕይወት የሚገባውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ጌታ ኢየሱስ ኀላፊነትን እንደ ሰጣቸው ልብ ሊሉ ይገባል (ሐሥ 20፥26-27 ይመ፣ ከሕዝ 3፥20-21 ጋር ያነጻጽሩ)። መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን አጠቃላይ ዕላማ (ሐሥ 20፥27) በተለይም መንጋውን ከመጠበቅ (ሐሥ 20፥28) አኳያ ተገቢውን ነገር ከመናገርና ከመፈጸም ወደኋላ ቢሉ፣ "ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆን" አይችሉም (20፥26 ግብ ይመ፣ ከሕዝ 34፥1-10 ጋር ያነጻጽሩ)። ይልቁን መንጋውን ቃሉን ከሚያጻኽሙና ከሚያጣምሙ ሐሰተኞች ሊጠብቁት ስላልቻሉ በጠፉት ሰዎች ሁሉ ደም ምክንያት መሪዎች በእግዚአብሔር ተጠያቂዎች ይሆናሉ (2ጢሞ 1፥14 ግብ ይመ፣ ራእ 2፥2 ግብ)።

(3) ሥነ መለኮታዊውን፣ አስተምህሮአዊውንና ግብረገባዊውን ጉዳይ በተመለከተ መገሠጽ በተለይ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ኀላፊነት ለተሰጣቸው መሪዎች እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የአስተምህሮና የሕይወት ንጽሕና እንዲሁም የቅዱሳት መጻሕፍት ሕጸጽ አልባነት በክሌጆች፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፣ በሥነ መለኮት ሰሚናሪዎች፣ በአሳታሚ ድርጅቶችና በቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ መዋቅሮች ውስጥ በጥንቃቄ ሊጠበቅ ይገባል (2ጢሞ 1፥13-14)።

(4) በዚህ ስፍራ ያለው ዋና ጉዳይ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "ለአጋው ቃል" (ሐሥ 20፥32) ብሎ ለጠራው መለኰታዊ ቅዱስ መጽሐፍ ነው ሊኖረው የሚገባውን አስተሳሰብ በተመለከተ ነው። የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች፣ ሐሰተኛ እረኞችና ሐሰተኛ መሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን ተቃውሞ አዘል በሆነ ትምህርታቸውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መርሐአቸው ለማዳከም ሙከራ ሊያደርጉ ይችላሉ። የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉ ሥልጣን በመቃወም፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት እውነተኛነትና ተአማኒነት ይክዳሉ (ሐሥ 20፥28-31፣ ገላ 1፥6 እና ግብ፣ 1ጢሞ 4፥1፣ 2ጢሞ 3፥8 ይመ)።

(5) መንፈስ ቅዱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ንጽሕና ያለውን የውስጥ መቃጠል የማታስተላልፍ ቤተ ክርስቲያን (ሐሥ 20፥18-35) ለእውነት ሊኖራት የሚገባውን ጽኑ ዐቋም ሳትይዝ ትቀራለች፣ የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣን የሚንቁትንም ለመገሠጽ ዐቅም ታጣለች፣ በተለመደው የአዲስ ኪዳን አሠራር መሠረትም ቤተ ክርስቲያን መሆኗ ይቀራል (ሐሥ 12፥5) እና ግብ እንዲሁም (በገጽ 1453 ላይ፣ "ቤተ ክርስቲያን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ከአዲስ ኪዳን ዕላማ፣ ኀይልና ሕይወት ሸርተት ማለት ክርስቶስና ሐዋርያት ከገለጡት ከመሠረታዊው እውነት ፈቀቅ ብሎ በክሕደት ጉራ ውስጥ ራሳን መፈረጂ ነው።

ቃል ዐደራ አሰጣችኋለሁ። 33የማንንም ብር
ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤
34እነዚህ እጆቼ ለእኔና ከኔ ጋር ላሉት በሚያ
ስፈልገን ነገር እንዳገለገሉ እናንተ ራሳችሁ
ታውቃላችሁ። 35በጒልበታችን ደክመን
ችግረኞችን መርዳት እንዳለብን ባደ
ረግሁት ሁሉ አሳይቻችኋለሁ፤ 'ከሚቀበል
ይልቅ የሚሰጥ ብሁዕ ነው' ያለውን የጌታ

20+33
1ሳሙ 12+3፤
1ቆሮ 9+12፤
2ቆሮ 2+17፤ 7+2፤
11+9፤ 12+14-
17፤ 1ተሰ 2+5
20+34 ሐሥ 18+3


20+36
ሉቃ 22+41፤
ሐሥ 9+40፤ 21+5

የኢየሱስን ቃል እናስታውስ።"
36ይህን ካለ በኋላ፣ ተንበርክኮ ከሁሉም
ጋር ጸለየ። 37ሁሉም እጅግ አለቀሱ፤
ጳውሎስንም አንጥቱን ዐቅፈው ሳሙት፤
38ከሁሉም በላይ ልባቸውን የነካው፣
ከእንግዲህ ወዲህ ፊቱን እንደማያዩ
የተናገራቸው ቃል ነበር። ከዚያም እስከ
መርከቡ ድረስ ሸኙት።

20+37 ሉቃ 15+20 20+38 ቍ 25፤ ሐሥ 21+5

20+33 የማንንም ብር ... አልተመኘሁም፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ሁሉ የሚሆን ምሳሌነትን ትቶ ዐልፎአል። በወንጌል አገልግሎት ባለጠጋ ለመሆን ወይም ሀብትን ለማከማቸት ጥረት አላደረገም (ከ2ቆሮ 12+14 ጋር ያንጻጽሩ)። ጳውሎስ ሀብትን ለማከማቸት ብዙ ዕድሎች ነበሩት። ምክንያቱም በብዙ አማኞች ዘንድ ታላቅ ተቀባይነትን ያገኘ ሐዋርያና አያሌ የፈውስ ታምራትን የሠራ አገልጋይ ነበር። ከዚህም በላይ የጥንት ክርስቲያኖች በችግር ላይ ላሉት ወገኖች እርዳታቸውን ይሰጡ ቸው ዘንድ ታዋቂ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘባቸውንም ሆነ ንብረታቸውን የመሰዉት ልምድ ነበራቸው (4+34-35+37)። ሐዋርያው መንፈሳዊ ስጦታዎቹን፣ ሥልጣኑንና የአማኞችን ለጋሽነት ለራሱ ጥቅም ቢያውለው ኖሮ የተቀማጠለ ኑሮ ይኖር ነበር። ይህን ያላደረገው ከመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ለወንጌል ካለው ፍቅር የተነሣ ነው (ከ1ቆሮ 9+4-18፣ ከ2ቆሮ 11+7-12፣ 12+14-18፣ ከ1ተሰ 2+5-6 ጋር ያነጻጽሩ)።

20+37 ሁሉም እጅግ አለቀሱ፣ በዚህ የመለያየት ሁኔታ የታየው ነገር የክርስቲያናዊ ኅብረትና ፍቅር ምሳሌ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች ያገለገለው በራስ ወዳድነት ላይ በተመሠረተ ፍቅርና እንክብካቤ ሳይሆን፣ ደስታቸውንና ሐዘናቸውን በመካፈል እንዲሁም በእንባና መከራን በመቀበል (ቍ. 19+31) ነበር። ፊቱን እንደ ገና እንደማያዩ የተናገራቸውን ቃል ሰሰሙ (ቍ. 38) ልባቸው በመንካቱ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ። በሐዋርያው ጳውሎስና በእነዚህ ሽማግሌዎች መካከል የተገለጠው ጥልቅ ፍቅር በወንጌል አገልግሎት አብረው ሠራተኞች በሆኑ ክርስቲያኖች መካከልም ሊታይ የሚገባ ባሕርይ ነው።



© 1989 The Zondervan Corporation

ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ

21 ከእነርሱ ከተለየን በኋላ ቀጥታ
በመርከብ ወደ ቆስ ተጓዝን፤
በማግስቱም ወደ ሩድ፣ ከዚያም ወደ ጳጥራ
አመራን። 2በዚያም ወደ ፊንቄ የሚሄድ
መርከብ ስላገኘን፣ ተሳፍረን ጕዞአችንን
ቀጠልን። 3ቆጵሮስ በታየችን ጊዜ፣ ወደ
ግራ ትተናት ዐለፍንና ወደ ሶርያ አመራንና
መርከባችን ጭነቱን በጢሮስ ማራገፍ ስለ
ነበረበት፣ እኛም እዚያው ወረድን። 4ደቀ
መዛሙርትንም በዚያ አግኝተን፣ ሰባት
ቀን ከእነርሱ ጋር ተቀመጥን። እነርሱም
በመንፈስ ሆነው ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም
እንዳ ይሂድ ነገሩት። 5ዋ3ይታ ጊዜያችን
ባለቀ ጊዜ፣ ተተናችው ጕዞአችንን ቀጠልን፤
ደቀ መዛሙርቱም ሁሉ ከሚስቶቻቸውና
ከልጆ ቻቸው ጋር እስከ ከተማው ውጭ ድረስ
ሸኙን፤ በባሕሩም ዳር ተንበርክከን ጸለይን፤
ግተሰነባበትንም በኋላ እኛ ወደ መርከቡ
ገባን፤ እነርሱም ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

7ከጢሮስ ተነሥተን ጕዞአችንን
በመቀጠል ጴጤሊማይስ ደረስን፤ ከመርከብ
ወርደንም ለወንድሞች ሰላምታ ኳቀረብን
በኋላ፣ አንድ ቀን ከእነርሱ ጋር 3የን።
8በማግስቱ ከዚያ ተንሥተን ቂሳርያ ደረስን፤
ከሰባቱ ወንጌላውያን አንዱ በሆነው በፊልጶስ
ቤትም ዐረፍን። 9አርሱም ትንቢት የሚናገሩ
አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት።

10በዚያም ብዙ ቀን ከተቀመጥን በኋላ
አጋቦስ የተባለ ነቢይ ከይሁዳ ወረደ፤ 11ወደ

21፥1 ሐሥ16፥10
21፥2 ሐሥ11፥19
21፥3 ሉቃ2፥2
21፥4 ቊ11፤ ሐሥ11፥26፤ 20፥23
21፥5 ሉቃ22፥41፤ ሐሥ9፥40፤ 20፥36
21፥7 ሐሥ1፥16፤ 12፥20
21፥8 ሐሥ6፥5፤ 8፥5-40፤ ኤፌ4፥11፤ 2ጢሞ4፥5
21፥9 ዘሁ15፥20፤ መሳ4፥4፤ ዝክ6፥14፤ ሉቃ2፥36፤ ሐሥ2፥17፤ 1ቆሮ11፥5
21፥10 ሐሥ11፥28
21፥11 ቊ33፤ ነገ 22፥11፤ ኢሳ20፥2-4፤ ኤር13፥1-11፤ ማቴ20፥19፤ ሐሥ8፥29
21፥13 ዮሐ15፥21፤ ሐሥ9፥16፤ 20፥24
21፥14 ሩት1፥18፤ ማቴ26፥39
21፥15 ሐሥ19፥21
21፥16 ቊ3፥4፤ ሐሥ8፥40

እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወሰደ፤
የራሱንም እጅና እግር በማሰር፣ "መንፈስ
ቅዱስ፣ 'በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁድ የዚህን
መታጠቂያ ባለቤት እንዲህ አድርገው
በማሰር ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል'
ይላል" አለ።

12ይህን ስንሰማ እኛና በዚያም የሚኖሩት
ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ (ሥሚ
ለመነው። 13ጳውሎስ ግን፣ "ለምን እንዲህ 1፥11
እያለቀሳችሁ ልቤን ታሳብሱታላችሁ? እኔ
መታሰር ቀርቶ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም
በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳን ዝግጁ
ነኝ" አላቸው። 14ምክራችንን አልቀበል
ስላለን፣ "እንግዲህ የጌታ ፈቃድ ይሁን"
ብለን ተውነው።

15ከዚህ በኋላ፣ ተዘጋጅተን ወደ
ኢየሩሳሌም ወጣን። 16በቂሳርያ ከነበሩት
ደቀ መዛሙርትም አንዳንዶቹ ወደ ምናሶን
ቤት ይዘውን መጡ፤ እኛም በዚያው
ተቀመጥን። ምናሶን የቆጵሮስ ሰው ሲሆን፣
ከመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት አንዱ
ነበረ።

ጳውሎስ ኢየሩሳሌም ደረሰ

17ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ፣ ወንድሞች
በደስታ ተቀበሉን። 18በማግስቱም
ጳውሎስና ሌሎቻችንም ያዕቆብን ለማየት
ሄድን፤ ሽማግሌዎችም ሁሉ በዚያ ነበሩ።
19ጳውሎስም ሰላምታ ኳቀረበላቸው በኋላ፣

21፥17 ሐሥ9፥30፤ 15፥4 21፥18 ሐሥ11፥30፤ 15፥13
21፥19 ሐሥ1፥7፤ 14፥27፤ 15፥4፤12

21፥4 **በመንፈስ ሆነው ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ** ነገሩት፤ "በመንፈስ ሆነው" የሚለው ሐረግ "መንፈስ ቅዱስ ከተናገረው ነገር የተነሣ" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ አልከለከለውም፤ ወደዚያ ይሄድ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበርና (ቊ 14፤ 23፥11 ይመ)። ይሁን እንጂ ቢሄድ ብዙ መከራ እንደሚጠብቀው እግዚአብሔር በማስጠንቀቅ ነግሮት ነበር። ምናልባትም መንፈስ ቅዱስ በጢሮስ የተናገረውን በቂሣርያም ሳይደግመው አልቀረም (ቊ 8-14)። ነገር ግን ጳውሎስ ዋጋውን በመተመን ስለ ወንጌል ለመሞት እንኳ ፈቃደኛ ነበር (ቊ 10-14)።

21፥10 **አጋቦስ የተባለ ነቢይ**፤ በ46 ዓ.ም. ስለነበረው ራብ ትንቢት የተናገረው አጋቦስ (11፥27-28) አሁን ደግሞ ጳውሎስ እንደሚያዝና እንደሚታሰር ትንቢት ተናገረ። ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም በተረጨ ቊጥር ትንቢቱ ግልጽና ተጨባጭ ይሆናል (ቊ 11)። አጋቦስ የተናገረው ትንቢት ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ፈጽሞ መሄድ የለበትም የሚል አይደለም፤ ነገር ግን ቢሄድ የሚጠብቀውን ነገር በግልጽ አሳይቶአል።

በቅዱሳት መጻሕፍት መርሖች መሠረት ሊወሰኑ የሚችሉ የግል ጕዳዮች በትንቢት ምሪት የተሰጠበት አጋጣሚ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ እንኳ እንደሌለ ልብ በሉ። ከግብረገባዊ፣ ከመግዛት ወይም ከሽፍጥ፣ ከጋብቻ፣ ከትዳርና ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጕዳዮች በትንቢት ላይ ብቻ በመደገፍ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል መርሖችን በመቀበልና በመታዘዝ ውሳኔ ማድረግ ይገባል። የአዲስ ኪዳን የትንቢት ስጦታ በመሠረቱ ማበረታታትን፣ ማደፋፈርንና ማጽናናትን (1ቆሮ 14፥3) እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ የወንጌል መልእክተኝነትን በተመለከተ ምሪት መስጠትን (16፥6 እና ማብ የመ) የሚያካትት ነው።

21፥13 **ጳውሎስን ግን ... አላቸው**፤ የአብዛኛው ሕዝብ አስተያየት ወይም በፍጹም እውነተኝነት የሚንቀሳቀሱን ምእመናን የጋራ በጎ ፈቃድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ላይሆን ይችላል። ጳውሎስ የወዳጆቹን ልመናና እንባ አልናቀም፤ ሆኖም ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም በእስር ለመሠቃየት እንዲሁም እስከሞት እንኳ ቢሆን ዋጋ ለመክፈል የነበረውን ጽኑ ዕሳማ ሊለውጠው አልቻለም።

21፥14 **የጌታ ፈቃድ ይሁን**፤ ብዙ ደቀ መዛሙርት (ቊ 4) ነቢይ አጋቦስም ጭምር (ቊ 11)፣ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ቢሄድ ስለሚጠብቀው መከራ ትንቢት ተናገሩ። እነዚህ ክርስቲያኖች የተገለጠውን የትንቢት ቃል ለጳውሎስ የግል ምሪት አድርገው በመቀሩጠር ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንደሌለበት ተረጕመለት (ቊ 4፤12)። ሐዋርያው ጳውሎስ የመገለጡን እውነተኝነት ቢረዳም (ቊ 11)፣ ደቀ መዛሙርቱ በቅንነት የተረጕመትን የትንቢት መገለጥ አልተቀበለም (ቊ 13)። ይህን በመሰለው ቸልቅ ውሳኔን በሚጠይቅ ጕዳይ መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ቃል እንዲሄድ በግሉ በለጠት ምሪት ላይ ብቻ ተደገፈ (23፥11፤ 21፥4 እና ማብ ይመ)። የወደፊቱን አገልግሎት በተመለከተ አንድ ሰው እግዚአብሔር በግሉ የሚናገረውን መጠበቅ እንጂ የሌሎቹን ቃል በመስማት መደገፍ የለበትም።

እግዚአብሔር በእርሱ አገልግሎት አማካይነት በአሕዛብ መካከል ያደረገውን ሁሉ በዝርዝር አስረዳቸው።

20እነርሱም ይህን ሲሰሙ፣ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ጳውሎስንም እንዲህ አሉት፤ "ወንድም ሆይ፤ በብዙ ሺህ የሚ3ቆጠሩ አይሁድ እንዳመኑ ተመልከት፤ ሁሉም ደግሞ ለሙሴ ሕግ የሚቀኑ ናቸው። 21በአሕዛብ መካከል የሚኖሩ አይሁድ ሁሉ ሙሴን እንዲተዉና ልጆቻቸውን እንዳይገርዙ፣ በቄየውልማዳችን መሠረት እንዳይኖሩ እንደምታስተምር ሰለ አንተ ተነግሮአቸዋል። 22መምጣትህን መስማታቸው የማይቀር ነውና፣ እንግዲህ ምን እናድርግ? 23ስለዚህ የምንልህን አድርግ። ስእለት ያለባቸው አራት ሰዎች በእኛ ዘንድ አሉ፤ 24እነዚህን ሰዎች ይዘህ ከእነርሱ ጋር የመንጻቱን ሥርዐት ፈጽም፤ ራሳቸውንም እንዲላጩ የሚጠየቀውን ገንዘቡን ክፈልላቸው፤ በዚህም ስለ አንተ የተነገራቸው ሰዎች ሁሉ፣ የሰሙት እውነት እንዳልሆነና አንተ ራስህ ሕጉን ጠብቀህ የምትኖር መሆንህን ያውቃሉ። 25ከአሕዛብ ወገን ያመኑትን በተመለከተ ግን ለጣዖት የተሠዋ ምግብ፣ ደምና ታንቆ የሞተ ከብት እንዳ ይበሉ፣ ዝሙትም ከዝሙት ርኵሰት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ወስነን ጽፈንላቸዋል።"

26ጳውሎስም በማግስቱ ሰዎቹን ይዞ ሄደ፤ አብሮአቸውም የመንጻቱን ሥርዐት ፈጸመ። ከዚያም የመንጻቱ ሥርዐት መቼ እንደሚያበቃና የእያንዳንዳቸውም መሥዋዕት መቼ እንደሚቀርብ ለማስታወቅ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ።

ጳውሎስ ተያዘ

27ሰባቱ ቀንም ሊፈጸም ሲቃረብ፣ ከእስያ አውራጃ የመጡት አይሁድ ጳውሎስን በቤተ መቅደስ ባዩት ጊዜ፣ ሕዝቡን ሁሉ እነሣ ሥተው ያዙትና፤ 28እንዲህም እያሉ ጮኹ፤ "የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ርዱን! ሕዝባችንንና ሕጋችንን እንዲሁም ይህን ስፍራ በማጥላላት በደረሰበት ስፍራ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ የሚያስተምረው ሰው ይህ ነውና፤ ከዚህም በላይ ግሪኮችን ወደ ቤተ መቅደስ እያስገባ ይህን የተቀደሰ ስፍራ የሚያረክሰው እርሱ ነው።" 29ይህንም ያሉት ቀደም ሲል፣ የኤፌሶኑን ሰው ጥሮፊሞስን ከጳውሎስ ጋር በከተማው ውስጥ ስላዩትና፣ ጳውሎስ እርሱንም ወደ ቤተ መቅደስ ይዞ የገባ ስለ መሰላቸው ነበር።

30ከተማው በሙሉ ታወከ፤ ሕዝቡም ከየአትጣጫው እየተራሯሯጡ መጡ፤ ጳውሎስንም ይዘው እየጐተቱት ከቤተ መቅደሱ ግቢ አወጡትና በሮቹም ወዲያውኑ ተዘጉ። 31ሊገድሉት ሲፈልጉም የኢየሩሳሌም ከተማ ፍጹም ታወከች፤ ወሬውም ለሮማ ጦር አዛዥ ደረሰው። 32እርሱም ወዲያው አንዳንድ የጦር መኰንኖችንና ወታደሮችን ይዞ እየሮጠ ወደ እነርሱ ወረደ፤ እነርሱም መኰንኖቹንና ወታደሮቹን ባዩ ጊዜ ጳውሎስን መደብደብ ተዉ።

33የጦር አዛዡም ቀርቦ ያዘው፤ በሁለት ሰንሰለትም እንዲታሰር ትእዛዝ ሰጠ፤ ከዚያም ማን መሆኑንና ምን እንዳደረገ ጠየቀ። 34ሕዝቡም ከፊሉ አንድ ነገር ሲናገር፣ ከፊሉ ደግሞ ሌላ ይናገር ነበር፤ ከግርግታው የተነሣም አዛዡ ምንም ነገር ሊሰማ አልቻለም፤ ስለዚህ ጳውሎስ ወደ ጦር ሰፈር እንዲወሰድ አዘዘ። 35ከሕዝቡ ውኪታ የተነሣ፣ ጳውሎስ ወደ መውጫው ደረጃ ሲደርስ ወታደሮቹ ይሸከሙት ዘንድ ግድ ሆነባቸው። 36ከኋላ የተከተለውም ሕዝብ፣ "አስወግደው!" እያለ ይጮኽ ነበር።

ጳውሎስ ለሕዝቡ ተናገረ

37ወታደሮቹ ወደ ጦር ሰፈር ይዘውት ሊሄዱ ሲሉ፣ ጳውሎስ ጦር አዛዡን፣ "እንድ ነገር እንድነግርህ ፍቀድልኝ?" አለው።

አዛዡም እንዲህ አለው፤ "የግሪክ ቋንቋ ታውቃለህ? 38አንተ ከዚህ ቀደም ዐመፅ አስነሥተህ፣ አራት ሺህ ነፍስ ገዳዮችን ወደ በረሓ ያሸፈትኸው ግብፃዊ አይደለህምን?"

39ጳውሎስም፣ "እኔስ በኪልቅያ ያለችው የታዋቂዋ የጠርሴስ ከተማ ነዋሪ የሆንሁ አይሁዳዊ ነኝ፤ ለሕዝቡ ንግግር እንዳደርግ ፍቀድልኝ" አለው።

40ጳውሎስም የጦር አዛዡን ካስፈቀደ በኋላ፣ በደረጃው ላይ ቆሞ ሕዝቡን በእጁ ጠቀሰ፤ ሁሉም ጸጥ ባሉ ጊዜ፣ በዕብራይ ስጥ[ሀ] ቋንቋ እንዲህ አለ፤

22 "ወንድሞችና አባቶች ሆይ፤ አሁን የማቀርብላችሁን የመከላከያ መልሴን ስሙኝ።"

2እነርሱም በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲናገር በሰሙ ጊዜ ከፊት ይልቅ እጥ አሉ።

ጳውሎስም እንዲህ አለ፤ 3"እኔ በኪልቅያ በምትገኘው በጠርሴስ የተወለድሁ አይሁዳዊ ስሆን፣ ያደግሁት ግን በዚህ ከተማ ነው። የአባቶቻችንን ሕግ በማለ ያል እግር ሥር ተቀምጬ በሚገባ ተምሬ አለሁ፤ ዛሬ እናንተ እንዲህ የምትቀኑለትን

21፥20 ሐሥ15፥1፥5፤ 22፥3፤ ሮሜ10፥2፤ ገላ1፥14፤ ፊል3፥6 21፥21 ቊ28፤ ሐሥ6፥14፤ 15፥19-21፤ 1ቆሮ7፥18፡19 21፥23 ዘኍ6፥2፡5፤ ሐሥ18፥18 21፥24 ቊ26፤ ሐሥ18፥18፤ 24፥18 21፥25 ሐሥ15፥20፡29 21፥26 ዘኍ6፥13-20፤ ሐሥ24፥18 21፥27 ኤር26፥8፤ ሐሥ24፥18፤ 26፥21፤ 1ተሰ2፥16 21፥28 ማቴ24፥15፤ ሐሥ6፥13፤ 24፥5፡6 21፥29 ሐሥ18፥19፤ 20፥4፤ 2ጢሞ4፥20 21፥30 ሐሥ16፥19፤ 26፥21

21፥32 ሐሥ23፥27 21፥33 ቊ11፤ ሐሥ12፥6፤ 20፥23፤ 22፥29፤ ኤፌ6፥20፤ 2ቆሮ2፥9 21፥34 ቊ37፤ ሐሥ19፥32፤ 22፥24፤ 23፥10፡16፡32 21፥35 ቊ40 21፥36 ሉቃ23፥18፤ ዮሐ19፥15፤ ሐሥ22፥22 21፥37 ቊ34 21፥38 ማቴ24፥26፤ ሐሥ5፥36 21፥39 ሐሥ6፥9፤ 9፥11 21፥40 ዮሐ5፥2፤ ሐሥ12፥17 22፥1 ሐሥ7፥2 22፥2 ዮሐ5፥2፤ ሐሥ21፥40 22፥3 1ነገ19፥10፤ ሉቃ10፥39፤ ሐሥ5፥34፤ 6፥9፤ 9፥11፤ 21፥20፡39፤ 26፥5

አማኞች ክርስቶስን በትክክል አምነው ተቀብለው፥ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት አግኝተውም በእርሱ ተሞልተዋል። ለሕግና ለወግ ያላቸው ቅንዓት ከሕግ አክራሪነት አስተሳሰብ የመጣ ሳይሆን፣ ልባቸው ለክርስቶስ ከመሰጠቱና ለእግዚአብሔር መንገድ ታማኞች ከመሆናቸው የተነሣ ነበር (ማቴ 7፥6 ይመ)።

ሀ21፥40 ወይም አራማይክ፤ እንዲሁም ቊ

ያህል እኔም ስለዝሕብሔር እቀና ነበር። ⁴ይህን መንገድ የሚከተሉትንም እስከ ሞት ድረስ እያሳደድሁ፣ ወንዶችንም ሴቶችንም አስሬ ወደ ወህኒ እጥላቸው ነበር። ⁵ይህን ተግባሬን ሊቀ ካህናቱም ሆነ ሽንጎው ሁሉ ሊመሰክሩ ይችላሉ። ከእነርሱ ደብዳቤ ተቀብዬ ደማስቆ ወዳሉት ወንድሞቻቸው በመሄድ፣ እነዚህን ሰዎች አሳስሬ ወደ ኢየሩሳሌም አምጥቼ ለማስቀጣት ወደ ዚያ እሄድ ነበር።

⁶"ስንጓዝም እኩለ ቀን ገደማ ወደ ደማስቆ እንደ ተቃረብሁ፣ ድንገት ታላቅ ብርሃን ከሰማይ በዙሪያዬ በራ፤ ⁷እኔም ምድር ላይ ወደቅሁ፤ ከዚያም፣ 'ሳውል፤ ሳውል፤ ለምን ታሳድደኛለህ?' የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ።

⁸"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?' አልሁት።

"እርሱም፣ 'እንተ የምታሳድደኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ' አለኝ። ⁹ከእኔ ጋር የነበሩትም ብርሃኑን አዩ፤ ነገር ግን የሚናገ ረኝን የእርሱን ድምፅ በትክክል አልሰሙም።

¹⁰"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ ምን ላድርግ?' አልሁት።

"ጌታም፣ 'ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ሂድ፤ በዚያም ልታደርገው የሚገባህን ሁሉ ይነግሩሃል' አለኝ። ¹¹ከብርሃኑም ጸዳል የተነሣ ዐይኔ ስለ ታወረ፣ ከእኔ ጋር የነበሩት እጁን ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አደረሱኝ።

¹²"ከዚያም ሐናንያ የተባለ ሰው ሊያየኝ ወደ እኔ መጣ፤ እርሱም ሕግን የሚጠብቅና በዚያ በሚኖሩት አይሁድ ሁሉ ዘንድ እጅግ የተከበረ ሰው ነበረ። ¹³በአጠገቤም ቆሞ፣ 'ወንድም ሳውል ሆይ፤ ዐይኖችህ ይብሩልህ!' አለኝ፤ እኔም በዚያችው ቅጽበት አየሁት።

¹⁴"እርሱም ቀጥሎ እንዲህ አለ፤ 'የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን እንድታውቅ፣ ጻድቁን እንድታይና ቃሉን ከአንደበቱ እን ድትሰማ መርጦሃልና፤ ¹⁵ስላየኸውና ስለ ሰማኸው ነገር በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆነዋለህና። ¹⁶ታዲያ፣ አሁን ምን ትጠብቃለህ? ተነሥተህ ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ።'

¹⁷"ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ በቤተ መቅደስ ስጸልይም ተመሰጥሁ፤ ¹⁸ጌታም ሲናገረኝ አየሁ፤ እርሱም አሁኑኑ፣ 'ፈጥነህ ከኢየሩሳሌም ውጣ! ስለ እኔ የምትመሰክረውን አይቀበሉህምና' አለኝ።

¹⁹"እኔም እንዲህ አልሁት፤ 'ጌታ ሆይ፤ በአንተ የሚያምኑትን ሰዎች ለማሰርና ለመደብደብ፣ በየምኵራቡ ስዞር እንደ ነበር እነዚህ ሰዎች ያውቃሉ፤ ²⁰ደግሞም የአንተን ሰማዕት የእስጢፋኖስን ደም በሚያፈሰበት ጊዜ፣ በድርጊታቸው ተስማምቼ በቦታው ቆሜ የነዳዮቹን ልብስ እጠብቅ ነበር።'

²¹"ጌታም፣ 'ሂድ፤ በሩቅ ወዳሉት አሕዛብ እልክሃለሁና' አለኝ።"

22፥19 ሐሥ፰፥3 ; 22፥20 ሐሥ፯፥57-60፤ ፰፥1
22፥21 ሐሥ፱፥15፤ 13፥46

22፥4 ቍ፲፱፥20፤ ሐሥ፰፥3፤ ፱፥2
22፥5 ሉቃ22፥66፤ ሐሥ1፥16፤ 2፥29፤ 9፥2፤ 13፥26፤ 23፥1፤ 28፥17-21፤ ሮሜ7፥1፤ 9፥3
22፥6 ሐሥ9፥3
22፥8 ማር1፥24
22፥9 ሐሥ9፥7፤ 26፥13
22፥10 ሐሥ16፥30
22፥11 ሐሥ9፥8
22፥12 ሐሥ፯፥17፤ 10፥22
22፥14 ሐሥ3፥13፤ 7፥52፤ 1ቆሮ15፥8
22፥15 ቍ፲4፤ ሐሥ23፥11፤ 26፥16
22፥16 ዘሌ8፥6፤ መዝ51፥2፤ ሕዝ36፥25፤ ዮሐ3፥5፤ ሐሥ2፥38፤ ሮሜ10፥13፤ 1ቆሮ፲፤ 1ጴጥ3፥21
22፥17 ሐሥ9፥26፤ 10፥10
22፥19 ቍ4፤ ማቴ10፥17፤

22፥16 **ተጠመቅ**፤ የውሃ ጥምቀት ከቤተ ክርስቲያን የመንጌል ተልእኮ ዐዋጅ ጋር የተጀመረ ነው (2፥38፡41)። አንድ ሰው ራሱን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ መስጠቱን የሚያመለክት በአዲስ ኪዳን ሥራ ላይ የዋለ ክርስቲያናዊ ሥርዐት ነው። በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማለትም በሥላሴ ስም (ማቴ 28፥19) ወይም አብንና ወልድን አስቀድመው ላመኑ ምእመናን በክርስቶስ ስም (19፥5) በሚደረግ የውሃ ጥምቀት ሥርዐት አማኞች በክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ፊት እምነታቸውን በግልጽ ይመሰክራሉ።

(1) ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን የሚደረግ የውሃ ጥምቀት (ገላ 3፥27) ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ (2፥38 ይመ፤ ከማቴ 28፥19 ጋር ያነጻጽሩ)፥ አንድ ሰው ይህን ሥርዐት ሲፈጽም አሁን የክርስቶስ ንብረት እንደሆነ እንዲሁም የእሱን ሕይወት መንፈስና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ርስት አብሮ ተካፋይ መሆኑን ያመለክታል (ሮሜ 8፥14-17፤ ገላ 3፥26—4፥7)።

(2) የውሃ ጥምቀት አማኝ ክርስቶስ ላደረገለት ነገር የሚሰጠው ምላሽ ነው። ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው ከንሰሓ (2፥38) እና በግል ክርስቶስን ከማመን (ቁላ 2፥12) በኋላ ሲደረግ ነው።

(3) የውሃ ጥምቀት በቅን ልብ በማመንና ኢየሱስን ጌታና አዳኝ አድርጎ ራስን በመስጠት ሲፈጸም ጸጋን ከክርስቶስ የመቀበያ መንገድ ይሆናል (ከ1ጴጥ 3፥21 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) የውሃ ጥምቀት ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገን የመቀበላችን ውጭአዊ ምልክትና ምስክርነት ሲሆን እንዲሁም ኮነኒኢታችንን መታጠብ ሁኔታ የሚገልጽ ነው (ከ2፥38፤ ዕብ 3፥5፤ ከ1ጴጥ 3፥21 ጋር ያነጻጽሩ)።

(5) የውሃ ጥምቀት አማኝ ከክርስቶስ ጋር በመሞት፣ በመቀበርና በመነሣት መተባበሩን የሚያመለክት ምሳሌያዊ መግለጫ ነው (ሮሜ 6፥1-11፤ ቈላ 2፥11-12)። ይህም የኀጢአት ሕይወት ማብቃቱን ማለትም ለኀጢአት መሞትን (ሮሜ 6፥3-4፤7፥10፡12፤ ቈላ 3፥3-14) እንዲሁም በክርስቶስ አዲስ ሕይወት መጀመሩን ያመለክታል (ሮሜ 6፥4-5፡11፤ ቈላ 2፥12-13)። ስለዚህ የውሃ ጥምቀት በዓለምና ከፉ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ ጀርባን በማዞር በአዲስ ዘመን ሁሉ ራስን ለክርስቶስ መስጠትን (ሮሜ 6፥6፡11-13) እንዲሁም የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሕይወት የሚያንጸባርቅ አዲስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ መኖርን ያካትታል (ቈላ 2፥1-17)።

22፥16 **ከኀጢአትህም ታጠብ**፤ ሐዋርያው ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ተለውጦና ድኖ ነበር (9፥5 እና ግብ ይመ)። መጠመቁ የኀጢአት ይቅርታ ማግኘቱን፣ ኀጢአቱን ሁሉ በመተው የክርስቶስን ዐላማ መቀበሉንና ራሱንም ለዚያ መስጠቱን በይፋ የመሰከረበት ነበር።

22፥17 **ተመሰጥሁ**፤ "መመሰጥ" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ የአንድ ሰው አእምሮ ከተፈጥሮአዊ ከሥጥት ይልቅ መንፈሳዊ እውነታን የሚረዳበትን ሁኔታ ለማመልከት የተጠቀሰ ነው። በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን መገለጥ ለመቀበል ዝግጁ ይሆናል። ይህም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጥልቅና ጥብቅ በሆነ ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር መሆንን የሚያመለክት ነው (ጴጥሮስ ፩10፡10 እና 11፥5 ላይ የተመሰጠበትን ሁኔታ ይመ፤ ከ2ቆሮ 12፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)።

ጳውሎስ የሮም ዜጋ መሆኑ ታወቀ

22 ²²ሕዝቡም ይህን ቃል እስኪናገር ድረስ ሰሙትና፤ ከዚህ በኋላ ግን ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ፣ "ይህስ ከምድር ገጽ ይወገድ! በሕይወት መኖር አይገባውም!" ብለው ጮኹበት።
²³እነርሱም እየጮኹና ልብሳቸውን እየወረወሩ፣ ትቢያም ወደ ላይ እየበተኑ ሳሉ፣ ²⁴የጦር አዛዡ ጳውሎስን ወደ ጦር ሰፈር እንዲያስገቡትና ሕዝቡ ለምን እንዲህ እንደ ሚጮኹበት እየተገረፈ እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጠ። ²⁵ጳውሎስም በጠፍር ወጥረው ሊገርፉት ሲሉ፣ አጠገቡ የቆመውን የመቶ አለቃ፣ "አንድን የሮም ዜጋ ያለ ፍርድ ለመ ግረፍ ሕግ ይፈቅድላችኋልን?" አለው።
²⁶የመቶ አለቃውም ይህን ሲሰማ፣ ወደ ጦር አዛዡ ቀርቦ፣ "ምን እያደረግህ እንደ ሆነ ዐውቀሃል? ሰውየው እኮ ሮማዊ ነው" አለው።
²⁷አዛዡም ወደ ጳውሎስ ቀርቦ፣ "አንተ ሰው እስቲ ንገረኝ፤ ሮማዊ ነህን?" አለው።
እርሱም፣ "አዎን፤ ነኝ" አለው።
²⁸አዛዡም መልሶ፣ "እኔ ይህን ዜግነት ያገኘሁት ብዙ ገንዘብ አውጥቼ ነው" አለ።
ጳውሎስም፣ "እኔ ግን ከተወለድሁ ጀምሮ ሮማዊ ነኝ" አለው።
²⁹ስለዚህ እነዚያ ሊመረምሩት ያሰቡት ሰዎች ወዲያው ከእርሱ ሸሹ፤ የጦር አዛዡም የሮም ዜጋ መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣ በሰ ንሰለት አስሮት ስለ ነበር ፈራ።

ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ

³⁰በማግስቱም የጦር አዛዡ፣ አይሁድ ጳውሎስን የከሰሱበት ትክክለኛው ምክንያት ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ስለ ፈለገ ፈታውቶ ከዚያም የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሸንጎ አባላት በሙሉ እንዲሰበሰቡ አዘዘ፤ ጳውሎስንም ከደረጃው አውርዶ በፊታቸው አቆመው።

23 ጳውሎስም ወደ ሸንጎው ትኵር ብሎ በመመልከት፣ "ወንድሞች ሆይ፤ እኔ እስከዚች ቀን ድረስ በእግዚአብሔር ፊት በንጹሕ ሕሊና ተመላልሻለሁ" አለ። ²በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ በጳውሎስ አጠገብ የቆሙትን ሰዎች አፉን እንዲመቱት አዘዘ። ³ጳውሎስም፣ "አንተ በኖራ የተለሰንህ ግድግዳ! እግዚአብሔር ዳግሞ አንተን ይመታሃልና፤ በሕጉ መሠረት ልትፈርድብኝ ተቀምጠህ ሳለህ፣ ያለ ሕግ ስላ ስመታኸኝ አንተ ራስህ ሕጉን ጥሰሃል" አለው።
⁴ጳውሎስ አጠገብ ቆመው የነበሩትም፣ "የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህናት ደፍረህ ትሰድባለህን?" አሉት።
⁵ጳውሎስም፣ "ወንድሞች ሆይ፤ ሊቀ ካህናት መሆኑን ባለማወቄ ነው፤ 'በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ አትናገር' ተብሎ ተጽፎአል ና" አላቸው።
⁶ጳውሎስም ሕዝቡ፣ ከፊሎቹ ሰዱቃው ያን፣ ከፊሎቹ ፈሪሳውያን መሆናቸውን ስላወቀ፣ "ወንድሞቼ ሆይ፤ እኔ ከፈሪሳዊ የተወለድሁ ፈሪሳዊ ነኝ፤ ለፍርድ የቀረ ብኩትም የሙታንን ትንሣኤ ተስፋ በማ ድረጌ ነው" ሲል በሸንጎው ፊት ጮኸ። ⁷ይህንንም በተናገረ ጊዜ፣ በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን መካከል ጠብ ተነሣ፤ ሸንጎውም ለሁለት ተከፈለ። ⁸ሰዱቃውያን የሙታን ትንሣኤ የለም፤ መላእክትም መናፍስትም የሉም የሚሉ ሲሆኑ፣ ፈሪሳውያን ግን በእነዚህ ሁሉ መኖር የሚያምኑ ነበሩ።
⁹ታላቅ ሁከትም ሆነ፤ ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑ አንዳንድ የኦሪት ሕግ መምህራንም ተነሥተውና "በዚህ ሰው ላይ ምንም ጥፋት አላገኘንበትም፤ መንፈስ ወይም መልአክ ተናግሮትስ እንደ ሆነ ምን ይታወቃል?" በማለት አጥብቀው ተከራከሩ። ¹⁰ጠቡ ከማየሉ የተነሣም አዛዡ ጳውሎስን እንዳይነ ጣጥሉት ፈራ፤ ስለዚህ ወታደሮቹ ወር ደው ከመካከላቸው ነጥቀው ወደ ጦሩ ሰፈር እንዲያስገቡት አዘዘ።
¹¹በሚቀጥለውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ፣ "ጳውሎስ ሆይ፤ አይዞህ! በኢየሩሳሌም እንደ መሰከርህልኝ፣ በሮምም ደግሞ ልትመሰክርልኝ ይገባሃል" አለው።

ጳውሎስን ለመግደል የተደረገ ሤራ

¹²በነጋም ጊዜ፣ አይሁድ ተሰብስበው በማ ሤር ጳውሎስን እስኪገድሉ ድረስ እህል ውሃ

22፥22 ሐሥ 21፥36፤ 25፥24
22፥23 2ሳሙ 16፥13፤ ሐሥ 7፥58
22፥24 ሥሥ 29፥ ሐሥ 21፥34
22፥25 ሐሥ 16፥37
22፥29 ሥሥ 24፥25፤ ሐሥ 16፥38፤ 21፥33
22፥30 ማቴ 5፥22፤ ሐሥ 21፥33፤ 23፥28
23፥1 ሐሥ 22፥5፤ 30፤ 24፥16፤ 1ቆሮ 4፥4፤ 2ቆሮ 1፥12፤ 1ጢሞ 1፥5፤ 19፤ 3፥9፤ 2ጢሞ 1፥3፤ ዕብ 9፥14፤ 10፥22፤ 13፥18፤ 1ጴጥ 3፥16፤ 21
23፥2 ዮሐ 18፥22፤ ሐሥ 24፥1
23፥3 ዘሌ 19፥15፤ ዘዳ 25፥1፤ 2፤ ማቴ 23፥27፤ ዮሐ 7፥51
23፥5 ዘፀ 22፥28
23፥6 ሥሥ 7፥8፤ ሐሥ 4፥1፤ 22፥5፤ 24፥15፤ 21፤ 26፥5፤ 8፤ ፊሌ 3፥5
23፥8 ማቴ 22፥23፤ 1ቆሮ 15፥12
23፥9 ሥሥ 29፥ ኤር 26፥16፤ ማር 2፥16፤ ሉቃ 23፥4፤ ሐሥ 22፥7፤ 17፤ 18፤ 25፥25፤ 26፥31፤ 28፥18
23፥10 ሐሥ 21፥34
23፥11 ማቴ 14፥27፤ ሐሥ 19፥21፤ 28፥23
23፥12 ሥሥ 14፥21፤ 30፤ ሐሥ 20፥3፤ 25፥3

23፥1 በንጹሕ ኅሊና፣ ኅሊና የድርጊታችንን ትክክል መሆን አለመሆን በግል የምናውቅበት የውስጥ ምስክርነት ነው። «ንጹሕ ኅሊና» እግዚአብሔርንም ሆነ ፈቃዱን እንዳልጣሰን ትክክለኛ ፍርድ የሚሰጥ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ምናልባትም በሰዎች ፊት የነበረውን የአይሁት ምስክርነት ለማመልከት የተናገረው በቅንነት ነበር፤ በፊል 3፥6 ላይ፣ «ሕግን በመፈጸም ስለሚገኝ ጽድቅ ከነንም፣ ያለ ነቀፋ ነበርሁ» ያለውን ልብ በሉ። ከመለወጡ በፊት አማኞችን በሚያሳድድበት ጊዜ እንኳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርግ ያምን ነበር (26፥9)።
ሐዋርያው ጳውሎስ የነበረው ሙሉ በሙሉ የመሰጠት ሕይወትና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ያደረገው ቁርጥ ውሳኔ እንዲሁም በክርስቶስ ከመለወጡ በፊት እንኳ የነበረው ነቀፋ የሌለበት ኑሮ፣ አማኞች ነን የሚሉትን ነገር ግን ሁሉም ሰው ነጢአትን ስለሚሠራ በእግዚአብሔር ፊት በንጹሕ ኅሊና መመላለስ አይቻልም በማለት ታማኝ ላለመሆናቸው መሸፋፈኛ ምክንያት የሚደረድሩትን ሰዎች የሚያሳፍርና ለፍርድ የሚጸርግ ነው።
23፥11 ጌታ በአጠገቡ በጳውሎስ? ቆሞ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለሚያጋጥመው ነገር በመሥጋት እጅግ ፈርቶ ነበር። በኢየሩሳሌም የሚገደል ይመስላል፤ ስለዚህም ወደ ሮምና ፈቀቅ ብሎም ወደ ምዕራብ ወንጌልን ለማሠራጨት የነበረው ዕቅድ እውን አይሆንም ማለት ነው። በዚህ ወሳኝ ጊዜ እግዚአብሔር ተገለጠለት፤ ልቡንም በማበረታታት በሮም የእግዚአብሔር ምስክር እንደሚሆን አረጋገጠለት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታ ይህንኑ እንደ ገና ሊያረጋግጥለት ለጳውሎስ ሦስት ጊዜ እንደ ተገለጠለት ተመቅሰአል (18፥9-10፤ 22፥17-18፤ 23፥11፤ ከ27፥23-24 ጋር ያነጻጽሩ፤ 18፥10 ማብ ይመ)።

ላለመቅመስ ተማማሉ። በዚህ ሤራ ¹³የተማማሉትም ከአርባ በላይ ነበሩ። ¹⁴እነርሱም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ሽማግሌዎች ሄደው እንዲህ አሉ፤ "ጳውሎስን ሳንገድል እህል ላለመቅመስ ጽኑ መሐላ እድርገናል። ¹⁵እንግዲህ እናንተ ከሸንጎው ጋር ሆናችሁና ስለ ጒዳዩ ትክክለኛ የሆነ ተጨማሪ መረጃ ከእርሱ እንደምትፈልጉ አስመስላችሁ ጳውሎስን ወደ እናንተ እንዲሰደው የጦር አዛዙን ለምኑት፤ እኛም ገና ወደዚህ ሳይደርስ ልንገድለው ዝግጁ ነን።"

¹⁶ነገር ግን የጳውሎስ የእኅት ልጅ ስለ ሤራው በመስማቱ፣ ወደ ጦሩ ሰፈር ገብቶ ሁኔታውን ለጳውሎስ ነገረው።

¹⁷ጳውሎስም ከመቶ አለቆቹ አንዱን ጠርቶ፣ "ይህ ልጅ ለጦር አዛዡ የሚነግረው ነገር ስላለ ወደ እርሱ ውሰደው" አለው። ¹⁸እርሱም ወደ ጦር አዛዡ ወሰደው።

የመቶ አለቃውም፣ "እስረኛው ጳውሎስ ጠርቶኝ፣ ይህ ጕልማሳ የሚነግርህ ነገር ስላለው ወደ አንተ እንዳቀርበው ለመነኝ" አለው።

¹⁹አዛዡም የጕልማሳውን እጅ ይዞ ለብቻው ገለል በማድረግ፣ "ልትነግረኝ የምትፈልገው ምንድን ነው?" አለው።

²⁰ልጁም እንዲህ አለው፤ "አይሁድ ስለ እርሱ ትክክለኛ የሆነ ተጨማሪ መረጃ ለማ ግኘት የፈለጉ በመምሰል፣ ጳውሎስን ነገ ሸንጎው ፊት እንድታቀርብላቸው ሊለምኑህ ተስማምተዋል። ²¹ስለዚህ እሺ አትበላቸው፤ ምክንያቱም ከመካከላቸው ከአርባ በላይ የሚሆኑት ሊገድሉት አድፍጠው እየጠበቁት ነው፤ ደግሞም እስኪገድሉት ድረስ እህል ውሃ ላለመቅመስ ተማምለዋል፤ አሁንም ተዘጋጅተው የአንተን መልስ እየተ ጠባበቁ ነው።"

²²የጦር አዛዡም፣ "ይህን ለእኔ የነገርህልኝን ነገር ለማንም እንዳትናገር" ብሎ ጕልማሳውን አስጠንቅቆ አሰናበተው።

ጳውሎስ ወደ ቂሳርያ ተላከ

²³ከዚያም ከመቶ አለቆቹ ሁለቱን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "ከምሽቱ ሦስት ሰዓት፣ ወደ ቂሳርያ የሚሄዱ ሁለት መቶ ወታደሮች፣ ሰባ ፈረሰኞችና ሁለት መቶ ባለ ጦር ፋፍራ አዘጋጁ፤ ²⁴ደግሞም ጳውሎስ ተቀምጠበት ወደ አገረ ገዥ ወደ ፊሊክስ በደኅና የሚደርስበት ከብት ይዘጋጅ።"

²⁵ደብዳቤም ጻፈ፤ እንዲህ የሚል፦

²⁶"ከቀላውዴዎስ ሉስዩስ፤

ለክቡር አገረ ገዥ ለፊሊክስ፤

ሰላም ለአንተ ይሁን።

²⁷አይሁድ ይህን ሰው ይዘው ሊገድሉት ነበር፤ ነገር ግን የሮም ዜጋ መሆኑን ስላወቅሁ፣ ከወታደሮቹ ጋር ደርሼ አተረ ፍሁት። ²⁸ለምን ሊከሱት እንደ ፈለጉ ለማወቅም፣ ወደ ሸንጎአቸው አቀረብሁ-ት። ²⁹የተከሰሰውም ሕጋቸውን በተመለከተ እንጂ ለሞት ወይም ለእስራት የሚያበቃ

23፥14 ሥሩ 12 ፡፡
23፥15
ሥሩ 1ሐሥ 22፥30
23፥16 ሥሩ 10፣ ሐሥ 21፥34 ፡፡
23፥18 ኤፌ 3፥1
23፥20
ሥሩ 1፡14፡15
23፥21
ሥሩ 12፡13፡14
23፥23 ሥሩ 33፣ ሐሥ 8፥40
23፥24 ሥሩ 26፡33፣ ሐሥ 24፥1-3፡10፣ 25፥14
23፥26 ሉቃ 1፥3፣ ሐሥ 15፥23፣ 24፥3፣ 26፥25
23፥27
ሐሥ 21፥32፡33፣ 22፥25-29
23፥28
ሐሥ 22፥30
23፥29 ሥሩ 9፣ ሐሥ 18፥15፣ 25፥19

23፥30
ሥሩ 20፡21፡35፣ ሐሥ 20፥3፣ 24፥19፣ 25፥16
23፥32 ሥሩ 23፣ ሐሥ 21፥34
23፥33
ሥሩ 23፡24፡26፣ ሐሥ 8፥40
23፥34 ሐሥ 6፥9፣ 21፥39
23፥35 ሥሩ 30፣ ሐሥ 24፥19፡27፣ 25፥16
24፥1 ሐሥ 23፥2፣ 24፥30፡35
24፥3 ሉቃ 1፥3፣ ሐሥ 23፥26፣ 26፥25
24፥5 ሥሩ 14፣ ማር 1፥24፣ ሐሥ 16፥20፣ 17፥6፣ 21፥28፣ 26፥5፣ 28፥22
24፥6 ሐሥ 21፥28
24፥9 1ተሰ 2፥16
24፥10
ሐሥ 23፥24
24፥11 ሥሩ 1፣ ሐሥ 21፥27

እንዳልሆነ ተረድቻለሁ። ³⁰አይሁድ ግን በዚህ ሰው ላይ ማሤራቸውን በተረዳሁ ጊዜ፣ ወዲያው ወደ አንተ ላክሁት፤ ከሳሾቹም ከእርሱ ጋር ያላቸውን ክርክር ለእንተ እንዲያቀርቡ አዘዝኋቸው።

³¹ስለዚህ ወታደሮቹ በታዘዙት መሠረት፣ ጳውሎስን ይዘው በሌሊት አስከ አንቲጳጥሮስ ድረስ ወሰዱት። ³²በማግስቱ፣ ፈረሰኞቹ ብቻ እንዲያደርሱት አድርገው፣ ሌሎቹ ወደ ጦር ሰፈር ተመለሱ። ³³ፈረሰኞቹም ቂሳርያ በደረሱ ጊዜ፣ ደብዳቤውን ለአገረ ገዥው ሰጡት፤ ጳውሎስንም አስረከቡት። ³⁴አገረ ገዥም ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ፣ ጳውሎስን ከየትኛው አውራጃ እንደ መጣ ጠየቀው፤ የኪልቅያ ሰው መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣ ³⁵"የአንተን ጒዳይ ከሳሾችህ ሲቀርቡ አያለሁ" አለው። ከዚያም ጳውሎስ በሄሮድስ ግቢ ውስጥ እንዲጠበቅ አዘዘ።

ጳውሎስ በፊልክስ ፊት ቀረበ

24 ከአምስት ቀን በኋላ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ ከአንዳንድ ሽማግሌዎችና ጠርቱሰስ ከሚባል ጠበቃ ጋር ወደ ቂሳርያ ወረደ፤ በጳውሎስም ላይ ያላቸውን ክስ ለአገረ ገዥ አቀረቡ። ²ጳውሎስ ተጠርቶ በቀረበ ጊዜ፣ ጠርጠሉስ እንዲህ ሲል ክሱን አቀረበ፤ "ክቡር ፊልክስ ሆይ፣ በአንተ ዘመን ሰላም ለብዙ ጊዜ ሰፍኖልናልና፣ አርቆ አስተዋይነትህም ለዚህ ሕዝብ መሻሻልን አስገኝቶለታል፤ ³በየቦታውና በየጊዜው ይህን ውለታ በታላቅ ምስጋና እንቀበላለን። ⁴ነገር ግን ይበልጥ እንዳላደክምህ፣ በአጭሩ እንድ ትሰማን መልካም ፈቃድህን እለምንሃለሁ።

⁵"ይህ ሰው፣ በዓለም ባሉት አይሁድ ሁሉ መካከል በሽታ ሆኖ ሁከት የሚያስነሣ፣ ደግ ሞም የናዝራውያን ወገን ቀንደኛ መሪ ሆኖ አግኝተነዋል። ⁶ከዚህም በላይ ቤተ መቅደሱን ለማርከስ ሲሞክር አግኝተን ያዝነው። በሕጋችንም መሠረት ልንፈርድበት አስ በን ነበር፤ ⁷ነገር ግን የጦር አዛዥ ሉስዮስ መጥቶ በታላቅ ኀይል ከእጃችን ነጥቆ ወሰደው፤ ከሳሾቹም ወደ አንተ እንዲመጡ አዘዘ። ⁸እንግዲህ አንተ ራስህ መርምረኸው እርሱን የከሰስንበትን ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን ልታረጋግጥ ትችላለህ።"

⁹አይሁድም ነገሩን እንደተባለው መሆ ኑን በመደገፍ በክሱ ተባበሩ።

¹⁰አገረ ገዥውም እንዲናገር በእጁ ምልክት በሰጠው ጊዜ፣ ጳውሎስ እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ከብዙ ዘመን ጀምሮ የዚህ ሕዝብ ፈራጅ መሆንህን ዐውቃለሁ፤ ስለዚህ የመከላከያ መልሴን የማቀርበው በደስታ ነው። ¹¹ልሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣሁት ከዐሥራ ሁለት ቀን በፊት መሆኑን አንተው ራስህ በቀላሉ ማረጋገጥ ትችላለህ።

ᵃ23፥23 በግሪኩ የዚህ ቃል ትርጕም አይታወቅም። ᵇ24፥6-8 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሥ 7 እና የሥ 6 ከፊል የላቸውም።

12ካህናቱም በቤተ መቅደስ ከማንም ጋር
ስከራ ክር ወይም በምንራብ ወይም በከተማ
ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ሕዝብን ሳንሣሣ
አላገኙንም። 13እሁንም ስተከሰስሁበት ነገር
ማስረጃ ሊያቀርቡልህ አይችሉም። 14ይሁን
እንጂ፣ እንርሱ ኑፋቄ በሚሉት በጌታ
መንገድ የአባቶቻችንን አምላክ አመልካለሁ፤
በሕጉ የታዘዘውንና በነቢያት የተጻፈውን
ሁሉ እምናለሁ፤ 15ደግሞም እንደነዚህ
ሰዎች ሁሉ፣ ጻድቃንና ኀጥአን ከሙታን
እንደሚነሡ በእግዚአብሔር ተስፋ አለኝ።
16ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ
ኅሊና እንዲኖረኝ ሁል ጊዜ እጥራለሁ።

17"ከብዙ ዓመት በኋላም፣ ስድሬው ወገኔ
ምጽዋትና መባ ይገር ወደ ኢየሩሳሌም
መጣሁ። 18እነርሱም በቤተ መቅደስ የመንጻት
ሥርዐት ፈጽሜ ይህንኑ ሳደርግ አገኙኝ፤
የሕዝብ ሁካታ ወይም ረብሻ አልነበረም።
19ነገር ግን ክስ ካላቸው አንተ ፊት ቀርበው
ሊከሱ የሚገባቸው ከእስያ አውራጃ የመጡ
አንዳንድ አይሁድ አለ፤ 20ወይም በዚህ
ያሉት እነዚህ በሸንጎው ፊት ቀርቤ በነበረበት
ጊዜ ያገኙብኝ ወንጀል ካለ ይናገሩ፤
21ባመካከላቸው በቆምሁበት ጊዜ ስለ ሙታን
ትንሣኤ ከተናገርሁት አንድ ነገር በስተቀር
ዛሬ ተከሰሽ የቀረብሁበት ሊላ ነገር የለም።"

24፥12 ሥሪ18፡
ሐሥ25፥8፡
28፥17
24፥13 ሐሥ25፥7
24፥14 ሥሩ5፡
ሐሥ3፥13፡ 9፥2፡
26፥6፡22፡ 28፥23
24፥15
ማቴ25፥46፡
ሐሥ23፥6፡
28፥20
24፥16 ሐሥ23፥1
24፥17
ሐሥ11፥29፡30፡
ሮሜ15፥25-
28፡31፡
1ቆሮ16፥1-4፡15፡
2ቆሮ8፥1-4፡
9፥2፡10
24፥18 ሥሩ12፡
ሐሥ21፥26
24፥19 ሐሥ23፥9፡
23፥30
24፥21 ሐሥ23፥6
24፥22 ሐሥ9፥2
24፥23
ሐሥ23፥16፡35፡
27፥3፡ 28፥16
24፥24
ሐሥ20፥21
24፥25
ኤር36፥16፡

22ፊልክስ ግን የጌታን መንገድ በሚገባ
ዐውቆ ስለ ነበር፣ "የጦር አዛዥ ሉስዮስ ሲመጣ
ለጕዳያችሁ ውሳኔ እስጣለሁ" ብሎ ነገሩን
በቀጠሮ አሳደረው። 23ከዚያም ለጳውሎስ
መጠነኛ ነጻነት እየሰጠ እንዲጠብቅ ውና
ወዳጆቹም ገብተው እንዲጠይቁት ፈቃድ
እንዲሰጣቸው የመቶ አለቃውን አዘዘው።

24ካሦቂት ቀን በኋላ፣ ፊልክስ ከአይሁ
ዳዊት ሚስቱ ከድሩሲላ ጋር መጣ፤
ጳውሎስንም አስጠርቶ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ
ማመን ሲናገር አዳመጠው። 25ጳውሎስ ስለ
ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት ስለሚመጣውም
ፍርድ በሚናገርበት ጊዜ ግን ፊልክስ
ፈርቶ፣ "ለጊዜው ይህ ይበቃል፤ ወደ ፊት
ሲመቸኝ አስጠራሃለሁ፤ አሁን ልትሄድ
ትችላለህ" አለው። 26ደግሞም ከጳውሎስ
ጉቦ ለመቀበል ተስፋ ያደርግ ስለ ነበር፣
በየጊዜው እያስጠራ ያነጋግረው ነበር።

27ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላም፣ ፊልክስ
በጶርቅዮስ ፌስጦስ ተተካ፤ ፊልክስም
አይሁድን ለማስደሰት ሲል፣ ጳውሎስን
እንደ ታሰረ ተወው።

24፥25 ሐሥ10፥42፡ ገላ5፥23፡ 1ተሰ5፥6፡
1ጴጥ4፥7፡ 5፥8፡ 2ጴጥ1፥6 24፥27 ሐሥ12፥3፡ 23፥35፡
25፥1፡4፡9፡14

24፥14 **በጌታ መንገድ**፣ በክርስቶስ የተሰጠን ድነት "የጌታ መንገድ" ይባላል (ከ9፥2፡ 16፥17፡ 19፥9፡23፡ 24፥14፡22 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የግሪክ ቃል ("ሆዶስ") የአግሪኛ መንገድን ወይም ሰፊ መንገድን የሚያመለክት ነው። የአዲስ ኪዳን አማኝ በክርስቶስ ያገኘውን ድነት የሚገነዘበው ክርስቶስን ከመቀበሉ እንጻር ብቻ ሳይሆን ከኢየሱስ ጋር ኅብረት በማድረግ በእምነት የሚጓዝበት መንገድ እንደ ሆነም ጭምር ነው። በሚመጣው ዘመን እውን ወደሚሆነው ፍጽመተ ድነት ለመግባት እስከ መጨረሻው በጽናት በዚህ መንገድ ላይ ብቻ መንዝ አለብን (በገጽ 1736 ላይ፡ "ድነትን ምኒገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩሩት ጽሑፍ ይመ)።

24፥14 **የተጻፈውን ሁሉ አምናለሁ**፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍት በሁሉም ነገር ሕጸጽ አልባና እንከን አልባ እንዲሁም ተአማኒነት ያላቸው አድርጉ ሣመኑ በእነዚህ በመጨረሻዎቹ ዘመናት በሕማና በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉትን "እንዳንድ ነገሮች" ብቻ ሣመን ይዘቃል ከሚሉ የሃይማኖት አስተማሪዎች አስተያየት ጋር በእጅጉ የሚቃረን ነው (በገጽ 1941 ላይ፡ "መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩሩት ጽሑፍ ይመ)። የክርስቶስ (ማቴ 5፥18) እንዲሁም የሐዋርያት መንፈስና ልብ ያላቸው (2ጢሞ 3፥16፡ 1ጴጥ 1፥11) ቃሉን ያምናሉ፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጻፈውን እውነት ሁሉ ለመጠበቅ ይቈማሉ። እንደዚህ ዐይነቱ ልብ የሌላቸው ግን ከታላቁ ሐዋርያ ቃል ጋር አይስማሙም።

24፥15 **ጻድቃንና ኀጥአን ከሙታን እንደሚነሡ**፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ጻድቃንና ኀጥአን ከሞት እንደሚነሡ ያስተምራል። ጻድቃን ከጌታ ጋር ለዘላለም ይኖሩ ዘንድ ቤዛነትን ባገኘው አካላቸው ሲነሡ (1ተሰ 4፥13-18) ኀጥአን ግን በእግዚአብሔር ሊፈረድባቸው ይነሣሉ (ስለ ሁለቱ ዐይነት ትንሣኤ ዳን 12፥2 ማብ፡ የሐ 5፥29 ማብ፡ ራእ 20፥6-14 ማብ ይመ)። ሁለቱ ዐይነት ትንሣኤ በተመሳሳይ ጥቅስ ውስጥ መነገራቸው ሁለቱ ክሥተቶች በአንድ ጊዜ ይፈጸማሉ ማለት አይደለም (የሐ 5፥29 ማብ ይመ)።

24፥16 **ንጹሕ ኅሊና እንዲኖረኝ**፣ ፍሬያማ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት ይኖረን ዘንድ ንጹሕ ኅሊና እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ መሣሪያዎች አንዱ እንደ ሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በገርዝር ተጠቅሶአል (2ቆሮ 1፥12፡ 1ጢሞ 1፥19)። (1) ሐሳባችንና ድርጊታችን እግዚአብሔርን የሚያስቈጣ እንደሆነ በምንረዳበት ጊዜ ንጹሕ ኅሊና የመንፈስን ውስጣዊ ነጻነት ያካትታል (23፥1 ማብ፡ መዝ 32፥1፡ 1ጢሞ 1፥5፡ 1ጴጥ 3፥16፡ 1ዮሐ 3፥21-22 ይመ)። (2) ኅሊና ሲቈሽሽ እምነት፣ የጸሎት ሕይወት፣ ከአማዚአብሔር ጋር ሊኖር የሚገባ ኅብረት እንዲሁም በጉ ሥራ የሚታይበት ሕይወት ክፉኛ ይጉዳል (ቲቶ 1፥15-16)። ሰዎች ንጹሕ ኅሊናን ቢታመሙ እምነታቸው እንዲጠፋ ማድረጋቸው ነው (1ጢሞ 1፥19)።

24፥25 **ስለ ጽድቅና ራስን ስለመግዛት ስለሚመጣውም ፍርድ**፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልክስ ፊት በኢየሱስ ክርስቶስ ስለማመን፡ "ስለ ጽድቅና ራስን ስለመግዛት ስለሚመጣውም ፍርድ" ሲሰብክ ፊልክስ እጅግ ፈራ። ይህ ሁኔታ ጌታ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ፡ "በሚመጣበትም ጊዜ ዓለምን ስለ ኀጢአት፡ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሰል" (ዮሐ 16፥8) በማለት ከተናገረው ጋር የሚመሳሰል ነው። ለሰዎች ሁሉ ድነት የሚሆነው እንዲህ ዐይነት መሠረታዊ አውነቶችን በማወጅ መንፈስ ቅዱስ ሥነ ሕሊናቸዎችን ልብ እየነካ በሚያካሂደው ሥራ ነው (ዮሐ 16፥8 እና ማብ ይመ)።

ጳውሎስ በፊስጦስ ፊት ቀረበ

25 ፊስጦስም ወደ አውራጃው ከገባ ከሦስት ቀን በኋላ ከቂሳርያ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። [2]የካህናት አለቆችና የአይሁድ መሪዎች ፊቱ ቀርበው ጳውሎስን ከሰሱት። [3]ጳውሎስን መንገድ ላይ እድፍጠው ሊገድሉት ስለ ፈለጉ፣ ፊስጦስ ለእነርሱ እንዲያዳላላቸውና ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያስመጣው አጥብቀው ለመኑት። [4]ፊስጦስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "ጳውሎስ ታስሮ በቂሳርያ እስር ቤት ይገኛል፤ እኔም በቅርቡ ወደዚያው እሄ ዳለሁ፤ [5]ስለዚህ ከባለሥልጣኖቻችሁ መካከል አንዳንዶች ከእኔ ጋር ይምጡና ሰውየው ጥፋት ካለበት ክሱን በዚያው ያቅርቡ።"

[6]ከእነርሱም ጋር ስምንት ወይም ዐሥር ቀን ያህል ከሰነበተ በኋላ ወደ ቂሳርያ ወረደ፤ በማግስቱም ፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ጳውሎስን እንዲያመጡት አዘዘ። [7]ጳውሎስ በቀረበ ጊዜ፣ ከኢየሩሳሌም የመጡት አይሁድ ከበቡትና በማስረጃ ያልተደገፉ ብዙ ከባድ ክሶችም አቀረቡበት።

[8]ጳውሎስም፣ "እኔ በአይሁድም ሕግ ሆነ በቤተ መቅደሱ ወይም በቄሣር ላይ የፈጸምሁት በደል የለም" ሲል የመከላከያ መል ሱን ሰጠ።

[9]ፊስጦስም ለአይሁድ በጎ ለመዋል ፈልጎ፣ ጳውሎስን "ስለዚህ ጕዳይ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተህ በእኔ ፊት ለመፋረድ ፈቃደኛ ነህን?" አለው።

[10]ጳውሎስም እንዲህ አለ፤ "አሁንም ቢሆን ፍትሕ ማግኘት በምችልበት፣ በቂሳር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ፤ አንተ ራስህ በሚገባ እንደምታውቀው በአይሁድ ላይ ምንም በደል አልፈጸምሁም፤ [11]ይሁን እንጂ ለሞት የሚያበቃ በደል ኩተገኝብኝ፣ አልሙት አልልም፤ እንዚህ አይሁድ የሚያቀርቡብኝ ክስ እውነት ካልሆነ ግን፣ እኔን ለእነርሱ አሳልፎ ሊሰዋ የሚችል የለም፤ ወደ ቄሳር ይግባኝ ብያለሁ።"

[12]ፊስጦስ ከመማክርቱ ጋር ኩተመካከረ በኋላ፣ "ወደ ቄሳር ይግባኝ ስላልህ፣ ወደ ቄሳር ትሄዳለህ" አለው።

ፊስጦስ ከንጉሥ አግሪጳ ምክር ጠየቀ

[13]ከጥቂት ቀንም በኋላ፣ ንጉሥ አግሪጳና በርኒቂ ፊስጦስን እጅ ሊነሡ ወደ ቂሳርያ ወረዱ፤ [14]በዚያም ብዙ ቀን ተቀመጡ፤ ፊስጦስም የጳውሎስን ጕዳይ አንሥቶ ለን ጉሡ እንዲህ አለው፤ "ፊልክስ በእስር ቤት የተወው አንድ ሰው እዚህ አለ፤ [15]ወደ ኢየሩሳሌም በሄድሁ ጊዜ፣ የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሽማግሌዎች እንድፈርድበት ክሰውት ነበር።

[16]"እኔም፣ ተከሳሽ በክሳሾቹ ፊት ቆሞ ለተከሰሰበት ነገር መልስ ለመስጠት ዕድል ሳያገ"ኘ አሳልፎ መስጠት የሮማውያን ልማድ እንዳልሆነ ነገርኋቸው። [17]ስለዚህ ከሳሾቹ ከእኔ ጋር ወደዚህ በመጡ ጊዜ፣ ጕዳዩን ሳላጓትት በማግስቱ ችሎት ተቀምጬ ያን ሰው እንዲያቀርቡት አዘዝሁ። [18]ከሳሾቹም ተነሥተው በመቆም ሲናገሩ፣ እኔ ያሰብሁትን ያህል ከባድ ክስ አላቀረቡበትም፤ [19]ይልቁን ስለ ገዛ ሃይማኖታቸውና ሞቶ ስለ ነበረው፣ ጳውሎስ ግን ሕያው ነው ስለሚለው ሰውነ ስለ ኢየሱስ ይከራከሩት ነበር። [20]እኔም ይህን ነገር እንዲት እንደምፈታው ግራ ስለገባ"ኝ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ሂዶ ስለዚህ ጕዳይ እንዲፋረድ ፈቃደኝነቱን ጠየቅሁት። [21]ነገር ግን ጳውሎስ ጕዳዩ በንጉሠ ነገሥቱ እንዲታይለት ይግባኝ ባለ ጊዜ፣ እኔም ወደ ቄሳር እስከምል ክው ድረስ እስር ቤት እንዲይ አዘዝሁ።"

[22]አግሪጳም ፊስጦስን፣ "እኔም እኩ ይህ ሰው ሲናገር መሰማት እፈልግ ነበር" አለው።

እርሱም፣ "እንግዲያውስ ነገ ትሰማዋለህ" አለው።

ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት

[23]በማግስቱም አግሪጳና በርኒቂ በታላቅ ክብር መጥተው፣ ከከፍተኛ መኰንኖችና ከከተማዪቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ወደ መሰ ብሰቢያው አዳራሽ ገቡ፤ በፊስጦስም ትእዛዝ ጳውሎስ እንዲቀርብ ተደረገ። [24]በዚህ ጊዜ ፊስጦስ እንዲህ አለ፤ "ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ እንዲሁም እዚህ አብራችሁን ያላችሁ ሁሉ፤ ይህን ሰው ታዩታላችሁ? በአ, የሩሳሌምና እዚህ በቂሳርያም የሚኖሩ አይሁድ ሁሉ፣ ይህ ሰው ከእንግዲህ በሕይወት መኖር አይገባውም በማለት እየጮኹ ለመኑ። [25]እኔም ለሞት የሚያበቃ እንዳች ነገር አለ ማድረጉን ተረዳሁ፤ ሆኖም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ይግባኝ በማለቱ ወደ ሮም ልልከው ወሰንሁ። [26]ነገር ግን ስለ እርሱ ወደ ጌታዬ የምጽፈው የተረጋገጠ ነገር አላገኘሁም፤ ስለዚህም ኩተመረመረ በኋላ የም ጽፈውን

25፥8 በአይሁድ ሕግ ... የፈጸምሁት በደል የለም፤ ሐዋርያው ጳውሎስ በአይሁድም ሆነ በሕጉ ላይ ምንም ዐይነት በደል እንዳልፈጸመ ያውቃል፤ በእርግጥም የብሉይ ኪዳንን ግብረገባዊ ሕግ ጠብቆአል (ከ21፥24 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር ካለው በላይ የሕጉ ግብረገባዊ መለኪያዎች ሊለወጡ አይችሉም። ለእርሱ ሕጉ የእግዚአብሔርን ባሕርይና የጽድቅ ሕይወት መስፈርቶች የሚገልጽ (ከማቴ 5፥18-19 ጋር ያነጻጽሩ) ቅዱስ፤ በጐና መንፈሳዊ ነው (ሮሜ 7፥12፤14)። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ራሱን ለማጽደቅ ሕጉን እንደ ደንብ ወይም እንደ የሕይወት መስፈርት አድርጎ አልጠበቀውም። የጽድቅ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ በሰው ሕይወት ውስጥ በሚሠራው ሥራ ይገኛል፤ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ያለንን ፍላጐት በመግለጽ የእግዚአብሔርን ሕግ በተሳካ ሁኔታ ልንታዘዝ የምንችለው በክርስቶስ ጸጋ ዳግም ልደትን ካገኘን በኋላ ብቻ ነው። በክርስቶስ ሕግ ሥር ከሆንን ከእግዚአብሔር ሕግ ውጭ አንሆንም (1ቆሮ 9፥21፤ ማቴ 5፥17 ማብ፤ ሮሜ 3፥21፤ 8፥4 ይመ)።

25፥1፡ ሐሥ8፥40፤ 24፥27
25፥2 ቍ15፤ ሐሥ24፥1
25፥3 ሐሥ20፥3
25፥4 ሐሥ8፥40፤ 24፥23
25፥6 ቍ10:17
25፥7 ማር15፥3፤ ሉቃ23፥2፡10፤ ሐሥ24፥5፡6:13
25፥8 ሐሥ6፥13፤ 24፥12፤ 28፥17
25፥9 ቍ20፤ ሐሥ12፥3፤ 24፥27
25፥10 ቍ8
25፥11 ቍ21፡25፤ ሐሥ26፥32፤ 28፥19
25፥13 ሐሥ8፥40
25፥14 ሐሥ24፥27
25፥15 ቍ2፡ ሐሥ24፥1
25፥16 ቍ4:5፤ ሐሥ23፥30
25፥17 ቍ6:10
25፥19 ሐሥ17፥22፡ 18፥15፤ 23፥29
25፥20 ቍ9
25፥21 ቍ11፡12
25፥22 ሐሥ9፥15
25፥23 ቍ13፤ ሐሥ26፥30
25፥24 ቍ2:3:7፤ ሐሥ22፥22
25፥25 ቍ11፤ ሐሥ23፥9

ነገር ለማግኘት ሁላችሁም ፊት በተለይ ደግሞ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ በእንተ ፊት አቀርብሁት፤ 27ይኸውም እንድ እስ ረኛ ወደ በላይ ሲላክ የተከሰሰበትን ምክንያት አለመግለጽ ትክክል ስላልመሰለኝ ነው።"

26 አግሪጳም ጳውሎስን፣ "ስለ ራስህ እንድትናገር ተፈቅዶልሃል" አለው። ፡ በዚህ ጊዜ ጳውሎስ እጁን ዘርግቶ እንዲህ ሲል መከላከያውን አቀረበ፤ 2"ንጉሥ አግ ሪጳ ሆይ፤ አይሁድ በእኔ ላይ ላቀረቡት ክስ ሁሉ ዛሬ በፊትህ የመከላከያ መልስ ለማቅረብ በመቻሌ ራሴን እንደ ዕድለኛ እ3ቆጥ ሮለሁ፤ 3ይኸውም አንተ በተለይ የአይሁድን ልማድና ክርክር ሁሉ በሚገባ ስለምታውቅ ነው፤ ስለዚህ በትዕግሥት እንድታደምጠኝ እለምንሃለሁ።

4"ገና ከልጅነቴ ጀምሮ፣ በአገሬም ሆነ በኢየሩሳሌም እንዴት እንደኖርሁ አይሁድ ሁሉ ያውቃሉ፤ 5ደግሞም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ስለሚያውቁኝ ከሃይማኖታችን እጅግ ጥብቅ በሆነው ወገን ውስጥ ሆኜ እንደ አንድ ፈሪሳዊ መኖሬን ሊመሰክሩ ፈቃደኞች ከሆኑ ቃላቸውን ሊሰጡ ይችላሉ። 6አሁንም ተከሰሽ እዘህ የቀረብሁበት ምክንያት ስዝእስብሔር ለአባቶቻችን ቃል የገባውን ነገር ተስፋ በማድረጌ ነው። 7ዐሥራ ሁለቱ ነገዶቻችን ቀንና ሌሊት እግዚአብሔርን ከልብ እያገለገሉ፣ ሲፈጸም ለማየት የሚተጉለትም ተስፋ ይኸው ነው። ንጉሥ ሆይ፤ አይሁድም የሚከሱኝ ስለዚሁ ተስፋ ነው። 8ለመ ሆኑ፣ እግዚአብሔር ሙታንን ማስነሣት እንደማይችል አድርጋችሁ የምትቍ3ሩት ለምን ድን ነው?

9"እኔም ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን ስም በምችለው መንገድ ሁሉ መቃወም እንዳለብኝ ወስኜ ነበር። 10በኢየሩሳሌምም ያደረግሁት ይህንኑ ነበር፤ ከካህናት አለቆች ሥልጣን ተቀብዬ ብዙ ቅዱሳንን አሳስሬ

26፥1 ሐሥ9፥15፣ 12፥17፣ 25፥22
26፥2 መዝ119፥46፣ ሐሥ24፥1፡5፣ 25፥2፡7፥11
26፥3 ቍ7፣ ሐሥ6፥14፣ 25፥19
26፥4 ገላ1፥13፡14፣ ፊል3፥5
26፥5 ሐሥ22፥3፣ 23፥6፣ 24፥5፣ ፊል3፥5
26፥6 ሐሥ13፥32፣ 23፥6፣ 24፥15፣ 28፥20፣ ሮሚ15፥8
26፥7 ቍ2፣ 1ተሰ3፥10፣ 1ጢሞ5፥5፣ ያዕ1፥1
26፥8 ሐሥ23፥6
26፥9 ዮሐ15፥21፣ 16፥2፣ 1ጢሞ1፥13
26፥10 ሐሥ8፥3፣ 9፥2፡13፡14፡21፣ 22፥20
26፥11 ማቴ10፥17
26፥14 ዮሐ5፥2፣ ሐሥ9፣7
26፥16 ሕዝ2፥1፣ ዳን10፥11፣ ሐሥ22፥14፡15
26፥17 ኤር1፥8፡19፣ ሐሥ9፥15፣ 13፥46
26፥18 መዝ18፥28፣ ኢሳ35፥5፣ 42፥7፡16፣ ሉቃ24፥47፣ ሐሥ2፥38፣ 20፥21፣ አለሁ፤ በመገደላቸውም ተስማምቻለሁ፤ 11ሳስቀጣቸውም ብዙ ጊዜ ከምኵራብ ምኵራብ እየተዘዋወርሁ፣ የስድብ ቃል እንዲ ናገሩ አስገድዳቸው ነበር፤ በቍጣም ተሞልቼ በውጭ አገር እስከሚገኙ ከተሞች ድረስ ተከታትዬ አሳደድኋቸው።

12"በዚህ መሠረት አንድ ቀን ከካህናት አለቆች ሥልጣንና ትእዛዝ ተቀብዬ ወደ ደማስቆ በምጓዝበት ጊዜ፣ 13ንጉሥ ሆይ፤ እኩለ ቀን ላይ በመንገድ ሳለሁ፣ ብሩህነቱ ከፀሓይ የሚበልጥ ብርሃን በእኔና በባልንጀሮቼ ዙሪያ ከሰማይ ሲያበራ አየሁ፤ 14ሁላችንም በምድር ላይ ወደቅንና እኔም በዕብራይስጥ ቋንቋ፣ 'ሳውልኤ፣ ሳውልኤ፣ ለምን ታሳድደኛለህ? መውጊያውን መታፋት ጉዳቱ በአንተ ይብሳል' የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ።

15"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?' " አልሁ።

"ጌታም እንዲህ አለኝ፤ 'እኔ፣ አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ። 16አሁንም፣ ተነሣና በእግርህ ቁም፤ ስለእኔ ስላየኸውና ወደ ፊትም ስለማሳይህ ነገር አገልጋይና ምስክር እንድትሆን ልሾምህ ተገልጬልሃለሁ። 17ከገዛ ሕዝብህና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ፤ 18አንተም ዐይናቸውን ትከፍታለህ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሰይ ጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ትመልሳቸዋለህ፤ እነርሱም የኃጢአትን ይቅርታ ይቀበላሉ፤ በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስት ያገኛሉ።'

19"እንግዲህ፣ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ ከሰማይ ለታዮኝ ራእይ አልታዘዝ አላልሁም፤ 20ነገር ግን በመጀመሪያ በደማስቆ ለሚ

26፥18 ኤፌ5፥8፣ ቈላ1፥13፣ 1ጴጥ2፥9 26፥19 ኢሳ50፥5 26፥20. ኤር18፥11፣ 35፥15፣ ማቴ3፥8፣ ሉቃ3፥8፣ ሐሥ3፥19፣ 9፥15፡19-25፡26-29፣ 13፥46፣ 22፥17-20

[a] 26፥14 ወይም አራማይክ

26፥18፤ ይህ ለጳውሎስ የተሰጠው መለኮታዊ ተልእኮ ነው። ይህ ዋቅስ ወንጌልን ለጠፉት ከመስበክ አንጻር ጌታ ኢየሱስ የሚፈልገውን ሐሳብ የሚገልጽ የታወቀ ወረፍተ ነገር ነው።

(1) "ዐይናቸውን ትከፍታለህ"። ሰዎች የጠፉና የወደቁ መሆናቸውን እንዳይገነዘቡ እንዲሁም የወንጌልን እውነት እንዳይረዱ ሰይጣን አሳውሮአቸዋል (2ቆሮ 4፥4)። በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ መስበክ ዐይናቸው ተከፍተው እንዲያስተውሉ ያደርጋል (ከ2ቆሮ 4፥5፣ ከኤፌ 1፥18 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) "ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ትመልሳቸዋልህ"። ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዥ ነው፣ በክርስቶስ ያላመኑ ሁሉ በእርሱ ቍጥጥር ሥርና የሥልጣኑ ባሪያዎች ናቸው። የሰይጣን መንፈስ በኀጢአተኞች ሁሉ ውስጥ ማለትም "በማይታዘዙት ሰዎች ላይ" (ኤፌ 2፥2) ይሠራል። በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ወንጌል ሲሰበክ፣ ሰዎች ከሰይጣን ኀይል ነጻ ይወጣሉ፣ ወደ ክርስቶስም መንግሥት ይገባሉ (ቈላ 1፥13፣ 1ጴጥ 2፥9 ይመ)።

(3) "እነርሱም የኃጢአትን ይቅርታ ይቀበላሉ"። ይቅርታ የሚገኘው፣ እርሱ የመሥዋዕትነትን ሞት በመስቀል ላይ እንደሞተ መሠረት በማድረግ በክርስቶስ ላይ ባለ እምነት ነው።

(4) "በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስት ያገኛሉ"። ምሕረትን የተቀበለ፣ ከኀጢአትና ከሰይጣን እስራት ነጻ የወጣ፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነና በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ከዓለም ተለይቶ አሁን በክርስቶስ በማመን ከዳኑት ሁሉ ጋር ኅብረት በሚደረግ ለእግዚአብሔር ይኖራል።

26፥19 አልታዘዝ አላልሁም፤ ጳውሎስ በክርስቶስ አምኖ የተለመጠው ወደ ደማስቆ ሲጓዝ በመንገድ ላይ ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስን ጌታውና አዳኙ አድርጎ በመቀበል እርሱን ለመታዘዝ ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ሰጠ (ከሮሚ 1፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

26፥20 ንስሓ እንዲገቡና ... የንስሓም ፍሬ እንዲያሳዩ፤ አንዳንዶች እንደሚያደርጉት ድነት የሚገኘው "በክርስቶስ በማመንና የሚያስተሰርየውን ሞቱ በመቀበል ብቻ ነው" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ አልሰበከም። የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት አንድ ሰው "ንስሓ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር ካልተመለሰና የንስሓ ፍሬ ካሳየ" ድነትን ፍጹም እንደማያገኝ አጥብቀው አስተምረዋል (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን ያትኩሩት ጽሑፍ ይመ)።

ኖሩ፤ ቀጥሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላሉት ሁሉ፣ ከዚያም ለአሕዛብ፣ ንስሓ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ፣ የን ስላም ፍሬ እንዲያሳዩ ገልጬ ተናገርሁ። 21አይሁድም በመቅደስ ይዘው ሊገድሉኝ የሞከሩት በዚሁ ምክንያት ነው። 22የእግዚአብሔር ርዳታ እስከ ዛሬ ስላልተለየኝ፣ እነሆ፤ እዚህ ቆሜ ለትንሹም ለትልቁም እመሰክራለሁ፤ ነቢያትና ሙሴ ይሆናል ይፈጸማል ካሉት በስተቀር አንዳች ነገር አልተናገርሁም፤ 23ይኸውም ክርስቶስ መከራን እንደሚቀበልና ከሙታን ቀዳሚ ሆኖ በመነሣት ለሕዝቡና ለአሕዛብ ብርሃንን እንደ ሚሰብክ ነው።"

24ፊስጦስም የጳውሎስን ንግግር እዚህ ላይ በማቋረጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "ጳውሎስ ሆይ፤ አእምሮህን ስተሃልኛ፤ የትምህርትህም ብዛት አሳብዶሃል" አለው።

25ጳውሎስ ግን እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ክቡር ፊስጦስ ሆይ፤ የምናነባረው እውነተኛና ትክክለኛ ነገር እንጂ አብድስ አይደ ለሁም። 26ይህን የምናነባረውን ነገር ንጉሡ ያውቀዋልና፤ በፊቱ በልበ ሙሉነት እናገራለሁ፤ ደግሞም በድብቅ የተደረገ ነገር ባለመኖሩ፣ ከዚህ ነገር አንድም እንደማይሰወርበት ርግጠኛ ነኝ። 27ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ ነቢያትን ታምን የለም ወይ? እምንኝ እንደምታምን ዐውቃለሁ።"

28አግሪጳም ጳውሎስን፣ "እንዲህ በቀላሉ ክርስቲያን የምታደርገኝ ይመስልሃልን?" አለው።

29ጳውሎስም፣ "በቀላሉም ሆነ በብዙ፣ እንተ ብቻ ሳትሆን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ፣ ከዚህ ከታሰርሁበት ሰንሰለት በስተቀር፣ እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔርን እለምናለሁ" አለ።

30ከዚህ በኋላ ንጉሡም፣ አገረ ገቦም፣ በርኒቄም፣ ከእነርሱ ጋር የተቀመጡትም ተነሡ፤ 31ወጥተውም ሲሄዱ፣ "ይህ ሰው እንኳን ለሞት ለእስራት የሚያበቃው ነገር አላደረገም" ተባባሉ።

32አግሪጳም ፊስጦስን፣ "ይህ ሰው ወደ ቄሳር ይግባኝ ባይል ኖሮ መልቀቅ ይቻል ነበር" አለው።

ጳውሎስ በመርከብ ወደ ሮም ተወሰደ

27 ወደ ኢጣሊያ እንድንሄድ በተወሰነ ጊዜ፣ ጳውሎስንና ሌሎችን እስረኞች የንጉሡ ነገሥቱ ክፍለ ጦር አባል ለሆነው፣ ዩልዮስ ለተባለ የመቶ አለቃ አስረከቧቸው። 2ከአድራሚቲስ ተነሥቶ በእስያ አውራጃ ባሉ ወደቦች ላይ ወዳሉት ወደቦች በሚሄደው መርከብ ተሳፍረን የባሕር ጕዞ ጀመርን፤ በተሰሎንቄ ይኖር የነበረው የመቄዶንያ ሰው፣ አርስጥሮኮስም ከእኛ ጋር ነበረ።

3በሚቀጥለው ቀን ሲዶና ደረስን፤ ዩልዮስም ለጳውሎስ ደግነት በማሳየት ወደ ወዳጆቹ ሄዶ ርዳታ እንዲቀበል ፈቀደለት።

4ከዚያም ተነሥተን በባሕር ተጓዝን፤ ነፋስ ከፊት ለፊት ስለገጠመን፣ የቆጵሮስን ደሴት ተገን አድርገን ሀለፍን። 5በኪልቅያና በጵንፍሊያ ዳርቻ ያለውን ባሕር ከተሻገርን በኋላ በሉቅያ አገር ሙራ የተባለ በታ ደረስን። 6ከዚያም የመቶ አለቃው ወደ ኢጣሊያ የሚሄድ የእስክንድርያ መርከብ አግኝቶ አሳፈረን። 7ብዙ ቀን በዝግታ እየተ ጓዝን ቀኒዶስ አካባቢ በድንት ደረስን፤ ነፋሱም ወደ ፊት እንዳንሄድ በከለከለን ጊዜ፣ በሰልሙና አጠገብ አድርገን በቀርጤስ ተተ ግነን ሄድን፤ 8ዋግ ጥቂንም ይዘን፣ በላሲያ ከተማ አጠገብ ወዳለው፣ 'መልካም ወደብ' ወደ ተባለ ስፍራ በሞንት ደረስን።

9ብዙ ጊዜ ባክኖ፤ የጸሙ ጊዜ ስላለፈ በመርከብ መጓዙ አደገኛ ሆኖ ነበርና ጳውሎስ፣ 10"እናንት ሰዎች፤ ጕዞው አደገኛ እንደሚሆን፣ በመርከቡና በሞንቱ እንዲሁም በእኛ በራሳችን ላይ እንኳ ትልቅ ጕዳት እንደሚደርስ ይታየኛል" ብሎ አስ ጠነቀቃቸው። 11የመቶ አለቃው ግን ከጳውሎስ ምክር ይልቅ የመርከቡ መሪና የመርከቡ ባለቤት ያሉትን ይሰማ ነበር። 12ክረምቱንም በዚያ ለማሳለፍ ወደቡ አመቺ ስላልነበረ፣ አብዛኞቹ ፍንቂ ወደ ተባለው ወደብ ደርሰው በዚያ ለመክረም ተስፋ በማድረግ ጕዞአችንን እንድንቀጥል ውሳኔ አስተላለፉ፤ ወደቡም በቀርጤስ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ ትይዩ የሚገኝ ነበር።

የባሕሩ ማዕበል

13መጠነኛ የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜም እንዳሰቡት የሆነላቸው መስሎአቸው መልሕቁን ነቅለው፣ የቀርጤስን ዳርቻ በመያዝ ተጓዙ። 14ብዙም ሳይቈይ ግን፣ 'ሰሜናዊ ምሥራቅ' የሚሉት ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ከደሴቲቱ ተነሥቶ ቍልቍል መጣባቸው። 15መርከቢቱም በማዕበሉ ስለ ተያዘች፣ ወደ ነፋሱ ልትገፋ አልቻለችም፤ ስለዚህ መንገድ ለቀን በነፋሱ ተነዳን። 16ቄዳ የተባለችውን ትንሽ ደሴት ተገን አድርገን በማለፍ፣ የመርከቢን ሕይወት አድን ጀልባ በብዙ ደክሙ ለማትረፍ ቻልን፤ 17ጀልባዋ ንም ወደ ላይ ጐትተው ካወጧት በኋላ መር ከቧ እንዳትፈራርስ ዙሪያዋን በገመድ ለም ጥመው አሰሯት፤ ስርቲስ ከተባለው አሸዋማ ደለል ጋር ሄዶ እንዳይላተሙ ስለ ፈሩም፣ የመርከቧን ሸራ አውርደው እንዲሁ በዘረቀዩ እንድትነዳ አደረጉ። 18ማዕበሉም ክፉኛ ስላንገላታታን፣ በማግስቱ ሞኙቱን እያሙ ወደ ባሕር ይጥሉ ጀመር፤ 19በሦ ስተኛውም ቀን፣ የመርከቢን ሸራ ማውጫና ማውረጃ መሣሪያ በገዛ እጃቸው ነቃቅለው ወደ ባሕር ጣሉት። 20ብዙ ቀን፣ ፀሓይንም ከዋክብትንም ማየት ስላልተቻለና ነፋስ ስለ በረታብን፣ ለመትረፍ የነበረን ተስፋ ሁሉ ተሟጠጠ።

21ሰዎቹ እህል ሳይቀምሱ ብዙ ቀን ከቈዩ

---

*26፥23 ወይም መሲሕ

+27፥9 የዐርዮትን ዕለት ያሳያል።

26፥21 ሐሥ21፥27፣30፣31
26፥22 ሉቃ24፥27፣44፤ ሐሥ10፥43፤ 24፥14
26፥23 ማቴ16፥21፤ ሉቃ2፥32፤ 1ቆሮ15፥20፣23፤ ቈላ1፥18፤ ራእ1፥5
26፥24 ዮሐ7፥15፤ 10፥20፤ 1ቆሮ4፥10
26፥25 ሐሥ23፥26
26፥26 ቍ3
26፥28 ሐሥ11፥26
26፥29 ሐሥ21፥33
26፥30 ሐሥ25፥23
26፥31 ሐሥ23፥9
26፥32 ሐሥ25፥11፤ 28፥18
27፥1 ሐሥ10፥1፤ 16፥10፤ 18፥2፤ 25፥12፥25
27፥2 ሐሥ2፥9፤ 16፥9፤ 17፥1፤ 19፥29
27፥3 ቍ43፤ ማቴ11፥21፤ ሐሥ24፥23፤ 28፥16
27፥4 ቍ7
27፥5 ሐሥ2፥10፤ 6፥9
27፥6 ቍ41፤ ሐሥ18፥22፤ 25፥12፥25፤ 28፥11
27፥7 ቍ4፥12፥13፥21፤ ቲቶ1፥5
27፥9 ዘሌ16፥29-31፤ 23፥27-29፤ ዘኍ29፥7
27፥10 ቍ21
27፥12 ቍ7
27፥14 ማር4፥37
27፥16 ቍ30
27፥17 ቍ26፥39
27፥18 ቍ19፥38፤ ዮና1፥5
27፥21 ቍ7፥10

በኋላ፣ ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እንዲህ አለ፤ "እናንት ሰዎች ሆይ፤ የነገርኋችሁን ሰምታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ ከቀርጤስ ባልተነሣችሁና ይህ ጕዳትና ጥፋት ባልደረሰባችሁ ነበር። 22አሁንም ቢሆን አይዟችሁ መርከቢ እንጂ ከእናንተ አንዲት ነፍስ እንኳ አትጠፋምና። 23በትላንትናዋ ሌሊት፣ የአ ርሱ የሆንሁትና የማመልከው እግዚአብሔር የላከው መልአክ በአጠገቤ ቆሞ፣ 24 'ጳውሎስ ሆይ፤ አትፍራ፤ በቄሳር ፊት መቆም ይገባሃል፤ ከአንተ ጋር የሚጓዙትንም ሰዎች ሕይ ወት እግዚአብሔር አትርፎልሃል' አለኝ። 25ስለ ዚህ፣ እናንት ሰዎች ሆይ፤ አይዞአችሁ እርሱ እንደ ነገረኝ እንደዚ ያው እንደሚሆን በእግዚአብሔ አምናለሁና። 26ይሁን እንጂ፣ ወደ አንዲት ደሴት በናፋስ ተወሰደን እዚ ያ መጣላችን አይቀርም።"

በመርከቡ አደጋ መድፈሉ

27በዐሥራ አራተኛው ሌሊት በአድሪያ ባሕር ላይ ከወዲያ ወዲህ ስንንሳፈት፣ እኩለ ሌሊት ገደማ መርከበኞቹ ወደ መሬት የተቃረቡ መሰላቸው፤ 28የቁልቁት መለኪ ያውን ገመድ ወደ ታች ጥለው ሲመለከቱት ያሥሃው ጥልቀት አርባ ሜትር ያህል ሆኖ አገኙት፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ደግመው ሲጥሉ ጥልቀቱ ሠላሳ ሜትር ያህል ሆነ። 29ከቋጥኞቹም ጋር እንዳንላተም በመፍራት፣ አራት መልሕቆች ከመርከቡ ብስተ ኋላ ጣሉ፤ ምነው በነጋ አያሉም ይለምኑ ነበር። 30መርከበኞቹም ከመርከቡ በስተ ፊት መልሕቅ ይሚጥሉ መስለው፣ ትንሿን ጀልባ በማውረድ ከመርከቧ ሊያመልጡ ሞከሩ። 31ጳውሎስም የመቶ አለቃውንና ወታደሮቹን፣ "እነዚህ ሰዎች መርከቡ ላይ ካልቁዩ እናንተም ልትተርፉ አትችሉም" አላቸው። 32በዚህ ጊዜ ወታደሮቹ ገመዶቹን ቈርጠው ትንሿ ጀልባ ባሕሩ ላይ ተን ሳፋ እንድትቀር ለቀቋት።

33ልክ ሊነጋጋ ሲል፣ ጳውሎስ ሁሉም ምግብ እንዲበሉ አንዲህ ሲል ለመናቸው፤ "ዐሥራ አራት ቀን ሙሉ ልባችሁ ተንጠልጥሎ ምንም ሳትቀምሱ ጠማችሁን ሰነበታችሁ፤ 34ስለዚህ ስለሚያበረታችሁ አሁን እህል እንድትቀምሱ እለምናችኋለሁ፤ ከእ ናንተ መካከል ከራሱ ጠጕር አንዲት እንኳ የሚነካበት ማንም የለምና።" 35ይህን ካለ በኋላም፣ እንጀራ ይዞ በሁሉም ፊት እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ቈርሶም ይበላ ጀመር። 36ሁሉም ተበራቱና እንጀራውን ራሳቸው ወስደው በሉ። 37በመርከቡም ላይ በአጠቃ ላይ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሰዎች ነበርን። 38በልተውም ከጠገቡ በኋላ ስንዴውን ወደ ባሕር በመጣል የመርከቡን ክብደት አቃለሉ።

39በነጋም ጊዜ፣ ወደ የብስ መቅረባቸውን አላወቁም ነበርኤ ነገር ግን ዳር ዳሩ አሸዋማ የሆነ የባሕር ሰርጥ አይተው፣ ቢቻላቸው መርከቡን ገፍተው ወደዚያ ለማድረስ ወሰኑ። 40ከዚያም መልሕቆቹን ፣ርገው ባሕር ውስጥ ዋለው ሄዱ፤ የመቅዘፊያውንም ገመድ በዚያው ጊዜ ፊቱ የፊተኛውንም ሸራ ለነፋስ ከፍ አድርገው ወደ ባሕሩ ዳርቻ አቀኑ። 41ነገር ግን መርከቡ ከአሸዋ ቀ-ልል ጋር ተላትሞ፤ መሬት ነካ፤ የፊተኛው ክፍሉም አሸዋው ውስጥ ተቀርቅሮ አል ነቃነት አለ፤ የኋለኛው ክፍሉም በማዕበሉ ክፉኛ ስለ ተመታ ይሰባበር ጀመር።

42ወታደሮቹም ከእስረኞች ማንም ዋኝቶ ለማምለጥ ቢሞክር ለመግደል ተስማሙ። 43የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስ እንዲተርፍ ስለ ፈለገ፣ ያሰቡትን እንዳይፈጽሙ ከለከላቸው፤ መዋኘት የሚችሉ ከመርከብ እየዘለሉ አስቀድመው ከባሕሩ ወደ ምድር እንዲወጡ፣ 44የተቀሩት ደግሞ በሳንቃዎች ወይም በመርከቡ ስብርባሪ እየተንጠላጠሉ እንዲወጡ አዘዘ። በዚህ መንገድ ሁሉም በደኅና ወደ ምድር ደረሱ።

ጳውሎስ በማላጥያ ደሴት

28በደኅና ወደ ምድር ከደረስን በኋላ ደሴቲቱ መላጥያ ተብላ እንደምትጠራ ተረዳን። 2የደሴቲቱ

ሮሜ 4፡19-21

27፡22 ቁ-25፡36.
27፡23 ሐሥ5፡19፡ 18፡9፣ 23፡11፣ ሮሜ1፡9፡ 2ጢሞ4፡17
27፡24 ቁ-44፡ ሐሥ23፡11
27፡25 ቁ-22፡36፣ ሮሜ4፡20፡21
27፡26 ቁ-17፡39፡ ሐሥ28፡1
27፡30 ቁ-16
27፡31 ቁ-24
27፡34 ማቴ10፡30
27፡35 ማቴ14፡19
27፡36 ቁ-22፡25
27፡38 ቁ-18፡ ዮና1፡5
27፡39 ሐሥ28፡1
27፡40 ቁ-29
27፡41 2ቆሮ11፡25
27፡43 ቁ-3
27፡44 ቁ-22፡31
28፡1 ሐሥ16፡10፡ 27፡26፡39

[a] 27፡27 በጥንት ጊዜ ይህ ስም ሰፊውን የኢጣሊያ ደቡባዊ ክፍል ያመለክታል።

27፡24 ጳውሎስ ሆይ፤ አትፍራ፤ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ሕይወት በምድር ላይ ስፍራና ዕላማ አስነለው ድረስ እንዲህም ይህ ሰው እግዚአብሔርን አስከፈለገና የመንፈስ ቅዱስን ምሪት አስከተከተለ ድረስ (ከ23፡11፡ ከ24፡16 ጋር ያነጻጽሩ) እግዚአብሔር ያንን ሰው ከሞት ይጠብቀዋል። የእግዚአብሔር ታማኞች የሆኑ ሁሉ፤ «አምላክ ሆይ፣ መጠጊያዬ ነህና በከለላዉ ሰውረኝ» (ከመዝ 16፡1-2 ጋር ያነጻጽሩ) ብለው የመጸለይ መብት አላቸው።

27፡25 እይዞአችሁ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ጊዜ በመርከብ ውስጥ አስረኛ ነበር፡ ይሁን እንጂ ከእርሱ ጋር አስረኛ የነበሩት በመርከቡ ላይ በደረሰው ዐደጋ ምክንያት ተሸብረው ሽባ ሲሆኑ፣ እርሱ ግን በክርስቶስ ነጻ ከመሆኑ የተነሣ በእግዚአብሔር ሀልዎት ከፍርሀት ነጻ ነበር። በዚህ ዓለም ሕይወት ያእግዚአብሔርን ቅርብነት የተረዳ እውነተኛና ታማኝ አማኝ የሚጥሥመው ዐደጋ በክርስቶስ ባለ ድፍረትና ዋስትና ሊጋፈጥ ይችላል።

27፡31 እነዚህ ሰዎች መርከቡ ላይ ካልቁዩ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የተናገረው ዐረፍተ ነገር በቁጥር 22 እና 24 ላይ ከተገለጸው ጋር የሚቃረን ይመስላል። ከእርሱ ጋር በመርከብ ላይ የተሳፈሩትን መንገደኞች ሕይወት እንደሚያተርፍ እግዚአብሔር ለሐዋርያው ጳውሎስ ቃል ከገባለትና (ቁ- 24) ጳውሎስም አርግጠኛ በመሆን የተገበውን ቃል፣ «አንዲት ነፍስ እንኳ አትጠፋምና» (ቁ- 22) በማለት ከተናገረ የመርከበኞቹ ማምልጥ ለተሳፋሪዎቹ መሞት እንዴት ምክንያት ሊሆን ይችላል? መልሱ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የሚከተለው ነው፣ የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል መፈጸም የሚወሰነው ሕዝቡ ፈቃዱን በመታዘዛቸው ነው (ዘፍ 1፡26-31 እና 6፡5-7፣ ዘፀ 3፡7-8 እና ዘጸ 14፡28-34፣ 2ሳሙ 7፡12-16 እና 1ነገ 11፡11-13፣ 12፡16)።

ነዋሪዎችም የሚያስገርም ደግነት አሳዩን፤ ዝናብና ብርድ ነበርና እሳት አንድደው ሁላችንን ተቀበሉን። ³ጳውሎስም ሴራሮ ሰብስቦ ወደ እሳቱ ሲጨምር፣ ከሙቀቱ የተነሣ እፉኝት ወጥታ እጁ ላይ ተጣበቀች። ⁴የደሴቲቱ ነዋሪዎች እባብ በእጁ ላይ ተንጠልጥላ ባዩ ጊዜ፣ "ይህ ሰው በርግጥ ነፍስ ገዳይ ነው፤ ከባሕር ቢያመልጥ እንኳ የፍርድ አምላክ በሕይወት እንዲኖር አልፈቀደለትም" ተባባሉ። ⁵ጳውሎስ ግን እባቢቱን ወደ እሳቱ አራገፋትና አንዳችም ጒዳት አልደረሰበትም። ⁶ሰዎቹ ከአሁን አሁን ሰውነቱ ያብጣል ወይም ድንገት ሞቶ ይወድቃል ብለው ይጠባበቁ ነበር፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ጠብቀው ምንም የተለየ ነገር እንዳልደረሰበት ባዩ ጊዜ፣ ሐሳባቸውን ለውጠው፣ "ይህስ አምላክ ነው" አሉ።

⁷በዚያም ሰፍራ አጠገብ የደሴቲቱ አለቃ የፑፕልዮስ ርስት የሆነ መሬት ነበረ፤ እርሱም በቤቱ ተቀብሎን ሦስት ቀን በወዳጅነት አስተናገደን። ⁸የፑፕልዮስም አባት በትኵሳትና በተቅማጥ ሕመም ተይዞ ተኝቶ ነበር፤ ጳውሎስም ሊጠይቀው ገብቶ ከጸለየለት በኋላ እጁን ጭኖ ፈወሰው። ⁹ይህም በሆነ ጊዜ፣ በደሴቲቱ የነበሩ ሌሎች ሕመምተኞችም እየመጡ ተፈወሱ። ¹⁰እኛንም በብዙ መን ገድ አከበሩን፤ በመርከብም ለመሄድ በተዘጋጀን ጊዜ፣ የሚያስፈልገንን ሁሉ ሠጡልን።

ጳውሎስ ሮም ደረሰ

¹¹ከሦስት ወር በኋላም፣ በደሴቲቱ ክረምቱን ቆሞ በሰነበተ በእንድ መርከብ ተነሥተን ጒዞ ጀመርን። ይህም መርከብ የእስክንድርያ ሲሆን፣ በላዩ ላይ የመንታ አማልክቱ የዲዮስቆሮስ አርማ ነበረበት። ¹²ወደ ሰራኩስ ከተማ ገብተን ሦስት ቀን በዚያ ተቀመጥን። ¹³ከዚያም በመርከብ ተጒዘን ሬጊዩም ደረስን፤ በማግስቱም የደቡብ ነፋስ ስለ ተነሣ ፑቲዮሉስ የደረስነው በሚቀጥለው ቀን ነበር። ¹⁴በዚያም ወን ድሞችን አገኘንና እነርሱምሰባት ቀን አብረናቸው እንድንቀመጥ ለመኑን፤ ከዚያም በኋላ ወደ ሮም ሄድን። ¹⁵በዚያ የነበሩ ወንድሞችም መምጣታችንን ስለ ሰሙ፣ እስከ አፍዩስ ፋሩስና፣ እንዲሁም 'ሦስት ማደሪያ' እስከሚባለው ቦታ ድረስ ሊቀበሉን ወጡ፤ ጳውሎስም ባያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ተጽናናም። ¹⁶ሮም በደረሰን ጊዜም፣ ጳውሎስ ይጠብቀው ከነበረው መኮንደር ጋር፣ ለብቻው በዚያ እንዲቈይ ተፈቀደለት።

ጳውሎስ በጥበቃ ሥር ሆኖ ሰበከ

¹⁷ከሦስት ቀንም በኋላ ጳውሎስየአይሁድን መሪዎች በአንድነት ጠራ፤ በተሰበሰቡም ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "ወንድሞች ሆይ፤ እኔ ሕዝባችንን ወይም የአባቶቻችንን ሥርዐት የሚቃረን ምንም ሳላደርግ፣ በኢየሩሳሌም አስረው ለሮማውያን አሳልፈው ሰጥተውኛል። ¹⁸እነርሱም መርምረው ለሞት የሚያበቃ በደል ስላላገኙብኝ፣ ሊፈቱኝ ፈልገው ነበር፤ ¹⁹አይሁድ በተቃወሙ ጊዜ ግን፣ ለቄሳር ይግባኝ ማለት ግድ ሆነብኝ እንጂ ሕዝቤን የምከስበት ምክንያት ኖሮኝ አይደለም። ²⁰እናንተንም ለማየትና ለማነጋገር የጠራኋችሁ በዚሁ ምክንያት ነው፤ በዚህ ሰንሰለት የታሰርሁትም ለእስራኤል በተሰጠው ተስፋ ምክንያት ነው።"

²¹እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "ስለ አንተ ከይሁዳ ምድር የተጻፈ እንድም ደብዳቤ አልደረሰንም፤ ከዚያ የመጡ ወንድሞችም ስለ እንተ ያቀረቡት ወይም የተናገሩት አንዳች መጥፎ ነገር የለም። ²²ይሁን እንጂ፣ ሰዎች ስለዚህ የእምነት ክፍል በየቦታው ክፉ እንደሚያወሩበት እናውቃለን፤ የአንተ አስተያየት ደግሞ ምን እንደ ሆነ መስማት እንፈልጋለን።"

²³ቀን ከቀጠሩለትም በኋላ፣ ብዙ ሆነው ወደ ማረፊያ ስፍራው መጡ፤ እርሱም ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየመሰከረ ያብራራላቸው ነበር፤ ከሙሴ ሕግና ከነቢያትም በመጥቀስ ስለ ኢየሱስ ሊያሳምናቸው ሞከረ። ²⁴አንዳንዶቹ እርሱ የሚለውን አምነው ተቀበሉ፤ ሌሎች ግን አላመኑበትም፤ ²⁵እርስ በርሳቸውም አልተስማሙም፤ ጳውሎስም እንዲህ የሚል የመጨረሻ ቃል ከተናገራቸው በኋላ ሄዱ፤ "መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ አማካይነት ለአባቶቻችሁ በትክክል እንዲህ ብሎ ተናግሮአል፤

²⁶" 'ወደዚህ ሕዝብ ሂድና እንዲህም
በላቸው፤
"መስማትን ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን
አታስተውሉም፤
ማየትን ታያላችሁ፤ ነገር ግን
አትመለከቱም።"
²⁷የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና፤
ጆሮአቸውም ተደፍኖአል፤
ዐይናቸውንም ጨፍነዋል።

28፥4 ማር16፥18፤ ሉቃ13፥2፤4
28፥5 ሉቃ10፥19
28፥6 ሐሥ14፥11
28፥8 ሐሥ6፥6፤ 9፥40፤ ያዕ5፥14፡15
28፥10 መዝ15፥4
28፥11 ሐሥ27፥6
28፥14 ሐሥ1፥16
28፥15 ሐሥ1፥16
28፥16 ሐሥ24፥23፤ 27፥3
28፥17 ሐሥ6፥14፤ 22፥5፤ 25፥2፡8
28፥18 ሐሥ22፥24፤ 23፥9፤ 26፥31፡32
28፥19 ሐሥ25፥11
28፥20 ሐሥ21፥33፤ 26፥6፡7
28፥21 ሐሥ22፥5
28፥22 ሐሥ24፥5
28፥23 ማቴ3፥2፤ 8፥35፤ 17፥3፤ 19፥8
28፥24 ሐሥ14፥4፤ 17፥4፡5
28፥25 ዕብ3፥7
28፥27 መዝ119፥70፤ ኢሳ6፥9፡10፤ ማቴ13፥15

28፥5 **ጳውሎስ ... ጒዳት አልደረሰበትም፤** ለጳውሎስ የሆነው ኢየሱስ በማር 16፥18 የተናገረውን የተሰፋ ቃል በተለየ ሁኔታ የሚገልጽ ነው (በሉ. 16 ላይ ያለውን ማብ ይመ)።

28፥16 **ሮም በደረሰን ጊዜም፤** ወንጌልን በሮም መስበክ የጳውሎስ መሻት ነበር (ሮሜ 15፥22-29)፤ ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔር ፈቃድም ነበር (23፥11)። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ሮም የደረሰው በሰንሰለት ታስሮ እንዲሁም ከእያሊ መሰናክሎች፣ ማዕበሎች፥ የመርከብ መሰባበርና መከራ በኋላ ነበር። ጳውሎስ በታማኝነቱ ጸንቶ ቢቆምም እግዚአብሔር መንገዱን ቀላል ከችግርም ነጻ አላደረገውም። ልክ እንደዚሁ እኛም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ፣ ሙሉ በሙሉም ለእርሱ ታማኞች ልንሆን እንችላለን፣ ቢሆንም እግዚአብሔር ችግር በሞላበትና ደስ በማያሰኝ መንገድ ሊመራን ይችላል። ይሁን እንጂ "እግዚአብሔር ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን" (ሮሜ 8፥28) በሚለው ቃል እንጽናናለን።

አስዘያማን በዐይናቸው አይተውን
በጆሮአቸው ሰምተውን
በልባቸው አስተውለውን
ይመለሱና እፈውሳቸዋለሁ።'
28 "ስለዚህ የእግዚአብሔር ማዳን ለአሕዛብ
እንደ ተላከ እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤
እነርሱም ይሰሙታል።" 29ይህንንም
ከተናገረ በኋላ አይሁድ እርስ በርሳቸው
እጅግ እየተከራከሩ ሄዱ።
30ጳውሎስም ራሱ በተከራየው ቤት

28፥28 ሉቃ2፥30፡ ሐሥ13፥46

28፥31 ሉ23፡ ማቴ4፥23፡ ሐሥ4፥29

ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፤ ወደ
እርሱ የሚመጡትንም ሁሉ በደስታ
ይቀበል ነበር፤ 31ማንም የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ፣ ስለ
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ግልጽነት
ያስተምር ነበር።

*28፥29 አንዳንድ የጥንት ትርጒሞች ይህ ቊጥር የላቸውም።

28፥30 **ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፤** ሉቃስ የጻፈው የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እዚህ ላይ ይፈጸማል። ከዚህ በኋላ የሐዋርያው ጳውሎስ ታሪክ በአጠቃላይ እንደሚከተለው ይታሰባል። ጳውሎስ ሁለት ዓመት ሙሉ በግዞት ቤት ተቀመጠ። ጌቭኒዎቹን መቀበልና ለእነርሱም ወንጌልን መስበክ ይችል ነበር። በዚህ ጊዜ የኤፌሶንን፣ የፊልጵስዩስን፣ የቈላስይስንና የፊልሞናን መልእክቶች ጽፎአል። በግምት በ63 ዓ.ም. በነጻ ተለቀቀ ከእስር ተፈታ። በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የወንጌል ተልእኮውን እንዳሰበው በመቀጠል ምናልባት ወደ ስፓኝ ሳይሄድ አልቀረም (ሮሜ 15፥28) ። በዚህ ጊዜ 1ኛ ጢሞቴዎስንና ቲቶን ጽፎአል። እንደ ገና በ67 ዓ.ም. ጳውሎስ ታስሮ ወደ ሮም ተወሰደ። ለሁለተኛ ጊዜ በሮም በታሰረበት ወቅት 2 ኛ ጢሞቴዎስን ጻፈ። የጳውሎስ እስራት ያበቃው ኔሮ በተባለው የሮም ቄሣር ትእዛዝ ሐዋርያው በሰማዕትነት እንዲሞት በመደረጉ ነው፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ሰማዕትነትን የተቀበለው አንገቱን በሰይፍ ተሰይፎ እንደ ሆነ ትውፊት ይናገራል።

28፥31 **የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ፤** የሐዋርያት ሥራ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስና በአዲስ ኪዳን ሐዋርያት አማካይነት ለሠራው ሥራ የተመሰነ ማጠቃለያ ሳይሰጥ ድንገት ያበቃል። የእግዚአብሔር ዐላማ የመንፈስ ቅዱስ ሥራና የወንጌል ስብከት በክርስቶስ ሕዝብ ሕይወት ውስጥ እስከዘመኑ መጨረሻ ድረስ ሳያቋርጥ እንዲቀጥል ነው (2፥17-21፡ ማቴ 28፥18-20)። ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ቤተ ክርስቲያን መሆን ያለባትንና ማድረግ የሚገባትን ነገር በመግለጥ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ አሠራር አሳይቶአል። የአማኞችን ታማኝነት የሚያመለክቱ በጠላት ተቃውሞ ላይ የወንጌልን አሸናፊነት የሚያበሥሩ፣ በቤተ ክርስቲያንና በአማኞች ሕይወት ላይ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሠራውን ነገር የሚገልጹ ምሳሌዎች አሳይቶአል። ይህ ለእኛም ሆነ ለወደፊቱ የአብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ እግዚአብሔር የሰጠን መለኮታዊ መመሪያ ነው፡ እኛም በታማኝነት ይህንን ማመጅና እንዳወጅነውም መኖር ይገባናል (2ጢሞ 1፥14)። አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ መንፈስ ቅዱስ ለጥንት አማኞች ከተናገረውና ካደረገው ነገር አንጻር ራሳቸውን መመዘን ይገባቸዋል። በቤተ ክርስቲያኖቻችን ያለው ኀይል፡ ጽድቅ፣ ደስታና እምነት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከምናነበው ጋር ካልተመሳሰለ፤ እምነታችን በክርስቶስ ትንሣኤ እንዲታደስ እንዲሁም እግዚአብሔር በአዲስና ትኩስ በሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንደ ገና እንዲሞላን መለመን ይኖርብናል።